
# ሐመር

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሐመር ፲፫ ዓመት ቁጥር ፪ መጋቢት-ሚያዝያ ፲፱፻፺፯ ዓ.ም



# ከአንባብያን ለአንባብያን

## ትኩረት ለፍልፍል ሕንጻ አብያተ ክርስቲያናት

አገራችን ኢትዮጵያ ከሌላው ዓለም በተለየ መልኩ ከምትታወቅባቸው ነገሮች አንዱ በመንፈስ ብርቱ ደገኛ አባቶች የታነጹልን ከአንድ ቋጥኝ /አለት/ ተፈልፍለው የተሠሩ ሕንጻ አብያተ ክርስቲያናት ባለቤት በመሆኗ ነው።

ይሁንና በተለያዩ ስፍራዎች የሚገኙ ፍልፍል ሕንጻ አብያተ ክርስቲያናት ከዘመን ብዛት የተነሣ በውስጥና በውጭ ገጽታዎቻቸው እየተጎዱ ናቸው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ከሚገኙት መካከል በደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት በወግዲ ወረዳ በቀበሌ 01 እና 02 አዋሳኝ በአባ ያዕቆብ የተፈለፈለው የደብረ ከርቤ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ነው። የሕንጻው አካባቢም ኾነ ውስጡ ክረምት ሲኾን በዛፍ ሥራ ሥር ውስጥ በሚገባ የዝናብ ውኃ እየራሰ በመፈራረስ ላይ ነው። በመኾኑም ቦታውን የሚያውቁ ምእመናንና ሌሎችም ገባርያነ ሠናይ አካላት ዐቅማቸው በፈቀደ መጠን ጥገናና ክብካቤ በማድረግ እንዲተባበሩ ጥሪዬን አስተላልፋለኹ።

*ካሣው ዋለልኝ*
*ወግዲ ወረዳ*

## እህቶች በዙ፥ ወንድሞች ጥቂት ኾኑ

በጋሞጎፋ ሀገረ ስብከት በጨንቻና ዶርዜ አካባቢ አብያተ ክርስቲያናት በመስፋፋት ላይ ይገኛሉ። የሰንበት ት/ቤቶች ቁጥርም እንዲሁ። ችግሩ ግን የአብዛኞቹ ሰንበት ት/ ቤቶች አገልግሎት ለእኅቶች ብቻ የተፈቀዱ እስኪመስሉ ድረስ የወንድሞች ቁጥር ውስን ነው። በአንዳንዶቹም ዘንድ ፈጽሞ የሉም ለማለት ይቻላል። በዚህም ላይ መምህራንን በመመደብ ረገድ ከሚመለከተው አካል በኩል በቂ ክትትል ባለመኖሩ ሰንበት ት/ቤቶቹ በራሳቸው መንገድ የሚሄዱበት ሁኔታ ይታያል። ስለዚህም ክፍተቱን ለማስ ወገድ በሰንበት ት/ቤቱ የወጣቶች ሙሉ ተሳትፎ ቢኖርና እንደ አስፈላጊነቱ የመምህራን ምደባ ቢከናወን መል ካም ነው እላለሁ።

*ወልደ ጊዮርጊስ መለሰ*
*ጨንቻ*

## ወደ ቤተ መቅደስ ሲገቡ የሞባይል ስልክዎን ይዝጉ !!

ቤተ ክርስቲያን የጸጥታ ወደብ፣ መካነ ሰላም ናት። ይሁንና በቤተ መቅደሱ ውስጥ በኪዳኑ፣ በቅዳሴውና በጉባኤው ወቅት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በመነጋገር የሚያውኩን እንዳሉ ከዚህ ቀደም እያነሣን መታረም እንዳለበት ተነጋግረናል። ዛሬ ደግሞ ይባሱኑ የቆምንበትን አስረስቶ በቢሮው ጭቅጭቅ፣ በገበያው ትርፍና ኪሳራ በቤታችን ጣጣ ሳንወድ በግድ የሚዘፍቀን መፈተኛ መጥቶብናል። ሠቂለ ኅሊናን፥ አንቃዕዶ ልቡናን አሳጥቶናል። ይኸውም «የተንቀሳቃሽ ስልክ /Mobile/» ነው። እንደ ቤተ መጻሕፍት፣ እንደ ስብሰባ አዳራሾች ወይም እንደ ነዳጅ ማደያ ጣቢያዎች ሁሉ «ፀጥታ ይከበር» እንበል ይሆን? እባክዎን፥ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገቡ የሞባይል ስልኩዎን ይዝጉ።

*ዘኬዎስ - ቤላ*

## እየተስተዋለ

እኔ የማገለግለው በአቡዳቢ ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ነው። የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ልደት በዓል ምክንያት በማድረግ በሥነ ጽሑፍ ክፍል ድራማ ቀርቦ ነበር። በዚህ ድራማ ላይ አይቼም ሰምቼም የማላውቀው ነገር ዐየሁ። አንዲት እኅታችን እንደ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆና፣ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ደግሞ በአሻንጉሊት መስለው አቅርበዋል። ምእመናንን በተለያየ መንገድ ማስተማር የሚገባ ነው። ነገር ግን በድምፅ፣ በመብራትና በሌሎች ማሳያዎች ብቻ ተጠቅመን መልእክት ማስተላለፍ ስንችል እንዲህ ባለው መንገድ ማቅረብ ስሕተትና ጥፋት መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። ስለዚህ ለወደፊቱ መሰል ጥፋቶች እየታረሙ ትምህርት ሊወሰድባቸው ይገባል እላለሁ።

*እኅታችሁ*
*አቡዳቢ*


## ዜና ጳጳሳት ኢትዮጵያውያን

በክህነታቸው ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን አገልግለው ያረፉ

⇒ 3 ቅዱሳን ፓትርያርኮችን

⇒ 50 ብፁዓን አበው ጳጳሳትንና ሊቃነ ጳጳሳትን

ዜና ሕይወት በሰፊው አትቶ በፎቶ ግራፍ በማ ስደገፍ ያቀረበ፤

ኢትዮጵያውያን ለ1600 ዓመታት ተነፍጓቸው የነበረውን የጵጵስናና የፓትርክና ሥልጣን ከግብፃውያን ለመረከብ ነገሥታት በቤተ መንግሥታቸው፥ ካህናት በቤተ ክህነታቸው ለ1600 ዓመታት ያደረጉትን የትግል ታሪክ በማስረጃዎች አስደግፎ ያቀረበ ጠቃሚ መጽሐፍ በገበያ ላይ ውሏል። ይግዙ፥ ታሪክዎንና አባቶችዎን ይወቁ! ለልጆችዎም ያሳውቁ።

*አዘጋጅ:- ዲ/ን መርሻ አለኸኝ*

*አከፋፋይ:-*በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን

በሁሉም የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ማከፋፈያዎች ውስጥ ያገኙታል !!

ስልክ:- 22-86-01/23-45-29/13-81-30

E-mail:mk_distribution@yahoo.com



| የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ደንበኛ ይሁኑ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ | | ሐመር መጽሔት | |
| | የ6 እትም | 12 እትም | የ6 እትም | 12 እትም |
| ለአዲስ አበባ | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| ለክፍለ ሀገር | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| አፍሪካ | 9 ዶላር | 18 ዶላር | 12 ዶላር | 24 ዶላር |
| አውሮፓና መካከለኛው ምሥራቅ | 12 ዶላር | 24 ዶላር | 15 ዶላር | 30 ዶላር |
| አሜሪካና ሩቅ ምሥራቅ | 15 ዶላር | 30 ዶላር | 18 ዶላር | 36 ዶላር |

ለማኅበረ ቅዱሳን ልማት ተቋማት የባንክ ሂሣብ ቁጥር 81164 ሥላሴ ቅርንጫፍ
Mahibere kidusan Lemate Tequamat
አድራሻዎንና የከፈሉበትን ደረሰኝ ኮፒ በመልእክት ሣጥን ቁጥር 80078 ይላኩልን
ወይም በ E-mail Mk_ distribution @ Yahoo.com

በሕዝብ ፊት ባሕረ ኤርትራን የከፈለ ማዕበሉንም ጸጥ ያደረገ ከእግዚአብሔር ጋርም የተነጋገረ ሙሴ ወይም ስለ ስእለቱ ሴት ልጁን ለእግዚአብሔር የሠዋ ዮፍታሔ አንተ ነህን?

በትንቢቱ ጌታን መንክር ብሎ የሰየመው /የጠራው/ ነቢዩ ኢሳይያስ ወይም እግዚአብሔርን በሰረገላው ሁኖ ያየው ሕዝቅኤል አንተ ነህን?

የአንበሶችን አፍ የዘጋ ዳንኤል ወይም በእሳት ወላፈን ያልነካቸው ሠለስቱ ደቂቅ አንተ ነህን?

## በረከተ ወንጌል

የቅዳሴ አገልግሎት ከሌላው አገልግሎት የሚለየው የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን መፈጸሚያ በመሆኑ ነው። በዚህም መሠረት ከላይ ለመግለጥ እንደ ሞከርነው በአዲስ ኪዳን የቊርባን ምሥጢር፦ ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኰት፣ ወይኑም ተለውጦ ደመ መለኰት የሚሆነው በቅዳሴ ነው። ይህም ነገረ ድኅነትን ያመለክታል። ምክንያቱም በቅዳሴ ላይ የሚፈተተው ለድኅነተ ምእመናን በመልዕልተ መስቀል የተሰጠ አማናዊ የክርስቶስ ሥጋና ደም ነውና። ይኸንንም ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ላይ ገልጦታል። 1ኛ. ቆሮ. 11፥26-32።

## ትምህርተ ሃይማኖት

አይደለም። በጃማይካ በዓመቱ ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት የሙዚቃ ኮንሰርቶች ይዘጋጃሉ። በሁሉም ዝግጅቶች ላይ መንፈሳውያን አባቶችን ጋብዞ ማስባረክ በጃማይካውያን ዘንድ ልማድ ነው። ይህን በማድረግ የዝግጅታቸው ተልእኮና ግብ እንደ ሚሳካ ያምናሉ። ቤተ ክርስቲያንም ለምታካሂዳቸው የአገልግሎትና የግንባታ እንቅስቃሴዎች /የካቴድራል ሥራ/ የገንዘብ ድጋፎችን ታገኝበታለች። ከዚህም በላይ ለሙዚቃ ኮንሰርቱ ብሎ የመጣውን ሕዝብ ለማስተማር ከእነርሱም ጋር ለመወያየት የምትጠቀምበት አጋጣሚ ነው።

## ቃለ መጠይቅ


| | |
|---|---|
| ዋና አዘጋጅ | - ዲ.ን መርሻ አለኸኝ |
| ም/ዋና አዘጋጅ | - አሉላ ጥላሁን |
| ከፍተኛ ሪፖርተር | - መ/ር ኃይለ ማርያም ላቀው |
| መ/ ሪፖርተር | - ዲ.ን ፋሲል አስረስ |
| ኮምፒዩተር ዲዛይን | - ወይንሸት ወጉ |
| ኮምፒዩተር ጸሐፊዎች | - ፍቅርተ ኃይሌ |
| | - ጸዳሉ ሁንዴሳ |

ስልክ 556328
ፖስታ 80078
አዲስ አበባ

E -mail:Hamer@EOTC-Mkidusan.org
Website: - www.EOTC-Mkidusan.org


«ማኅበረ ቅዱሳን»

እግዚአብሔር ያከበራቸው የነቢያት፣የሐዋርያት፣የጻድቃን፣ የሰማዕታት በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ትሩፋትና አማላጅነት የሚዘከርበት በመሆኑ ይህን ስያሜውን አግኝቷል።


ሐመር
፲፫ኛ ዓመት ቁጥር ፪
መጋቢት/ሚያዝያ ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.


## ይዘት


የማኅበሩ መልእክት
- ትምህርተ ወንጌል ለሁሉም ........ ፪

ደብዳቤዎች ........ ፬

ከሰሞኑ በረከት
- በአንቀጸ ገነት የተደረገ ቃለ ምልልስ ........ ፮

ትምህርተ ሃይማኖት
- ምሥጢረ ሥጋዌ በውዳሴ ማርያም ........ ፱
- የክርስቶስ ሕማሙ ፥ ሞቱ ፥ ትንሣኤውም በፈቃዱ ........ ፲፩
- ነገረ ድኅነት በመጽሐፈ ቅዳሴ ........ ፲፫

የጥያቄዎቻችሁ መልስ
- ተአምረ ማርያም ........ ፲፮

ኪነ ጥበብ
- አርነት ........ ፲፱

እናስተዋውቃችሁ
- መካነ ስብኤ ወተመስጦ ጀር ቅድስት ሥላሴ ........ ፳፩
- ለንጊኖስ ሰማዕት ........ ፳፬

ቃለ መጠይቅ
- ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የረጅምና አድካሚ ........ ፳፭

ሐመረ ሕይወት
- የጠባይ ለውጥ እንዴት ........ ፳፱

ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ
- በሃይማኖት ከማይመስሉን ጋር እንዴት እንኑር? ........ ፴፩

ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ
- አርባ ቁጥር ........ ፴፬

ወቅታዊ ጉዳዮች
- አሜሪካ የኢትዮጵያ ካህናት የፈተና ቦታ ........ ፴፭

አቡጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት
- ዐቢይ አንቀጽ ........ ፴፯


በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ዝግጅት ማስተባበርያ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ።

# የማኅበሩ መልእክት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ።

## «ምድርንም የሚሠራባት ሰው አልነበረም»

*ዘፍ.2÷6*

እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ጋር ያለው ግንኙነት የተገለጸው በሥራ /በመፍጠር/ ነው። ሙሴም ስለ እግዚአብሔር መናገር የጀመረው ከሥራው በመነሣት ነው። ዘፍ.1÷1። እግዚአብሔር ሃያ አንዱን ፍጥረታት ፈጥሮ ከፈጸመ በኋላ ምድርን ሲመለከታት የሚሠራባት ፍጥረት አልነበረም። ሙሴም ይህን ቃል የገለጸው እግዚአብሔር አዳምን ከመፍጠሩ በፊት የሚሠራውንና የሚሠራበትን መሬት አስቀድሞ ማዘጋጀቱን ለመግለጽ ነው። ይህንም «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው።» የሚለውን በማስከተል ሰው በምድር እንዲሠራባት ሥልጣን ያለው መሆኑን አስረድቷል።

እግዚአብሔር መሬትንና መሬታውያን ፍጥረታትን ወይም ይህን የመሰሉትን ብቻ ፈጥሮ በመስጠት አልተቆጠበም። ሊቀ ነቢያት ሙሴ «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ።» ብሎ እንደ መሰከረው «እፍ» በማለት አእምሮ፣ ለብዎን እውቀትንና ማስተዋልን አሳድሮበታል። ዘፍ.2÷7። ይህም እግዚአብሔር የሰው ልጅ ይሠራ፣ ይራቀቅና ይመጥቅ ዘንድ የሚያስችለውን ጥበብ /Intellect/ እንደ ሰጠው ያስረዳናል። ሙሴ ከላይ እንደ ተገለጸው ስለ ሥራ ከአስቀደመ በኋላ ነበር ስለ ሰባተኛው ቀን ስለ ዕረፍትም የጻፈው። ዕረፍትና በሰዓት ያለ ሥራ ሊገለጹ አይችሉምና። ዘፍ.2÷3።

በመጽሐፍ ቅዱስም ከመጀመሪያው መጽሐፍ ከኦሪት ዘፍጥረት ጀምሮ በአሥራውም ሆነ በአዋልድ የሥራ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ በሰፊው ተነግሯል። ይህም ብቻ ሳይሆን ሥራ ስለሚወዱት ትጉሃንና ሥራን ስለ ሚጠሉት አብዳንም /ሰነፎችም/ በሰፊው ተናግረዋል። ጥበበኛው ሲራክ «... የሥራንም ነገር ከሰነፍ ሰው ጋር አትማከር፤ ጨክኖ የመሥራትንም ነገር ከምንደኛ ጋር አትማከር።» እያለ የሚመክረው ሥራን በሠራተኛው የሥራ ፍቅር ለመግለጽ ነው። ሲራ.37÷11።

ጠቢቡ ንግግር በማሳመር ጠንካራ መስለው ስለሚኖሩት ሰነፎችም «የሰነፎች ዕውቀታቸው በአፋቸው ነው» በማለት ተናግሯል። ሲራ.22÷6። አንድ ቦታ ላይ በመቀመጡ፣ ወይንም ወርኃዊ ገቢን በሚያስገኝ ቦታ በመቀጠሩ ብቻ እንደ ሠራና እንደ ሚሠራም የሚያስብም አይጠፉም። ከዚህም አልፎ ትጉሃንን እንዳይሠሩ በማድረግ ለነገራቸው እንቅፋት፣ ለሥራቸው መሰናክል የሚሆኑ÷ የሠራተኞችንም ሥራ ስለ ተቹና ስለ ነቀፉ የሠሩ የሚመስላቸው ሰነፎችንም ቢሮ ይቆጠራቸው። ጥበበኛው ሲራክ «ሰነፍ ሰው በተቀመጠበት ቦታ እንደ ዋሻ ደንጊያ ነው፤ በጽኑ ስንፍናው ሁሉን ያቦዝናል።» በማለት የተናገረው ለእነዚህና መሰል አካላት ነው።

ቤተ ክርስቲያን ሥራንና ሠሪውን ለይታ ስለ ምታውቃቸው በሚታወቁበት ግብር ትጠራቸዋለች። በመሆኑም ሥራን እንደ ሚከተለው ትገልጻለች።

1. ***ሥራ ትእዛዘ እግዚአብሔር ነው፡-*** አዳም የእግዚአብሔርን ስሙን ቀድሶ ክብሩን ወርሶ እንዲኖር ሲፈጠር የኑሮውን መሠረት ሥራ አድርጎ ሰጥቶታል። ሊቀ ነቢያት ሙሴ ይህን ነገር ሲያስረዳ የሥነ ፍጥረትን ነገር ከዘረዘረ በኋላ «ምድርንም የሚሠራባት ሰው አልነበረም፤... እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው» ብሏል። ዘፍ.2÷6። ይህ የሚያመለክተው ሰው የተፈጠረው ለክብረ ሥጋ፣ ለክብረ ነፍስ ብቻ ሳይሆን ምድርን ይሠራባትም ዘንድ ነው። ሥራ ለሕይወተ ሥጋው መሠረት ሆኖ የተዘጋጀለት ነውና። በኋላም «ወደ መጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ» ተብሎ የታዘዘው ካልሠራ ሊበላ አለመቻሉን ካልበላም በሕይወተ ሥጋ መኖር የማይቻለው መሆኑን ለማስረዳት ነው። ዘፍ.3÷19። ቅዱስ ጳውሎስም «ሊሠራ የማይወድ አይብላ» በማለት አጠንክሮ ያስተማረው ሕይወተ ሥጋ ያለሥራ ሊታሰብ የማይችል ጉዳይ በመሆኑ ነው። 2ኛተሰ.3÷10።

ይሁን እንጂ «ሊሠራ የማይወድ አይብላ» የሚለው ቃለ ሐዋርያ «የማይሠራ አይብላ» ከሚለው የኮሙኒስቶች መፈክር ጋር የማይገናኝ መሆኑን ማስተዋል ይገባል። ሊሠራ እየወደደ በተለያየ ምክንያት /በሕማም፣ በእርጅና፣ በልጅነት.../ የማይሠራ አለና። ይልቁንም መሥራት እየቻለ፣ ሊሠራ የሚገባው ሆኖ ሳለ÷ የሚበላው እንኳ ባይቸግረው ሊሠራ ይገባዋል ለማለት ነው። ሰው ሠርቼ አከማችቼአለሁና ከአሁን በኋላ ገንዘብ በቃኝ በማለት እንኳ ሥራ ሊተው እንደ ማይገባው ምክር ተጽፎለታል። ሲራ.5÷1። ከላይ እንደ ገለጽነው መሥራት የማይችሉትን ሊረዳበት ይችላልና። እነዚህ ሁሉ የሚያመላክቱት ሥራ ለመብላት አስፈላጊ መሆኑን ብቻ ሳይሆን መፈጸም ያለበት የእግዚብሔር ትእዛዝ መሆኑንም ጭምር ነው።

2. ***ሥራ ጸሎትም ነው፡-*** ሠራተኞች ይልቁንም ሰብአ ዓለም /በዚህ ዓለም የሚኖሩ/ ለሠራተኛ ከሚገባው ጸሎት በላይ እንደ ገዳማውያኑና ዓለምን እንደ ናቁት መናንያን ረጅም ጊዜ እንዲጸልዩ አልታዘዙም። የእነርሱ ሥራቸው ጸሎታቸውም ጭምር ነውና። ወደ ገዳም የገቡት ወጣንያን እንኳን የመጀመሪያው የረጅም ጊዜ ድርሻቸው ሥራ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ነው:: በሥራ ተጋድለው በትሕትናቸውና በትጋታቸው ሳይፈተኑ በጸሎት ወደ መጠመድና ወደ መዝጋት አይመጡም፤ ታላላቆቹም አይፈቅዱላቸውም:: በሥራ ዓለምን ያላሸነፈ ሰይጣንን በተጋድሎ ለማሸነፍ ልቡናው ይዝላልና:: ጥበበኛው ሲራክም ስለ ትጉሃን ሠራተኞችና ስለ ሥራቸው በሰፊው ከዘረዘረ በኋላ «ያገርን ፈቃድ ያጸናሉ እንጂ ነገርን መስሎ በመናገር አይኖሩም፤ ጸሎታቸውም በሥራቸው ይራቀቁ ዘንድ ነው::» በማለት ጸሎታቸው ስለ ሥራቸው፣ ሥራቸውም ጸሎታቸው መሆኑን ገልጿል:: ሲራ.38÷34:: ሥራ ሕሊናን ንጹሕ የሚያደርግ ሰውነትንም በጤንነት የሚጠብቅ ከመሆኑ በላይ ሰውን ክፉ ለመሥራት ዕድል የማይሰጥ ኃጢአትም እንዳይሠራ የሚከላከል በመሆኑ ተግባራዊ ጸሎት ነው::

3. **የሰይጣን ድል መንሻ መሣሪያ ነው:-** ዓለምን ጥሎ የመነነው ርእሰ መነኮሳት አባ እንጦንስ በበረሃ በሚጋደልበት ወቅት ቅዱሳት መጻሕፍትን ከመመልከትና ከጸሎት ባረፈ ጊዜ የሰይጣን ፈተና እንዳያንገላታው ቅዱስ ሚካኤል ሰሌን መታታትን አስተምሮታል:: በዚህም ጠላቱን ሰይጣንን ድል ነስቶበታል:: ጉልበታቸው ደክሞ ዓይናቸው ፈዝዞ በተለያዩ ገዳማት ያሉ አባቶችና እናቶችም እስከ አሁን ይህን ሥራ ይሠሩታል:: ሥራ የፈታ ሕሊና የሰይጣን ፈተና የዚህ ዓለምም ጾር ይታገለዋልና:: ስለዚህ ሥራ ሰይጣንን ድል የምንነሣበት መሣሪያችንም ነው::

ቤተ ክርስቲያን ስለ ሥራ ማወቅና ማስተማርም ብቻ ሣይሆን የሥራ ይልቁንም የሥነ ጥበባት ማዕከል ናት:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ተናገረው አንዱ በሌላው ላይ እንዳይከብድ መሥራት የሚቻለውና የሚገባው ሁሉ እንዲሠራ አስተምራለች፤ እያስተማረች ነው፤ ወደ ፊትም ታስተምራለች:: ሐዋርያው ስለ ራሱ «ከእናንተ ዘንድ በአንድ ስንኳ እንዳንከብድበት÷ ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን እንኖር ነበር እንጂ÷ ከማንም እንጀራን እንዲያው አልበላንም::» በማለት ከገለጸ በኋላ ስለ ትጉሃኑና ስለ ሰነፎቹ «ሥራ ከቶ ሳይሠሩ÷ በሰው ነገር እየገቡ÷ ያለ ሥርዓት ከእናንተ ዘንድ ስለ ሚሔዱ ስለ አንዳንዶች ሰምተናልና:: እንደነዚህ ያሉትንም በጸጥታ እየሠሩ የገዛ እንጀራቸውን ይበሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናዛቸዋለን፤ እንመክራቸውማለን::» ሲል አስተምሮአል:: 2ኛተሰ.3÷7-13::

የቤተ ክርስቲያን ትምህርትና ሕይወት ይህን የመሰለ ሆኖ ሳለ ቤተ ክርስቲያን ለሥራ ፈትነት አስተዋፅዖ እንዳደረገች አድርጎ ማቅረብ ግን የችግሩ መፍትሔ ሊሆን አይችልም:: የበዓላትም ሁኔታ የሚመለከተው የሚሠራውን እንጂ የማይሠራውን አይደለም:: ምጽዋትም በቤተ ክርስቲያናችን÷ ሰው በሃይማኖት፣ በጾታና በተለያዩ ሁኔታዎች ሳይመዘን በረሀብ ከመሞት ይድን ዘንድ የሚደረግ እውነተኛ ቸርነት ነው:: የሀገራችንም ተመጽዋቾች ብዙዎች ሠርተው፣ ከብረውና ገንነው ይኖሩ የነበሩ በተለያዩ ምክንያቶች ግን በችግር ማጥ ተይዘው መሥራት የማይቻላቸው ሆነው የሚጠሉትንና ሊያደርጉ የማይፈልጉትን ልመና አማራጭ በማጣት ቢይዙት ከሥራ ባህል ጋር ተያይዞ ሊነቀፉ የሚገባቸው አይደሉም:: ይልቁንም ይህ ፖሊሲንና ሌሎችን መሰል ጉዳዮች እንድናጠናና መፍትሔ እንድናፈላልግ የሚያደርግ ነው::

አሁን የሚሠሩ ሰዎች ፈጽመው አልጠፉም፤ ነገር ግን ስለ ሚሠሩት ከሚናገሩት ይልቅ ስለ ማይሠሩት የሚናገሩት ይበዛሉ:: ሁሉም ራሱን ተጠያቂ ሳለማድረግ ችግሩን ይገፋል፤ ሌላውንም ይወቅሳል እንጂ ወደ መፍትሔ በድፍረት የሚገባ እጅግ ጥቂት ነው:: ምድሪቱ የሚናገሩባትን እንጂ አሁንም የሚሠሩባትን አላገኘችም:: ችግሮቿን አውርተው ሌሎቹንም ተችተው የሚለያዩ እንጂ እኔም ተጠያቂ ነኝ የሚሉ አንሰውባታል::

የቤተ ክርስቲያናችን ምእመናን ሁነው ሰነፎች ሊኖሩ ይችላሉ:: ስንፍና ብርቱ በሁሉም ቦታ አለና:: እነዚህ ደግሞ ስንፍናቸው ለሥጋቸው ብቻ ሳይሆን ለነፍሳቸውም ጭምር ነው:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥተ ሰማያትን በዐሥሩ ደናግል በመሰለበት አንቀጹ አምስቱ ብልሆች /ትጉሃን/፣ አምስቱ ደግሞ ሰነፎች መሆናቸውን ገልጾ መንግሥተ ሰማያት የትጉሃን መሆኗን ያስተማረው ስንፍና የነፍስም የሥጋም ጠላት መሆኑን ለመግለጽ ነው:: ማቴ.25÷1-13:: በእነዚህ ሰነፎች መኖር ግን ቤተ ክርስቲያን ልትወቀስ አትችልም:: ከአንድ ቤተሰብ አባላት ጥቂቶቹ ሰነፎች ቢሆኑ ሰነፎቹ ለብቻው ይወቀሳሉ እንጂ ቤተሰቡ እንዳለ ሊወቀስም ሊነቀፍም አይችልም:: እነዚህን አካላት ቤተ ክርስቲያንም «ሥራ ፈትታችሁ ቀኑን ሁሉ በዚህ ስለ ምን ትቆማላችሁ?» በሚለው የጌታችን ትምህርት ትገሥጻቸዋለች እንጂ ዝም ብላ አትመለከታቸውም:: ማቴ.20÷6-7::

ሥራ ያላቸው ሥራ ፈቶችንም ሆነ ሥራ የሌላቸውን ሥራ ፈላጊዎች ቤተ ክርስቲያን እንዲገባ ትመክራቸዋለች፣ ትገሥጻቸዋለች እንጂ በዝምታ አታልፋቸውም:: ይሁን እንጂ ቅቡጻነ ተስፋ እንዳይሆኑም ታጽናናቸዋለች፤ ወደ መጥፎ ሥነ ምግባርም እንዳያመሩ ተስፋ ታሳያቸዋለች እንጂ አትዘልፋቸውም:: በመሆኑም በሥራ ባህልም ሆነ ድህነትን ለማስወገድ በሚነሡ ነገሮች ዙሪያ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት የረታ የቀና ነው:: አንዳንድ ያልተረዱ አካላትም አሻግረው ሊተቹ አይገባቸውም:: ለችግሩ ዋና ተጠያቂ አድርጎ በድፍረት ከመናገር በፊትም ትምህርቷን ማወቅ ከዚህም አልፎ ያላትን በጐ ጐን በቅን ልቡና መመርመር ያስፈልጋል::

ፍጹም ድህነት ውስጥ የሚኖሩ አካላት ሰላማዊ እንዲሆኑና አንዱ ሌላውን እንዳይበላው የጠበቀው ምንድን ነው? ብሎ ማሰብም ያስፈልጋል:: በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት የማይሠሩት ወደ ምንፈልገው ሥራ እስከ ሚመለሱ ድረስስ ምን ይብሉ? በዩትኛው መንገድ? የሚለውም ጤነኛ ሰው ሁሉ ሊያስበው የሚገባው ጉዳይ ነው::

ሁሉንም ችግሮች አስወግዶ ከስንፍና ተላቅቆ ለመኖር ግን ሃያ አንዱ ሥነ ፍጥረት÷ ቀድመው እንደ ተፈጠሩልን፣ ሰውም በእነርሱ ይጠቀም ዘንድ ዕውቀትና ጥበብ የተቸረው መሆኑን ማስተዋል ይገባል:: መሬት አሁንም የሚሠራባትን ትፈልጋለች:: ዕውቀትም ከሰውነቱ መዝገብ አውጥቶ የሚተገብርባትን ትጉህ ሁል ጊዜ ትናፍቃለች:: ይሁን እንጂ ዕውቀቱን ለሥራ የሚያወጣ ትጉህ አልተገኘም፤ ምድርም የሚሠራባትን አሁንም አላገኘችምና እባካችሁ እንንቃ::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ደብዳቤዎች

## ከወትሮው በተሻለ ለመረዳት አግዞናል

በ«አቡጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት» ዓምድ እየቀረበ ባለው ትምህርት ብቻ ቋንቋውን ሙሉ በሙሉ ለማጥናት የሚያዳግት ነው:: ይሁን እንጂ በቋንቋው የተጻፉትን የጸሎት መጻሕፍትንና ጸሎተ ቅዳሴውን ከወትሮው ይልቅ በተሻለ መልኩ ለመረዳት አግዞናል:: የትምህርቱን ተከታታዮችንም ለማወቅ ምእመናን በጥያቄና መልስ ላይ መሳተፍ ይኖርባቸዋል::

*ሰሎሞን በርሔ*
*ብላቴ ኮማንዶ አየር ወለድ ማሠልጠኛ ማዕከል*
*አዋሳ*

## ትዕግሥት - አለማወቅ ይሆንን?

ባለሁበት አካባቢ በዝተው ከሚገኙ መናፍቃንም ይሁን ከሌላ ለመለየት ባልችልም ለቤተ ክርስቲያናችን ምእመናን በግልና በመሥሪያ ቤት የፖስታ አድራሻቸው የሚላክላቸው የኑፋቄ «ትምህርት» እየበረከተ ሄዷል:: ሕዝቡም ግራ እየተጋባ ይገኛል:: ለመሆኑ ፖስታ ቤት የላኪ አድራሻ የሌለበትን ደብዳቤ መቀበሉ ግለሰቦችን የእምነት ነጻነት የሚጻረር ድርጊቶች አይሆንም ወይ? መናፍቃኑስ የምእመኑን ትዕግሥት ከአላዋቂነት ቆጥረውት ነው ወይ? በሕግ አምላክ! ይኽ ችግር ከወዲሁ መፍትሔ ቢሰጠው ይበጃል::

*ገብረ ሃና*
*አጋርፋ ግ/ቴ/ሙ/ማ/ኮሌጅ*

## ሕገ እግዚአብሔርና የአሜሪካ ፕሬዘዳንታዊ ምርጫ

በቅርቡ ተካሂዶ በነበረው የአሜሪካ ፕሬዘደንታዊ ምርጫ የዓለምን መገናኛ ብዙኃን ትኩረት ስበው የነበሩት የሪፐብሊካኑ ፓርቲ ዕጩ ጆርጅ ቡሽና የዲሞክራቲክ ፓርቲው ዕጩ ጆን ኬሪ በመጨረሻዋ ሰዓት (neck-to-neck) ሳሉ 154 ለ152 ድምፅ እንደ ተከተላቸው ነበሩ:: ከአሜሪካ 335 አጠቃላይ ድምፅ 170 ያህሉን ያገኘው ነበር ወደ ኋይት ሐውስ መግባት የሚችለው:: ለዚህ ደግሞ ወሳኝ የነበረው 20 ድምፅ ከኦሃዮ ግዛት የሚጠበቅ ነበር::

ይሁን እንጂ ኦሃዮ ከአሜሪካ ግዛቶች ሁሉ ትንሽ ብትሆንም ግብረ ሰዶምንና ውርጃን ፈጽመው የሚያወግዙ ነዋሪዎች የገኑኑባት ነበረች:: ጆን ኬሪ በምርጫ ዘመቻቸው ወቅት «ብመረጥ የተመሳሳይ ጾታ ጋብቻንና ውርጃን እፈቅዳለሁ» ማለታቸው በአንጻሩ ጆርጅ ቡሽ ይህን መቃወማቸው ዲሞክራቱን ዕጩን ወሳኙን 20 ድምፅ አሰጣቸው:: ሥልጣንን የሚነሳም የሚሰጥም እግዚአብሔር ነውና ግብረ ሰዶምንና ውርጃን የተቃወሙት ጆን ኬሪ በ174 ድምፅ የኋይት ሐውስ የአራት ዓመት ቆይታቸውን አጸኑ:: የአሜሪካ ፕሬዘዳንታዊ ምርጫና የሕገ እግዚአብሔር አሸናፊነት አይገርምም::

*ያረጋል ገዳሙ*
*ደሴ*

## «ታቦት ደም ይወዳል»

የዘንድሮን የጥምቀት በዓል ያከበርኩት በአየር ጤና አካባቢ ልዩ ስሙ «የዓለም ባንክ» እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ነበር:: በጥምቀተ ባሕሩ ያደሩት ሦስት ታቦታት ናቸው:: የደብረ ራማ ቅዱስ ገብርኤልን ታቦት አክ ብሬ ከቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ስንደርስ ለዐይኔ እንግዳ የኾነ ክስተት ተመለከትኩ:: ይኸውም ታቦቱ ከመግባቱ በፊት ቀንድ የሌለው ነጭ በግ አምጥተው አረዱ፤ ታቦቱን ያከበሩት ካህናትም ደሙን ረግጠው ገቡ:: ይህ ድርጊት በወቅቱ የነበሩ በርካታ ክርስቲያኖችን አሳዝል:: ድርጊቱስ የተዋጀ ንበትን መለኮታዊ ሥጋና ደም ዋጋ የሚያቃልል አይሆንምን? የአጥቢያው አስተዳደርስ ፈቃዱን ያሳየው ከምን ተነሥቶ ነው? በርግጭ በወቅቱ ስለ ሁኔታው አንድ ካህንን ብጠይቅ፡- «እንዲህ ያለ ነገር በገጠር አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ በብዛት ይታያል፤ ምክንያቱም ደስታን ለመግለጥ ነው» አሉኝ:: በእውነት፥ ድርጊቱ በአጽራረ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ በእጅጉ የሚያስተቸን ከመሆኑ አኳያ የካህኑ መልስ በቂ አልመሰለኝም:: ስለዚህም ያለቦታቸው ከሚፈጸሙና ለትችት ከሚዳርጉን ልማዶች ልንጠነቀቅ ያስፈልጋል:: «ታቦት ደም ይወዳል» ፈጽሞ የተሳሳተ እምነትና ብሂል ነውና ሊታረም ይገባል::

*ተክለ ማርያም*
*አየር ጤና*

## ይዞታችንን እናልማ

በደቡብ ኦሞ ዞን ስለሚገኘው የጂንካ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ይዞታ መደፈር ጩኸቴን አሰማለሁ፤ የቤተ ክርስቲያኑ ጠቅላላ ይዞታ 700 ካሬ ሜትርና ከዚያ በላይ ነው:: ይሁንና አጽራረ ቤተ ክርስቲያን በልማት ስም እንደ ፍልፈል ይዞታችንን እየተጋፉ ነው፤ ይባስ ብለው በመቃብር ክልላችን ሳይቀር የባሕር ዛፍ ተክላ እያካሄዱ ነው:: በአንጻሩ የአጥቢያው የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤም ኾነ የልማት ክፍሉ ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ አያደርጉም:: «ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ» እንዲሉ ይዞታችን ተነጥቆ በነበር ከመቅረታችን በፊት ሳንውል ሳናድር ተነሥተን እናልማው፤ ልኩን ዳር ድንበሩንም ተባብረን እናስከብረው::

*ብርሃን መለኮት ኪዳኔ*
*ኃ/ሚካኤል ገ/ክርስቶስ*
*ጂንካ*

## ሳይደርቅ በርጥቡ ሳይርቅ በቅርቡ

በሐመር መጽሔት 13ኛ ዓመት ቁጥር 1፥ 1997 ዓ.ም እትም ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ ዓምድ፡- «ቸልተኝነት» በሚል ርእስ የቀረበው ጽሑፍ አእምሮዬን የነካውን፣ አንጀቴን ያሳረረውን፣ ቆሽቴን ያደበነውን በአጠቃላይ ዕረፍት የነሳኝን ነገር እንዳነሣላችሁ አስገደደኝ:: ይኸውም እኔ ባለሁበት ከተማ የሚገኙ፥ ሁሉም ባይባልም ጥቂት የማይባሉት፥ የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባላት፡-

* የሙስናና የምዝበራ ሥራ፣
* በመዘበሩት የሙዳየ ምጽዋት ገንዘብ ለክህነታቸውና ለመንፈሳዊ ሕይወታቸው ተቃራኒ በኾነ መልኩ በየመሸታ ቤቱ መታየታቸው፣
* ከመደበኛ ገቢያቸው ጋር በማይመጣጠን ሁኔታ የግል ሀብት ማካበታቸው፤
* ብልሹ ድርጊታቸውን የሚቃወሙ ካህናትን የአገልግሎት ዋስትና እየነሱ፣ ደመወዝ እየቆረጡ ማሸማቀቃቸው፤ በዚህም ሳቢያ ካህናቱ አንገታቸውን ደፍተው ድምፃቸውን አጥፍ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ተው ለእነርሱ የልብ ልብ መስጠታቸው፣ የሚጠቀሱ ናቸው:: ምን ይኼ ብቻ፣ ምእመናኑም እንደ ካህናቱ «ምን አገባኝ» በሚል ስሜት ዝምታን የመረጡ ይመስላሉ:: በመሆኑም የአመራር አባላቱ የመልካም ምግባርና አስተዳደር ብልሽት ቤተ ክርስቲያናችንን በብዙ መልኩ የጎዳና የሚጎዳ መሆኑ ይታወቃል:: ነገር ግን በቸልተኝነት እየታየ ከመባባሱ በፊት ተገቢ እርምት እንዲደረግበት መልእክቴን አስተላልፋለሁ:: ሳይደርቅ በርጥቡ ሳይርቅ በቅርቡ ነውና::

*እንግዳ ወርቅ ጥላሁን*
*ወላይታ ሶዶ*

## ብቃት ላለው የምክር አገልግሎት

በሐመር መጽሔት 13ኛ ዓመት ቁጥር 1 ጥር /የካቲት 1997 ዓ.ም እትም በሐመረ ሕይወት ዓምድ:- «የጠባይ ለውጥ እንዴት?» በሚል ርእስ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ችግሮችን በሚዳስስ መልኩ ያቀረባችሁት ጽሑፍ አስደስቶኛል:: ማኅበረ ቅዱሳንም ከአክሽን ኤይድ ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር ይህን እጅግ ወቅታዊና አስፈላጊ ዓምድ መጀመሩ ሥርቼ ውጤታማ እንደ ምሆንበት ሞያ ያህል የምረካበት አድርጎኛል:: በተጠቀሰው እትም ያነሣችሁትን ርእሰ ጉዳይ በተመለከተ ያሉኝን ገጠመኞች እንድገልክ ጠይቃችሁን ነበር:: እኔ በተጨባጭ ካየሁትና ሞያዊ ግዴታዬ ከመኾኑም አኳያ የጠባይ ለውጥ በሚፈለገው መጠን ያለመምጣቱን ችግር ከደም ምርመራ በፊትና በኋላ ከሚሰጠው ብቃት የሌለው የምክር አግልግሎት እክሎች ጋር አያይዘዋለሁ:: ከደም ምርመራ በፊት የሚሰጥ የምክር አገልግሎት:- ሰዎች ስለ ቫይረሱ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና በራሳቸው ጊዜ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የደም ምርመራ እንዲያደርጉ ያበቃቸዋል:: ከደም ምርመራ በኋላና በቀጣይነት የሚሰጠው የምክር አገልግሎትም ከቫይረሱ ነጻ የኾኑቱ ራሳቸውን እንዲጠብቁ፣ ከቫይረሱ ጋር አብረው የሚኖሩቱም እውነታውን በጸጋ ተቀብለው ለራሳቸውም ይሁን ለሌላው ተጠንቅቀው እንዲኖሩ ያስችላቸዋል:: ዳሩ ግን በምክር አገልግሎት ረገድ የሚታዩ ድክመቶች ቫይረሱ በደማቸው የተገኘባቸውን ወገኖች የአካልና የመንፈስ ብርታት የሚያደክም፥ በቀቢጸ ተስፋ ውስጥ እንዲገቡ፥ ኅብረተሰቡን እንዲጠሉና ለበቀል እንዲነሣሡ በአጠቃላይ የሚጠበቀው የጠባይ ለውጥ እንዳይመጣ ምክንያት ሆኗል:: ስለዚህም በሚመለከታቸው አካላት የሚመደቡ የምክር አገልግሎት ባለሞያዎች ብቃት እንዲኖራቸው ቀጣይነት ያለው ክትትል በበላይ አካል መደረግ ይገባዋል እላለሁ::

*ኃይለ ሚካኤል*
*አፋር*
*ታዬ በላይነህ*
*ባሌ ዞን- ሃሮ ቅዱስ ገብርኤል*

## ማዕከላት ይኑሩ

«በአባቶችሽ ፈንታ ልጆች ተወለዱልሽ» ተብሎ የተነገረው ቃል በማኅበረ ቅዱሳን የቅዱሳት መካናትና የአብነት ት/ ቤቶች መርጃና ማቋቋሚያ ክፍል እየተፈጸመ ነው:: ይህንንም ለማለት ያበቃኝ በ12ኛ ዓመት ቁጥር አራት እና በ13ኛ ዓመት ቁጥር አንድ እትም በእናስተዋውቃችሁ ዓምድ ስር የቀረቡት የተጠኑ፣ የተተገበሩና በመተግበር ላይ የሚገኙ የልማት ፕሮጀክቶች ዝርዝር ነው:: በተመሳሳይ መልኩ ሌሎች አካላትም በተለያዩ መንገድ /የስብከተ ወንጌል መድረኮችን፥ የመዝሙር ትዕይንቶችን በማዘጋጀት/ በሚያስገኙት ገቢ የገጠር አብያተ ክርስቲያናትን መርዳታቸውም ተገቢ ነው:: በዘላቂነት ከችግራቸው የሚያላቅቅ ዕቅድ ቢያወጡላቸው ደግሞ መልካም ነው:: እንደ ማኅበረ ቅዱሳን ሁሉ ለገዳማትና ለአድባራት መርጃና ማቋቋሚያ የምንለግሣቸውን ርዳታዎች በተሟላ መንገድ የሚያዳርሱ የድጋፍ ማዕከላት በየሥፍራው መኖር ይገባቸዋል:: ይህን የምለው አጋጣሚዎችን ተጠቅመን የምናበረክተው ድጋፍና ርዳታ ለብክነትና ለጥፋት ስለሚዳረግ ነው:: በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም የሚካሄድ ሕገ ወጥ ልመናንም ለመቆጣጠር ይበጃል:: ምእመኑም ለተቸገሩ አብያተ ክርስቲያናት ጊዜያዊና ዘላቂ ርዳታ ለማድረግ ይነቃቃል::

*ለምለም ቦጋለ*
*ናዝሬት ቴክኒክ ኮሌጅ*
*አዲስ መኩሪያና ጓደኞቹ*
*አዲስ አበባ*

## መዝሙርም ወረት ኾነን?

በአሁኑ ወቅት በግልና በማኅበር እየተዘጋጁ በኦዲዮና በቪድዮ ካሴቶች እየታተሙ የሚወጡ መዝሙራት እንዳሉ ይታወቃል:: ይኼም ከነ ችግሩ መልካም እንደ ኾነ እናያለን:: ይሁንና በብዙዎቹ ሰንበት ት/ቤቶች ዘንድ እንደ ፋሽን ልብስ የቅርቡን ብቻ ይዞ «ማድመቅ» ሆኗል:: ቅሬታዬ የፊተኞቹ መዝሙራት መዘንጋታቸውና መረሳታቸው ነው:: ዘላለማዊ አምላክን የምናመሰግንባቸው መዝሙራት ሕያዋን እንጂ በወረትና በስሜት ብቻ የማንገለገልባቸው አለመሆናቸው ይስተዋል::

*ቄስ ሰሎሞን ታዬ*
*ባሌ-ስዌና ሚጫ ወረዳ*

## «የቦብ ማርሌይ ኮንሰርት»

በጥር ወር መጨረሻ 1997 ዓ.ም የቦብ ማርሌይን 60ኛ ዓመት የልደት በዓል ምክንያት በማድረግ በመስቀል አደባባይ የተዘጋጀው ኮንሰርት ላይ የታዘብነው ነገር በእጅጉ አሳዝኖናል:: የዘፈን፣ የዳንስና የዳንኪራ ዝግጅት በጸሎትና በቡራኬ ሲከፈት ለዐይናችን እንግዳ የኾነ ነገር ነው:: በእውኑ በመድረኩ የነበሩ ካህናትን ቤተ ክርስቲያናችን ታውቃቸዋለች ወይ? እንዴትስ ነው የተላኩት? ሐቁን ለመናገር ሁኔታው ለመውደቅ የተቃረቡትን ደካማ ምእመናን እንደ መገፍተር ቆጥረነዋል:: እርስበርሳችንም በብዙም ያበጣበጠን ስለሆነ ከላይ ላቀረብነው ጥያቄ ምላሽ አፈላጋችሁ በቶሎ እንድታሳውቁን ይሁን:: አካሄዳችን ሁሉም በጥበብና ውጤቱም ከወቅቱ ሁኔታና ከረጅም ጊዜ አኳያ እየታሰበበት ይሁን::

*ምእመናን*

<u>ከአዘጋጁ</u>:- ጉዳዩን አስመልክቶ በአካል፣ በስልክና በፖስታ በርካታ ጥያቄዎች ደርሰውናል:: በመሆኑም ከላይ በተገለጸው መንገድ ጠቅለል አድርገን አቅርበነዋል:: ለተጠቀሱትና ላልተጠቀሱት ሌሎች ዝርዝር ጥያቄዎች ምላሽ ወይም ማብራሪያ ይሆን ዘንድም በተሰጣቸው ተልእኮ መሠረት በዝግጅቱ ላይ ተገኝተው ጸሎትና ቡራኬ ያደረጉትን ቄስ ኃይለ ጊዮርጊስን አነጋግረን የዚህ እትማችን እንግዳ አድርገናቸዋል:: በቦታው ይከታተሏቸው ዘንድ ተጋብዘዋል::

*ደብዳቤዎቻችሁ የደረሱን:-*

ውባለም ደመቀ /ቤሩት-ሊባኖስ/፣ ዓባይነህ አስሙ/ ደብረ ማርቆስ/፣ ኅብረ ተሰብ ዘመነ፣ ዮሴፍ ታምራት/ጨፋ ሮቢት/፣ አስፋው አባተ/ማሻ/፣ ዕውቀት ደባስ/ደንባጫ/፣ ዘላለም ቡሩክና ገ/መድኅን አየለ /ምዕ.ትግራይ/፣አዲሱ ያደታ/ሆሎታ/፣ ወ/ሪት ፍሬ ሕይወት መገርሳ/ላሊበላ/፣ ሰይፈ ገብርኤል/ዓለማያ ዩኒቨርስቲ/፣ ፈቃደ ወልድ፣ ወልደ ሩፋኤል፣ ትርሲተ ማርያም፣ ዓሥራተ ማርያም/ምዕ.ሸዋ-ጌዶ ደብረ ገነት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት/፣ ዐደጸ ሥላሴ /አርሲ-አሣሣ/፣ ደረጀ መንግሥት/ባሌ-ሮቤ/፣ ግርማ ግንጫ/ሚዛን ተፈሪ/፣ ዓለማየሁ ከበበ/ሙገር/፣ ዲ.ን ቦጋለ ገላዬ ካሣሁን አያሌው /የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ግቢ ጉባኤ/፣ ነጋ ዋጂን/ወለጋ/፣ ጋሻው አይቼው /ጭዳ/፣ ፍሬው መለስ /ምሥ.ጎጃም-ደብረ ኤልያስ/፣ ሙሉነህ አላምረው/መተከል-ማምቡክ/፣ ደግፌ ታደሌ /አርባ ምንጭ-ኔልሰን ማንዴላ ኮሌጅ/፣ እንዳልካቸው ገላዬ /5ኛ ክፍለ ጦር-ነቀምት/፣ መ/ር አቤንኤዘር ሙሉጌታ /ደቡብ ጎንደር-እብናት/፣ ቴዎድሮስ ደምሴ፣ ኤፍሬም ስለሽ፣ መንግሥቱ ተመስገን::

*በተሳትፏችሁ ቀጥሉ::*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# በአንቀጸ ገነት የተደረገ ቃለ መጠይቅ!

## «መላ ዘመኔን በመበደልና ነፍስ በመግደል አሳለፍኩ፤ በመጨረሻዋ ቀኔም የጌታ ምሕረት ወደ ሕይወት ሳበችኝ።»

*የጌታችንንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስ ቶስን ዕለተ ስቅለት ስናስብ ከእርሱ ጋር የሚታወሰን ወንበዴው ፈያታዊ ዘየማን ነው። ፈያታዊ ዘየማን መላ ዘመኑን ያሳለፈው ነፍስ በመግደል፣ ዝርፊያና የተለያዩ ወንጀሎችን በመፈጸም ነበር። ከጥቁር ላም ብብት ነጭ ፀጉር፣ ከነጭ ላም ብብት ጥቁር ፀጉር ቢፈልጉ እንደ ማይታጣ በፈያታዊ ዘየማን ልቡናም ጥቂት ፈሪሃ እግዚ አብሔር ምሕረት እንደ ነበር አሳዛኙ የሕይወት ታሪኩ እማኝነት ይሰጠናል።*

*የገሊላው ንጉሥ ሄሮድስ በገሊላ የሚገኙትን ሕ ፃናት በሰይፍ ባስፈጀበት ወቅት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ልጇን ይዛ ወደ ግብፅ ስትሰደድ ፈያታዊ ዘየማን «ከሥራ ባልደረባው» ከደክርስ ጋር እንዳገኛቸውና ዳክርስ «እንዝረፋቸው» ሲል ፈያታዊ ዘየማን «እንማራቸው» በማለት ጌታችንን ታቅፎ ግማሽ መንገድ መሸኘቱን የተለያዩ የትርጓሜ መጻሕፍት ይተርካሉ። ፈያታዊ ዘየማን በዚያን ወቅት ያደረገው የ ጽድቅ ሥራ በሕይወት ዘመኑ ተከትሎታል። ከጌታችን ጋር በተሰቀለ ጊዜ ከግራ የተሰቀለው ሲዘብትበት እርሱ ግን «እኔ በሠራሁት ወንጀል ተሰቅያለሁ። በመንግሥ ትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ» ማለቱ በቅዱስ ወንጌል ተ ጽፏል።*

*ፈያታዊ ዘየማን ከጌታ ባገኘው ማረጋገጫ ከውድቀት በኋላ ከፍጥረተ ዓለም ማንም ወደ አልገባባት ገነት በአካለ ነፍስ አምርቷል። ታድያ ገነት ከአዳም በደል ወዲህ የሚገለባበጥ የእሳት ሰይፍ በያዙ መላእክት ትጠበቅ ስለነበር ፈያታዊ ዘየማን ወደ ገነት ማን እንደ ላከውና እንዴት እንደ መጣ የእግዚአብሔር መልአክ በአንቀጸ ገነት ጥያቄ እንዳቀረበለትና ፈያታዊ ዘየማን ለመልአኩ መልስ እንደ ሰጠ «ግብረ ሕማማት» ተብሎ በሚጠራው መጽሐፍ ተጽፎ ይገኛል።*

*«ግብረ ሕማማት» መጽሐፍ የጌታችንን የኢ የሱስ ክርስቶስ መከራ መስቀል ለማዘከር ከሆሳዕና ዋዜ ማ እስከ ትንሣኤ መንፈቀ ሌሊት ከሚነበቡ ቅዱሳት መጻሕፍት አንዱ ነው። ይህ መጽሐፍ በቤተ ክርስቲ ያናችን ከሚገኙ በርካታ አዋልድ መጻሕፍት መካከል አንዱ ሲሆን ይዘቱም ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ ከአዋልድ መጻሕፍት፣ ከአበው ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ድርሳናት ተግሣጽ እና ምክር የተውጣጣ ነው። መጽሐፈ ግብረ ሕማማትን እስትጉቡእ በማድረግ ያዘጋጁት በዕውቀት የመጠቁ በምግባር በትሩፋት የታወቁ በግብፅ የአባ መቃርስ ገዳም መነኮሳት መሆናቸው ይነገራል። በልሳነ ግእዝ የተተረጎመው በ14ኛው ምዕተ ዓመት በነበሩት ዝነኛ መተርጉም አቡነ ሰላማ ካልዕ (1340–1380) ነው። በቅርቡም ከግእዝ ወደ አማርኛ ተተርጉሟል። መጽሐፉ የምሥጢረ ሥጋዌን፣ የምሥጢረ ቁርባንን፣ የትንሣኤ ሙታንንና የነገረ ስቅለትን ጥልቅ ትርጓሜ ከመያዙም በላይ ግእዝን በግእዝ የሚያብራራ ድርሰት መሆኑ ከሌሎች መጻሕ ፍት ይለየዋል። እኛም ከዚሁ መጽሐፍ የሥሩን ኤጲስ ቆጶስ ያዕቆብ ከደረሰው ድርሳነ ፈያታይ ከተባለው ክፍለ ንባብ ውስጥ በፈያታዊ ዘየማንና በእግዚአብሔር መልአክ መካከል በአንቀጸ ገነት የተደረገውን «ቃለ ምልልስ» ይዘን ቀርበናል፤ መልካም ንባብ።*

*ፈያታዊ ዘየማን*

**መጽሐፈ ግብረ ሕማማት**

ፈያታዊ ዘየማን «በመ ንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስ በኝ» እያለ ወደ ፈጣሪ ክርስቶስ ጮኸ። የፈታያዊ ዘየማን ሃይማኖቱ ተገለጠ፤ በሃይማኖቱም ጽናት የፀሐ ይን ብርሃን አቸነፈ ።

የከሐድያን አይ ሁድ ቁጣን እንደ ባሕር ማዕበል በአቸነፈ ጊዜ በጌትነት ህና በትንሣኤህ አስበኝ እያለ ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጮኸ ጌታችን በእንጨት መስቀል ላይ ራ ቁቱን ተሰቅሎ እያለ ያን ጊዜ የመላእክት ሠራዊትን ወይም ኪሩቤል የሚሸከሙ ትን መንበር አላየም፤ የባሕ ርይ ክብሩንም አላየም።

የፈያታዊ ዘየማን ውስ ጣዊ አእምሮው በራ፤ በሃይ ማኖቱም ጽናት «አቤቱ በጌትነትህ አስበኝ» አለ። ፈያታዊ ዘየማን ጌታችን ክርስቶስን በትሕትናው አየው፤ በትንሣኤው በሚገ ለጥበት በባሕርይ ክብሩ አይደለም።

ከእርሱም ይቅርታ ንና ምሕረትን ፈለገ፤ በጌ ትነትህ በምትመጣ ጊዜ አቤቱ አስበኝ አለ።

ልመናውም ወደ ሰማ ይ ደረሰች በጩኸቱም ጽናት «አቤቱ የምሕረት ህን ደጅ ክፈትልኝ፤ ፊ ጽመህ አትጣለኝ» ተድላ ደስታ ወደ አለባት ገነት አስገባኝ አለ።

አቤቱ አዲስ ክብርን ስጠኝ፤ በይቅርታህ ብዛት አድነኝ። ከማያልቀው ከቸ ርነትህ መዝገብ አቤቱ ሰ ማያዊ ሀብትን ስጠኝ፤ የቀድሞውን በደሌንና ኃጢ አቴን አታስብብኝ። ከምግ ባር ከትሩፋት ድኃ ለሆን ኩት ለእኔ ወዮልኝ በዓሥ ራ አንድ ሰዓት ወደ ወይ ንህ ቦታ የገባሁትን እንደ ይቅርታህ ገናናነት ይቅር በለኝ። በወይኑ ቦታ ከጥ ዋት እስከ ማታ ያገለገሉ ደመወዛ ቸውን ለመውሰድ የተገባቸው ዝግ ጁዎች ይሆናሉ፤ እኔ ግን ከቀኑ ያለ አንዲት ሰዓት አላገለገልኩም።

ከጥዋት እስከ ማታ ካገለገሉ ትና ዋጋቸውን ያለ ማፈር ከሚቀበ ሉት ጋራ አቤቱ አንድ አድርገኝ። እኔም አቤቱ እስከ ሚመሽ ቀይቼአ ለሁ፤ ከእኔ በፊት ሲያገለግሉ ለዋሉ ዋጋቸውን በምትሰጥ ጊዜ ይቅርታ ህና ቸርነትህ ትደረግልኝ። አቤቱ ÷ ለእኔ ዋጋ መስጠትን አስቀድሞ፤ ከእኔ በፊት ሲያገለግሉ የዋሉ ደስ ይላቸው ዘንድ። አቤቱ ÷ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ÷ ከአንተ ጋራ መከ ራ ስቀበል ደከምሁ ወደ ሰማያዊ ሰርግህ ጥራኝ። አቤቱ ÷ የጠፋውን ትፈልግ ዘንድ በመጣህ ጊዜ ጻድ ቃንን ልጠራ አልመጣሁም፤ ኃጥአ ንን ወደ ንስሐ ልጠራ ነው እንጂ ብለሃልና። እነሆ እኔ ተጥያለሁ፤ ንስሐ ለሚፈልጉ ሁሉ አርአያ እሆን ዘንድ ከወደቅሁበት አንሣኝ፤ በኃጢአተኛው ንስሐ መግባት በአ ንተ ዘንድ ደስ ይበላቸው።

ጌታዬ ሆይ በሰማያት በአባ ትህ ፊት እመነኝ ፤ በቀያፋ ሠራ ዊት ፊት አምኜብሃለሁና። ፍጥረቱ ሁሉ በፊትህ በሚቆሙ ጊዜ አቤቱ አታርቀኝ። እኔ ከበጎ ሥራ ድኃ የሆንኩ ለሞት የተሰጠሁ በደለኛ እንደ በደሌ በእንጨት ላይ ተሰ ቀልኩ፤ እኔም በማታለሌና ነፍስ ገዳይ በመሆኔ ለሞት የተገባሁ ሆንኩ፤ ከሞትም ወደ ሕይወት ሄድሁ። እኔ መላ ዘመኔን በኃጢ አትና በጨለማ ውስጥኖርኩ፤ በመ ጨረሻዪቱ ቀኔ ግን ብርሃን ተገለ ጸልኝ። አቤቱ እለምንሃለሁ ÷ እማ ልድሃለሁም፤ በታላቂቱ ቀን በጌትነ ትህ በመጣህ ጊዜ ታስበኝ ዘንድ ከቸርነትህ እሻለሁ።

### የኢየሱስ ክርስቶስ መልስ

ጌታ ኢየሱስም ለፈያታዊ መለሰለት፤ አንተ እንዳልከ ይሁን ልህ፤ ተድላ ደስታ በሚደረግበት በገነት ዛሬ ከእኔ ጋራ እንደምት ኖር ደስ እንደሚልህም እውነት እውነት እልሃለሁ።

አንተ ሰው ሆይ ÷ እመነኝ፤ እነሆ አንተ በጨለማ ውስጥ አለህ፤ አንደበትህ ግን ከአብርሃም ጋራ በሕይወት ማዕድ ላይ ክብር ያለ ውን ፍሬ ቃል ይናገራል። እነሆ ÷ አንተ በጨለማ ደመና ውስጥ ነበ ርህ፤ በሃይማኖትህ ብርሃን ግን በሕ ይወት ሰርግ ቤት ውስጥ በራ። ከመላእክት ጋራ ደስ ይልሃል፤ ጆሮ ችህ የስድብ ቃልን ሰምተዋልና ከብርሃን ሠራዊት ጋር ስለ አመንክ ብኝና የቀያፋን ሠራዊትና የአ ይሁድንም ካህናቶቻቸውን ስለ




©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

አሳፈርሃቸው ደስ አሰኝሃለሁ፣ በገነት
የሚገኘውን የክብር ዘውድ አቀዳ
ጅሃለሁ::

አንተ ሰው ሆይ ÷ አንተን እል
ሃለሁ፣ የብርሃን መክፈቻ ውሰድ፣
ተድላ ደስታ ወደ ሚገኝባት ወደ
ገነት ሂድ፡ ለብርሃን ንጉሥም መንገ
ዱን ጥረግ:: በነፋሳትም ላይ ተቀመጥ፣
ያለ ፍርሃት የእሳቱን ባሕር በነበልባሉ
መካከል ተሻገር:: ለመላእክት ሠራዊት
ሁሉ ንግራቸው ድሉንም ሰበክ፣ በገነት
ውስጥም የሰላምን ዐዋጅ ንገር:: ወንጀ
ለኛው አዳምም ወደ ቀድሞ መኖሪ
ያው እንደ ተመለሰ ንገራቸው:: በመን
ገድህም የመላእክትን ሠራዊት ብታገኝ
አትፍራ፣ እነርሱ በያዘ ከው መልእክት
ደስ ይላቸዋልና በክንፎቻቸውም ይሸከ
ሙሃል::

ከዚህም በኋላ ጌታችን ለፈያ
ታዊ የሕይወት መጽሐፍን ጻፈ፣ ያቺ
ንም መጽሐፍ በክበረ ደሙ አተማት፣
አከበራት:: ፈያታዊም በጌታችን ደም
ከበረ፣ ሕይወትንም አገኘ፣ ልጅነትንም
ተቀበለ:: ከጌታ ጐን በፈሰሰው ደምና
ውኃ በመጠመቅ ፈያታዊ ነጻ፣ ብርሃ
ንና ክብር ያሉትንም ልጅነት ተጎና
ጸፈ:: የገነትን መክፈቻ ያችንም መ
ጽሐፍ ተቀብሎ የእሳቱን ባሕር ተሻ
ገረ፣ ነበልባሉም አላቃጠለውም:: ከእ
ሳቱ መካከል ካለው መንገድ በደረሰ
ጊዜ መልአክ አገኘው፣ በቁጣ መረመ
ረው፣ አንተ ማን ነህ? ንገረኝ፣ ከወዴ
ትስ መጣህ? በእሳቱ ውስጥስ እንደምን
አለፍክ? አለው::

ነፋሳቱስ በቃጠሎው ውስጥ እን
ዴት በኃይላቸው ተሸከሙህ? ደካማ
አንተንስ እንዴት አላቃጠለህም::

የእሳቱን ባሕር እንዴት አለፌክ?
ወይም ትእዛዙን የጠበቀ፣ የእግዚአ
ብሔር አገልጋይ የተባለ መልከ ጼዴቅ
አንተ ነህን? የማዕበሉቿ ነበልባል
እንዴት አላቃጠሉህም፣ በእሳቱ ባሕር
ላይ ሥልጣን የሰጠህ ማነው? አንተ
ሰው ሆይ ÷ እስቲ ንገረኝ:: ታላቋን
አስደንጋጭ የእሳት ባሕር መሻገርን
እንዴት አልፈራህም? አንተ እግዚ
አብሔር በእጁ የፈጠረው አዳም ነህን?
ወይም ትሩፋቱ ብዙ የሆነ ጻድቁ ሴት
ነህ? ወይም የጥፋት ውኃ ማዕበልን
ድል የነሣና በንጹሕ መሥዋዕቱ እግዚ
አብሔርን ደስ ያሰኘ ኖኅ አንተ ነህን?
የአባቶች አባት አብርሃም ወይም
በሾተል ከመታረድ የዳነው ይሥሐቅ
አንተ ነህን?

እግዚአብሔርን በመሰላል ላይ
ፊት ለፊት ያየው ያዕቆብ ወይም
ኃይለኛ እንደ መሆኑ የሰይጣንን ጦር
ድል ያደረገ ዮሴፍ አንተ ነህን?

በሕዝብ ፊት ባሕረ ኤርትራን
የከፈለ ማዕበሉንም ጸጥ ያደረገ ከእግዚ
አብሔር ጋርም የተነጋገረ ሙሴ
ወይም ስለ ስእለቱ ሴት ልጁን ለእግዚ
አብሔር የሠዋ ዮፍታሔ አንተ ነህን?

በትንቢቱ ጌታን መንክር ብሎ
የሰየመው /የጠራው/ ነቢዩ ኢሳይያስ
ወይም እግዚአብሔርን በሰረገላው ሁኖ
ያየው ሕዝቅኤል አንተ ነህን?

የአንበሶችን አፍ የዘጋ ዳንኤል
ወይም በእሳት ወላፈን ያልነካቸው ሠለ
ስቱ ደቂቅ አንተ ነህን?

በባሕር ላይ የሄደ ስምዖን ጴጥሮስ
ወይም በጌታ ኢየሱስ አጠገብ የተቀ
መጠ ዮሐንስ ወይስ በጌታ ኢየሱስ ራስ
ላይ እጁን የጫነ በርግብ አምሳልም
መንፈስ ቅዱስ በላዩ ሲወርድ ያየና
«የምወደው ልጄ ይህ ነው፣ በእርሱም
ደስ የምሰኝበት» የሚል የአብን ቃል
የሰማ የዘካርያስ ልጅ ዮሐንስ አንተ
ነህን?

አንተ ደካማ ሰው ንገረኝ፣ አንተ
ማነህ? የእሳት ባሕሮችን በርትተህ የተ
ሻገርህ፣ አቃጥለው ያላጠፉህ ብሎ ጠ
የቀው::

ፈያታዊ ዘየማንም መለሰ፣ ተወ
ዳጅ መልአክ ሆይ ÷ አትቆጣ ÷ እኔ
ማን እንደ ሆንኩ የላከኝም ማን እንደ
ሆነ እነግርሃለሁ አለው::

መላ ዘመኔን በክፉ ሥራ ያሳለ
ፍኩ ወንበዴ ነኝ፣ የሰውን ደም ተቀባሁ፣
እቀማ ዘንድ በመንገድ እሸምቅ ነበረ::
ባለጸጎችን አደኸየኋቸው፣ ድኾችንም
አጠፋኋቸው፣ ሽማግሌዎችን ሕፃናትንና
ወጣቶችን /ጎልማሶችን/ አልራራሁላ
ቸውም፣ ብዙ ግድያም ገደልኋቸው፣
በሰው ደምም እንደ ውኃ ታጠብሁ::

መልአኩም:- የፈያታዊን ነገሩን
በሰማ ጊዜ ተደነቀ፣ ደነገጠም:: ረቂቃን
መላእክት ሠራዊትንም ጠራቸው፣ ወደ
እርሱም ፈጥነው መጡ:: የመላእክት
ማኅበር ሆይ ÷እስኪ ኑ ዛሬ ከእኔና ከዚ
ህ ከምድራዊው ሰው ጋራ በመሆን
አድንቁ፣ ማለት /አስደናቂ ነገርን
ስሙ/::

ወደ ፈያታዊ ዘየማን ተመልሶ
አንተ ደካማ ÷ወደ ሕያዋን መላእክት
ሀገር እንግዲህ ምን ልታደርግ መጣህ?
አለው::

አንተ የሰው ደም የተቀባህ ÷
በየትኛው መንገድ ወደኛ መጣህ? የእ
ሳት ወላፈን ያላቃጠለህ:: አንተ ሌባ ÷
በሀገራችን ውስጥ ምንም ምን የምትሰ
ርቀው የለም:: ነፍሰ ገዳይ ሆይ ÷ መላ
እክትን ልትገድላቸው አትችልም:: አን
ተ ሰዎችን ያጠፋህ ረቂቃን መላእክትን
ታጠፋቸው ዘንድ አትችልም:: የሣር
ገለባ ሆይ ÷ የእሳቱን ባሕር እንዴት
አለፍክ፣ በረቂቃን መላእክት መካከል
ምን ትሠራለህ? የብርሃናውያን መላእ
ክት እሳት የሆነው የክንፋቸው ዋዕይ
እንዳያቃጥልህ ወደ መጣህበት ሀገርህ
ተመልሰህ ሂድ::

አንተ ዐፈር ሆይ ÷የገነት ቅጽርዋ
እሳት እንደ ሆነ አስተውል፣ ወደ
እርስዋም መቅረብ አትችልም፣ ወደ እር
ስዋም ብትቀርብ ደካማ አንተን ታቃ
ጥልሃለች:: አንተ ሽፍታ ÷ በእሳቱ
መከማቻ ላይ ትሻገር ዘንድ እንዴት
በረታህ አለው::

ፈያታዊ ዘየማንም መልሶ መል
አኩን እንዲህ አለው:- ረቂቅ መልአክ
ሆይ ÷ ነገሬን ስማኝ፣ ምንም በክፉ
ሥራ ሁሉ ብኖር ነገር ግን የጌታ
ምሕረት ከጥፋት ወደ ሕይወት አነሣኝ
ከበደሌ ሁሉም አነጻኝ:: መላ ዘመኔን
በመበደልና ነፍስ በመግደል አሳለፍኩ፣
በመጨረሻዋ ቀኔም የጌታ ምሕረት
ወደ ሕይወት ሳበችኝ::

መልአክ ሆይ ÷ቃሌን ስማኝ፣
እነሆ ሰማያዊ ንጉሥ ጌታህ ሕይወትን
የሰጠኝ እርሱ ነዋ! አምኜበታለሁና
በአመንኩበት ጊዜ ወደ ሕያዋን ሀገር
እገባ ዘንድ የይቅርታውን በር ከፈተ
ልኝ:: መልአክ ሆይ ÷ ኃጥኡ ንስሐ
በገባ ጊዜ ደስ ይልህ ዘንድ ይገባሃል፣
ጌታህም እንደ እኔ ያለው ወደ እርሱ
በንስሐ በተመለሰ ጊዜ ደስ ይለዋልና::
ዳግመኛም ንስሐ በሚገባ ጊዜ ስለ
አንድ ኃጥእ መላእክት ሁሉ ደስ ይላ
ቸዋል አለው::

መልአኩም ለሽፍታው መለሰ፣
መንገዱን ይጠርግ ዘንድ ከመላእክት
አንዱን ያልላከ እንዴት ነው፣ የአባ
ቶች አለቃ አብርሃምን ትቶ እንግዲህ
አንተን ለምን ላከ አለው:: ሙሴንስ
እንዴት አልላከም? የነዌ ልጅ ኢያሱን
ወይም አልያስን ወይም ደቀ መዝሙሩ
አልሳዕን እኒህ ሙታንን ያነሡ መንፈ
ሳውያን ነቢያት ሳሉ አንተን እንዴት
ላከ? ልደቱን ሕማሙን ሞቱን ትንሣ
ኤውን ወደ ሰማይ ማረጉን አይቶ
ትንቢት የተናገረ ነቢዩ ዳዊትን ለምን
አልላከም? በሠረገላው ላይ ሁኖ ሳለ
እግዚአብሔርን ያየው ሕዝቅኤልን
ለምን አላልከም? የዕለቲቱን የድካ
ሟን ክብደት የተሸከሙ፣ የፀሐዩንም
ትኩሳት የቻሉ ከመምጣቱ በፊት
በትንቢታቸው እንደ ነጋሪት ድምፅ
አሰምተው የተናገሩትን ትቶ አንተን
እንዴት ላከ?

ጻድቁን አቤል የበጎ ሥራ ተመ
ልካች የነበረ ሴት ÷ የተመረጠ ኖኅና
ወዳጁ አብርሃም ልጁ ይስሐቅና እስራ
ኤል የተባለው የከበረ ያዕቆብስ ወዴት
አሉ? እነዚህ የተመረጡ የመንግሥት
ልጆች ናቸው፣ እርሳቸውን ትቶ የሰው
ደም የተቀባህ አንተን መንገዱን ትጠ
ርግ ዘንድ አንዴት ላከህ? አለው::

ፈያታዊ ዘየማንም ለመልአኩ
መለሰለት፣ መንፈሳዊ ሆይ ÷ ቃሌን ስ
ማኝ፣ ከመላእክት ጋራ ለመከራከር
ሳይሆን ጌታህ ወደ ገነት ስለ ላከኝ
ነው እንጂ:: ከወደቅሁበት የጌታ ምሕ
ረት አንሥታኛለችና፣ ስለዚህም አንተ
ያልካቸውን ጻድቃን ትቶ እኔን ላከኝ
እነዚህ ደጋጎች በታላቅ ክብር ከጌታ
ጋራ ይመጣሉና:: እኔን ግን በመስቀል
ላይ ሳለ ወደ ገነት ላከኝ፣ በሽተ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ኞች ባለ መድኃኒትን ይሹታል፤ ፈውስ የሚሹ ጤነኞች አይደሉም። እኔን ፈጽሞ ይቅር አለኝ፤ የእኔንም ወደ ገነት መላክ አስቀደሞ ከዕለቷም ያለ አንዲት ሰዓት አላገለገልኩም ነበር። አሁንም የጌታ መልአክ ሆይ ÷ የእግዚአብሔርን ቃል ስማ የእሳቱንም መክፈቻ አንሣ፤ ንጉሡ ጌታህ በእንጨት መስቀል ላይ ሳለ መክፈቻ ሰጥቶ ልኮኛልና።

መልአኩም መለሰ ፈያታይ ሆይ ÷ አንተን እናገራለሁ፤ ጌታህ እስከ ሚመጣ ድረስ ከቶ ከሕያዋን ሀገር አትገባም፤ በእርሱ ዘንድ እስካይ ድረስ ያችን ጸጋ አታያትም። የአዳም ጌታው እስከ ሚመጣና እስከ ሚከፍት በአዳም ምክንያት የተዘጋውን በር አልከፍትም። አንተ ፈያታዊ ስማ፤ መላእክት ስንኳ ክብርዋን ያዩ ዘንድ አይችሉም፤ የሰውን ደም የተቀባኸውን አንተን ወደ ገነት ይልካልን? አለው።

ሽፍታውም ለመልአኩ መለሰለት፤ ሰማይ ሲታወክ ምድርም ጸጥ ብላ ሳለች ወልድ ፍቁርም በእንጨት ላይ ተቅሰሎ ሳለ በጌታ እኔ አመንኩበት አለው፤ በአመሰገንሁትም ጊዜ ፍጥረቱ ሁሉ አደነቁ፤ ይህንንም መጽሐፍ ጻፈልኝ።

አንተ ሰው ሆይ ÷ እመነኝ፤ ዛሬ ከእኔ ጋራ በገነት እንደ ምትኖር እውነት እውነት እልሃለሁ አለኝ። የሰማይ መላእክትም በእኔ ደስ ተሰኙብኝ።

ጌታህ መከራ በተቀበለበት ቦታ ምእመናን በዚያ አልነበሩም፤ ፍጥረት ሁሉ በድንጋጤዋ ጸጥ ባለ ጊዜ የሰማይ ሠራዊት በመፍራትና በመንቀጥቀጥ ፊታቸውን በሸፈኑ ጊዜ ገብርኤል አንገቱን ሲደፋ ሚካኤልም ወደ እርሱ ሲመለከት ከእኔ ከብቻዬ በቀር ማንም የለም ነበር። የእሾህ አክሊልን በራሱ ላይ ነው፤ ረቂቃን የመላእክት ሠራዊት በመደንገጥ ቆመው ነበር። ከመፍራት የተነሣ ሐዋርያት ሰጉ፤ እናቱ ማርያምም ከሩቅ ቆማ ታለቅስ ነበር። የከሀድያን አይሁድ ሁከትም እንደ ባሕር ማዕበል ሆነ፤ ቀኑንም ጨለማ ሸፈነው።

የቀያፋም ሠራዊት ፈጥነው ሸሹ፤ ከዚህም ሁሉ ጋራ እኔ ዝም አላልኩም፤ በጽኑዕ ሃይማኖት ብቻዬን እግዚአብሔርን አመሰገንሁት እንጂ። ሕዝቡም እየጮኹ የስድብ ቃል ይናገሩ ነበር። እኔ ግን የክብር ባለቤት የሆነ የእግዚአብሔርን በግ በእንጨት መስቀል በተሰቀለ ጊዜ አመሰገንሁት፤ የቀያፋ ሠራዊትም በእርሱ ላይ ይዘባበቱ ነበር። ያን ጊዜ አንተ ወዴት ነበርክ? መላው መላእክትስ ሰማይና ምድር ፍጥረት ሁሉ በድንጋጤ ጸጥ ባለ ጊዜ ዓለሙንም ጨለማ በዋጠው ጊዜ ያን ጊዜ አንተ ወዴት ነበርክ?

የኃይልህን ብርታት በኔ ላይ ነውን የምትገልጽ፤ ጌታችሁን በቸነከሩት ጊዜ ለምን ዝም አላችሁ፤ ፊቱን በጸፉትስ ጊዜ አንዲት አልተናገራችሁም፤ ምራቃቸውን በተፉበት ጊዜ ከእርሱ ለምን ራቃችሁ፤ ራስህን አድን በአሉት ጊዜስ ለምን ተንቀጠቀጣችሁ፤ ከእርሱ ጋራ የሚኖር የሐዋርያት አለቃ ስምዖን ጴጥሮስ ካደ ፤ እንደ ማያውቀውም ማለ። በግምጃ ቤቱ ላይም አምኖ የሾመው ይሁዳ አሳልፎ ሸጠው፤ የሽያጩንም ዋጋ ወሰደ፤ ከአጠገቡ የሚቀመጠው ግን በመከራው ጊዜ ከእርሱ ጋር በመታገሥ አልተለየም። በበረሀ ውስጥ በአምስት እንጀራና በሁለት ዓሣ አምስት ሺህ ሰው በአጠገበ ጊዜ እኔ ከእርሱ ጋራ አልነበርሁም። ውኃውን ጣፋጭ ጠጅ ባደረገው ጊዜ ከጠጁ አልጠጣሁም። ባሕሩንና ነፋሳቱን በገሠጸና እነሱም በታዘዙለት ጊዜ፤ ከእርሱ ጋራ አልነበርኩም። ከአራት ቀን በኋላ የሞተውን ከመቃብር ባስነሣ ጊዜ አላየሁም። ክፉዎች ሰዎች የቄሣርን ግብር ከእርሱ በፈለጉ ጊዜ ከእርሱ ጋራ አልነበርኩም፤ክፉዎች አጋንንትን ከሰዎች ላይ አስወጥቶ በሰደዳቸው ጊዜ አላየሁም። ከአስደናቂዎች ተአምራት ምንም ምን ያየሁት አልነበረም። ደግሞም አላየሁትም፤ በእንጨት መስቀል ላይ ተሰቅሎ አይቼ አመንሁበት እንጂ።

የድንግልን ማኅፀን ድንግልናዋ ሳይለወጥ ጠብቆ ሲወለድ አላውቅም ነበር። በበረት ውስጥ እንደ ሕፃን በጨርቅ ተጠቅልሎ ሳለ አላየሁም። ሰብአ ሰገል ወርቅ ይዘው መጥተው በአዩት ጊዜ አላየሁም። ደግሞም በደብረ ታቦር ላይ መልኩ በተለወጠና ለደቀ መዛሙርቱ ክብር በገለጠ ጊዜ አላየሁም። የአብ ቃል ከሰማይ የምወደው ልጄ ይህ ነው ፤ በእርሱም ደስ ይለኛል ባለ ጊዜ አልሰማሁም። በስምዖን ዘለምጽ ቤትም ሳለ ሴቲቱን «ኃጢአትሽ ተሰረየልሽ» በአላት ጊዜ ከእርሱ ጋራ አልነበርሁም። የኢያኢሮስን ልጅ ከሞት በዳናት ጊዜ ከእርሱ ጋራ አልነበርሁም። መፃጉዕን በአስነሣውና «አልጋህን ተሸክመህ ወደ ቤትህ ግባ» በአለው ጊዜ አላየሁም።

ደንቆሮዎችን እንዲሰሙ ዲዳዎችን እንዲናገሩ ባደረገ ጊዜ ከእርሱ ጋራ አልነበርኩም። ነገር ግን በእንጨት መስቀል ላይ ተሰቅሎ ስለ አመንሁት እንጅ።

አይሁድ ልብሱን በተካፈሉና በቀሚሱ ላይ ዕጣ በተጣጣሉ ጊዜ ሐዋርያት በሩቅ ቆመው ሲመለከቱ መላእክትም ከፍርሃት ብዛት የተነሣ ዝም ባሉ ጊዜ ከእርሱ ጋራ ነበርኩ፤ ያን ጊዜም አየሁት። ጎኑን በጦር በተወጋ ጊዜ ያቺም እንጨት በከበረ ደሙ በተቀባች ጊዜ ፍጥረት ሁሉ በመፍራትና በመንቀጥቀጥ ሁኖ ሳለ ከዚህ ሁሉ መከራ ውስጥ ሁኖ ወልድን አየሁት። መልአክ ሆይ ÷ እነግርሃለሁ፤ እኔ ዝም አላልኩም፤ በጌትነቱ በሚመጣ ጊዜ እንዲያስበኝ ያን ጊዜ ለመንሁት፤ ልመናዬንም ወዲያውኑ ተቀብሎ ወደ አንተ ላከኝ። አሁንም የተላከ ሁበትን ጽሑፍ ተቀበል፤ አንብባትም፤ የታላቁንም ንጉሥ ማኅተም ተመልከት።

መልአክ ሆይ ÷ የእሳቱ መዝጊያ የሚከፈትበትንም የእሳቱን መክፈቻ ያዝ አለ። በጌታችን ደም የታተመ ያችን መጽሐፍ በአያት ጊዜ በፊቱ ሰገደ፤ አከበረው፤ አቀፈውም በረቂቃን ክንፎቹም ጋረደው።

ፈያታዊ ዘየማንንም መሬታዊ ሆይ ÷ በጌታህ ትእዛዝ መጥተሃልና ሰላምታ ይገባሃል አለው፤ በረቂቃን መላእክት ማደሪያ ውስጥ ግባ፤ በዚያም ደስ ይበልህ። አዳም ከወጣባት ተድላ ደስታ ከሚፈጸምባት ገነት ውስጥ ግባ። በሰማያት ካለ የመላእክት ሠራዊት ጋራ ወደ ሰማያዊ መንግሥት ገብተህ አንድ ሁን፤ ፈያታዊ ሆይ ገብተህም ከቁስልህ ተፈወስ፤ ለዚህች ክብር ጌታህ ዝግጁ አድርጎሃልና። እነሆ ሰማያውያንና ምድራውያን በየነገዳቸው ስለ አንተ ያደንቃሉ። በምድር ወንበዴ ቀማኛ ሁነህ ኑረህ በኋለኛዪቱ ቀን የመንግሥተ ሰማይ ወራሽ ሁነህልና።

በዚያች ምድር ነፊስ ገዳዩ ነበርክ፤ በኋላኛዪቱ ቀን ረቂቁን የኋለኛ ይቱ ክብር ለመቀበል በቃህ። ፈያታዊ ሆይ ÷ የላከህ ንጉሥ ወዴት አለ? ምን ይሠራል መምጣቱስ እንዴት ዘገየ? ይፈልገው ዘንድ ከከፍተኛ ማደሪያው ወርዶ የነበረው ጌታ እነሆ አዳምን አድኖታልና።

ፈያታይም ለመልአኩ መለሰ፡- ሲኦልን ይበዘብዝ ዘንድ በዚያም ተማርከው የሚኖሩትን ነፍሳት ያወጣ ዘንድ ንጉሡ ወደ ሲኦል ወረደ አለው። ሙታንን ሕያዋን የሚያደርግበት ታላቅ ጥበብ አለው፤ ሞትን ያጠፋ ዘንድ ወዶአልና። እነሆ ንጉሡም የታሰሩ ነፍሳትን ያወጣ ዘንድ ወደ ምውታን አገር ገባ፤ ኀፍረቱን ይሸፍንለት ዘንድ ለአዳም የሕይወት ልብስ አዘጋጅቶለታል።

ንጉሥ ሙታን ወደ አሉበት ገባ፤ እነርሱም ስለ ድኅነታቸው አመሰገኑት፤ ዘር ዝናምን በተስፋ እንደ ሚጠብቅ፤ እነርሱ በተስፋ ይጠብቁት ነበርና። መላእክት ሆይ ÷ ወደ ሲኦል ትወርዱ ዘንድ በዚያም የኃይላችሁን ጽናት ታሳዩ ዘንድ ለእናንተ ተገቢ ነው። ገብርኤል ሆይ ÷ቀድሞ ለቅድስት ድንግል ማርያም ልደቱን እንደ አበሠርሃት አስቀድመህ በዚያም እንደ ሰው ሲተኛ ታየው ዘንድ ይገባሃል። አንተም ጽኑዕ ኃያል የሆንክ ሚካኤል ሆይ ÷ጽኑዕ የሆነውን ኃይልህን በግብጻውያን ላይ ገልጸህ

/ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል/





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

*ባለፈው እትማችን ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም በውዳሴ ማርያም ድርሰቱ እመቤታችንን እየመሰለ ያመሰገነባቸውን ቃላትና ሐረጋት ከነምሳሌያቸውና ትርጉማቸው ዐይተናል:: ተከታዩን ክፍል ደግሞ እንደ ሚከተለው አቅርበናል:: መልካም ንባብ::*

# ምሥጢረ ሥጋዌ በውዳሴ ማርያም

*/መምህር ኃይለ ማርያም ላቀው/*

*/የመጨረሻ ክፍል/*

## ከጸኑ የጸናች

ከሌሎች አንጻር ስንመለከተው ጽኑዕ ሲባል በአንድ በኩል ጉድለት የሌለበት በዓለም ዘንድ አይገኝም:: እመቤታችን ከመጸነሷ በፊት፣ በጸነሰች ጊዜ፣ ከጸነሰችም በኋላ ከመውለዷ በፊት፣ በወለደች ጊዜ፣ ከወለደችው በኋላ፣ ማኅተመ ድንግልዋ ያልተለወጠ ጽንዕት ነች:: የብሉይ ኪዳን ቅድስተ ቅዱሳን፦ ከሊቀ ካህናቱ በስተቀር ወደ እርሷ ሌላ ባለመግባቱ፣ ድምፅ ሰምቶ በመውጣቱ፣ ቅድስተ ቅዱሳን ተብላ ተጠርታለች:: ይኸውም የብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህን ብቻ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን እንደ ሚገባ ሁሉ በእመቤታችን ማኅፀን ያደረውም የሐዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት ተብሎ የተጠራ፣ ራሱን መሥዋዕት አድርጐ ያቀረበ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::

የብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናት ከሐዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት /ኢየሱስ ክርስቶስ/ ልዩ የሚያደርጉት ነጥቦች አሉ:: የብሉይ ኪዳኑ ሊቀ ካህናት ለመሥዋዕቱ ይዞት የሚገባው የእንስሳትን መሥዋዕት ነበር:: ሥግው ቃል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ራሱን መሥዋዕት አድርጐ አቅርቧል::

## የወርቅ ማዕጠንት

ሊቁ የመለኮትንና ትስብእትን ተዋሕዶ በመንፈሳዊ ዘዴ ለማስተማር እመቤታችንን በወርቅ ማዕጠንት ይመስላታል:: «አንቲ ውእቱ ማዕጠንት ዘወርቅ እንተ ጾርኪ ፍሕመ እሳት፤ እሳትነት ያለውን ፍሕም የተሸከምሽ የወርቅ ማዕጠንት አንቺ ነሽ::» ይላል:: «በሰማያውያን የካህናት አለቆች እጆች ውስጥ ባለ የወርቅ ማዕጠንት እንመስልሻለን» ይላል:: /አንቀጸ ብርሃን/:: እግዚአብሔር ባሪያውን ሙሴን የወርቅ ማዕጠንት ሠርቶ በውስጡም ፍሕምና ዕጣን እንዲጨምርበት አዝዞታል:: ዘጸ. 30÷1–10:: ይህን ለሊቀ ነቢያት ሙሴ ከብዙ ዓመታት በፊት የተሠራውን ምሳሌያዊ ሥርዓት ሊቁ በማገናዘብ የመለኮትንና የትስብእትን ተዋሕዶ ያሳየናል:: እመቤታችን በወርቅ ማዕጠንት ትመሰላለች:: ወርቅ የንጽሕናዋና የቅድስናዋ ምሳሌ ነው:: የሙሴ መሶበ ወርቅ ከሞት የሚያድነውን መና ስትይዝ እመቤታችንም ከሞት የሚያድነውን መና ኢየሱስ ክርስቶስን ይዛ ተገኝ ታለች::

ፍሕም፦ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የመለኮቱ ምሳሌ ሲሆን ዕጣን ደግሞ የሰውነቱ ምሳሌ ነው:: ዕጣንና ፍሕም በሚገናኙበት ጊዜ ከማዕጠንት ውስጥ መልካም መዓዛ ይወጣል:: በእመቤታችን ሥጋና መለኮት በተዋሐዱ ጊዜ ዓለም በትምህርቱ የሚማረከበት፣ የሚድንበት የሚለወጥበት የሥነ ምግባር መዓዛ የድኅነት መዓዛ ኢየሱስ ክርስቶስ ተገኝቷል:: ማዕጠንት እመቤታችን ነች:: የብሉይ ኪዳን ማዕጠንት ፍሕምና ዕጣን ይዛ እንደ ተገኘች እመቤታችን ድንግል ማርያም መለኮትና ትስብእት /መለኮትና ሰውነት/ ተዋሕደውባታል:: ሊቁ በእመቤታችን ማዕጠንትነት መድኃኒታችን ራሱን መሥዋዕት አድርጐ እንደ ቀረበ ሲገልጥ፦ «ዘአዕረገ ለአቡሁ ርእሶ ዕጣነ ወመሥዕተ ሥሙረ፤ ለአባቱ ራሱን ያማረ የተወደደ መሥዋዕት አድርጐ ያቀረበ» ይላል:: ይኸውም የእግዚአብሔር ወልድ መሥዋዕትነቱ የተወደደ ያማረ መሥዋዕት ሆኖ በቀረበ ጊዜ በመሥዋዕትነቱ እግዚአብሔር አብ እንደ ተደነቀ የሚገልጥ ኃይለ ቃል ነው:: እንግዲህ ሊቁ በመለኮትና በትስብእት መዋሐድ የተገኘውን ድኅነት ገልጾልናል::

## የኪዳን ታቦት

ሊቁ ቃለ እግዚአብሔር ሥጋ መሆኑን ከድንግል ሥጋንና ደምን መዋሐዱን በታቦቱና ታቦቱ ላይ በሚጻፈው ቃል መስሎ ሲያስተምር፦ «ከማይነቅዝ እንጨት የተቀረጸ በውስጥና በውጭ በወርቅ የተለበጠ ታቦት ያለመለወጥ ሰው የሆነን የእግዚአብሔርን ቃል ይመስልልናል:: የእሥራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን ብቻ እንዲከተሉ ከእርሱ ሌላ ባዕድ አምላክ እንዳያመልኩ ይህም ፍላጐቱ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሕግ ሆኖ እንዲኖር በሙሴ አማካይነት ትእዛዝ የተጻፈባቸውን ጽላት ሰጥቷል:: ዘጸ. 33÷10 -18:: ለጽላቱም ታቦት እንዲዘጋጅ ተደረገ:: ጽላት ሕጉ የተጻፈባቸው ሰሌዳዎች ሲሆኑ ታቦት ደግሞ ጽላት የሚቀመጥበት ማኅደረ እግዚአብሔር ነው:: በብሉይ ኪዳን የነበረው ሥርዓት ይህን ይመስላል::

«ታቦትን ደግሞ ከማይነቅዝ እንጨት ሥራ፤ በዚያም ተገልጬ እነጋገርሃለሁ» ሲል ልዑል እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ የተመላበትን ትዕዛዝ እናነባለን:: ዘጸ.25÷5፤ ዘጸ.33÷10:: ሙሴም እንደታዘዘ አድርጓል:: ከዚህ በኋላ ጽላትን ለብቻው ታቦትን ለብቻ ለይቶ የሚጠራ አናገኝም:: በጠቅላላ አጠራሩ ስሙ ታቦተ እግዚአብሔር፣ ታቦተ ሕግ፣ ታቦተ ኪዳን፣ ታቦተ ሰምዕ የሚልና ይህን የመሳሰሉ ስያሜዎች አለው:: ትርጓሜውም እግዚአብሔር ያደረበት፣ አድሮበት የሚኖር ሕጉ የሚጠበቅበት ኪዳኑ የሚጸናበት አምልኮቱ የሚመሰከርበት ነው:: ሕዝበ እሥራኤል በዚህ ታቦት አማካኝነት ሁሉን ቻይ የሆነውን ኃያል አምላክ እግዚአብሔርን ሲያመልኩ ሥርዓተ አምልኮትን ሲፈጽሙ ኑረዋል::

በጽላቱ የተጻፈው /የተጻፈበት ሕግ /ቃል/ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሲሆን ሕጉ የተቀረጸባት ጽላት የእመቤታችን የድንግል ማርያም ተምሳሌት ነው:: ሊቁ በግልጽ «ሰው የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ይመስልልናል::» በማለት «መጀመሪያ ቃል ነበር፤ ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበር» ዮሐ.1÷1· የሚለውን አምላካዊ ቃል ያጠናክራል::

ሕጉ በጽላቱ ላይ በግብር አምላካዊ ወይም በአምላክ ጣቶች እንደ ተጻፈ ቅድስና የተጻፈባት፣ የአምላክ ሰውነት የተቀረጸባት መለኮት ሰውነትን የቀረጸባት እውነተኛይቱ ጽሌ እመቤታችን ድንግል



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

ማርያም ናት። የሙሴ ጽላት እሥራኤል ሊጠብቁት የሚገባ ሕግ እንደ ተጻፈባቸው እኛም ልንከተለው የሚገባ አካላዊ ቃል የመልእኩን ብሥራት «ይሁንልኝ፣ ይደረግልኝ» ባለች ጊዜ የዕለት ጽንስ ሆኖ ተቀርጾባታል። መለኮት ከሥጋ ጋር የተዋሐደባት እመቤታችን ነች። ሊቁ ኤራቅሊስ «ሥጋን በማኅፀኗ ፈጥሮ ተዋሐደው» ይላል። ሃይማኖተ አበው ዘኤራቅሊስ። በማኅፀኗ ሥጋን ፈጠረ፣ ያንን ተዋሐደው፣ አንድ አምላክ አንድ ባሕርይ በመሆኑ አንድ አምላክ ተባለ።

እንግዲህ እውነተኛ የእግዚአብሔር ማደሪያ ታቦት ምሳሌዋ የሆነችው እመቤታችን ድንግል ማርያም ናት። ይኸውም እግዚአብሔር ለእሥራኤል ምድረ ርስትን እንደሚያወርሳቸው ቃል እንደ ገባ ሁሉ እኛንም መንግሥተ ሰማያትን እንደ ሚያወርሰን ቃል ገብቶልናል። በታቦቱ ያደረ እግዚአብሔር ለእሥራኤል ጠላቶቻቸውን እንደ ረታላቸው ሁሉ በድንግል ማርያም አድሮ ሰው የሆነ እግዚአብሔር ቃል እግዚአብሔር ወልድ ጠላቶቻችንን አጋንንትን ድል እንደ ምናደርግ ቃል ገብቶልናል።

የብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናት ከታቦቱ ላይ በመነጋገር ድምፅ ይሰማ እንደ ነበር ከእመቤታችን ሰው የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለምእመናን የይቅርታ ድምፅን ማለትም «ኃጢአትህ ተሰረየልህ፣ ኃጢአትሽ ተሰረየልሽ» በማለት አሰምቷል። ያ ታቦት የይቅርታ መገኛ እንደ ኾነ ሁሉ ከእመቤታችን ሥግው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው በሆነ ጊዜ ምሕረትና ይቅርታ ተገኝቷል።

## መና ያለባት የወርቅ መሶብ

ከላይ ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም እመቤታችንን በማዕጠንተ ወርቅ፣ ልጇን ከፍሕም ጋር በተዋሐደ ዕጣን በማስከተልም እርሷን በታቦት፣ ልጇን በታቦቱ ላይ በተጻፈው ቃል መስሎ የሰበከውን ምሥጢረ ሥጋዌ ተመልክተናል። ዳግመኛ ሊቁ እመቤታችንን በወርቅ መሶብ ልጇን በመና /በእንጀራ/ መስሎ ያመሰገነውን ምስጋናና ትምህርት እንመለከታለን። ይህን ትምህርት ሊቁ እንዲህ በማለት ያስተምረናል። «የተሰወረ መና ያለብሽ ንጹሕ የወርቅ መሶብ አንቺ ነሽ» ይላል። እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ገበሬ በሚያርስበት፣ ዝናም በሌለበት፣ ዘር በማይበቅልበት በረሃማ ሥፍራ መግቦቱን ለመግለጽ መና ከሰማይ አውርዶ መግቧቸዋል። ዘጸ.16÷16። ይህን መና ትውልድ አልፎ ትውልድ ሲተካ ትምህርት፣ አርአያ አድርገው የእግዚአብሔርን ቸርነት እንዲያስታውሱበት መናውን በወርቅ መሶብ አድርጎ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ እንዲያስቀምጥ ሥርዓት ሠርቷል። ዘጸ.16÷33።

እንግዲህ በወርቅ መሶብ እንዲቀመጥ የታዘዘው መና የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሲሆን መናው የተቀመጠባት የወርቅ መሶብ ደግሞ የእመቤታችን የድንግል ማርያም ምሳሌ ናት። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሕይወት እንጀራ ሲያስተምር እስራኤል በበረሃ ከተመገቡት መና የእርሱ መናነት እንደ ሚከብር ሲያስተምር፦ «አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ፤ ሞቱም ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው» ብሏል። ዮሐ. 6÷45-51። የእርሱን እንጀራነት አምኖ የሚመገብ የዘላለም ሕይወት እንዳለውና በመጨረሻውም ቀን እርሱ እንደ ሚያስነሣው አስተምሮናል። ዮሐ. 6÷ 55። ያ እስራኤል በበረሃ የተመገቡት ግን ምሳሌ እንጂ ዘላለማዊ ሕይወት የሚሰጥ አይደለም። ምክንያቱ በበረሃ ያንን የተመገቡ ሁሉ የዘላለማዊ ሕይወትን አላገኙምና ነው።

ነቢዩ ኤልያስ ከኤልዛቤል ፊት በሸሸ ጊዜ «መና በወርቅ መሶብ አግኝቶ ተመግቧል። ይህንም አስመልክቶ አባ ሕርያቆስ እመቤታችንን፦ «የኤልያስ የወርቅ መሶብ አንቺ ነሽ» ሲል አመስግኗታል። እመቤታችንም በመሶብነቷ ይዛው የተገኘችው መና ዘላለማዊ፣ ቀዳማዊና ደኃራዊ ነው። ደኃራዊነቱ ከቅድስት ድንግል ሰው በመሆኑ ፊተኛው ልደቱ ዘመን ሳይወሰንለት በዚህ ጊዜ በዚህም ሰዓት በማይባልበት ወራት ከአብ መወለዱን ያመለክተናል። ስለዚህ እመቤታችን «የከበረች፣ የሕይወት መና የተገኘባት» ተብላ ትኖራለች። ነቢዩ ኤልያስ ከመሶበ ወርቅ ያገኘውን መና ተመግቦ በዚያ ምግብ ኃይል አርባ ሌሊትና አርባ መዓልት ተጉዞ ወደ ብሔረ ሕያዋን ሞት ከሌለበት ሥፍራ ገብቷል። መጽ.ነገ.ቀዳ. 19÷8።

እኛም በእርሷ መሶብነት የተገኘውን ምግብ ተመግበን ሁለተኛ ሞት በማንሞትበት ሐዘንና ለቅሶ ጥርስ ማፋጨት የዚህ ዓለም ስቃይ በሌለበት ሥፍራ የመኖራችንን ምሥጢር የሚያመላክት ነው።

## የአሮን በትር

የአሮን በትር የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እመቤታችን በድንግልና ጸንሳ በድንግልና መውለዷን ያስተማሩበትና ያመሠጠሩት ነው። የእመቤታችንን ድንግልና በአሮን በትር ምሳሌ ነገረ ሥጋዌን ቅዱስ ኤፍሬም ሲናገር «ሳይተክሏትና ውኃ ሳያጠጧት የለመለመች የአሮን በትር ነበረች» ይላል። እግዚአብሔር የሙሴን ክህነት መምረጡን ለማሳወቅ «የዐሥራ ሁለቱን ነገድ በትር ሰብስበህ ከቤተ መቅደስ አኑረው። እኔ ምልክት አሳይሀለሁ» ሲል አዝዞታል። ሊቀ ነቢያት ሙሴም እግዚአብሔር ያዘዘውን አድርጓል።

የዐሥራ ሁለት ነገደ እስራኤል በትሮች ተሰብስበው በቤተ መቅደስ ውስጥ ገብተው ሲጸለይባቸው ታደረና የሌሎቹ በትር ከበትርነታቸው አልተለወጡም። የአሮን በትር ግን ሊቁ እንደ ነገረን ውኃ ሳያጠጧት ለምልማ አብባና አፍርታ ተገኝታለች። እንግዲህ የአሮን በትር ሰው ሳይተክላትና ውኃ ሳትጠጣ ለምልማ አብባ ፍሬ ይዛ ተገኝታለች። ይህ ለእመቤታችን ምሳሌ ነው። ያቺ በትር እግዚአብሔር የአሮንን ክህነት ለመምረጡ ምልክት ሆና ተገኝታለች። ይቺ በትር አብባ ለምልማ እንደ ተገኘች እመቤታችን ከተፈጥሮአዊ ሕግ ውጭ በሆነ መንገድ ያለ ወንድ ዘር አምላክን በድንግልና ጸንሳ በድንግልና ወልዳለች። ያች በትር ወደ ቤተ መቅደስ ገብታ 12 ሰዓት ከቆየች በኋላ እንደ ለመለመች እመቤታችን ቤተ መቅደስ በገባች በ12 ዓመቷ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ጸንሳለች። የአሮን በትር ለአሮን ክህነት ምልክት እንደ ሆነች ለእኛም እመቤታችን ለደኅንነታችን ምልክት ነች። ምክንያቱም መድኃኒታችን ሰውን ያዳነው የሰውን ባሕርይ ተዋሕዶ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቶስ የሰውን ባሕርይ እንደ ተዋሕደ ሲያስረዳ «የአብርሃምን ዘር ይዟል እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም።» ይላል። ዕብ.2÷14። ስለዚህ በደለኛ የነበረ ሥጋ መለኮትን በመዋሐዱ ዓለምን አድኗል።

ሌላው በትር የጠላት መቅጫ መሣሪያ ሲሆን ይኸውም «በአንተና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፤ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ።» ዘፍ.3÷16 ተብሎ የተነገረው ትንቢታዊ ምሳሌ ለጊዜው ለሔዋን ቢነገርም ፍጻሜው ግን የአሮን በትር ምሳሌዋ በሆነ በድንግል ማርያም ተከናውኗል። የተቀጠቀጠው ጠላት ዲያብሎስ ከድንግል ሰው በሆነው አምላክ ፍጻሜውን አግኝቷል። ኤር.2÷14-15። እንግዲህ ሶርያዊው ቅዱስ ኤፍሬም በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ከደረሰው የምስጋና መጽሐፍ በጥቂቱ ጨልፈን ያቀረብነውን ትምህርተ ሃይማኖት በዚህ እንቋጫለን።

*አነሣስቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን አምላክ ምስጋና ይሁን። አሜን።*

♣ ♣ ♣



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የክርስቶስ ሕማሙ ፥ ሞቱ ፥ ትንሣኤውም በፈቃዱ

**ውድ አንባብያን፣ ባለፉት ተከታታይ እትሞች ኢትዮጵያዊው ሊቀ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ በዘመኑ ለተነሱት መናፍቃን መልስ የሰጠባቸውን ምንባባት ማቅረባችን ይታወቃል:: በአሁኑ እትም ደግሞ ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ የእስክንድርያው ታወደስዮስና የህንድኪያው ጳጳስ ሳዊሮስ «የእግዚአብሔር ልጅ ታሞ የሞተው በፈቃዱ ሳይሆን ያለፈቃዱ ነው» ሲሉ ሳስተማሩት የክሕደት ትምህርት ሊቁ፦ ክርስቶስ ታሞ የሞተው ተገዶ ሳይሆን በፈቃዱ መሆኑንና በፈቃዱ ከሞት መነሣቱን ከቅዱሳት መጻሕፍት እያጣቀሰ የሰጠውን መልስ ይዘን ቀርበናል:: መልካም ንባብ::**

በሰማይና በምድር፣ በባሕርና በውቅያኖስ ለዘላለም ምስጋና ይግባውና በቅድስና መንግሥቱ ንጹሕ በሚሆን አኗኗር፣ በልዕልና ከፍ ያለ፣ በልቡና የማይታወቅ፣ በኅሊና የማይገኝ፣ ያለጥፋት ለዘላለም በሚኖር፣ በክብር የመለኮት ዘውግ በሆነ፣ በአኗኗሩ ሥልጣን ያለው፣ በአካል ሦስት በሚሆን ቅዱስ ፥ ቅዱስ ፥ ቅዱስ ተብሎ በሚመሰገን በእግዚአብሔር ስም እንጀምራለን::

«የእግዚአብሔር ልጅ ያለ ፈቃዱ ሞተ» የሚሉ የዝንጉእን የእስክንድርያው ታወደስዮስና የህንድኪያው ጳጳስ የሳዊሮስን ዘለፋ እንጀምራለን:: «የእግዚአብሔርን ልጅ ያለ ፈቃዱ ታሞ ሞተ» እንዴት ይሉታል? እንደ ዚህ ያለ ዝንጋኤንና ስንፍናን ምን ሲል አመጣ?

ሳዊሮስና ታውደስዮስ ሃይማኖትን አክፍተው በክርስቶስ ሕማማት ላይ ስድብን ተናገሩ:: ከወንጌል ቃልም በሐሙስ ሌሊት ስለ ሕማሙ «አባት ሆይ፤ ይህችን ሰዓት ከእኔ አሳልፋት» የሚለውን ምክንያት አደረጉ:: በዚህ ቃል አትዘኑ:: ነገር ግን ስለዚህ መጣሁ፤ ደረስኩባትም:: ይታመም ዘንድ በመምጣቱ ግን በፈቃዱ ታመመ፤ በፈቃዱም ሞተ:: «አባት ሆይ ቢቻልስ ይህችን ሰዓት ከእኔ አሳልፋት» ስላለው ልንገራችሁ ስሙ:: አድምጡ::

ዝንጉአን ሆይ፤ እንግዲህ ሰይጣን አይሁድ ልቡናቸው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ይከፉ ዘንድ አወከ:: ነገር ግን የክርስቶስን ተአምራት የኢያኢሮስን ልጅ ከሞተች በኋላ «ጣቢታ ተነሽ» ብሎ በጠራት ጊዜ እንደ ተነሣች ሲያስቡ በልቡናቸው ውስጥ ትዝብት አለ:: ዳግመኛም ናይን በሚባል አገር የመበለቲቱን ልጅ ጉኑን በዳሰሰ ጊዜ ከሞተ በኋላ እንሥቶታል:: አስነሥቶታል:: እንደ ገናም በሀገረ ቢታንያ ከተቀበረ አራት ቀን የሆነው አልዓዛርን በታላቅ ድምፅ «አልዓዛር ሆይ፤ ወደ ውጭ ና» ብሎ ጠራው:: የሞተውም እጆቹና እግሮቹ በመግነዝ እንደ ተገነዙ ወጣ:: ፊቱም በጨርቅ እንደ ተጠመጠመ ነበር:: ዳግመኛም መድኃኒታችን በዕውራንና በስቡራን፣ በእግራቸው መሄድ በተሳናቸውና በሽባዎች፣ በወረሐዎችና ርኩሳን መናፍስት በሚያሰቃዩአቸው፣ በለምጻሞች በኃጢአተኞች ያደረገውን ተአምራት አሰቡ:: እንግዲህ ሰይጣን ከጌታ ተአምራት ፈርቶ ለክፋት ሲተጋ ይህን አሰበ:: ከዚህ በኋላ የእግዚአብሔር ልጅ በምሥጢር አነጋገር «አባት ሆይ፤ ይህችን ሰዓት ከእኔ አሳልፋት» ባለ ጊዜ ሰይጣንን አበረታው:: ሰይጣንም ሊቃነ ካህናትን ሰይፍ፣ ገመድና በትር የያዙ ወታደሮችን ልከው መድኃኔ ዓለምን ይይዙት ዘንድ አበረታቸው:: በኃጢአተኞች እጅ ተላልፎ ተሰጥቶ የርኩሳንን ምራቅ ተቀበለ:: እንደ ሌባ አስረው እንደ ክፉ አድራጊ አሰቃዩት:: በነጋ ጊዜም ወስደው በፍርድ አደባባይ በጲላጦስ ፊት አቆሙት:: ይሰቅለው ዘንድ አሳልፈው ሰጡት:: እንዲገድለውም ከሰሱት፤ ጲላጦስ «ንጉሣችሁን ልስቀለውን?» አላቸው:: «ከቄሳር በስተቀር ንጉሥ የለንም» አሉት:: ራሱን የሚያነግሥ ሁሉ ንጉሥን የሚተላለፍ ነውና የዳዊትን ልጅ ከደው ለሮም መንግሥት ዘመሩለት:: በአፋቸው የይሁዳን መንግሥት አስቀርተው ለአሕዛብ መንግሥት ራሳቸውን አስገዙ:: በእሥራኤል ቅዱስ ፊት ላይ ርኩስ ምራቃቸውን ተፉ:: የአሪት ካህናትና የእሥራኤል ነገሥታት የሚቀቡበትን የጽዮን ቀንድ ቅባትን ቅድስናን አስወገዱ:: ሊቀ ካህናቱም ልብሱን ቀደደ:: የአሮንን ልጆች ክህነትን ሻረ:: አሮንና ልጆቹ ናዳብና አብዩድ በሞቱ ጊዜ «ልብሳችሁን አትቅደዱ፤ ጸጉራችሁንም አትላጩ፤ የእግዚአብሔር ኃይል በእናንተ ላይ አለና፤ ዘይት ተቀቡ» እንዳላቸው በኦሪት ዘሌዋውያን ተጽፏልና የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ተቀደደ:: የያዕቆብ በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም:: የገዥም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል ገዥ የሆነ እስኪመጣ ድረስ ያለው ቃል በእነርሱ ላይ ተፈጸመ:: እርሱ ለአሕዛብ ተስፋቸው ነው:: ዕፀ መስቀል በአይሁድ እጅ ተተክሎ ቤተ ክርስቲያን በኢየሱስ ክርስቶስ እጅ ታነጸች፤ በሰቃልያን እጅ በዕፀ መስቀል ላይ የእግዚአብሔር በግ ታርዶ ለምእመናን የበረከት ማዕድ ተሠራ:: መድኃኒታችን ጉኑን ተወግቶ የቤተ ክርስቲያን ደጃፍ በሙሽራዋ ደም ተቀባ::

«የእግዚአብሔር ልጅ ያለፈቃድ ታሞ ሞተ» ወደ ሚሉ የታወደስዮስና የሳዊሮስ ዘለፋ እንግባ:: ዳግመኛ መድኃኒታችን «ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ ፥ አምላኬ አምላኬ ስለምን ተውኸኝ?» ያለው ምክንያት ሆኗቸው የደከመ (ሽባ) ልብ ያላችሁ ሆይ፤ በዚህስ አትሳቱ:: ሰይጣን አሳልፎ ስለ አሰጠው እንዳይታበል ይሸነግለው ዘንድ «አባት ሆይ፤ ይህችን ሰዓት ከእኔ አሳልፋት» የሚል ቃል አሰማው:: እንዲሁም ለመልአከ ሞት መቅረብ እንዳይፈራ የሸንገላ ቃል አሰማው:: እሱም አስቀድመን ያስታወስነውን የጌታን ተአምራት ያፈራ ዘንድ አስቧልና:: ከዚህም በኋላ ጌታችን «አምላኬ አምላኬ ስለ ምን ተውኸኝ?» ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ:: ከዚህ በኋላ የጥፋት መልአከ ሞትን በመፍራት እንደ ሚጮኽ አሰበ:: መልአከ ሞት አፉን ከፍቶ መዋጥ እንደ ለመደ ለዘላለም ሕያው ሁኖ የሚናገረው ነፍስ ይቀበል ዘንድ ወደ ተሰቀለበት መስቀል ቀረበ:: ነፍሱን ይነጥቃት ዘንድ ጨከነ:: ለሆዱ የሚሳሳ ሰይጣን ትስብእትን እንደ ምግብ በጉረሰ ጊዜ የሚሰነቅር የመለኮት ወጥመድ አስተፋው:: ባላመጣት ጊዜም ጥርሱን የሚሰብር አለት:: በዋጣትም ጊዜ ሆዱን የሚሰነጥቅ ሰይፍ አገኘ:: «የሚያስገብረው እንዴት ተሻረ? የሚወነጅለው እንዴት ተሻረ?» ያለው የኢሳይያስ ቃል በእርሱ ላይ ተፈጸመ:: «ሞት ድል መንሳትህ ወዴት አለ? መቃብርስ ይዞ ማስቀረትህ ወዴት አለ?» የተባለውም ተፈጸመ::

ልቡናችሁ በቁሙ የጠፋ ሆይ፤ እንግዲህ ስሙ:: አስተውሉም:: ሰይጣንና ሞትን ስለ መሸንገል እነዚያን ቃላት የተናገረ ሕማምና ሞትን ስለፈራ አይደለም:: ሰነፎች ሆይ፤ ያለፈቃድ አለመታመሙን፣ ያለፈቃድ አለመሞቱን አስተውሉ:: የእግዚአብሔር ልጅ አምላክ መሆንን ትከለክሉታላችሁን? ከልቡናችሁ አምልኮቱን ታስታጉሉ ዘንድ ትፈቅዳላችሁ? እርሱ አምላክ ከሆነ ይታመም ዘንድ ማን ያስገድደዋል? ማንስ ይሞት ዘንድ ያዘዋል? ስለእኛ ፍቅር ይታመም ዘንድ ቸርነቱ አስገደደችው:: ስለ እኛ ኃጢአት የሞት ጽዋን ይጠጣ ዘንድ የሰው ልጅ ፍቅር ሳበችው:: ደቀ መዛሙርቱን የሰው ልጅ በጻፎችም እንደ ሚጣል፣ እንደ ሚገደልም፤ ከሦስት ቀን በኋላም እንደ ሚነሣ ለደቀ መዛሙርቱ የተናገረውን አምላክ እንዴት ያለ እግዚአብሔር ፈቃ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ድ ሞተ ትሉታላችሁ?

ጴጥሮስም ወደ እርሱ ወስዶ ይገሥጸው ጀመር። እርሱ ግን ዘወር አለ። ደቀ መዛሙርቱንም አይቶ ጴጥሮስን ገሠጸውና፡- «ወደ ኋላዬ ሂድ፤ አንተ ሰይጣን የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን ነገር አታስብምና» ያለውን ልብ ሰነፎች ሆይ፤ ስለ እርሱ ሞትንና ሕማምን ያልፈቀደውን ጴጥሮስን እንደ ተቆጣው አትሰሙምን? ዳግመኛም «ጴጥሮስ፤ ሰይፍህን ወደ ሰገባው ክተተው፤ አብ የሰጠኝን ጽዋ አልጠጣትምን?» አለው። ዳግመኛም ለደቀ መዛሙርቱ «ስለ ወዳጆቹ ነፍሱን አሳልፎ ከመስጠት የሚበልጥ ፍቅር የለም» አለ። ዳግመኛ አይሁድን «ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፤ ሦስት ቀንም አነሣዋለሁ» አላቸው። ስለዚህ አይሁድ «ይህ ቤተ መቅደስ ከዓርባ ስድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ ነበር። አንተስ በሦስት ቀን ታነሣዋለህን? አሉት። እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ይል ነበር።» እነሆ ለአይሁድ ሥጋውን ለማፍረስ አሳልፎ ሰጣቸው። ያለ ፈቃድ ቢሞት ግን ይገድሉት ዘንድ ተላልፎ ባልተሰጣቸው ነበር። «ዳግመኛም ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ እኖ ራለሁና፤ ስለዚህ አብ ይወደኛል። እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት ሥልጣን አለኝ። ደግሞም ልነሳት ሥልጣን አለኝ። ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ» አለ። እንግዲህ ራሱ በመፍቀዱ እንገላቱት፣ ራሱ በመውደዱ ገደሉት። ራሱ በፈቀደበት ቦታ በሥጋ ሞትን ቀመሰ። ራሱ በመፍቀዱ መራራ ሐሞት አጠጡት። በእርሱ በፈቃዱ ነፍሱን ወደ አባቱ አማፀነ። ራሱ በመፍቀዱ በወታደር ጦር ተወጋ። ራሱ በመፍቀዱ ደምና ውኃ ከጐኑ ፈሰሰ። ራሱ በመፍቀዱ ያለመንቀሳቀስ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አደረ። ራሱ በመፍቀዱ ነፍሱን ወደ ሥጋው መልሷት በመለኮቱ ኃይል ተነሣ። የክብር መብረቅ ብልጭ ብሎ የመቃብር ጠባቂዎችን አስደነገጣቸው። ስድስቱ ከዋክብት ለየራሳቸው በሁለት በሁለት ተከፍለው ታዩ። ሰባተኛው ግን ዘወትር በቅዱሳን ላይ የሚያበራ የጽድቅ ፀሐይ ነው።

ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ንጹሕ በሆነ በፍታ ሥጋውን ጠቀለሉት (ከፈኑት)። እነሆ አንዱ ሥርዓት ነው። ዳግመኛ ሚካኤልና ገብርኤል የሚያንጸባርቅ ልብስ ለብሰው የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ካረፈበት አንዱ ከትራሱ አንዱ ከግርጌው ተቀምጠው ታዩ። የመቃብር በር በቤተ ክርስቲያን ተመሰለች። ዮሴፍና ኒቆዲሞስ መሥዋዕት ለማሳረግ እንደኛው በክህነት እንደ ኛው በተልእኮ በተዘጋጁ ቀሳውስት አምሳል ተመሰሉ (ይመስላሉ)። ዳግመኛ ጴጥሮስና ዮሐንስ በፓትርያርክና በቄስ ይመሰላሉ። እነርሱም የጳጳሳትንና የኤጲስ ቆጶሳትን ሹመት በመከተል በቤተ ክርስቲያን በመሾም የሰለጠኑ ናቸው። ማርያም መግደላዊት በዲያቆናዊ ስትመሰል ከእርሷ ጋር ያሉት በምእመናን ተመስለዋል (ይመሰላሉ)። የንብስቱ ቁርባንና የመድኃኒት ጽዋ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በምሳሌ አይደለም። በተግባር እንጂ። ሥጋው የተከፈነበት ከፈን (በፍታ) ሥርዓተ ቁርባን (ሕብስት) የሚከፈንበት ሞጣህት ይመስላል። ለብቻው በአንድ ሥፍራ ተጠቅልሎ የነበረው ጨርቅ የመለኮት ደም ጽዋ በሚከደንበት ይመስላል። ዕፀ መስቀሉም የቤተ ክርስቲያን መብራት በሚሸከም የወርቅ መቅረዝ ተመስሏል። (ይመስላል)። ቀራንዮ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ተቀደሰች። ጎልጎታም ንጹሕና ነውር በሌለበት በበድን ሥጋው ተቀደሰች። በቀራንዮ የሕማም አልጋ ተተክሎ ጎልጎታ የመኝታው ሥፍራ ሆነች። ቀራንዮ የሙሽራው ዐጸድ፣ ጎልጎታ ደጃፍ ነው። ቤተ ክርስቲያን ስለ ቀራንዮ «ወንድሜ ቀትር በሆነ ጊዜ የት ትተኛለህ? ወደ የት ትመለከታለህ?» ትላለች። ስለ ጎልጎታም «እነሆ የሰሎሞን አልጋ ናት፤ ከእሥራኤል ኃያላን ስድሳ ኃያላን በዙሪያው ናቸው» አለ። ስለ ቀራንዮ ምሥጢር ዳዊት «እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ ÷ አጥንቶቼን ቆጠሩ ÷ ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ። በቀሚ ሴም ዕጣ ተጣጣሉ» አለ። ስለ ጎልጎታም «እኔ ተኛሁ፣ አንቀላፋሁም፤ እግዚአብሔርም ደግፎኛልና ነቃሁ» ይላል።

ከዛሬ ጀምሮ ግን በፈቃዱ ታሞ፤ በፈቃዱም ለሞተ በመለኮቱም ኃይል ለተነሣ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን እንበል፤ እንደዚህ እናምናለን፤ እንደዚህም እንታመናለን።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

## በአንቀጸ ገነት...

/ከገጽ ፰ የዞረ/

/ከገጽ ፰ የዞረ/

የእስራኤልን ሕዝብ በባሕር መካከል እንዳሳለፍካቸው ወደ ጌታህ ፈጥነህ ግባ።

እናንተ የብርሃን ሠራዊት ሁላችሁም ከምስጋናና ከማሕሌት ጋራ ጌታችሁን ለመቀበል ውረዱ፤ በሲኦልም ውስጥ ብቻውን ይሆን ዘንድ አይገባም፣ እንግዲህስ በክብር፣ በማሕሌት፣ በመዝሙርና በምስጋና ተቀበሉት። በመስቀል ላይ ብትተውትም በሲኦል ውስጥ ከእርሱ ትርቁ ዘንድ አይገባችሁም።

መልአኩም ለፈያታዊው እንዲህ ብሎ መለሰ፡- አንተ ድኩም፣ በእርሱ ላይ ሞት ሥልጣን የለውምና ዝም በል፤ ጭላት አንበሳን ያድነው ዘንድ ይችላልን፤ ደካማ ዝንጀሮስ በርቱውን ነብር ይነጥቀው ዘንድ እንዴት ይችላል? ድል አድራጊነት ለጌታ ብቻ ነውና አለው። ተአምራት አድርጎ ሙታንን በሕይወት ያስነሣቸው ገብርኤል አይደለም። የኢያኢሮስንም ሴት ልጅ ከሞተች በኋላ ያስነሣት ሚካኤል አይደለም። ከመላእክትም አንዱ ለዓለም መድኃኒት ውኃና ደምን ያፈሰሰ የለም።

አዳምንና ልጆቹን ያድን ዘንድ ከቅድስት ድንግል በነሳው ሥጋ የእግዚአብሔር ልጅ በዚህ ሁሉ መከራ ታገሠ እንጂ። በእርሱ ላይ የሞት ፍርድ እስከ ሚያመጡበት አይሁድን እስከ አነሣሡበት ድረስ ዲያብሎስን የእግዚአብሔር ልጅ ሸነገለው። አስ ቀድሞ በእርሱ ድል በተነሣው በዚህ ሥጋ ድል ያደርገው ዘንድ ወደደ እንጅ፤ በመለኮቱ ኃይል ድል አድርጎት ቢሆን ባልተደነቀም ነበር።

ፈያታዊ ሆይ ÷ አንተን እናገርሃለሁ እነሆ የንጉሥን ቃል ሰምተን ለክብሩ ሰግደናል፤ ለመልእክቱም ታዝዘናል።

ከዚህ በኋላ መልአኩ የእሳቱን መውጊያ አንሥቶ የገነትን መዝጊያዎች ደቃ፤ መዝጊያዎቹም ተከፈቱ።

ፈያታዊውንም አባት፡- «አዳም ከወጣበት የሕያዋን ሀገር ወደ ሆነች ገነት ገብቶ ከመላእክት ጋራ ደስ ይበልህ፤ የክብር ባለቤት ጌታ አንተን ለማዳን ሰው ሁኖአልና» አለው።

ደሙን በማፍሰሱም ለአባቱ ያማረ መሥዋዕት ሆነ፤ በእኛና በእናንተ መካከል የነበረውን የጥል ግድግዳ ምንም አፈረሰ።

ፈያታዊውም መልሶ መልአኩን እንዲህ አለው፤ እንግዲህስ ወደ ቦታህ ተመልሰህ ወደ ሥራህ ግባ፤ እነሆ እኛ ወደ ሀገራችን ተመልሰን ወደ ቀድሞውም ርስታችንም እንኖር ዘንድ ዝግጁዎች ሁነናልና፤ በዚያም ፈጽሞ ደስ ይለናል።

በውኑ የሰማያዊ ንጉሥ ቀን በሩ ጫንቃህን አቁስሎታልን? ስለዚህ የገነት ጠባቂ ትሆን ዘንድ ትወዳለህን? እንዲህ አይደለም፤ በኃጢአታችን ምክንያት ገነት ማረፊያ አልሆነችም ነበር።

እንዲህ ግን ገነትን ከመጠበቅ ይሻልሃልና ወደ ተግባርህ ተመልሰህ ግባ። ገነትን እንድትጠብቅ አዞህ የነበረ ቃል ይህን ደብዳቤ የጻፈልኝ እርሱ እንደ ሆነ አስተውል። ሰማያዊ መንግሥቱን ያወረሰን ጌታህ ቡሩክ ምስጉን ነው።

ምስጋናና ክብር ገዢነትና ኃይል ለእርሱ ገንዘቡ የሆነ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን በእውነት ይሁን ይሁን።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ነገረ ድኅነት በመጽሐፈ ቅዱሳ

መምህር ደጀኔ ሽፈራው

## መግቢያ

ነገረ ድኅነት፦ማለት ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ለማዳን ያደረገውን ጉዞ የሚናገር የሚያስረዳና የሚያመስጥር ማለት ነው፡፡ «ነገረ» የሚለው ቃል በቤተ ክርስቲያን ትምህርት የአንድን ትምህርት መስከ መግለጫ ሆኖ ያገለግላል፡፡ «ነገረ ማርያም» እንዲል፡፡ «ድኅነት» የሚባለውም፦ ከኃጢአት ነጽቶ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ መብቃት ነው፡፡ «ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና፥ ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ፤» እንዲል፡፡ ማቴ.1፥21፡፡

የነገረ ድኅነትን ትምህርት የምናየው በሁለት ወገን ነው፡፡ አንደኛው «አባታችን አዳም ከተፈረደበት ፍርድ እንዴት ዳነ?» የሚለው ሲሆን፡ - ሁለተኛው ደግሞ፦ «እኛ ልጆቹስ እንዴት እንድናለን?» የሚለው ነው፡፡ በመሆኑም የነገረ ድኅነት መሠረቱ የአዳም መንጸፈ ደይን መውደቅ ነው፡፡

በአጠቃላይ «ድኅነት» ማለት በጌታችን የባሕርይ አምላክነት አምኖ እንደ ቃሉ በመኖር የዘለዓለም ሕይወት ባለቤት መሆን ነው፡፡ ይኸውም ከላይ እንደ ተገለጠው የማታልፍ ርስት መንግሥተ ሰማያትን መውረስ ነው፡፡ «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና፡፡ ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና፡፡ በእርሱ የሚያምን አይፈረድበትም፥ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል፡፡» እንዲል፡፡ ዮሐ.3፥16-18፡፡

በሰው ልጅ ድኅነት ውስጥ የእግዚአብሔር ድርሻ እንዳለ ሁሉ የሚድነውም ሰው ለድኅነቱ የሚያበረክተው ድርሻ አለ፡፡ ይኸውም፦ ሃይማኖት ይዞ ምግባር ሠርቶ መገኘት ነው፡፡ ሃይማኖት መያዝ ማለት፦ በምሥጢረ ሥላሴ ፥በምሥጢረ ሥጋዌ፥ በምሥጢረ ጥምቀት፥ በምሥጢረ ቁርባን፥ በምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ማመን ነው፡፡ ከዚህም ጋር ሃይማኖት ያለ ምግባር ስለማይሆን እግዚአብሔር ያዘዘውን እና የሚወድደውን በጎ ምግባር መሥራት ያስፈልጋል፡፡ መቼም ቢሆን «ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው፤» የሚለውን መዘንጋት አይገባም፡፡ ያዕ. 2፥17፡፡ ከዚህም ጋር በጾም በጸሎትና በስግደት ተወስኖ በገድል መቀጥቀጥ ይገባል፡፡ ተጋድሏችንም ከሥጋና ከደም ጋር አይደለም፡፡ «የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልብሱ፡፡ መጋደላችን ከሥጋዊ ከደማዊ ጋር አይደለምና፤» እንዲል፡፡ ኤፌ. 6፥11፡፡ ጌታችንም «እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ ፥ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ፡፡»ብሏል፡፡ ማቴ. 16፥24፡፡ ይህም ሰይጣን የሚያ መጣበትን መከራ በትዕግሥት ይቀበል ማለት ነው፡፡

የሰው ልጅ የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ለማግኘት የድርሻውን ከተወጣ እግዚአብሔር የድርሻውን የማይወጣ አምላክ አይደለም፡፡ ለምሳሌ ወደ ቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት ብንሄድ፦ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፦ «የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም፤» ብላ ለልጇ ለኢየሱስ ክርስቶስ በመንገር የአማላጅነት ድርሻዋን ተወጥታለች፡፡ በወይን ጠጁ ማለቅ ተጨንቀው የነበሩ ሠራተኞችም እመቤታችን እንደ ነገረቻቸው ጌታ ባዘዛቸው መሠረት ውኃ ቀድተው ስድስቱን የድንጋይ ጋኖች የመስፈር ያህል በመሙላት የድርሻቸውን ተወጥተዋል፡፡ ጌታ ደግሞ ውኃውን ወይን በማድረግ የድርሻውን ፈጽሟል፡፡ ዮሐ.2፥1-10፡፡ ወደ አልዓዛር መቃብር ስንሄድም ይኸንን የመሰለ ነገር እናገኛለን፡፡ እነርሱ ጌታ ባዘዛቸው መሠረት በአልዓዛር መቃብር ላይ ተገጥሞ የነበረውን ትልቅ ድንጋይ በማንሣት የድርሻቸውን ተወጥተዋል፡፡ ጌታ ደግሞ አልዓዛርን ከሞት አስነሥቶ ከመቃብር በማውጣት የድርሻውን ፈጽሟል፡፡ ደቀ መዛሙርቱም የአልዓዛርን መግነዝ በመፍታት የድርሻቸውን ተወጥተዋል፡፡ ለደቀ መዛሙርቱም «ፍቱትና ይሂድ፤» በማለት የሥራ ድርሻ የሰጣቸው ራሱ ጌታችን ነው፡፡ ዮሐ.12፥26፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ነገረ ድኅነት የማይነገርበት የአገልግሎት ክፍል የለም፡፡ የአገልግሎቷ መነሻም መድረሻም፣ ንባብም ትርጓሜም ነገረ ድኅነት ነው፡፡ በአጠቃላይ አገላለጽ የሁሉ ነገሯ አስኳል ነገረ ድኅነት ነው፡፡ በመሆኑም እንደ መላእክት ያለ ዕረፍት በምትፈጽመው መንፈሳዊ አገልግሎት በቅዳሴዋም ሆነ በማኅሌቷ፣ በሰዓታቷም ሆነ በመዝሙሯ የምትመሰክረው ነገረ ድኅነትን ነው፡፡ «ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ» ያሰኛትም በነገረ ድኅነት ላይ ያላት የማይናወጥ ፍጹም እምነት ነው፡፡ ኦርቶዶክስ ማለት ቀጥተኛ ማለት ሲሆን፦ ተዋሕዶ፦ ማለት ደግሞ በተዋሕዶ፦ አምላክ ሰው፣ ሰውም አምላክ ሆነ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ነው፤ ብሎ ማመን ነው፡፡ በሥርዓቷም ቢሆን በጣት ከማማተብ ጀምሮ ነገረ ድኅነትን ትናገራለች፡፡ ቄሱ የሚባርኩበት የእጅ መስቀል፥ ዲያቆኑ በቅዳሴ ጊዜ የሚይዘው የመጾር መስቀል የሚያውጅው ነገረ ድኅነትን ነው፡፡ በቅኔ ማኅሌትም ጸናጽሉ፥ መቋሚያውና ከበሮውም እንዲሁ ነው፡፡ ስለሆነም እንኳን የቅዳሴውና የማኅሌቱ ቀለም ንዋያተ ቅድሳቱ እንኳ ነገረ ድኅነትን እንደሚሰብኩ ማስተዋል ማመንም ያስፈልጋል፡፡

ቤተክርስቲያን የተመሠረተችው በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ላይ በመሆኑ መሠረቷ እርሱ ነው፡፡ ጉልላቷም እርሱ ነው፡፡ እርሷም የእርሱ አካል ናት፡፡ እውነቱ ይህ ነው፡፡ ይህን እውነት በመያዝም ከነገረ ድኅነት አንጻር መጽሐፈ ቅዳሴን ለመቃኘት እንሞክራለን፡፡ ከዚያ በፊት ግን ስለ ቅዳሴ የት መጣና ምንነት ጠቅለል ባለ መልኩ እንመለከታለን፡፡

## 2. ቅዳሴ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአንድ ላይ በአንድ መጽሐፍ የተጠረዙ ዐሥራ አራት ቅዳሴዎች አሉ፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ቅዳሴ ሐዋርያት፦ ይኸንን ቅዳሴ የጻፉት ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ናቸው፡፡ የጻፉበትም ምክንያት መናፍቃን፦ «ሐዋርያት ነን፤» እያሉ በሐዋርያት ስም መጽሐፍ እየጻፉ የዋሃን ምእመናንን በማታለላቸው የእነርሱን የሐሰት መጽሐፍ ለማጋለጥ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ፦«እንደ እነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋርያት እንዲመስሉ ራሳቸውን የለወጡ ውሸተኞች ሐዋርያትና ተንኰለኞች ሠራተኞች ናቸውና፡፡ ይህም ድንቅ አይደለም፤ ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና፡፡ እንግዲህ አገልጋዮቹ ደግሞ የጽድቅ አገልጋዮች እንዲመስሉ ራሳቸውን ቢለውጡ ታላቅ ነገር አይደለም፤ ፍጻሜአቸውም እንደ ሥራቸው ይሆናል፡፡» በማለት ስለ እነዚህ ሰዎች ተናግሯል፡፡ 2ኛ ቆሮ. 11፥13-15፡፡

2፦ ቅዳሴ እግዚእ፦ ይኸንን የጌታ ቅዳሴ ቅዱሳን ሐዋርያት ከጌታችን ቃል በቃል ሰምተው ጽፈውታል፡፡ የተማሩትም ከመጽሐፈ ኪዳን ጋር ከትንሣኤው በኋላ ነው፡፡ ይህም በመጽሐፈ ቅዳሴው መግቢያ ላይ፦ «እመጽሐፈ ኪዳን ዘነገሮሙ እግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ እምቅድመ ዕ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ርገቱ ውስተ ሰማይ እምድኅረ ትንሣኤሁ እሙታን:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ለሐዋርያት ከነገራቸው ከመጽሐፈ ኪዳን::» ተብሎ ተገልጧል::

3፡- *ቅዳሴ ማርያም፡-* ይኸንን ቅዳሴ የደረሰው አባ ሕርያቆስ ነው:: ከዚያ በፊት «ያልተማረ ነው» ብለው ይንቁት ነበር:: እርሱ ግን እንደ ጠሉኝ ልጥላቸው ሳይል በትሕትና ጸንቶ ይኖር ነበር:: ኤጲስ ቆጶስ አድርገው የሾሙት በጸሎቱ ይጠብቃል ÷በትሩፋቱ ያጸድቃል ÷ ትምህርቱን ውሎ አድሮ ያደርገዋል ብለው ነው:: ያልተማረ ግብረ ገብ ነበር:: በዕለታት አንድ ቀን በመሾሙ የቀኑበት ሰዎች: - «ቀድሰህ አቁርበን እንበለውና ሲያቅተው ይህን ምክንያት አድርገን እንሽረዋለን፤» ብለው ቅዳሴ ግባ አሉት:: እርሱም ፈቃደኛ ሆኖ ሥርዓቱን ጨርሶ ከፍሬ ቅዳሴ ሲደርስ «ከሊቃውንት ቅዳሴ» የሚያስቸግር ማንን እናውጣለት» እያሉ ተማከሩበት :: እርሱ ግን አድሮበት የሚኖር መንፈስ ቅዱስ ገልጦለት «ጐሥዐ ልብየ ቃለ ሠናየ÷ ወአነ አየድዕ ቅዳሴሃ ለማርያም::» ከሚለሙ አንሥቶ «ወይእዜኒ ንሰብሖ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፤» እስከሚለው ድረስ ስተት አድርጐ ተናግሮታል:: ጥንቱንም ተምኔቱ፡- «እንደ ቅዱስ ኤፍሬም የእመቤቴ ምስጋና እንደ ባሕር አሸዋ እንደ ሰማይ ከዋክብት በዝቶልኝ÷ እንደ ምግብ በልቼው÷እንደ ውኃ ጠጥቼው÷ እንደ ልብስ ለብሼው፤» የሚል ነበር::

4፡-*ቅዳሴ ዘዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ፡-* ይኸንን በስሙ የተጠራ ቅዳሴ የጻፈው ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ነው:: ሥርዓቱ እንደ ቅዳሴ ሐዋርያት ነው:: ታሪኩም እንደ ወንጌል ነው:: ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌሉን በምሥጢረ ሥላሴ በጀመረ ጊዜ መልአክ እግዚአብሔር አጀማመሩ ውቅያኖስን በጭልፋ ዓይነት መሆኑን በምሳሌ ስለ ነገረው «ወሀሎ አሐዱ ብእሲ» በማለት የጽሑፉን አካሄድ ለውጦ ቀጥሏል:: ዮሐ.1÷6:: ሲጀምር «ቀዳ ሚ ቃል» ዮሐ.1÷1 ብሎ ነበር:: ከዚህ በኋላ «ቀዳሚሁ ቃል» ባለውና «ወሀሎ አሐዱ ብእሲ ዘስሙ ዮሐንስ» በሚለው መካከል ይህን ቅዳሴ አግብቶ ተናግሮታል::

*5፡- ቅዳሴ ዘሠለስቱ ምእት፡-* ይኸንን ቅዳሴ በኒቂያ የተሰበሰቡ ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንት ሊቃውንት በአፍም በመጽሐፍም ተከራክረው አርዮስን መልስ አሳጥተው ከረቱት በኋላ የጻፉት ነው:: እኒህ ሊቃውንት አርዮስን በእነርሱ ውግዘት በንጉሡ ዐዋጅ ከለዩት በኋላ ብዙ ድርሰት ደርሰዋል÷ ብዙ ተግሣጽ ጽፈዋል:: ከብዙው ጥቂቱን ብንመለከት፡- ጸሎተ ሃይማኖትን ለምእመናን÷ ሕንፃ መነኰሳትን ለመነኰሳት ÷ ግሩም ቅዳሴን ለቀሳውስት ተናግረዋል::

*6. ቅዳሴ ዘአትናቴዎስ፡-* ይኸንን ቅዳሴ ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ጽፎታል:: የተናገረበትም ዕለት ዕለተ ሰንበት ነው:: አንድም ስለ ክብረ ሰንበት ተናግሮታል:: ከዚህም ሌላ ብዙ ድርሳን ብዙ ተግሣጽ ጽፏል::

*7. ቅዳሴ ዘባስልዮስ፡-* ይኸንን ቅዳሴ ቅዱስ ባስልዮስ ጽፎታል:: ከዚህም ሌላ ብዙ ድርሰት ደርሷል÷ ብዙ ተግሣጽ ጽፏል::

*8. ቅዳሴ ዘጎርጎርዮስ፡-* ይኸንን ቅዳሴ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ጽፎታል:: የቅዱስ ባስልዮስ ወንድም ነው:: «መንፈስ ቅዱስ ሕጹጽ ነው፤» ያለ መቅዶንዮስን ለማውገዝ በቁስጥንጥንያ ከተሰበሰቡ አንድ መቶ ኀምሳ ሊቃውንት መካከል አንዱ ነው:: በሹመቱ ጊዜ ብዙ ድርሳን ደርሷል÷ ብዙ ተግሣጽ ጽፏል::

*9. ቅዳሴ ዘቅዱስ ኤጲፋንዮስ፡-* ይኸንን ቅዳሴ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ጽፎታል:: በዘመኑም ብዙ ድርሳን ደርሷል ÷ ብዙ ተግሣጽ ጽፏል::

*10. ቅዳሴ ዘዮሐንስ አፈወርቅ፡-* ይኸንን ቅዳሴ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ጽፎታል:: በዘመኑም ብዙ ድርሳን ደርሷል÷ ብዙ ተግሣጽ ጽፏል::

*11. ቅዳሴ ዘቄርሎስ፡-* ይኸንን ቅዳሴ ቅዱስ ቄርሎስ ጽፎታል:: ቅዱስ ቄርሎስ የቅዱስ ቴዎፍሎስ የእኅት ልጅ ነው:: ትምህርት በጀመረ በአምስት ዓመት ውስጥ ብሉይ ከሐዲስ አጥንቷል:: ብዙ ድርሰት ደርሷል:: ከብዙውም አንዱ ይህ ቅዳሴ ነው::

*12. ቅዳሴ ዘቅዱስ ያዕቆብ፡-* ይኸንን ቅዳሴ ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ ጽፎታል:: በተወለደ በሦስት ዓመቱ ከእናቱ ጭን ወርዶ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቷል:: ሊቀ ጳጳሱም ጸጋ እግዚአብሔር እንደ ጠራችው ዐውቆ ደሙን በጽዋው ሦስት ጊዜ ግቶታል:: መልአከ እግዚአብሔርም ለዕዝራ ሱቱኤል እንደዳረገው ጽዋዓ እሳት አጠጥቶታል:: በሰባት ዓመቱ ብሉይና ሐዲስን አጥንቷል:: በዐሥራ ሁለት ዓመቱ ደግሞ ድርሰት መድረስ ጀምሯል:: ብዙ ድርሰት ደርሷል÷ ብዙ ተግሣጽ ጽፏል::

*13. ቅዳሴ ዘቅዱስ ዲዮስቆሮስ፡-* ይኸንን ቅዳሴ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ጽፎታል:: ይህ ቅዱስ ጉባኤ ከለባት በሚባለው በኬልቄዶን ጉባኤ ላይ የተወሰነውን «አንድ አካል ሁለት ባሕርይ» የሚለውን ክሕደት አልቀበልም በማለቱ ብዙ መከራ ደርሶበታል:: ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ብዙ ድርሳን ደርሷል÷ ብዙ ተግሣጽ ጽፏል::

*14. ቅዳሴ ዘቅዱስ ጎርጎርዮስ ካልዕ:* ይኸንን ቅዳሴ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ጽፎታል:: ይህም ገባሬ ተአምራት ወመንክራት ተብሎ የሚታወቀው ነው:: ብዙ ድርሳን ደርሷል÷ ብዙ ተግሣጽ ጽፏል::

## 2:1 ትርጉሙ:-

ቅዳሴ ማለት ምስጋና ማለት ነው:: የሚመሰገነውም በባሕርዩ ምስጉን የሆነ እግዚአብሔር ነው:: ጥንቱንም ቢሆን የሰው ልጅ እና ቅዱሳን መላእክት የተፈጠሩት ስሙን ለመቀደስ ክብሩን ለመውረስ ነው:: በመሆኑም በቅዳሴ ክብረ ሥጋ ክብረ ነፍስ÷ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ ይገኛል:: በሰማይ ካሉ ከቅዱሳን መላእክት ቅዳሴም ጋር አንድ ነው:: ነቢዩ ኢሳይያስ ሰማይ ተከፍቶለት /ምሥጢር ተገልጦለት/ በሰማይ ባለ ቤተ መቅደስ የሚፈጸመውን ሥርዓተ ቅዳሴ አይቷል:: «እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት÷ የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር:: ሱራፌልም ከእርሱ በላይ ቆመው ነበር ÷ ለእያንዳንዱም ስድስት ክንፍ ነበረው፤ በሁለት ክንፍ ፊቱን ይሸፍን ነበር ÷ በሁለቱም ክንፍ እግሮቹን ይሸፍን ነበር÷ በሁለቱም ክንፍ ይበር ነበር:: አንዱም ለአንዱ፡- ቅዱስ ÷ ቅዱስ ÷ ቅዱስ ÷ የሠራዊት ጌታ እግዚብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች እያለ ይጮኽ ነበር::» እንዳለ:: ኢሳ.6÷1-3:: ነቢዩ ኢሳይያስ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ያየውን ቅዳሴ ማለትም ስለ ዐጠንተ መንበሩ ሱራፌል ሲናገር፡- ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ደግሞ ስለ ጸወርተ መንበሩ ኪሩቤል ተናግሯል:: እነዚህም አርባዕቱ እንስሳ በመባል የሚታወቁት ናቸው:: «በዙፋኑም በመካከል በዙፋኑም ዙሪያ በፊትና በኋላ ዐይኖች የሞሏቸው አራት እንስሶች ነበሩ:: ፊተኛውም እንስሳ አንበሳን ይመስላል÷ ሁለተኛውም እንስሳ ጥጃን ይመስላል÷ ሦስተኛውም እንስሳ እንደ ሰው ፊት ነበረው÷ አራተኛውም እንስሳ የሚበረውን ንስር ይመስላል:: አራቱም እንስሳች ስድስት ክንፎች አሏቸው:: በዙሪያቸውና በውስጣቸው ዐይኖች ሞልቶባቸዋል:: ቅዱስ ÷ ቅዱስ÷ ቅዱስ÷ የነበረውና የሚመጣውም /ጥንትና ፍጻሜ የሌለው/ ሁሉንም የሚገዛ አምላክ፤ እያሉ፡ ቀንና ሌሊት አያርፉም::» እንዳለ:: ራእ. 4÷7-8:: ለዚህም ነው÷ ቀሳውስቱ: - «አሐዱ አብ ቅዱስ÷ አሐዱ ወልድ ቅዱስ÷ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ» እያሉ የሚቀድሱት:: ሕዝቡም፡- «በአማን አብ ቅዱስ÷ በአማን ወልድ ቅዱስ ÷ በአማን ውእቱ መንፈስ ቅዱስ፤» እያለ በተሰጥዎ ይመልሳሉ::

## 2.2 አገልግሎቱ፡-

የቅዳሴ አገልግሎት ብርቱ ጥንቃቄ የሚጠይቅ አገልግሎት ነው:: ዐሥ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ራ ስምንት ሰዓት መጾምን ይጠይቃል፡፡ ጾም ካልሆነና በዕለተ ሰንበት ከማለዳው ፀሥራ ሁለት ሰዓት ጀምሮ ጾም ከሆነ ደግሞ ከቀኑ ሰባት ሰዓት ጀምሮ ይፈጸማል፡፡ ከላይ እንደ ተገለጠው አገልግሎቱ ሰማያዊ ነው፡፡ በመሆኑም አገልግሎቱን ከሚፈጽሙት ቀዳስያን በስተቀር መንቀሳቀስ፥ መግባት መውጣት አይፈቀድም፡፡ እንደ ዓምድ ተተክሎ አገልግሎቱን መከታተል ብቻ ነው፡፡ ይኸውም ስለ እግዚአብሔር ክብር ነው፡፡ እኛም እግዚአብሔርን በማክበር ክብረ ሥጋ ክብረ ነፍስ እናገኛለን፡፡ ካህን እስካልጠፋ ድረስ አገልግሎቱ አይታጐልም፡፡ «የሺ ፍልጥ ማሰሪያው ልጥ!» እንዲሉ የአገልግሎቶች ሁሉ ማሰሪያው ቅዳሴ ነው፡፡ በመሆኑም ቅዳሴ ሥልጣነ ክህነት ባላቸው ካህናት የሚፈጸም የአገልግሎቶች ሁሉ ራስ ነው፡፡ በአጠቃላይ የሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን መፈጸሚያ ቅዳሴ ነው፡፡ በቅዳሴው ቄሱና ዲያቆኑ ብቻ ሳይሆኑ ምእመናኑም ድርሻ አላቸው፡፡ መጽሐፈ ቅዳሴው፦ ይዲ. /ይበል፡ ዲያቆን/፥ ይካ. /ይበል፡ ካህን/፥ ይሕ. /ይበሉ፡ ሕዝብ/ እያለ የሚያዝዘው ለዚህ ነው፡፡ ቅልቁ የቅዳሴ አገልግሎት ዓላማ የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ለምእመናን ማቀበል ነው፡፡ ምክንያቱም ያለ ሥጋ ወደሙ የዘለዓለም ሕይወት የለምና፡፡ «እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስን ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም፡፡ ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው፡፡» እንዳለ፡፡ ዮሐ.6፥53፡፡

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓርብ ሊሰቀል ሐሙስ ማታ በቤተ አልዓዛር ኅብስቱንና ወይኑን ለውጦ፦ «ይህ ሥጋዬ ነው፡፡ ... ይህ ደግሞ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ /የአዲስ ሕግ የወንጌል፥ የአዲስ ርስት የመንግሥተ ሰማያት መጽኛ/ ነው፡፡»በማለት የአዲስ ኪዳንን ቁርባን ለደቀ መዛሙርቱ ሠርቶ እንዳሳየ፦ ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኰት ወይኑም ተለውጦ ደመ መለኰት የሚሆነው በቅዳሴ ነው፡፡ በመሆኑም ቅዳሴ የድኅነታችን መሠረት የሆነ የጌታችንን ሥጋና ደም ለሕይወት የምንቀ በልበት አገልግሎት ነው፡፡

## 2:3 ከሌሎች አገልግሎቶች በምን ይለያል?

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት ከሥጋ ይልቅ ለነፍስ ያደላ ነው፡፡ «በመንፈስ ተመላለሱ፤ /የነፍስን ሥራ ሥሩ/፤ የሥጋና ምኞት ከቶ አትፈጽሙ፡፡» እንዲል፡፡ ገላ. 5፥16 በመሆኑም ከመጻሕፍተ ብሉያት፥ ከመጻሕፍተ አዲሳትና ከመጻሕፍተ ሊቃውንት በተውጣጣ ንባብና ምሥጢር በማኅሌት፥ በሰዓታት፥ በመዝሙርና በቅዳሴ፤ እግዚአብሔር ይመሰገናል፡፡ ምስጋናውም ለቅዱስ ያሬድ በተገለጠ የቅዱሳን መላእክት ዜማ እንደ ቅዱሳን መላእክት ያለ ዕረፍት ነው፡፡ «ቅዱሳን መላእክት ምስጋናቸው ዕረፍታቸው ነው፥ ዕረፍታቸውም ምስጋናቸው ነው፡፡» እንዲል፡፡

ቅዳሴ በንባብም በምሥጢርም ከሌሎች ምስጋናዎች ጋር አንድ ነው፡፡ ዓላማውም ለተፈጠሩበት ዓላማ የእግዚአብሔርን ስም ለመቀደስ፥ እግዚአብሔርም የሚያወርሰንን ክብር ለመውረስ ነው፡፡ ምክንያቱም ሰውና መላእክት የተፈጠሩት ስሙን ለመቀደስ ክብሩን ለመውረስ ነውና፡፡

የቅዳሴ አገልግሎት ከሌላው አገልግሎት የሚለየው የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን መፈጸሚያ በመሆኑ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ከላይ ለመግለጥ እንደ ሞከርነው በአዲስ ኪዳን የቍርባን ምሥጢር፦ ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኰት፥ ወይኑም ተለውጦ ደመ መለኰት የሚሆነው በቅዳሴ ነው፡፡ ይህም ነገረ ድኅነትን ያመለክታል፡፡ ምክንያቱም በቅዳሴ ላይ የሚፈተተው ለድኅነተ ምእመናን በመልዕልተ መስቀል የተሰጠ አማናዊ የክርስቶስ ሥጋና ደም ነውና፡፡ ይኸንንም ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮ ንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ላይ ገልጦታል፡፡ 1ኛ. ቆሮ.11፥26-32

በሌላ በኩል ደግሞ የቅዳሴውን አገልግሎት መፈጸም የሚችሉት ሥልጣነ ክህነት ያላቸው ዲያቆናትና ቀሳውስት ብቻ ናቸው፡፡ ከዚህ ውጭ ሥልጣን የሌላቸው ወይም ሥልጣናቸውን በተለያየ ምክንያት ያፈረሱ ሰዎች መቀደስ አይችሉም፡፡ በማኅሌትና በሰዓታት ግን ሞያው እስካላቸው ድረስ ማገልገል ይችላሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የማኅሌቱንም ሆነ የሰዓታቱን አገልግሎት በጸሎት የሚጀምሩትም ሆነ የሚፈጽሙት ሥልጣነ ክህነት ያላቸው ብቻ ናቸው፡፡ በአጭሩ ያለው ልዩነት ይህ ነው፡፡

የተወደዳችሁ አንባብያን፦ ስለ ቅዳሴ በአጭሩ ይኸንን ያህል ከተረዳን በሚቀጥለው እትማችን ደግሞ ለቅዳሴ ከሚደረገው ዝግጅት ጀምሮ እስከ ፍሬ ቅዳሴ ድረስ ያለውን ከነገረ ድኅነት አንጻር በዝርዝር ለመመልከት እንሞክራለን፡፡

*የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን፡፡*

## አርነት

/ከገጽ ፳ የዞረ/

ቢሞክርም አልተሳካለትም፡፡ ባለችበት ፀጉሯን በእጆቹ እየደባበሰ ሊያጽናናት ሞከረ፡፡ ያልጠበቀው ሁኔታ ዋና የሰውን ትኩረት መሳባቸው እያስጨነቀው «ምነው ሜሪ ደስ አላለሽም?» ብሎ ጠየቃት፡፡

ላለመናገር የማለች ይመስል ምንም ሳትናገር አቀፈችው፡፡ ከእቅፉ አውጥቶ ዐያት፡፡ ጉንጮቿ ላይ እርጥበት ቢኖርም ፊቷ በብርሃን ደምቋል፡፡

«ሜሪ ደስ ብሎሻል?» አላት ፊቷን ለማጥናት እየሞከረ፡፡

«በጣም!» ብቻ ነው ማለት የቻለችው፡፡

«ታድያ ለምን አለቀስሽ?»

«ይኼ የምሥራች እኮ የዕለት ከዕለት ናፍቆቴ ነው፡፡ እንደ ንጋት ጮራ የሚናፈቅ ተስፋ፣ ሕይወቴን ከጨለማ ወደ ብርሃን የሚመራ... አሰግድ እግዚአብሔር ለዘላለም መልካም ነው፡፡ የልብን መሻት ያዳምጣልና አመሰግነዋለሁ፡፡»

«እኔንስ?» አለ በቀልድ መልክ ወደ ሐዘን እንዳትመለስ እየፈራ፡፡

«አንተንም አመሰግናለሁ፡፡ በአንተ ልብ አድሮ ለበጎ ነገር ያነሣሣህን እግዚአብሔርን ሳስቀድም ብዬ ነው፡፡» አለችው፡፡

አስተዋይነቷ የሁልጊዜ ግርምቱ ነው፡፡ አመለካከቷን፣ ፍላጐቷን፣ ተስፋ ዋን ለማወቅ ረጅም ጊዜ ማጥናት አላ ስፈለገውም፡፡ ልቡ ከውጫዊ ውበቷ ይልቅ ለነዚህ ስንቆቿ ሰፊ ቦታ ሰጥቶ ታል፡፡

በዚህ ሕይወት ውስጥ ሆና እግዚአብሔርን መፍራቷና ጽድቁን መሻቷን እርሱ ካለ በት የተደላደለ ኑሮና ከቅብጠቱ ጋር ሲያስበው በሥራው ከወዲሁ መጸጸት ጀመረ፡፡

* * *

ልዑል ግራ ገብቶታል፡፡ አክስቱ ከመግባቷ ጌጣጌጦቿን ሁሉ ሰብስባ ስትወረውራቸው ደረት የሚያጋልጡ ልብሶቿን አጫጭር ቀሚሶቿን በአንድ ስትሰበስብና በቁጥር ጥቂት የሆኑትን ረጅም ቀሚሶቿን በክብር ስታስቀምጥ ዝም ብሎ ያያታል፡፡ ለወትሮው በዚህ ሰዓት ከተጠቀለሉት አጫጭር ቀሚሶች አንዱን ለብሳ፣ በማጫወቻ ቻው በተከተተው መዝሙር ፋንታ ሙዚቃ ተከፍቶ፣ እርሱ ወደ ኋዳ ሣር ፍራሹ ላይ እርሷ ውጭ ብርድ ላይ ነበሩ፡፡ ዛሬ ግን ሁሉ ነገሯ ግራ አጋብቶታል፡፡ እየመሸ ቢሆንም አትለብስም፡፡ አትኳኳልም፡፡

/ወደ ገጽ ፲፰ ዞሯል/



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ተአምረ ማርያም

## ታሪኩ * ምንጩ * ይዘቱ *ተአማኒ

ባለፈው እትማችን የተአምርን ምንነት፣ የተአምርን መገለጫዎች፣ መፈጸሚያዎችንና የሚፈጸሙባቸውን ምክንያቶች የተመለከቱ ዝግጅቶችን ማቅረባችን ይታወሳል:: በዚህ እትማችን ደግሞ ተአምራትና ቅዱሳን፣ የተአምረ ማርያም መጽሐፍን ታሪክና ምንጮችን የተመለከተ ዝግጅት ይዘን ቀርበናል::

ዲያቆን ዳንኤል ክብረት

### ተአምራትና ቅዱሳን

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ:- «በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል:: ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል::» /ዮሐ.14÷12/ በማለት በሰጣቸው ቃል ኪዳን መሠረት የእግዚአብሔር ሰዎች የሆኑት ቅዱሳን ልዩ ልዩ ተአምራትን ያደርጋሉ:: በቅዱሳን የሚፈጸመው ተአምር ሦስት ነገሮችን መሠረት ያደረገ ነው::

የመጀመሪያው የእግዚአብሔርን መግቦት፣ቸርነት፣መልእክት፣ቅጣት ወዘተ መግለጥ ነው:: ሁለተኛው ደግሞ የቅዱሱን ክብር፣ቃል ኪዳን፣ጸጋ መግለጥ ሲሆን የመጨረሻውም የምእመናንን ወይም የሕዝቡን ልመና መፈጸም፣እምነትን ማጽናት ወይም ዋጋ መክፈል ነው::

ቅዱሳን ሐዋርያትን ወደ ዓለም ሲልካቸው ስብከታቸውን በተአምራት እንደሚያጸናላቸው ቃል ገብቶላቸዋል:: /ማር.16÷15/:: ሐዋርያው ናትናኤል በተጠራ ጊዜ:- «ከበለስ በታች አየሁህ ስላልኩህ አመንክን፤ እውነት እውነት እላችኋለሁ÷ ሰማይ ሲከፈት የእግዚአብሔር መላእክት በሰው ልጅ ላይ ሲወጡና ሲወርዱ ታያላችሁ» ብሎታል:: /ዮሐ.1÷51-52/:: በዚህም መሠረት ድውይ ፈውሰዋል፣ ሙት አስነሥተዋል፣ ኅብስት አበርክተዋል:: እነ ቅዱስ እስጢፋኖስ ምስጢረ ሥላሴን አይተዋል:: /የሐዋ.7÷54-60/:: እነ ቅዱስ ጳውሎስ እስከ ሦስተኛው ሰማይ ተነጥቀዋል:: /2ቆሮ.2÷2/:: እነ ታዖሎጐስ ዮሐንስ ሰባቱ ሰማያትን አይተዋል:: /ራእይ ዮሐ./::

ከእነርሱም በኋላ የተነሡ ቅዱሳን ተአምራት እያደረጉና እያዩ ኖረዋል:: ፓፒያስ የተባለው በሁለተኛው መ/ክ/ዘ የነበረው ሐዋርያዊ አባት በእርሱ ዘመን የሞተ ሰው በጸሎት ሲነሣ ማየቱን ጽፏል:: ዮስጦስ የተባለው ክርስቲያን የሚገድል መርዝ በልቶ እንዴት ሳይሞት እንደ ዳነም ጽፎልናል:: (Eusebius, Citiny Papias 1.154). በሁለተኛው መ/ክ/ዘ የነበረው የሰሜን አፍሪካ ሊቅ ጠርጡለስ- «የክርስቲያን ቤተሰብ ልጅ የሆነች አንዲት ወጣት ዐውቃለሁ፤ በአበባነቷ ጊዜ በሰላም ዐረፈች:: ወደ መቃብርም ከማስገባታቸው በፊት ካህኑ ጸሎት ማድረግ ጀመረ:: ልክ ጸሎቱን ሲጀምር እጆቿን ከታሰሩበት አውጥታ በጸሎት ስልት ዘረጋቻቸው:: ልክ ጸሎቱ ሲጠናቀቅም ወደ ቦታቸው ተመለሱ:: በእኛ ሰዎች ዘንድ ሌላም የታወቀ ታሪክ አለ:: ከተቀበረ ብዙ ዘመን የሆነው ዐፅም ሌላ ዐፅም በመጣ ጊዜ÷ /ዘመኑ ስማዕታት በመሆኑ ለክርስቲያኖች የመቀበሪያ ቦታ ጥበት ነበር/÷ ማንም ሳይነካው በፈቃዱ ከቦታው ፈቀቅ ብሎ መላውን አስከሬ አስቀብሯል::» (Tertullian, 3.228).

### የተአምረ ማርያም መጽሐፍ ታሪክና ምንጮች

እንደ ፕሮፌሰር ሥርግው ሀብለ ሥላሴ:- ተአምረ ማርያም በመጽሐፍ መልክ የተዘጋጀው በአውሮፓ ሆኖ ከዚያም ወደ ሶርያ፣ ኢየሩሳሌምና ግብፅ ደረሰ፤ በዐረብኛ ተተረጐመ፤ ከዚያም በ14ኛው መ/ክ/ዘ ወደ ግእዝ ተመለሰ::

ለመጀመሪያ ጊዜ በግእዝ ተአምረ ማርያምን ያስተረጐሙት ዐፄ ዳዊት ናቸው:: ከግሸን ደብረ ከርቤ ማርያም ተወስዶ በማይክሮ ፊልም የተቀረጸው ተአምረ ማርያም እንደሚገልጠው:- «ዐፄ ዳዊት /1365-1395 ዓ.ም/ በ1892 ዓ.ም ተአምረ ማርያምን ከዐረብኛ ወደ ግእዝ አስተረጐሙት:: በዚያ ትርጉም ላይ የእመቤታችንን ስም በወርቅ ቀለም እያደረጉ አስጽፈው አንድ ቅጅ ለግሸን ደብረ ከርቤ ማርያም ሰጡ::»

በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን ተአምረ ማርያምን በተመለከተ ሁለት ነገሮች ተሠርተዋል:: የመጀመሪያው ቀድሞ በተተረጐመው ላይ መጨመር ወይም አዲስ መተርጐም እና መጽሐፉን በሥርዓተ ጸሎት መደንገግ (Canonization) ነው:: ይህም በነገሡ በስምንተኛው ዓመት /1433 ዓ.ም/ አቡነ ሚካኤልና አቡነ ገብርኤል የተባሉት ግብፃውያን ጳጳሳት በመጡ በሦስተኛው ዓመት ነው:: /መቅድመ ተአምረ ማርያም/::

ተአምረ ማርያም እንደ ተጠቃለለ መጽሐፍ ይህን የመሰለ ታሪክ ይኑረው እንጂ በውስጡ ያሉት ታሪኮች ግን በየዘመናቱ የነበሩ የቤተ ክርስቲያን አበው /ኤጲፋንዮስ፣ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ሄሮኒመስ፣ አውሳብዮስ፣ አትናቴዎስ፣ ቴዎፍሎስ፣ ጢሞቴዎስ፣ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም፣ ድሜጥሮስ ዘአንጾኪያ/ ተጽፈው የነበሩ ናቸው::

### የተአምረ ማርያም ታሪኮች ምንጮች

ስለ ተአምረ ማርያም ታሪኮች ምንጮች ከመግለጣችን በፊት ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ታሪኮች ምንጮች መግለጡ ጠለቅ ያለ ግንዛቤ ይሰጠናል ተብሎ ይታመናል::

ቅዱሳት መጻሕፍት ዋና ዓላማቸው ታሪክን መመዝገብ ሳይሆን የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ መግለጥ ነው:: በርግጥ እግረ መንገዳቸውን የየዘመኑን ታሪክ መዝግበውልናል:: ይህ ማለት ግን ሁሉም የቅዱሳት መጻሕፍት ታሪኮች በታሪክ መዛግብት ወይም በአርኪዎሎጂ ቁፋሮ በሚገኝ መረጃዎች መረጋገጥ አለባቸው ማለት አይደለም:: የዚህም ምክንያቱ በቅዱሳት መጻሕፍት ታላቅ ቦታ የተሰጣቸው የሰው ልጅ የድኅነት ታሪኮች በታሪክ ዘጋቢዎች ዘንድ ቦታ ላይሰጣቸው ስለሚችል ነው:: ከዚህም በተጨማሪ እግዚአብሔር ድንቅ ሥራውን የገለጠባቸው አንዳንድ ሰዎችና ቦታዎች በዚህ ዓለም ዘንድ እንደ ምናምንቴ የሚቆጠሩ በመሆናቸውም ይሆናል::

ለምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ታሪኮችን ሁሉ ከታሪክ መዛግብት ጋር በማመሳከር ብቻ የመቀበል አካኼድን ብንከተል ብዙዎቹን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን ወዳ ለመቀበል ይወስደናል:: ሌላው ቀርቶ የአይሁድን ታሪክ ከአዳም እስከ ኢየሩሳሌም ጥፋት በ20 ቅጽ መጽሐፍ የጻፈው ዮሴፍ ወልደ ኩርዮን በሰው ልጅ የመዳን ታሪክ ውስጥ የማይተካ? ቦታ ያለውን የጌታችንን ልደት፣ ዕድገት፣ ሞት፣ ትንሣኤና ዕርገት አልጠቀሰውም:: ይህ ማለት ግን ጌታችን አልተወለደም፣ አላስተማረም፣ አልሞተም፣ አልተነሣም፣ አላረገም ማለት አይደለም::

ወደ ኋላም ተመልሰን ከዓለም ታሪክ ጋር ትንቢቱ በቀጥታ የሚገናኝ ነቢይ የተባለለት ነቢዩ ዳንኤል የገለጠውን ዳርዮስ ዘሜዶን በታሪክ መዛግብትም ሆነ በባቢሎን በተደረጉ የአርኬዎሎጂ ምርምሮች በተገኙ መረጃዎች ህልውናውን ማረጋገጥ አልተቻለም:: ይህ ማለት ግን በመንፈስ ቅዱስ የተመራው ነቢዩ ዳንኤልን የተሳሳተ ታሪክ መዘገበ አያሰኘውም:: የኋላ ዘመን ሰዎች ዕውቀት ያልደረሰበት ምሥጢር አለ ያሰኛል .



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

እንጅ!

በሌላም በኩል ደግሞ ቅዱሳት መጻሕፍት አንድን እውነተኛ ታሪክ የሚገለጡበት መንገድ የዓለም ታሪክ ጸሐፊዎች ወይም መዝጋቢዎች ከሚገ ለጡበት መንገድ የሚለይበት ጊዜም አለ:: የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፍት መን ፈሳዊው ነገር ላይ በማተኮር ሌላውን ነገር ሲተውት የዓለም የታሪክ መዛግብት ግን ድርጊቱ ላይ በማተኮር መንፈሳዊውን እሴት ሊተዉት ይችላሉ::

የዓለም ታሪክ አባት የተባለው ሄሮዶቱስ በታሪክ መጽሐፍ ስለ ባቢ ሎንና ስለ ፋርስ የጻፈው የነገሥታቱ ን ሕይወት፣ ሞያና ውሎ፣ የሀገሪቱን ሥልጣኔና ሀብት ሲሆን ነቢዩ ዳንኤል በትንቢት መጽሐፉ የጻፈው ግን እግዚ አብሔር በነዚህ መንግሥታት ዘመን የፈጸመውን አምላካዊ ሥራና ከዚህ ጋር የሚገናኙ ታሪኮችን ብቻ ነው:: በመሆ ኑም በሄሮዶቱስ ትልቅ ቦታ የተሰጠውን ነቢዩ ዳንኤል ሲተወው በነቢዩ ዳንኤል ትልቅ ቦታ የተሰጠውን ደግሞ ታሪክ ጸሐፊው ሄሮዶቱስ ትቶታል::

*አሁን ወደ ተአምረ ማርያም እንመለስ::*

በተአምረ ማርያም የሚገኙ ታሪ ኮች ሁለት ዓይነት ናቸው:: የመጀመ ሪያዎቹ በሌሎች የቤተ ክርስቲያን መጻሕትም ሆነ በሌሎች የታሪክ መዛግ ብት ተጨማሪ ማረጋገጫ የሚገኝላቸው ሲሆኑ ሁለተኛዎቹ ደግሞ በተአምረ ማርያም ላይ ተመዝግበው የሚገኙ ናቸው::

በደብረ ምጥማቅና በደብረ ቀስ ቋም የተደረጉ ተአምራት፣ በአባ አብር ሃም ሶርያዊ ዘመን ስለተደረገው ተአ ምር፣ ስለ ገብረ ክርስቶስ የተፃፈው፣ ስለ እመቤታችን ፍልሰተ ሥጋ የተገለጠ ው/ነሐሴ 16 ስንክሳር/፣ ስለ ጌታችን ልደት የተጻፈው፣ ወዘተ በሌሎች መዛ ግብትም በተመሳሳይነት ታሪኮቹ የሚ ገኙ ሲሆን በምድረ ዳሞት ወድቃ ስለ ተነሣችው ዕጽ፣ ስለ አንዲት ዘማዊት፣ ስለ በለዔ ሰብእ፣ ስለ አንድ ነጋዴ ወዘተ የተገለጡት ግን በተአምረ ማርያም ተገልጠው የተገኙ ናቸው::

በተአምረ ማርያም መጽሐፍ ላይ የተመዘገቡት ታሪኮች ከኢትዮጵያ ውጭ የተፈጸሙት ተተርጉመው የገቡ ሲሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጸሙት ደግሞ ከሀገር ውስጥ ምንጮች ወደ ተአምረ ማርያም የገቡ ናቸው:: ከሀገር ውጭ የተፈጸሙትን ታሪኮች በሁለት መክፈል ይቻላል:: እነዚህም በጥንታ ውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ በመደበኛነት የሚታወቁ እና በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ብቻ የሚታ ወቁ ናቸው::

ስለ እመቤታችን መጸነስና መወ ለድ፣ ስለ ቤተ መቅደስ መግባቷና ስለ ጌታችንን ስለ መውለዷ ስለ ዕረፍቷ ወዘተ. የተገለጡት ታሪኮች በሁሉም ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የታወቁና የተመዘገቡ ሲሆኑ በግብፅና በሶርያ ገዳማትና በቁስጥንጥንያና በሮም የተፈጸሙ ተአምራት ደግሞ በየሀገራቸው የታወቁ ሆነው በዚያው ሀገር ከሚገኙ ምንጮች የተቀዱ ናቸው::

በኢየሩሳሌም በበዓለ ትንሣኤ ጊ ዜ ስለ ወረደው ብርሃን፣ በዳሞት ሀገር ወድቃ ስለ ተነሣችው ዕፅ፣ ለመስቀልና ለእግዝእትነ ማርያም ስግ ደት እንዲገባ፣ በተከዜ ወንዝ ማዶ ስለ ነበረች ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ ኢ ትዮጵያ ሰዎች የተናገረችው ሥዕል፣ እንዲሁም እመቤታችን በስደትዋ ወቅ ት በኢትዮጵያ ያደረገችውን ጉዞ የተመለከቱት ታሪኮች ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምንጮች የተወሰዱ ናቸው::

በተአምረ ማርያምም ሆነ በሌ ሎች የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት የእመቤታችንን መልክእ፣ ጠባይና ደግ ነት በተመለከተ የተገለጡት ሁለት ሊቃውንትን መሠረት ያደረጉ ናቸ ው:: የመጀመሪያው በዚህ ምድር በዐ ጸደ ሥጋ በነበረችበት ጊዜ አባቱ ቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድን ተከትሎ እርሷን ለማየት ዕድል የገጠ መውና ከመንፈስ አባቱ ከዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ጋር ባደረገው የደብ ዳቤ ልውውጥ ስለ እመቤታችን ብዙ መረጃ ያገኘው አግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ የጻፈው የመጀመሪያ ምንጫ ቸው ሲሆን፣ ከኋለኞቹ ሊቃውንት መካከል ደግሞ ከቀድሞ አባቶቹ ያገኘ ውን ትውፊት በመጽሐፉ ያሠፈረው የቅዱስ ኤጲፋንዮስ ዘሀገረ ቆጵሮስ የጻፈው ደግሞ ሁለተኛው ምንጭ ነው::

የኤጲፋንዮስ ገለጻ /320 -404 ዓ.ም/

*በሥራዋ ሁሉ ቁጥብና ልዕልት ናት፤ የምትናገረው እጅግ በጣም ጥቂት ሲሆን ያም አስፈላጊ ሲሆን ብቻ ነው:: ለማዳመጥ ሁልጊዜ ዝግጁ ና ትኩረት የምትሰጥ ናት:: ለሁሉም ሰው ክብርና ልዩ ቦታ ትሰጣለች:: ቁ መናዋ መካከለኛ ነው:: አንዳንዶች ግን ከዚያም ዘለግ ያለች ናት ይላሉ:: ለሁሉም ሰው ስትናገር በትሕትና ያለ ሳቅና ያለፌዝ ቁም ነገር በተሞላበት አኳኋን ነው:: ለቁጣ እጅግ የዘገየች በሁሉም ነገርዋ ግልጽና ቅርብ ናት :: መልክዋ የብስል ገብስ፣ ጸጉርዋ ትንሽ ቀላ ያለ፣ ዐይኖቿ ብሩኅና ቀላል ቡና ማ ናቸው:: ቅንድቧ ግማሽ ክብ ሆኖ በጣም ጥቁር ነው:: አፍንጫዋ ረዥምና ከናፍርዋ የፈካአበባ የመሰለ ሲሆን ከውስጡም እጅግ ጣፋጭ የሆኑ ቃላት ይወጣሉ:: ገጽዋ ወደ ክብ ሲ ያደላ እጅዋ ረዥም ነው:: ከኩራት ፍ ጹም ነጻ የሆነች፣ ቀና፣ ትሑትና ፍ ጹም ደግ ናት:: የምትለብሳቸው መጐ ናጸፊያዎች የተፈጥሮ ቀለም ያላቸው ናቸው /ያም ማለት ከተሠሩ በኋላ ሌላ ቀለም ያልገባባቸው ማለት ነው/:: ይህም እስከ ዛሬ በሚገኘው የጸጉርዋ መጐናጸፊያ ማረጋገጥ ይቻላል /በኤጲ ፋንዮስ ዘመን በነበረው/:: ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ ሁለመናዋ በመለ ኰታዊ ጸጋ የተሞላ ነው:: /ትርጉም በአዘጋጁ/*

Nice phorus cauisuts, Eccles. Hist. xx 111 /ed. migne/ patrologiae, serics Graeca, tome 145, col 815/

ቀጥሎ የተገለጠው ደግሞ አግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ የጻፈው ነው /35-107 ዓ.ም /:-

በስቃይና በመከራ መካከል እንኳን ሁልጊዜ ደስተኛ ናት:: አስቸ ጋሪ ሁኔታዎች በተፈጠሩ ጊዜ ሁሉ ሐሴት ታደርጋለች:: የእነርሱን ጉዳት ትካፈል ዘንድ ከምስኪኖችና ከተጐዱ ሁሉ ጋር ታዝናለች:: እነር ሱንም ለመርዳት ከቶ አትዘገይም:: ከተዛቡ እምነቶችና ጠባዮች ጋር የሚደረገውን የእምነት ተጋድሎ በ ጽናት እንደምትቋቋም ዐውቀናልና የአዲሱ እምነታችንና የሥርዓታችን እናት ናት:: የቅድስና ፍሬዎች ከሆ ኑት አማንያን ሁሉ ልቃ ተፈጥራ ለች:: ትሕትና ገንዘቧ ነው:: ከሁሉ በላይ ራስዋን በትሕትና ያስገዛች ናት:: ምንም እንኳን በፈሪሳውያንና በጸሮች ክብሯን ለመቀነስ ጥረት ቢ ደረግም በሚያስደንቅ ሁኔታ በሁሉም ዘንድ ከፍ ብላ ትታያለች:: ከዚህ ሁሉ በላይ ብዙ ሰዎች ስለ እርሷ አያሌ ነገሮችን ነግረውናል ሊታመኑ ከሚችሉ ሰዎች የጌታችን እናት ማርያም መልአካዊ ንጽሕናን ከሰብ አዊ ጠባይ ጋር ያስተባበረች መሆን ዋን ዐውቀናል:: እነዚህ ነገሮች መን ፈሳችንን እያነሣሡት፤ ይህችን ሰማያ ዊ ሰጦታና ድንቅ ቅድስት እናት ለ ማየት ያለን ጉጉትም በጣም ጨመ ረ::

/Ante- Niane Fathers, vol.1, I gnatius/

የእመቤታችንን እናትና አባት፣ የዘር ሐረግዋንና የልደቷን ነገር የሚመለከተው የተአምረ ማር ያም ክፍል የተወሰደው የታናሽ ያዕ ቆብ መጽሐፍ/ Protevan gelion/ ከተ ሰኘው ከሐዋርያት አንዱ የሆነው የኢ የሩሳሌም የመጀመሪያው ኤጲስ ቆጰ ስ ሐዋርያው ያዕቆብ ከጻፈው መጽሐ ፍ ነው:: በዚህ መጽሐፍ የሐናና የኢ ያቄም ታሪክ፣ እመቤታችን እንዴት እንደ ተጸነሰች፣ ወደ ሊባኖስ ተራ ራ ሐና ይዛት መሸሕን፣ የዘካርያስን መገደል እናገኛለን:: ይህ መጽሐፍ መጀመሪያ በዕብራይስጥ ተጽፎ የነበረ ሲሆን በኋላ ግን በሶሪያ፣በግብጽና በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ተተርጉሟል::

እመቤታችን ከቤተ ልሔም ወደ ግብጽ በተሰደደችበት ጊዜ ያጋጠማትን መከራና ስቃይ በተመ ለከተ በተአምረ ማርያም የተገለጡት



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ታሪኮች ሐዋርያው ማቴዎስ በዕብራይስጥ ቋንቋ በጻፈውና በኋላ ዘመን አባ ሄሮኒመስ /ጀሮም/- Liber de Ortu Beatae Mariae et Infantia Salvatoris በሚልርእስ ወደ ላቲን ከተረጎመው መጽሐፍ የተወሰዱ ናቸው። ይህን መጽሐፍ ከቀደምት የቤተ ክርስቲያን አበው መካከል አውሳብዮስ፣ አትናቴዎስ፣ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ርግጠኝነቱንና የታሪኩን ትክክለኛነት ተቀብለውታል። /Legends of the Virgin Mary, xxviii /

የሁለቱ ሽፍቶች የጥጦስና ዳክርስ ታሪክ /በጌታችን ስደት ጊዜ መገናኘታቸው/፣አራዊት በመጡባት ጊዜ ጌታችን እንዴት እንደገሠጻቸው፣ ሄልዮፖሊስ በተባለው የጣዖት ከተማ የተደረገው ተአምራት፣ በዚህ መጽሐፍ ቀድመው የተመዘገቡ ናቸው።

እመቤታችን በቤተ መቅደስ የነበረችበትን ኑሮ በተመለከተ ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም ሲገልጠው «መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል በሚያስደስት ቃሉ ሳያነጋግራት በፊት በቤተ መቅደስ ብቻዋን ነበረች። ለውበቷ መጠን የለውም፤ በመልካሙ መዓዛዋ የተነሣ ቤተ መቀደሱ በቅዱሳን መላእክት ይመላ ነበር ከርሷ ጋር በመነጋገርም መላክት ዘወትር ይጉበኟት ነበር።» ብሏል። /E.A. Wallis Budge, Miscellaneous coptic Texts in The dialect of upper Egypt, London,1915/.

የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳስ የነበረው ድሜጥሮስ በታኅሣሥ 29 ድርሰቱ። « እመቤታችን ሦስት ዓመት በሆናት ጊዜ እናትና አባቷ ወደ ቤተ መቅደስ ወሰዷት። በቤተ መቅደሱ በረንዳ ባቆመቻት ጊዜ ራስዋ ወደ ቤተ መቅደስ ገባች። ከዚያ በኋላ አልተመለሰችም። ካህናቱ ከርስዋ ጋር ለመገናኘት ይፈሩ ነበር። ሰውነቱ ቅዱስ ልቡናዋም በእግዚአብሔር የጸና ነበር። በውስጥም በውጭም ንጹሕ ነበረች፤ ፊቷንም ከቤተ መቅደስ ወደ ውጭ ተመልክታበት አታውቅም ነበር። በትሕትናና በትሕርምት እግዚአብሔርንም በማገልገል ኖረች።» በማለት ገልጦታል። /ዘኒ. ከማሁ/።

ይኸው ቅዱስ ቄርሎስ በ12 ዓመታዋ ወደ ዮሴፍ ቤት ከገባች በኋላ በትሕትና ከማገልገል፣ሐርና ወርቅ አስማምታ ከመፍተል በስተቀር ለመዝናናትና ለማረፍ ጊዜ እንዳልነበራት ገልጦታል።

ዓምደ ሃይማኖት የተባለ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ ደግሞ «ለዚህ ዓለም ደስታና ምቾት ትኩረት አልነበራትም፤በሕዝብ መታጠቢያም ታጥባ አታውቅም፤ ለገጽዋ ጌጥ፣ ለዐይኗም ሽልማት አልፈለገችም፤በሚያብረቀርቅ ልብስ ለማጌጥም ልቡናዋ አልተነሣም፤ ውኃን አልቀመሰችም፤ የምትቀመጠው ዘወትር ወደ ምሥራቅ በመዞር ነበር። ይህም የዓለምን ፈጣሪ መምጣት ለመጠበቅ ነው። ረብ ካለውና ሰውን ከሚያንጸው በቀር ከማንም ጋር አውርታ አታውቅም ከአባቷ፣ ከእናቷና ከወንድሞቿ በቀር» ብሏል /ዝኒ ከማሁ/

በተአምረ ማርያም መጨረሻ ላይ የምናገኛቸው የእመቤታችን የስደትዋን ነገር የሚገልጡት ታሪኮች ደግሞ ለእስክንድርያ ፓትርያርኮች ለአቡነ ቴዎፍሎስ እና ለአባ ጢሞቴዎስ ተገልጣ የነገረቻቸው ነው። ይህም በግብጽ /ቅብጥ/ . እና ፀዕርያ /ሱርስት/ ቋንቋዎች የሚገኝ ሲሆን ወደ ተአምረ ማርያም የገባው ከሁለት ምንጮች ሊሆን ይችላል። የመጀመሪያው ተአምረ ማርያም ወደ ግእዝ ሲተረጎም አብሮ የተተረጎመ ወይም ደግሞ በግእዝ ተጽፎ ከሚገኘው የአቡነ ቴዎፍሎስና የአቡነ ጢሞቴዎስ መጽሐፍ የተወሰደም ሊሆን ይችላል።

በመቅድመ ተአምረ ማርያም የሚገኘው የእመቤታችን ሰላምታ /ዘከመ ይደሉ ሰጊድ ለማርያም ብሎ የሚጀምረው/ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ምስጋና ሲሆን የተወሰነው ከታላቁ የሃይማኖት መጽሐፍ ከሃይማኖተ አበው ነው። /ሃይማኖተ አበው ዘዮሐንስ አፈወርቅ፣ ምዕ. 68፣ ክፍል 26/። የጻድቁ ገብረ ክርስቶስ ታሪክ ገድሉን መሠረት አድርጎ የተጻፈ ሲሆን የሶርያዊው ሊቀ ጳጳስ የአቡነ አብርሃምና የጫማ ሰፊው የስምዖን ታሪክ ደግሞ ግብጽ በእስላሞች እጅ በወደቀችበት ጊዜ የተፈጸመ በስንክሳርም በተጨማሪነት የሚገኝ በዓለም ታሪክም የተመዘገበ ታሪክ ነው/ The Book of coptic saints.vol.1/

በአጠቃላይ በተአምረ ማርያም ከሚገኙት ታሪኮች ከፊሎቹ ቀደምት የቤተ ክርስቲያን አበው መዝግበው ያስቀመጡአቸውና በኋላ ለተለየ አገልግሎት በተአምረ ማርያም መጽሐፍ ውስጥ የተጠቃለሉ ናቸው ማለት ነው። ይህ ደግሞ በሌሎች መጻሕፍት ብቻ ሳይሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም የሚገኝ አሠራር ነው። /2ዜና 9÷29-30፤ 12÷15-16፤ 16÷11-12/።

ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት የተወሰዱትንና ሌሎች ታሪኮችን በተመለከተ ደግሞ በቀጣዩ እትም የምንመለስበት ይሆናል።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

## አርነት

*/ከገጽ ፲፭ የዞረ/*

እራት ከበሉ በኋላ ወደ ጓዳ ሊገባ ሲል «ልዑሌ ና ዛሬ ከኔ ጋር ነው የምታድር» አለችው።

«ወንዶች አይመጡም?» ሊላት ፈልጎ ፈራና ምላሱ ላይ ቃሉን ያዘው። ዝም ብሎ አልጋዋ ላይ ወጣ። መብራት አጥፍተው ከመተኛታቸው በርተን ኳኳ። «ማነው ያለ የለም። ድምፃቸውን አጠፉ።

«አይ ሴት፤ እመጣለሁ አላልኩሽም?! ከምኔው አንዱን ጠልፈሽ ገባሽ?» «በስካራምኛ» ቃላቱን እየለጠጠ አንዱ ደንበኛዋ ተራገመ። ከቤቱ ውስጥ ምላሽ የለም። ሜሪ የሰማችው አት መስልም። ለወትሮዋ ቢሆን እንኳን ፈልገው የሚመጡ ወንዶች ሲለፈልፉ ልዑል በመስማቱ ትሳቀቅ ነበር። አሁን ግን ማንም ስለ እርሷ ምንም ቢል ግድ የላትም። ራሷን በጸጸትና በዝሙት ከምትኖርበት የኃጢአት ግዞት በእግዚአብሔር ፍጹም ፈቃድና በልቡናዋ መሻት አርነት አውጥታለች። ዛሬ ብሩህ ሕይወቷን በቆራጥነት አሐዱ ስላለች ለወደፊቱ ሰላሟ ማለም ጀምራለች። ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ስላለፈው ሕይወቷ ንስሐ ትገባለች።

«አንቺ ’ማትረቢ! ለመሆኑ የስንት ብር ጭማሪ አግኝተሽ ነው?» ሰካራሙ ሰው አልሄደም። የእርሱን ድምፅ ለማጥፋት የቴፑን ድምፅ ጨመረችው።

«ስሜ ተለውጦ ዘማዊ ብባልም፣
ራራልኝ ጌታ ነውሬን አልቆጠረም፤
ፈሪሳውያኑ አካልበው ሲወስዱኝ፤
ኢየሱስ ግን ያኔ በፍቅር ፊት አየኝ፤
ኢየሱስ ግን ያኔ በርኅራኄ ፊት አየኝ....»።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

*ክቡራን አንባብያን፤ በዚህ እትም በቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ ዓምድ መቅረብ የነበረባቸውን የ«ክርስትና ስም፣ ክርስትና አባትና እናት» እና «የሥርዓት መፈጸሚያ መጻሕፍት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን» ቀጣይ ጽሑፎች በቦታ ጥበት ምክንያት ማቅረብ ባለመቻላችን ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥለው እትም የምናቀርብ መሆናችንን እናሳውቃለን።*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# አርነት

*ትእግሥት ታፈረ*

«ፒያሳ አውቶብስ ተራ... አውቶብስ ተራ ፒያሳ...» የወያላዎች ድምፅ በተለመደ ዘዬአቸው ይሰማል:: ሜሪ አንድ ዐይኗን በትንሹ ከፈት ስታደርግ በጣሪያው ቀዳዳዎች፣ በመስኮቱና በበሩ የገቡ የብርሃን ጨረሮች ቤቱን ድፍን ካለ ጨለማ ነጻ እንዳወጡት ዐየች:: ቀስ ብላ ሁለቱንም ገለጠቻቸውና ከእርሷ ትራስ ጐን ያለውን ትራስ ተመለከተች:: ባዶ ነው:: እንባ በዐይኖቿ ዙሪያ ግጥም አለ:: ትንሽ ቆይታ ድምፅ አውጥታ ፊቷን በትራሱ ሰውራ ተንሰቀሰቀች:: አውሬ ዐይታ እንደ ደነበረች ደካማ እንስሳ ከመቅጽበት ተነሥታ መስተዋቱ ፊት ተገተረች:: ከንፈሯ ላይ ምልክት ብቻ ትቶ የጠፋው ቀለም ቆዳዋን እንደ ማድረቅ አድርጎታል:: ዐይኗን የተኳለችው ኩል በለቅሶዋ ምክንያት ጉንጮቿ ላይ ጥቁር ሸንተረር ሠርተዋል:: የፊቷ ቅላትም ድምቀታቸውን ያጋነነው ይመስላል:: ራሷን በደንብ አስተዋለችው:: ረጅም ናት:: ሰውነቷ ቁመቷን ይመጥነዋል:: ሜሪ «እስቀያሚ» በማለት የምታየውን ምስል ገላመጠችው:: ውበቷን መካድ አትችልም:: በሰው ሰውኛ «ቆንጆ» የምትባል ዓይነት ሴት ናት:: ከውበቷ በስተጀርባ መሸቶ በነጋ ቁጥር በእንባ ማዕበል የሚያንገላታትና በበደለኝነት ውስጧን ቀስፎ ይዞ የሚያጣድፏት ራሷን እስክትጠላ የሚያንገፈግፏትን ምግባሯን እንጂ... ያም ቢሆን በፍላጐቷ የሆነ አንዳች ነገር የለም:: ከምትጠላው ሕይወት መሸሽ ሳትችል ለዓመታት ኖራለች:: ለረጅም ጊዜ ከማይነጥፉት ዐይኖቿ እንባዎቿ ታልበዋል:: መስተዋቱ ፊት ተገትራ የሚታያትን የረከሰ ነገር ሁሉ አውግዛለች:: ከእንቅልፍ እንደ ነቃች የመጀመሪያ ሥራዋ ከጐኗ ያለውን ትራስ መመልከት ነው:: አብሯት ያደረው ሰው እንደ ሄደ ካረጋገጠች በኋላ እንባዋ ይተናነቃታል:: ዛሬም የተለመደውን ነው ያደረገችው::

ለሰዓታት ባለችበት ፈዛ የሆነውን፣ የሚሆነውንና እንዲሆን የምትፈልገውን ስታወጣና ስታወርድ ቆይታ ከእውን እንቅልፏ በቤተ ክርስቲያን ደወል ነቃች:: በቅርብ ያገኘችውን ለባብሳ እንባዋን እየዘራች ሮጠች:: ቆሻሻ ውኃ ለመድፋት የወጡ ሴቶች ያልወጡትን እየጠሩ እንደ ሁሌው በዝሙት ጆሮ ውስጥ ተሰንቅሮ በሚቀር ሳቅ አጅበው ሸኟት::

ቤቷ ከቱሪስት ሆቴል ጀርባ ነው:: መንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ለመድረስ ዐሥራ ሰባት ቁጥር የምታልፍበት መንገድ ይቀናታል:: ቀጥ ያለውን አስፋልት በፍጥነት ስለ ተያያዘችው ማለህ ለህ ግድ ሆነ:: እንደ ደረሰች ግቢውን በዐይኖቿ ቃኘች:: ነጠላ ለባሾች ሞልተ ውታል:: ሁሉም ከጉልበታቸው ሸብረ ክ... ሸብረክ ብለው ሰግደዋል:: የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ተዘጋጅተው ለቀረቡት እየተሰጠ መሆኑ ገባት:: ዛሬም በእግሯ የረገጠችው መሬት የተፀየፉት መሰላትና ተሸማቀቀች:: አልደፈረችም:: ዙሪያዋን በፍርሃት አማተረች:: እንደ እሷ ቀጥ ብሎ የቆመ ይቅርና ከአንገቱ ቀና ያለ ምእመን አይታይም:: ሰዎች በማንኛውም ሰዓት እየሰገዱ የሚያመሰግኑበትና የሚጸልዩበት የምስለ ፍቁር ወልዳ ሥዕል እንደ ቤት መጠለያ ተሠርቶለት ይታያል:: ሜሪ ለአምስት ኪሎ የሚቀርበውን በር የምትመርጠውም በቅርብ ርቀትም ቢሆን ከእመቤታችን ሥዕል ጋር መነጋገሩ ስለ ሚያስደስታት ነው:: አሁንም ዐይኖቿን ወደ ሥዕሊቱ ላከች:: እዛው ልታረጋቸው ግን አልቻለችም:: ዐይኖቿ አፈሩ:: አንገቷን ደፋች:: እንደ ገና ቀና አለች:: አላስቻላትም:: «አይዞሽ የኔ ልጅ፤ ይህ እየታደለ ያለው የልጄ ሥጋና ደም እኮ አንቺንም ለማዳን የተከፈለ መሥዋዕት ነው:: በይ ራስሽን እንደ ሌሎቹ ዝቅ አድርጊና አመስግኝ» ያለቻት መሰላት::

«እኔ እኮ እንደ ነሱ ንጹሕ አይደለሁም!?» እጅግ በተሰበረ ድምፅ ለራሷ ብቻ ተናገረች:: አሁን ከእመቤታችን ሥዕል መልስ አልጠበቀችም:: ከተቀደሰው ቅጥር የመግባቷ ድፍረት እያስጨነቃት የተባረከው ምድር ላይ በበደል የረከሰ ገላዋን ማነካካቱ እንዳያስቀስፋት እየሰጋች በርከክ አለች::

ካህናቱ ድርገት ወርደው ሲመለሱ ሁሉም ቀና ቀና ማለት ጀመረ:: ሜሪ ሰዎቹ እንዳደረጉት አደረገች:: «አንቺ ደፋር አስመሳይ፤ እዚህ ምን ትሠሪያለሽ?» በዕድሜ ጠና ያሉ ሴትዮ እንደ መገሠጽ እየቃጣቸው ጠየቋት:: ሲሰርቅ እንደ ተያዘ ሰው ውስጧ ሲሸማቀቅ ይታወቃታል:: «ስሚ፤ እንደ ጓደኞችሽ ቆሪጥ ቤት ብትሄጅ ይሻልሻል:: ለእንዳንቺ ዓይነቱ ዓላማ ቤተ ክርስቲያን መላ የላትም::» በቀድሞው ድምፃቸው ተናገሩ:: በፍርሃት ቀስ አድርጋ ዐየት አደረገቻቸው:: ታውቃቸዋለች:: ከእርሷ ቤት ትንሽ ራቅ ብለው የሚኖሩ ጠጅ ኮማሪት ናቸው:: ሁሌም ሲያይዋት ደማቸው ይንተከተካል::

«የዛሬ ልጆች ደፋር ናችሁ::» አሉ ዝምታዋ አሸናፊነቷን ያጐላው እየመሰላቸው:: የሜሪ ዐይን ሴትዮዋ ላይ አልቆየም:: ሳታስበው በእመቤታችን ሥዕል ላይ ዐይኗ ተወርውሮ ተሰካ::

«አይዞሽ የኔ ልጅ...» ርኅራኄ በዋጠው ቃና በምናብ መለሰችላት:: ከማሪዋ ከአጠገቧ ሲሄዱ ፊቷን በነጠላዋ ሸፍና ድምፅዋን ቀንሳ ብሶቷን በጸሎት መልክ መተንፈስ ጀመረች::

«አቤቱ አምላኬ፤ ስምህን ለመጥራት ፈራሁ:: አንደበቴ በሐሰት ረክሷልና፤ ቀና ብዬ ላይህ ዐይን የለኝም:: ዐይኖቼ ከመልካም ነገር ርቀዋልና የማደሪያህን የቤተ መቅደስህን ምድር ለመርገጥ ተሸማቀቅኩ:: በዝሙት አካሌ ቆሽሿልና...» ሳግ ያቋርጣታል::

«... ምንም እንኳን እጅግ ብቆሽሽም ጽድቅን የምሻ ባሪያህን ቸል አትበለኝ:: ከኔ የሆነ አንዳች መልካም ነገር እንደሌለ ከኔ ይልቅ አንተ ታውቃለህ:: አባት ሆይ፤ መልካ ምነትህን በውስጤ ሙላ:: ስለ እናትህ ስለ ድንግል ማርያም ብለህ የምሕረት ፊትህን መልስልኝ:: ሐዘኔ ይብቃ...» ሳግ ንግግሯን ሲይዝባት ለማልቀስ ፋታ ይሰጣታል::

«እምዬ መጽናኛዬ፤ ስለ እኔ እንባሽ ከጕርፍ እንደ ሚልቅ ዐውቃለሁ:: ምን ላርግ ... ምን ለሁን? አሁንስ የኑሮዬን ነገር አንድ መላ በይኝ?! እንደ ሰው አትጸየፊኝ... አትናቂኝ እምዬ... ዝም አትበይ ድንግል... እርኩሰቴን በተቀደሱ እጆችሽ ደባብሰሽ ቀድሽኝ::...»

ጸሎቷን በእንባዋ እያጀበች ታደርስ ስና መረጋጋት ስትጀምር ግቢውን ያጨናነቀውን ሕዝብ ቀና ብላ ስታይ መዘግየቷ ይገባታል:: ያ ሁሉ ምእመን የለም:: እንባዋን እየጠረገች በመጣችበት ሁኔታ እየሮጠች ሳይሆን አንገቷን በሐዘን ደፍታ ወደ ቤቷ የሚወስዳትን ቁልቁለት በዝግታ ትወርዳለች::

የቤቷ በር እርሷ እንደ ተወችው መለስ ብሎ አገኘችው:: ገፋ አድርጋ ከመግባቷ በፊት «ገበያ ቤተ ክርስቲያን በተመላለሰ መሰሏታል::» አንዷ ቤት ቡና ከሚጠጡ ሴቶች ተሰማት:: ሌሎችም ተናጋሪዋን በሳቅ ደገፏት:: ጓዳ ውስጥ ልዑል ያንኮራፋል:: ሣር ፍራሹ ላይ ያረፈው ጭንቅላቱ ብቻ ነው:: ሌላው አካሉ ወለሉ ላይ ተዘርግቷል:: «ታድለህ፤ የኔ ምስኪን በሰላም ታንቀላፋለህ::» አለችና ወደ ብር ማስቀመጫ ሙዳዩዋ ሄደች:: ከፈተ ቻት:: በቀይ ብሮች ታጭቃለች:: ብሮቹን በጥላቻ ገረመመቻቸውና በረጅሙ ተነፈሰች:: በረጅሙም አየር ሳበች:: የአየር ለውጥ ግን የፈራረሰ ባትን እርሷነቷን ሊገነባው አልቻለም:: ያልተነጠፈ አልጋዋን ላለማየት ጥረት እያደረገች ባለችበት ለዚህ አስከፊ ሕይወት የዳረጋትን ክስተት ወደ ኋላ መለስ ብላ መቃኘት ጀመረች::

ከዐሥር ዓመት በፊት በብቸና ዙሪያ ከገበሬዎቹ ቤተሰቦቿ ጋር ትኖር ነበር:: በትምህርቷ ስድስተኛ ክፍል እንደ ደረሰች በዝና እንጂ





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በውል የማታውቃት የብዙ ጊዜ ታላቅ እኅቷ ከሃያ ዓመት በኋላ ቤተሰቧቿን ለማየት ከአዲስ አበባ ብቅና ገባች። እኅቷ ስንቅነሽ ጠፍታ ከሄደች በኋላ ቤተሰቦቿ ጋር አልፎ አልፎ በደብዳቤ ትገናኝ ስለነበር ለእያንዳንዳቸው በቁጥራቸው ልክ ልብስና ሽራ ጫማ አመጣችላቸው። ልጆች ሁሉ ከእኅታቸው መምጣት ይልቅ በተበረከተላቸው አልባሳት ፈነደቁ። የትላንቷ «ላንቺ ስል» የዛሬዋ ሜሪም እንዲሁ። «ላንቺ ስል» ብለው እናቷ ያወጡላት ከባለቤታቸው ዘመዶች ጋር እሷ በተረገዘችበት ወቅት አለመስማማት ከሮ ነበር። ስትወለድ «ላንቺ ስል እኖራለሁ» ለማለት ፈልገው ይኼንን ስም እንዳወጡላት ለጐረቤቶቻቸው ሲያወጉ ሰምታለች። ሜሪ ያለቻት ግን እኅቷ ናት። «አስተምራታለሁ» ብላ ከቀዬዋና ከቤተሰቦቿ ነጥላ ከ10 ዓመት በፊት እንዳመጣቻት፣ መደበኛው የቀለም ትምህርት ቀርቶ እንዴት ውበቷን እንደ ምትጠብቅና ኋላ ቀር የሚያስኛትን ስሟን ትታ «ሜሪ»ን እንድ ትለምድ የተሰጣት ኮስተር ያለ ትእዛዝ ነበር። ከዚያም በአንድ ክፉ ምሽት እኅቷ ላንድ ሽማግሌ አሳልፋ ሰጠቻት። ከክብር አነሰች። በየዕለቱ ገላዋን በገንዘብ መለወጥና ገንዘቡን ለእኅቷ መገበር ሥራዋ ሆነ። ምንም ማምለጫ አልነበራትም። ቢሆንም ግን ከቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ገበሬ አባቷ ጋር በሰንበት ቀን ወደ ሰፈራቸው ደብር ስትሄድ «ዝሙት» የሚለውን ቃል ሲጠሩት ደጋግማ ሰምታለች። ማወቋ የበለጠ አሰቃያት። ቀን ቀን ባለቻት ደቂቃና ሴኮንድ ሁሉ ጽድቁንና መንግሥቱን ከመሻት አልቦዘነችም።

እኅቷ የጸጸትና የኃጢአት አሻራን ትታላት ከረጅም ጊዜ የአልጋ ቁራኛነቷ በሞት ስትለያት የሦስት ዓመት ልጇንም ትታላት አለፈች። ይኼ ከአምስት ዓመት በፊት መሆኑ ነው። ልዑል አሁን ስምንተኛ ዓመቱን ይዟል። እኅቷ አልጋ ላይ ስትውል አሉ የተባሉ የቤት ዕቃዎቿና ጌጣጌጦቿ ለሕክምና ወጪ ስለ ተሸጡ ሜሪ ሳትወድ የገባችባትን ሕይወት ለእኅቷ ልጅ ለልዑል እና እስትንፋሷን ለማቆየት ስትል ዕለት ዕለት ትኖረዋለች። ይኼም ሆኖ ደንበኞቿን ሥራ እንዲፈልጉላት ከመጠየቅ ወደ ኋላ አላለችም። አብዛኞቹ «ይኼን የመሰለ ሰውነት ይዘሽ እንዴት ሌላ ሥራ ትፈልጊያለሽ?» እያሉ ሲቀልዱባት ሌሎቹ ደግሞ ለወዲው «እሺ» እያሏት ይጠፋሉ። በቅርብ የተዋወቀችው ደንበኛዋ ግን «እሺታውን» ከልቡ ይመልሳል። እንደውም ዛሬ ከሰዓት በኋላ እንደ ሚፈልጋት ደውሎ ነግሯታል።

«ሜሪ» ልዑል ከሐሳቧ አናጠባት። የዐይኑን ቆሻሻ በእጆቹ በመሞዥቅ «ዛሬ አታነቢም እንዴ?» ብሎ ጠየቃት። ሙሉ ለሙሉ ሐሳቧን ወደ እሱ ለመመለስ እየሞከረች «እነባለሁ፤ ልዑሌ አንተ ግን ይሰለችሃል አይደል?»

«አይ፤ እንደውም ደስ ይለኛል። ከበላህ በኋላ አትነካካ ስላልሽኝ ነው እንጂ የቤት ሥራዬን ከጨረስኩ በኋላ ባነበው ደስ ይለኝ ነበር።» ወዲያው ፊቱን ታጥቦ መጽሐፍ ቅዱስንና ውዳሴ ማርያምን ጭኑ ላይ በአክብሮት ይዞ የእርሷን ንባብ መጀመር ሲጠባበቅ አፍታም አልቆየ።

ሜሪ በንጽሕናና በቅድስና እግዚአብሔርን አታገልግል እንጂ መንግሥቱን ዘወትር ትሻለች። ቃሉ መጽናኛዋ ነው። በተለይ በሐዲስ ኪዳን ያለውን ዘማዊ የነበረችዋን ሴት ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት ከመወገር ነጻ እንዳወጣት የሚተርከውን ክፍል ደጋግማ ታነበዋለች። አንድ ቀን ከዚህ ሕይወት ወጥታ በፍላጐቷ የምትኖርበትን ጊዜ በናፍቆት ታልማለች።

እኅቷ አልጋ ላይ በነበረችበት ጊዜ ሜሪ መጽሐፍ ቅዱስና ገድላትን እንዳሁኑ በልዑል እጅ ላይ እንዳለ ታነብላት ነበር። ስንቅነሽም ለወትሮው ግድ የማይሰጣት የእግዚአብሔር ሕያው ቃል ተስፋ በቆረጠችበት ጊዜ ተስፋ ይሆናት ነበር፤ ከእኅቷ ኅልፈት በኋላም ሜሪ ጸሎት ማድረሷን አላቋረጠችም። መጽሐፉን በልዑል የምታስይዘውም ሌሊት በዝሙት የረከሰ እካሏ እንዳይነካው በማሰብና በማክበር ነው። ጸሎቷን በተሰበረ መንፈስ አድርጋ ስትጨርስ ልዑል እጅ እንዳመጣለት ይገልጣል። እርሷ ታነባለች። ታድያ ቅድሚያ የምትሰጠው ለመዝሙረ ዳዊት ነው። ዛሬም መዝ.12/13/÷1-6 ያለውን ቃል ከሕይወቷ ጋር እያዛመደች ደጋግማ አነበነበችው።

*«አቤቱ እስከ መቼ ፈጽመህ ትረሳኛለህ?*
*እስከ መቼስ ፊትህን ከእኔ ትሰውራለህ?*
*እስከ መቼ በነፍሴ እመካከራለሁ?*
*ትካዜስ እስከ መቼ ይሆናል?*
*አቤቱ አምላኬ እየኝ ስማኝም፤*
*ጠላቴ አሸነፍኩት እንዳይል*
*የሚያስጨንቁኝም እኔ ብናወጥ ደስ እንዳይላቸው*
*ለሞትም እንዳልተኛ ዐይኖቼን አብራ፤*
*እኔ ግን በቸርነትህ ታመንሁ፤*
*ልቤም በመድኃኒትህ ደስ ይለዋል።*
*የረዳኝን እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ፤*
*ለልዑል እግዚአብሔር ስምም እዘምራለሁ።*

«ሜሪ መዝሙር ልዘምርልሽ?» ማንበብ ማቆሟን ዐይቶ መጽሐፍ ቅዱሱን እያስተካከለ ጠየቃት።

«እሺ፤ የኔ አባት መጽሐፎቹን ከቦታቸው አስቀምጥና መዝሙር ደብተርህን አምጣ።» ከማለቷ በደስታ የተባለውን አደረገ። እናቱ ከሞተች ጀምሮ እሑድ እሑድ የሕፃናት ሰንበት ት/ቤቱ የሕፃናት ክፍል እንዲማር ስለ ምትልከው በጥሩ ሥነ ምግባር እየታነጸ ማደጉ ያስደስታታል።

«ሜሪ ለምኝ ድንግል ለምኝ... የሚለውን ልዘምር ወይስ በኃጢአት ያደፈ የሚለውን?» ትወዳቸዋለች ብሎ ያሰበውን በድምፁ እየሞከረ አስታወሳት።

«እሱንም ትዘምርልኛለህ፤ መጀመሪያ ግን ያን በጣም የምወደውን መዝሙር እንዘምር። ታውቀዋለህ አይደል?»

«ዐይንህ እንዳዩ ን....?» አላት በእርግጠኝነት።

*«ዓይንህ እንዳዩ ያልፈረድክብኝ*
*ጆሮህ እንደሰማ ያልበየንክብኝ*
*ከጥፋቴ ሁሉ የራራህልኝ*
*አምላክ ተመስገን ተመስገንልኝ*
*ዝቅ ካልኩበት ከፍ ያደረከኝ።...»*

የሚለውን መዝሙር እርሷ በለቅሶዋ አጅባ ስትዘምር ልዑል በመገረም አቋርጦ ይመለከታታል።

በየሰዓቱ ለመልስ የሚከብዳት ጥያቄዎች ይጠይቃታል። «መጽሐፍ ቅዱስ እርሷ ለምን እንደማትነካ፣ ብዙ ጊዜ ለምን እንደምትተክዝና አሁን አሁን ቢተወውም ማታ ማታ የሚመጡት ሰዎች ምናችን ናቸው?» ብሎ ሲጠይቃት የምትገባበት ይጠፋታል። አሁን አሁን ገብቶት ይሁን መልሷ አላረካው እያለ ይሁን ባታውቀውም ጥያቄዎቹ ዕድሜው ሲጨምር እየቀነሱ ሄዱላት።

«በቃ፤ ሁሉንም ቦታቸው አስቀምጣቸው እኔ ቤቱን እስካፀዳ ጋዝ ለኩስና ሻይ ጣድ» አለችው። ውስጧን ከሚንጣት ስሜት ቀስ በቀስ ስትላቀቅ።

ከሰዓት በኋላ ልዑልን ወደ ሰንበት ት/ቤቱ ሸኝታ ወደ ቀጠሮዋ አመራች። ከቀጠሯቸው አምስት ደቂቃ ቀድማ ብትደርስም አስግድን መቅደም አልቻለችም። ፒያሳ ሄርሞን ካፌ በር ላይ ቁጭ ብሎ ሲጠብቃት አገኘችው። ከሰላምታ በኋላ ያዘዙትን እየወሰዱ ብዙ አወሩ። ስለ ሕይወት፣ ስለ ዘመኑ በሽታ አስከፊነት፣ ስለ ኃጢአትና ጽድቅ... አለመግባባት በመሐላቸው አልነበረም። ሜሪ በርግጥ በሙሉ ልቧ አታወራም ነበር። «በቃ የቀጠረኝ ለጨዋታ ብቻ ነው?» የሚለው ሐሳቧ ይጠልፋታል። አስግድም ነገሩ ዘግይቶ የገባው ይመስል በመጨረሻ የአጐቱ ድርጅት ውስጥ በተላላኪነት ከነገ ሰኞ ጀምሮ መግባት እንደ ምትችል አበሠራት። እርሱ እንደ ጠበቀው ዘላ አልተጠመጠመችበትም። ፊቷም ጥርስ ብቻ አልሆነም። በምትኩ ዐይኖቿ ደፈረሱ። ወዲያው ደግሞ ጉንጮቿ በእንባ ራሱ። ጠረጴዛው ላይ ተደፍታ ተንሰቀሰቀች። አስግድ ቀና አድርጎ ሊያባብላት

/ወደ ገጽ ፲፫ ዞሯል/



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# መካነ ሱባኤ ወተመስጦ ÷ ጀር ቅድስት ሥላሴ ገዳም

መምህር ኃ/ማርያም ላቀውና ምትኩ ዘለቀ



የጀር ቅድስት ሥላሴ ገዳም

ከጠዋቱ 12፡30። አዲስ አበባ፣ አውቶቡስ መናኸሪያ እንደ ደረስን አውቶብሶች ሁሉ ሞተራቸውን አሟሙቀዋል። ረጅም ዘመናት ያገለገሉ ትም ሆኑ አዳዲሶቹ በጠዋቱ የተነፈሷቸው ጢሶች ተባብረው ሰውን ከሰው እንዳይተያይ ጋርደ ውታል። በየአፍንጫውም እየገቡ ትንፋሽ እንዲያጥረው አድርገውታል። ይሁን እንጂ በዚህ መኻል ሁሉም የሚሄድበትን አውቶብስ ፍለጋ ይራወጣል። እኔና ምትኩም በሩ ላይ ሲጠብቁን የነበሩትን የጉዞአችን ኃባዥና ምክንያት የሆኑትን የጀር ቅድስት ሥላሴ ገዳም አበምኔት አባ ብርሃነ ሥላሴን ይዘን ጥቂት ከተራወጥን በኋላ ወደ ፈለግንበት ቦታ የሚያደርሰንን አውቶብስ አገኘነው። ጥቂት ዘግይተናል። የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡሱ ያገኘውን ሰው ተሸክሞ ጉዞውን ሊጀምር የመጨረሻውን ትንፋሽ ሲተነፍስ ደረስን። ፈጠን ብለን ተሳፈርን። ጉዞ ወደ ጀር ቅድስት ሥላሴ ገዳም።

ከአዲስ አበባ 80 ኪሎ ሜትር ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ። ሙከ ከ ጡሪ ከተማ። መኪናው እዚያች አነስተኛ ከተማ ብንደርስም ሾፌሩ ብዙም ዕረፍት እንድናገኝ የፈለገ አይመስልም። ጉዞ ቀጠለ። አውቶቡሱ አስፋልቱን መንገድ ትቶ ወደ ሰሜን ምስራቅ ከታጠፈ በኋላ የጠጠሩን መንገድ ይዞ ቁልቁል ወደ ለሚ ነጎደ። ለሚ ሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት እንሳሮና ዋዩ ወረዳ የምትገኝ አነስተኛ ከተማ ነች። አውቶቡሱ መንገዱ የተመቸው አይመስልም። ይንገጫገጫል። ነገር ግን ይህ ሳያስፈራው እንዲያውም ሌሎች ሰዎ ችን ጨምሮ እያሳፈረ መንገዱን ተያ ያዘው። ከአዲስ አበባ እስከ ሙከ ጡሪ በተዝናና ሁኔታ የየራሳችንን ወንበር ይዘን፣ መኪናው ባሉት ክፍተቶች ሁሉ ሽው የሚለውን ንፁሕ አየር እየሳ ብን፣ ከአባ ጋር እየተወያየን ጉዞአችን የተመቸ ነበር። ያ የጠጠር መንገድ በገፍ የሚጠቀጠቀው ሕዝብ ከፈጠረው መጨናነቅ ጋር ተባብሮ ጭንቅ ጭንቅ ይለን ጀምሯል። አባ ከሙከ ጡሪ በታች የተለመደ ጉዞ እንደሆነና እንድ ንበረታ በፍቅር ዓይን እያዩን ይመክሩናል። እኛም ብንሆን አማራጭ የለምና ምክራቸውን የመቀበል ዓይነት ግዳችንን ፈገግ እንላለን። መኪናው ይንገጫገጫል። ቁጥር አይሰጠው እንጂ እንደ ከተማ አውቶብስ የራሱን ፌርማታ አዘጋጅቶ በየመንገዱ አዳዲስ ተጓዦችን ይጭናል፣ የደረሱትን ደግሞ ያወርዳል። ከሚወርደው ግን የሚሳፈረው ይበልጣል። ድልድይ አልባ የሆኑ የዱበርና የአሌልቱ ወንዞችን እንደ ጀልባ እየቀዘፈ በማቋረጥ ፍጥነቱን ጨምሮ ጉዞውን ቀጥሏል።

ወርኅ ጥር ምርት የሚሰበሰብበት በመሆኑ የአካባቢው አርሶ አደር ክረምት ሲለፋበት የቆየውን አዝመራ ሰብስቦ አልፎ አልፎም መንሽ ይዞ ምርትና ገለባውን ሲለይ እዚህም እዚያም ይታያል። ምርቱንም ወደ ጎተራ ገለባውን ደግሞ ለመኖ ያዘጋጅ ነበር። «መንሹም በእጁ ነው አውድማውንም ፈጽሞ ያጠራል። ስንዴውንም በጎተራ ይከታል። ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል» ማቴ.3÷12። የሚለው ቃል ትዝ አለን። በአውቶብስ ውስጥ ምን ያህል ፍሬያማ? ምን ያህሎቻችን ደግሞ ገለባ እንሆን ይሆን? የአዝመራው ባለቤት እግዚአብሔር ምርቱን ከገለባው ለመለየት ሲመጣ ከየትኛው እንሆን ይሆን? የሚል ሀሳብም በአእምሮአችን ተመላለሰ።

በዚህ ዓይነት በሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡሱ ያደረግነው ጉዞ ለሚ ከተማ ከመድረሳችን አምስት ኪሎ ሜትር ሲቀረን ወረድን። ጊዜው ከረፋዱ አራት ሰዓት ተኩል ሆኗል። አባ «ተመስገን ÷ ኑ በሉ ደርሰናልና እንውረድ» ብለው ይዘውን ወረዱ። አባ እንደወረዱ ወጣት የአብነት ትምህርት ተማሪዎች ለአባታቸው የሚገባቸውን ሰላምታ ሰጥተው፣ መስቀላቸውንም ተሳልመው እኛንም በክርስቲያናዊ ሰላምታ ሰላም አሉን። ለካ እኛኑ ይጠብቁ የነበሩ የምንሄድበት ገዳም የአብነት ተማሪዎች ናቸው። ዕቃዎቻችንን ተቀብለውን የሦስት ሰዓት የእግር ጉዞአችንን ጀመርን። ወደ ጀር ቅድስት ሥላሴ ገዳም። ዕቃዎቻችን የያዙ ሁለቱ ተማሪዎች መንገዱን በመላመዳቸው ምክንያት በፍጥነት መጓዝ ጀመሩ። አባም ቀላል አልሆኑም። እኛን አይዞአችሁ እንግዲህ እያሉ ከልጆቹ እኩል ይራመዱ ጀመር። በተቻለን መጠን እኛም ባለ በሌለ ኃይላችን እንራመድ ጀመር።

ከአንድ ሰዓት የእግር ጉዞ በኋላ ገዳሙን በርቀት አመለከቱን። ዙሪያውን ሆን ተብሎ በተቀረጸ በሚመስል ተራራ ተከቦ መኻል ላይ በመቀመጡ በጎላ ድስት ውስጥ የተቀመጠ ወጥ ይመስላል ገዳሙ። በስተሰሜን የዳሊቲ በስተ ደቡብ የደብረ ሊባኖስ ተራሮች ክሩቅ ዙሪያውን ከበውታል። ጥቅጥቅ ባለ ደን ከተከበበው ጋራ ስር ጥንታዊና ታሪካዊ የጀር ሥላሴ ገዳም ጥጉን ይዞ ጉልላቱን እያበራ በሩቅ የሚፈነ ጥቀ




©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ብርሃን ይጣራል:: ጥሪው ያን ጓል:: ጉጉቱ ደግሞ ጉልበት ሆነንና ከእግራችን ነጠቅ ነጠቅ እያልን ጉዟችን ተፋጠነ:: ቶሎ የመድረስ ጉጉትና ስፋ ጉልበት ሆኖን ተጓዝንና አጠገቡ ደረስን:: ከላይ ያልነው ቅርጽ የበለጠ እውን ሆነልን:: ገዳሙ ለመድረስ ቀጥ ያለውን ቁልቁለት:: በተማሪዎቹ መሪነት እየተንደረደርን መውረድ ጀመርን::

የአሁኑ ጉዞአችን ማንም ሳይነካን ቁልቁል መንደርደር ነው:: ፍጥነታችን እየጨመረ መጣ:: አባና ተማሪዎቹ በሚያውቁት መንገድ ሳይቸገሩ ቁልቁል ይራመዳሉ:: እኛ ግን እንደነሱ አል ሆነልንም:: አልፎ አልፎም ልንወድቅ እንደርሳለን:: ይህንን ያዩት አባና ተማሪዎች የእነሱን ምርኩዝ ሰጡን:: ከተራራው አናት ወደ ታች ወደ ገደሉ ዝቅ እያልን ስንሄድ ሙቀቱ የበለጠ እየጨመረ መጣ:: በሰውነታችን ያለው ፈሳሽ ከሙቀቱ የተነሳ በላቦት መልክ ጥርግ ብሎ ይወጣ ጀመር:: ጉሮሮአችንም መደራረቅ ጀመረ:: በአካባቢው ውኃ የለም:: ከመጠነኛ ፈታኝ የቁልቁለት ጉዞ በኋላ ወደ ገዳሙ ቀጥታ የሚያወርደን መሰላል ተጠርቦ በተዘጋጀ በሚመስለው ገደል ቁልቁል ተጋድሞ አገኘን:: ይህ መሰላል በ1988 ዓ.ም ሁለት የሐመር መጽሔት ባልደረቦች ወደ ሰሜን ወሎ ተጉዘው ያስቃኙንን የአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ገዳምን መወጣጫ መሰላል አስታወሰን:: መሰላሉ በግምት ርዝመቱ ወደ 15 ሜትር የሚደርስ ሲሆን መናንያኑ አበው መነኮሳትና ባሕታውያን ከገዳሙ ውጭ ለሚሰማሩበት አገልግሎት በመውጫና በመውረጃነት ለዘመናት ተገልግለውበታል::

ከአዲስ አበባ ጀምሮ በአባታዊ የፍቅር ዓይን እየተመለከቱ ሲያበረታቱን የነበሩት አባ ብርሃነ ሥላሴ አሁን የበለጠ ሳሱልን:: እግሩን ከታች ተክሎ በአየር ላይ ተዘርግቶ አፋፉ ላይ ከሚደርሰው መሰላል እንዳንወድቅ:: በመሰላሉ ወደታች ስንወርድ አዙሮን ከታች እንዳንከሰከስ በጥንቃቄ በምንራመድበት ጊዜ ዓይናችን ቁልቁል ወደ ገደሉ እንዳያይ አጥብቀው መከሩን:: ፍርሃት ቢያድርብንም የገዳሙ ሰዎች ሲሻገሩ ስናይ ልቡናችን ተጽናንቶ የመጀመሪያውን ዙር መሰላል ጨርሰን ቁልቁለቱን ተያያዝነው::

ሰው የገፈተረን ያህል ስንደረደር ለተመለከተን የ10 ሺ ሜትር ሯጮች እንመስል ነበር:: እጅግ ግዙፍ የሆኑ ድንጋዮች በአንድ አካባቢ ቁጭ ብለው ለተመለከታቸው ስብሰባ የያዙ ይመስላሉ:: በአካባቢው ያሉ ዝንጀሮዎች መተናኮል ሲያምራቸው የድንጋይ ናዳ ከላይ ሆነው ይለቃሉ ይባላል:: ስለዚህ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብን እየተነገርን ባለበት ሁኔታ በማለፍ ላይ እንዳለን በአጋጣሚ የዝንጀሮ መንጋ ተያይዞ ሲመጣ ተመልክተን፣ ናዳ እንዳይለቁብን በመፍራት ፍጥነታችንን የበለጠ ጨመርን::



*ወደ ገዳሙ የሚያስወርደው መሰላል*

የገዳሙ መሬት አቀማመጥ ለአፈር መሸርሸር የተጋለጠ ነው:: አብዛኛው የገዳሙ የእርሻ መሬት በጐርፍ ተሸርሽሮ ያለቀ ሲሆን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ የሚያደርሰው መንገድም በጎርፍ ከመሸርሸሩ የተነሣ እንደ ክር የቀጠነ በመሆኑ መንገዱን ለማለፍ አስቸጋሪ አድርጎታል::

መድረስ አይቀርም ሁሉንም አልፈን ከሦስት ሰዓት እልህ አስጨራሽ ጉዞ በኋላ ከመምህር አባ ብርሃነ ሥላሴ ባዕት ገባን:: እግሮቻችን ተሳስረዋል:: ሁሉም የሰውነታችን ክፍል በጹላ የተመታ ያህል ቆስሏል:: በድካም መነሳትም መቀመጥም አልቻልንም:: መምህር አባ ብርሃነ ሥላሴ ግን ድካም ሳይሰማቸው እኛን ለማስተናገድ ወዲህ ወዲያ ሲሉ ስናያቸው ሰውነታቸውን ተጠራጠርነው::

የቀረበልንን ማዕድ ጨርሰን ጀርባችንን መሬት ለማስነካት ሁላችንም ተቻኮልን:: በማግስቱ ምንም እንኳን እግሮቻችን ለመራመድ ቢተሳሰሩም እንደ ምንም ብለን እንደ ሕፃን ልጅ እየተውተረተርን የገዳሙን አጠቃላይ ገጽታና ሁኔታ ለመቃኘት ከገዳሙ አበምኔት ከመምህር አባ ብርሃነ ሥላሴ እና ከአቶ መሸሻ ጋር በመሆን መዘዋወር ጀመርን::

ጀር ቅድስት ሥላሴ ገዳም በአማራ ክልል በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት በእንሳሮ ወረዳ ለሚ ተብላ ከምትጠራ ከተማ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ ዙሪያውን በተራራ በተከበበ ገደል ውስጥ ይገኛል::

ገዳሙ በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት እንደ ተመሠረተ ይነገራል:: ገዳሙን ያቀኑትና የመሠረቱት ጻድቁ አቡነ ኢያሱ ናቸው:: አቡነ ኢያሱ ትውልዳቸው አማራ ሳይንት ነው::

የጀር ቅድስት ሥላሴ ገዳምን የተለያዩ ነገሥታትና መኳንንት ጎብኝተውታል:: ዓፄ ምኒልክ በዘመናቸው ገዳሙን እንደ ጎበኙት ይነገራል:: ለዚህም ደነባ በተባለ ቦታ አራት ጋሻ መሬት እንዲሁም አፈንጉሥ እስጢፋኖስ ሰባት ጋሻ መሬት ለገዳሙ መስጠታቸው ይታወቃል::

ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱም ለገዳሙ የሚሆን የእርሻ መሬት መርሐ ቤቴ የሚገኘውን የእናትና የአባታቸውን ርስት ጠቅልለው ለገዳሙ ሰጥተዋል:: እንዲሁም በዘላቂነት ለመተዳደሪያነት የሚያገለግሉ ቤቶች አዲስ አበባ አምስት ኪሎ አካባቢ ሰጥተዋል:: ገዳሙ እስከ አፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ድረስ በቤቶች ኪራይ ሲጠቀም መቆየቱን የገዳሙ አበምኔት መምህር አባ ብርሃነ ሥላሴ ታደሰ ገልጸውልናል::

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከግሪካዊ መሐንዲስ ሙሴ መንድሌ ጋር በመሆን በክቡር አባቴ ሐናመሪነት ጀር ቅድስት ሥላሴን ጎብኝተዋል:: በጉብኝቱ ወቅት ገዳሙ ያለበትን የቦታ አቀማመጥ ለአፈር መሸርሸር የተጋለጠና ተራራው እየተናደ ስለአስቸገረ ሌላ አማራጭ ቦታዎች በወቅቱ በመሐንዲሱ ቀርበው



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ነበር፡፡ ከነዚህም ውስጥ ይፈጭ አቦ፣ ሰቃ ወረንጨፌ እና ላይጀር ቦታዎች ነበሩ፡፡ ከነዚህ ከተጠቆሙት ሦስቱ ቦታዎች ውስጥ ከሁሉም የተሻለ ሆኖ የተመረጠው ስቃ ወረን ጨፌ የተባለ አካባቢ ሲሆን በወቅቱ በንጉሡ ትዕዛዝ ሦስት ጋሻ መሬት ተጨምሮለት የጀር ቅድስት ሥላሴ ገዳም ዋና ገዳም /አበምኔቱ የሚቀ መጡበት/ እንዲሆን ተወሰነ፡፡ የገዳሙ መምህር /አበምኔት/ በዚህ ቦታ ሆነው ጀር ቅድስት ሥላሴን እንዲያስተዳድሩ ተወሰነ፡፡ ውሳኔውም በግርማዊ ቀደማዊ ኃይለ ሥላሴ ቀርቦ ጸደቀ፡፡ ግርማዊት እቴጌ መነንም በሰቃ ወረን ጨፌ በተባለ ቦታ የመድኃኔዓለምን ቤተ ክርስቲያን በዚያው ወቅት በዘመ ናዊ ሁኔታ ማሠራታቸው ይታወቃል፡፡

የጀር ቅድስት ሥላሴ ገዳም ከሰቃ ወረንጨፌ ይዞታ ጋር በአንድ ላይ በአንድ አበምኔት ሲተዳደር ከቆየ በኋላ ከቅርብ ጊዜ በኋላ ስቃ ወረን ጨፌ መድኃኔዓለም ራሳችን እንቻል ብለው ከጀር ቅድስት ሥላሴ ገዳም አስተዳደር ተለይተው በአሁኑ ሰዓት በሰበካ ጉባኤ በመተዳደር ላይ ይገኛሉ፡፡ ጀር ቅድስት ሥላሴ ገዳም ግን በቀድሞው የገዳሙ ሥርዓት አሁን ድረስ በመተዳደር ላይ ይገኛል፡፡

በ1928 ዓ.ም ፋሺስት ጣሊያን አገራችን በማን አለብኝነት በወረረችበት ጊዜ ስቃ ወረንጨፌ የነበሩት መምህራና መነኮሳት ለቅርስ ጥበቃ አመቺ ወደ ሆነው ወደ ጀር ቅድስት ሥላሴ ገዳም ተመልሰዋል፡፡ በወቅቱም የሰቃ ወረንጨፌ ገዳም በምክትል መምህር እንዲተዳደር ተደርጓል፡፡ በአምስት ዓመቱ የጣሊያን ወረራ ዘመን ባንዶች በሩቅ ሆነው የጀር ቅድስት ሥላሴን ገዳም በመድፍ ደብድበውታል፡፡ በዚህም በገዳሙ የነበሩ የመነኮሳት ቤቶችና የገዳሙ ንዋየተ ቅድሳት ተቃጥለዋል፡፡ ብዙ መነኮሳትም ተገድለዋል፡፡ 22 የሚሆኑ መነኮሳት ተይዘው ፍቼ ድረስ ሄደው ታስረዋል፡፡ ከብዙ ወራት በኋላ መነኮሳቱም ከእስራት ተፈተዋል፡፡ በዚህ ወቅት የደብረ ሊባኖስ ገዳም መነኮሳት በግፈኛው የኢጣሊያን ፋሽስት መጨፍጨፋቸው ይታወቃል፡፡

የጀር ቅድስት ሥላሴ ገዳም ብዙ ቅዱሳን ጻድቃን እንደነበሩበትና አሁንም እንዳሉበት ይታወቃል፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በገዳሙ የተሠወሩ አባቶች ለብዙ አገልጋዮች በልዩ ልዩ ጊዜ እየተገለጡ እንደሚያነጋግሯቸው ይታወቃል፡፡ በአንድ ወቅት አንድ የተሰወሩ አባት አንድ የገዳሙ አገል ጋይ ውኃ ሊቀዳ ሲሄድ አገኙትና «ውኃውን አድርስና ለማንም ሳትናገር ተመልሰህ ና» ሲሉት አገልጋዩም ቸኩሎ ለሰዎች «ና ተብያለሁና» ብሎ ተናግሮ ሲመለስ ሳያገኛቸው ቀርቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በገዳሙ በተለያዩ አቅጣጫዎች አንዳንድ ጊዜ የሰዓታትና የማኅሌት ድምፅ እንደሚሰማ የገዳሙ አበምኔት አጫውተውናል፡፡

ከጋራው ስር እንደ ኤደን ገነት ውኃ የሚመነጭ ጠበል ለብዙ ምእመናን ድኅነተ ሥጋ ድኅነተ ነፍስ ሆል፡፡ ለአብነት አንድ ዓይነ ስውር በአንድ ወቅት በገዳሙ ጠበል ተጠምቀው ዓይናቸው እንደበራላቸው መምህር አባ ብርሃን ሥላሴ ነግረውናል፡፡ እንዲሁም ከውጭ ሀገር የመጣ አንድ ኢትዮጵያዊ ሐኪሞች «አልቆልሃል፣ አትተርፍም» ብለውት ተስፋ ቆርጦ ሞቱን ሲጠባበቅ በዚህ ገዳም ጠበል ተጠምቆ ከሕመሙ ሙሉ በሙሉ እንደተፈወሰ ገልጸውልናል፡፡

ሌላው በዚህ ገዳም የተደረገ ተአምር ነሐሴ 15 ቀን ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት መነኮሳቱ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ሰዓታት እንደቆሙ በጎርፍ ምክንያት የተሸረሸሩ እጅግ ትልልቅ ድንጋዮች ባልተጠበቀ ድንገተኛ ሁኔታ ተንከባለው ቤተ ክርስቲያኑን በእግዚአብሔር ፈቃድ ሳይነኩ ከቤተ ክርስቲያኑ ጎን ወደታች ሰምጠው ተቀምጠዋል፡፡ በዚህም እጅግ ሲፈራ የነበረው የድንጋይ ናዳ በጻደቁ በአቡነ ኢያሱ ክብረ በዓል ዋዜማ ጉዳት ሳያደርስ መቅረቱ አሁን ድረስ በመነኮሳቱ ኅሊና ሲዘከር የሚኖር ተአምር እንደሆነ አበምኔቱ ነግረውናል፡፡

ከ1966 ዓ.ም. ጀምሮ የጀር ቅድስት ሥላሴ ገዳም በወቅቱ በነበረው የመንግሥት ለውጥ በገዳማትና አድባራት መስፋፋት በጐ አመለካከት ከነበራቸው ነገሥታትና መኳንንት በተለያዩ ሥፍራዎች የተሰጠውን ጋሻ መሬቶች በ1967 ዓ.ም የመሬት ላራሹ አዋጅ ሙሉ በሙሉ ተነጠቀ፡፡ በዚህ የተነሣ የበርካታ ገዳማዊያንና መነኮሳት መጠጊያ የነበረው ገዳም በመተዳደሪያ እጦት መድከም ጀመረ፡፡

መነኮሳቱ ከጸሎትና ከምንኅላ ባሻገር ያርሱት የነበረው መሬት በመወሰዱ ለዕለት ጉርስ የሚሆን እህል በማጣታቸው ወደ ተለያዩ ገዳማት ሲሰደዱ የተወሰኑት ግን አጽንኦ በአታቸውን በመያዝ ገዳሙን አሁን ድረስ በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡

በጀር ቅድስት ሥላሴ ገዳም የሚገኙ ገዳማዊያን የነግህና የሠርክ ጸሎት የማኅበር ማዕድ ያከናወናሉ፡፡ ገዳሙ በርካታ ሊቃውንትን አፍርቷል፡፡ ለአብነት ብፁዕ አቡነ ኤርምያስን አስገኝቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የመጀመሪያ ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በጀር ሥላሴ ገዳም ሱባኤ ገብተው እንደ ነበረ ይታወቃል፡፡

ገዳሙ እንደ ድሮው በተጠናከረ ሁኔታ ባይሆንም አሁንም የአብነት ትምህርት እየተሰጠበት ይገኛል፡፡ ከተለያዩ አካባቢዎች የመጡ የቆሎ ተማሪዎች የንባብ፣ የቅዳሴና የዜማ ትምህርት በመከታተል ላይ ይገኛሉ፡፡ የገዳሙ የንባብ፣ የዜማና የቅዳሴ መምህራን ከሚያገኙት መቁኑን በስተቀር ምንም ሳይከፈላቸው ለቤተ ክርስቲያን ተተኪ የሚሆኑ ደቀመዛሙርትን በንቃትና በትጋት በማስተማር ላይ ይገኛሉ፡፡

የጀር ቅድስት ሥላሴ ገዳም አገር በቀል የሆኑ በርካታ የብራና መጻሕፍት ይገኙበታል፡፡ ከነዚህም የተለያዩ ከብራና የተዘጋጁ የሕግ መጻሕፍት፣ አክሲማሮስ፣ መጻሕፍተ መነኮሳት፣ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ድርሳን፣ የተለያዩ የትርጓሜ መጻሕፍት ይጠቀሳሉ፡፡ ገዳሙ በነዚህ መጻሕፍት ላይ የተቀመረውን አገር በቀል ዕውቀት ለደቀ መዛሙርቱ የሚያደ ርሱ የቅኔና የትርጓሜ መጻሕፍት መምህራን ይሻል፡፡ ለወደፊት ወደ ገዳሙ የሚሄዱ ምእመናን በቦታው ላይ የአብነት መምህራን ዕውቀታ ቸውን የሚያካፍሉበትን መንገድ ቢያመቻቹ ገዳሙ እንደ ጥንቱ የበርካታ ምሁራን መነኮሳትና ሊቃውንት ማፍ ሪያ ከመሆን የሚያግደው ነገር የለም፡፡

ጥንት ከአምስት መቶ በላይ የነበሩት መነኮሳት አሁን ግን ያሉት መነኮሳት ከሃምሳ የሚበልጡ አይደሉም፡፡ ድሮ በገዳሙ ኪዳን፣ ቅዳሴና ሰዓታት የሚደርሰው በተረኛ ነበር፡፡ አሁን ግን ያ ሁሉ ነገር ቀርቶ በዓመት ሦስት ጊዜ ብቻ ነው የሚቀደሰው፡፡ አሁን ገዳሙ የሚተዳደርበት ቋሚ ነገር የለውም፡፡ የእርሻ ቦታውም በጎርፍ ተሸርሽሮ ድንጋዩ ብቻ የቀረ ትንሽ መሬት ነው ያለው፡፡ በገዳሙ ያሉ መነኮሳት ኑሮአቸውን የሚገፉት አዲስ አበባ ያሉ አንዳንድ በጐ አድራጊ ምእመናን ከሚለግሷቸው ጊዜያዊ ርዳታ በቀር በቋሚነት የሚያገኙት ነገር የለም፡፡ በመሆኑም በአገር ውስጥና በውጭ ያላችሁ ምእመናን ጥንታዊውን የጀር ቅድስት ሥላሴን ገዳም መነኮሳቱ ሳይበተኑ ገዳሙም ሳይፈታ ባለበት እንዲቀጥል ለማድረግ ያቅማችንን እንድንወጣ በዚሁ አጋጣሚ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡ በቦታው ጥቅምት 16 ቀን የጻድቁ የአቡነ ኢያሱ ዕለተ ዕረፍት፣ ሐምሌ ሰባት ቀን ደግሞ የአጋእዝተ ዓለም ሥላሴ ዓመታዊ በዓላት ይከበራሉ፡፡

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ለንጊኖስ ሰማዕት

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በማመናቸውና አምላክነቱን በመ መስከራቸው በአሕዛብ ፊት መከራ የደረሰባቸው አያሌ ቅዱሳንና ቅዱሳት ሰማዕታት መኖራቸው ይታወቃል። ለ ጽድቅ ተጠርተው ለክብር ከበቁት ሰ ማዕታት መካከል አንዳንዶቹ ታሪካ ቸው ተዘግቦ ሥራቸው እየተነገረ ምሳ ሌነታቸው ለሌላው ሲገለጥ ሌሎች ደግሞ ታሪካቸው ተዳፍኖ ይኖራል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕ ዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪካቸውን ዘግባ ክብራቸውን ከምትነግርላቸው ሰማዕ ታት መካከል አንዱ አንድ ዓይናው ለንጊኖስ ነው።

ለንጊኖስ ትውልዱ ከዮናናው ያን ወገን ሲሆን ሥራው የሮማ ወታ ደር ሁኖ ከጲላጦስ ጭፍሮች ውስጥ አንዱ ነበር። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአይሁድ ክፋት ምን ም ወንጀል ሳይኖርበት የሰውን ልጅ ለማዳን ሲል በፈቃዱ በስቅላት እንዲ ቀጣ ሲፈረድበት ስቅላቱን እንዲፈ ጽሙ ጲላጦስ ትእዛዝ ከሰጣቸው ወታደሮች መካከል የነበረ ነው።

የሰው ልጆችን ለማዳን ከሰማየ ሰማያት በመውረድ ከእመቤታችን ከቅ ድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰው የሆነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስ ቶስ ታላላቅ ተአምራትን እያደረገ፣ የተጨነቁትን በማጽናናት፣ የተቸገሩ ትን በመርዳት ሸክም የከበደባቸውን ሁሉ እያቀለለላቸው በኢየሩሳሌም ከተሞች ሲመላለስ የእጁን ተአምራት የቃሉን ትምህርት አይተው ብዙ ሰዎ ች እንደ ተከተሉትና እንዳመኑበት የተመለከቱ አይሁድ በቅናት መንፈስ ተነስተው ሊገድሉት ፈለጉ።

ለሞት የሚያደርስ ቀርቶ አንዳች ጥፋት ባያገኙበትም በፍርድ አደባባይ አቆሙት። በጲላጦስ ፊትም ቀርቦ ጲላጦስ ወንጀል እንደ ሌለበት ሲያረጋግጥ ሊፈታው ቢፈልግም «አሳ ልፈህ ከልሰጠኸን የቄሳር ወዳጅ አይደ ለህም» ስላሉት እጁን በሕዝብ ፊት በመታጠብ «ከዚህ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ» በማለት አሳልፎ ሰጣቸው ።

አይሁድ ግን ደሙ በእኛና በልጅ ልጆቻችን ላይ ይሁን ብለው ክርስቶስን ለመስቀል ወደ ቀራንዮ ተጣደፉ። ያኔ ነው ለንጊኖስ ከሌሎች ጓደኞቹ ጋር ክርስቶስን እንዲሰቅል መመሪያ የተሰጠው። ክርስቶስ መል ካም ነገር ከማድረግ በስተቀር አንዳች በደል እንደሌለበት የተረዳው ለንጊኖስ ክርስቶስን ለመስቀል ልቡ አልፈቀ ደለትም። የአይሁድ ክፋትና ምቀኝነት የዋህ ደግና ሩኅሩኅ የሆነውን ክርስቶስ እንዲሰቅሉ መነሣሣታቸውን ሊቀበለው ስላልቻለ ማዳንም እንዳማይችል ስለ ሚያውቅ ከጓደኞቹ በመለየት አካባቢ ውን በመልቀቅ ሸሽቶ ቆይቷል።

ለበደላቸው ወሰን የሌለውና የሚ ያደርጉትን የማያውቁት አይሁድ ሥራ ቸው ሁሉ በተንኮል የተሞላ ነውና በክርስቶስ ላይ የፈጸሙት ጥፋት ሳይበ ቃቸው ማንኛውም ሰው ከእነርሱ ጋር ተባባሪ እንዲሆንላቸው እነርሱ ብቻ ወንጀለኞች እንዳይሆኑ በማሰብ «በክር ስቶስ ሞት ያልተባበረ እንደ ንጉ ሥ ጠላት ይቆጠራል ከምኩራብም ይባ ረራል» በማለት እጅግ በጣም የሚያስ ገርም ዐዋጅ ተናገሩ። በአንድ በኩል የክርስቶስን ንጹሕነት የተረዳው በሌላ በኩል ከምኩራብ መባረሩ ያሳሰበው ለንጊኖስ የአይሁድ ቅጣት እንዳይደ ርስበት በመፍራት ከሸሸበት ተመልሶ ወደ ቀራንዮ በመውጣት ክርስቶስ በመጨረሻዋ ሰዓት «ተፈጸመ» ካለ በኋላ ሮማውያን የሁለቱን ሽፍቶች አጥንት ሲሰብሩ እርሱ ደግሞ ከሞተ መቸም አልጐዳውም ብሎ የጌታን ጎኑን ወጋው። ያኔ ነበር ከጌታ ግራ ጎን ውኃና ደም ወጥቶ በሽተኛ ዐይኑን ስለ ነካው ዐይኑ የበራለት።

ክርስቶስ በሕይወት ዘመኑ ያከና ውናቸው የነበሩት ተግባራት ያስገ ርሙት የነበረው ለንጊኖስ የክርስቶስ ነፍስ ከሥጋው ተለይታ ባለችበት ሰዓ ት አይሁድን ለማስደሰት ጎኑን ሲ ወጋው የወጣው ውሃና ደም በጨለማ ተውጣ የነበረች ዐይኑን ሲያበራለት እጅግ ተደነቀ።

ለእርሱ የተደረገለት ድንቅ ተአ ምር ብቻ ሳይሆን ክርስቶስ በተሰቀለ ጊዜ ግዑዛን ፍጥረታት የሆኑት ፀሐ ይና ጨረቃ የክርስቶስን ዕርቃን ለመ ሸፈን ፀሐይ ስትጨልም ጨረቃ ደም ስትለብስ ተመለከተ። ዐለቶች ሲሰነ ጣጠቁ ሙታን ከመቃብር ሲነሡ አየ። ክርስቶስም በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ በተነሣ ጊዜ የሆነውን ሁሉ ሰምቶ እግዚአብሔር ምስጢሩን ይገል ጽለት ዘንድ በጸሎት ጠየቀ። በዚህ ጊዜ ነው በእግዚአብሔር ፈቃድ ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲያስተምረው የተላከለት።

ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮ ስም ነቢያት ስለ ጌታችን፣ ስለ መከራ መስቀሉ፣ ስለ ሞቱ ስለ መነሣቱ ስለ ዕ ርገቱም ትንቢት እንደ ተናገሩ እርሱም ከቅድስት ድንግል በሥጋ ተወልዶ ዓ ለምን ለማዳን የመጣ የሕያው እግዚ አብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስ ቶስ እንደ ሆነ አስረዳው። ለንጊኖስም በቅዱስ ጴጥሮስ ቃል አመነ።

አስቀድሞ በተአምራትና በልዩ ልዩ ድንቅ ምልክቶች ልቡ የተነካው ለንጊኖስ ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥ ሮስ እንደ አባት ሁኖ የክርስቶስን የመወለድና የመሞቱን ብሎም የማነ ሣቱን ደግሞ እንደ ሚመጣ የነገረውን ቃል በማሰብ የክርስቶስ ሐዋርያ ለመ ሆን ወስኖ የወታደርነት አገልግሎቱን በመተው ወደ ቀጰዶቅያ ሄደ በዚያም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንደ ሐዋርያ ሰበከ። ብዙ ወገኖችንም ወደ ክርስትና መልሷል።

ልቡናቸውን በማደንደን በሚደ ረገው ተአምራት በሚፈጸመው ማንናቸ ውም በጎ ነገር ሁሉ ከጥፋታቸው ለመ መለስ ያልፈለጉት ሮማውያንና አይ ሁድ ለንጊኖስ በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ በማስተማሩ ስለተበሳጩ አሳደዱት።

በክርስቶስ ላይ የፈጸሙት ግፍ ሳይበቃቸው ስለ ክርስቶስ የሚመሰክሩ ትን ሁሉ እያሳደዱ ማሰር መግደል ጀመሩ።የጽድቅ አርበኛ እንዲሆን የተመ ረጠውን ለንጊኖስንም ለመግደል በመ ወሰን ለንጉሥ ጢባርዮስ ቄሳር አመል ክተው በቀጳዶቅያ ከተማ ተይዞ ሐምሌ 23 ቀን አንገቱን ተሰይፎ በሰማዕትነት እንዲያርፍ አደረጉት።

ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። እኛንም በቅዱሳን ጸሎት ይማረን፤ ለዘ ለዓለሙ አሜን።

ምንጭ፡- ስንክሳር ሐምሌ 23

-ቤተ -ክርስቲያንህን ዕወቅ

ገጽ 146





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# «ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የረጅ ምና አድካሚ ፍለጋችንና ጥያቄያችን መልስ ሆነው ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጡን ወላጆቻችን ናቸው»

*ቀሲስ ኃ/ጊዮርጊስ /በኪንግስተን የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ*



*ቄስ ኃይለ ጊዮርጊስ ይባላሉ:: በጃማይካ ከሚገኙት ዘጠኝ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት /ቅድስት ሥላሴ፣ መድኃኔ ዓለም፣ ቅድስት ድንግል ማርያም፣ ቅዱስ ሚካኤል፣ ቅዱስ ገብርኤል፣ ቅዱስ ሩፋኤል፣ ቅዱስ ማርቆስና ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት/ መካከል የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ናቸው:: እ.ኤ.አ በ1980 በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት በጃማይካ በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ተጠምቀዋል:: በዚያው ቤተ ክርስቲያን በአናጉንስጢስነት እያገለገሉ በኪንግስተን መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ተገቢውን ትምህርት በመውሰድ በ1983 እ.አ.አ ወደ ተባበሩት የዌስት ኢንዲስ የነገረ መለኮት ኮሌጅ በመግባት ከሦስት ዓመት በኋላ በነገረ መለኮት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል:: በ1990 እ.ኤ.አ የቅስና መዓርግ ተሹመዋል:: የ44 ዓመት ጎልማሳ፣ ባለ ትዳርና የአራት ልጆች አባት፣ጃማይካዊ ካህን:- ቄስ ኃይለ ጊዮርጊስ በአገራችን ከጥር 24 ቀን 1997 ዓ.ም. ጀምሮ ለአንድ ወር በዘለቀው የሮበርት ኔስታ (ቦብ) ማርሌይ 60ኛ ዓመት የልደት በዓል አከባበር ላይ መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲሰጡ በተጋለፈላቸው ጥሪ መሠረት በመጡበት ወቅት አግኝተን ሰፊ ቃለ ምልልስ አድርገናል:: ባለፈው እትማችን የክፍለ አህጉሩ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ከሆኑት ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ ማቅረባችን ይታወሳል:: በዚህ እትም ደግሞ የቤተ ክርስቲያናችን እንቅስቃሴና አጠቃላይ ገጽታ በዚያው አገር ተወላጅ አንደበት ምን እንደሚመስል እንረዳ ዘንድ፣ ባለፈው ወር በአዲስ አበባ ተዘጋጅቶ በነበረው የሮበርት ኔስታ ቦብ ማርሌይ 60ኛ ዓመት የልደት በዓል አከባበር ኮንሰርት ላይ በመገኘት ቡራኬ የሰጡ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ በርከት ያሉ ጥያቄዎች ለዝግጅት ክፍላችን ስለደረሱን፣ ካህኑ የሚያገለግሉት በአስተዳደር ከእናት ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በተለዩት አብያተ ክርስቲያናት በአንዱ በመሆኑና ዕርቅና ሰላም ከመፈለግ አንጻር ከጃማይካዊው ካህን ቄስ ኃ/ጊዮርጊስ ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ አቅርበናል:: መልካም ንባብ::*

*ሐመር:- በጃማይካ ያለውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ርምጃ ቢገልጹልን?*

ቄስ ኃይለ ጊዮርጊስ:- በጃማይካ ያለው የቤተ ክርስቲያናችን የመን ፈሳዊ አገልግሎት ርምጃ ዘገምተኛ ነው ለማለት ነው የሚቻለው:: ለዚህም ምክንያት የኾነው አገልግሎቱ ከጥንቱም የተጀመረበት አኳኋን ነው:: እንደ ሚታወቀው በጃማይካ ያሉት «ራስ ተፈሪያውያን» በ1950ዎቹ እና 60ዎቹ ባሉት ዐሥርት ዓመታት ውስጥ በማዕከል ለሚገኘው መንበረ ፕትርክና ያለ ማቋረጥ ደብዳቤ ይጽፉ ነበር:: ይኸውም የአውሮፓውያኑን የካቶሊክና የፕሮቴስንታት እምነት ድርጅቶች አጥብቀው በመጥላት ለእነርሱ የአነዋወር ልምድና ዘይቤ አምሳያ የኾነ «ቤተ ክርስቲያን» እንዲኖራቸው በመሻት ነበር:: ከልብሶቻቸው ጀምሮ ሌሎች ገጽታዎቻቸው ሁሉ ልክ እንደ ኢትዮጵያ ባንዲራ በአረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ቀለሞች የሚገለጽ በመሆኑ:- የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን መረጡ:: አረንጓዴው ቀለም እነርሱ «የተስፋይቱ ምድር» ብለው የሚጠሯት የኢትዮጵያን ውበትና ልምላሜ ይወክላል፤ የትውልድ ሀገራቸውን ሀብት (ወርቅ) ለማመላከት ቢጫ ቀለም ይጠቀማሉ፤ ቀዩ ቀለም አንድም:- የቤተ ክርስቲያንን ድል አድራጊነት በሌላም በኩል በጥቁሮች የነጻነት ትግል የፈሰሰውን የሰማዕታት ደም ይወክላል:: የአፍሪካውያንን ቀለም ለመወከል ጥቁር ቀለም ያስገባሉ::

«የራስ ተፈሪያውያን» እንቅስቃሴ በ1930ዎቹ እ.አ.አ መጀመሪያ ላይ የተከሰተ ሃይማኖታዊ ትርጉም ያለው የትግል ምዕራፍ ነው:: ፋሽስት ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ያካሄደችውን ወረራ በመቃወም በስደት ላይ በነበሩት ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ መመሪያ «የኢትዮጵያ ዓለም አቀፋዊ ፌዴሬሽን እንቅስቃሴ» ተመሠረተ:: ዓላማውም የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ዳግም ለማስመለስ የሚደረገውን ትግል ለማስተባበር ነበር:: እርሳቸውም በወቅቱ የተቋቋመውን «የኢትዮጵያ ዓለም አቀፋዊ ፌዴሬሽን እንቅስቃሴ» (Ethiopian World Federation Movement) ወደ አሜሪካ (USA) ላኩ:: ፋሽስት ጣልያን ከተሸነፈና ጦርነቱ ካበቃ በኋላ፤ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አገራቸው መመለስ ለሚፈልጉ የምዕራቡ ዓለም ጥቁሮች በሻሸመኔ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

2500 ሜትር ካሬ (500 ጋሻ) ያህል መሬት ሰጡ:: ዳሩ ግን በጊዜው በምዕራቡ ዓለም ጥቁር ሕዝቦች ዘንድ የተለያዩ ማኅበረሰቦች እየተቋቋሙ ነበር:: እንዲህም ስለሆነ ከ«የኢትዮጵያ የዓለም ፌዴሬሽን እንቅስቃሴ» ልዑካን መካከል ጃማይካዊ የኾነው ሰው ቻርተር አዘጋጅቶ ወደ ጃማይካ በመሄድ በዚያ ላሉ አፍሮ-አሜሪካውያን ጥቁሮች፡- «ወደ አፍሪካ ስለ መመለስ (Repatriation) እና ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ አምላክ ስለ መሆናቸው» ማስተማር ጀመረ:: ከዚህ ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው የ«ራስ ተፈሪያውያን» እንቅስቃሴ ተነሣሥቶ፡- «ከእኛ አመለካከት፣የኑሮ ልማድና ዘይቤ ጋር አይጣጣሙም» ያሏቸውን የካቶሊክና የፕሮቴስታንት የእምነት ተቋማትን በመተው የራሳቸውን «ቤተ ክርስቲያን» ለማቋቋም ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ይጽፉ ነበር::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በ1966 እ.አ.አ ጃማይካን ጎበኙ:: በጉብኝታቸው ሂደት እርሳቸውን እንደ አምላክ የሚያመልኩ የተለያዩ «ራስ ተፈሪያውያን» ቡድኖችን (ንያቢንጊ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ኮንግረስ፣ ቦብ ድሬድስ፣ የእስራኤል ዐሥራ ሁለት ነገዶች ወዘተ) አገኙ:: ወዲያውኑም እርሳቸው አምላክ አለመኾናቸውን፣ ይህም እምነታቸው ከባድ በደልና መተላለፍ መኾኑን በግልጽ በማሳወቅ አማናዊውን አምላክና ትክክለኛውን ትምህርተ ክርስትና ለማሳወቅ የሚያስችል ሐዋርያዊ አገልግሎት እንደ ሚያስፈልጋቸው ተመለከቱ:: እንደ አምላክ መቆጠራቸው ስላሳደረባቸው ስሜት ቀርበው ለጠየቋቸው መገናኛ ብዙኃንም ሁኔታው አሳፋሪ÷ አስቸጋሪና አስጨናቂ መኾኑን አስረዱ:: ጉብኝታቸውን አጠናቀው ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱም በወቅቱ በዐቃቤ ነት በፓትርክናው መንበር ከነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ጋር በመነጋገር የቀድሞው «ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ» በ1970 እ.አ.አ እንዲላኩ ተደረገ:: እርሳቸውም በዚያው ዓመት 750 ያህል ምእመናንን አስተምረውና አሳምነው አጠመቁ:: የሮበርት ኔስታ (ቦብ) ማርሌይ ሕጋዊ ባለቤት የኾነችው ሪታ አንደርሰን ማርሌይ በዚያ ዓመት ከተጠመቁት 750 ምእመናን መካከል አንዷ ነበረች:: በጊዜው እርሷን ጨምሮ «የራስ ተፈሪያውያን» እንቅስቃሴ ተሳታፊ የነበሩት ቤተሰቦች በቅድስት ሥላሴ (በአብ ÷ በወልድ ÷ በመንፈስ ቅዱስ) ስም መጠመቅን ተቃውመው ነበር:: መጠመቅ ሽተው የነበረው በ«ራስ ተፈሪ ስም» ነበር:: በዚህ ሳቢያ የማጥመቁ ሥነ ሥርዓትና ሂደት ተስተጓጉሎ የነበረ ቢሆንም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ሊቀጥል ቻለ:: ይሁንና በሁኔታው፡- «ራስ ተፈሪያውያኑ» ቀድሞ እንዳሰቡት የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና አስተምህሮ ከእነርሱ እምነትና አስተምህሮ ጋር አንድና ያው ኾኖ ስላላገኙት በቤተ ክርስቲያናችንና በ«ራስ ተፈሪያውያን» መካከል ሌላ የግጭት ምዕራፍን ከፈተ:: «ራስ ተፈሪያውያን» ክርስቶስን [ክብር ምስጋና ለእርሱ ይሁንና] በጨቋኝነት ከሚጠሏቸው ነጮች ጋር በማመሳሰል፡- የዐይኑ ብሌን ሰማያዊ፣ ፀጉሩ ሉጫ፣ በሰማይ የሚኖር፣ እንደ ግዑዝ ዕቃ በባርነት ይሸጡና ይለወጡ የነበሩ የጥቁር ባሪያዎች አለቃ (Slave Master) አድርገው ይመለከቱታል:: ቤተ ክርስቲያናችን ደግሞ ክብር ምስጋና ይግባውና እነርሱ እንዲህ የሚሉትን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝና የባሕርይ አምላክ እንደኾነ በግልጽ የምታስተምር ናት::

በመሆኑም «የራስ ተፈሪያውያኑ» እንቅስቃሴ አባል የኾኑና ተጽዕኖው ያደረበት ጃማይካዊ ኅብረተሰብ ከቤተ ክርስቲያን ተገለለ፤ ተለየ:: ቤተ ክርስቲያናችን ደግሞ ይህን ችግር በመጋፈጥ ወደ ኅብረተሰቡ ገብታ ብዙዎችን ወደ በረትዋ መጥራትና ማስገባት ነበረባት:: በመካከሉም «ራስ ተፈሪያውያኑ» በክርስትና እምነት የተጠመቁትንና ወደ ቤተ ክርስቲያን በሚመጡ ምእመናን ላይ እስከ ግድያ ሙከራ ድረስ ግልጽ ጥቃቶችን በመሰንዘር ቤተ ክርስቲያናችንን ያጥላሉ ነበር:: እኛም የቅድስት ቤተ ክርስቲያን አባልና ቤተሰብ ሊኾኑ የሚችሉት በአግባቡ ተጠምቀው ክርስቲያን ሲኾኑ ብቻ እንደ ኾነ በማስተማር ይኸንኑ በበጎ ፈቃዳቸው እንዲያደርጉት መክረናቸዋል:: ምክራችንን ተቀብለው በቤተ ክርስቲያን የጸኑ አሉ፤ ከቤተ ክርስቲያን ወጥተው በመሐል ሰፋሪነት ያሉ አሉ፤ ወደ «ራስታ » እምነታቸው የተመለሱ አሉ:: በጃማይካ ባለችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቆየብን ጉልህ ችግር ይህ ነው:: ከዚህ ሁሉ ጋር ግን እስከ አሁን ድረስ ከ40,000 በላይ ምእመናንን አስተምረን፣ ልናሳምንና ልናጠምቅ ችለናል:: እኒህ ሁሉ ደግሞ በዐበይት በዓላት ካልሆነ በቀር መደበኛ ሱታፌ የላቸውም:: እንደ ልደት፣ ጥምቀትና ትንሣኤ በዓላት ወቅት ግን ብዙዎቹ መጥተው ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ይሳተፋሉ:: የሥርዓቱ አፈጻጸም ተካፋይ ይሆናሉ::

*ሐመር፡- ጃማይካውያን ሕዝቦች ማንነታቸውንና ተምኔታዊ ግባቸውን እንደ አጠቃላይ ከአገራችን ኢትዮጵያ በተለይም ደግሞ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር በማድረጋቸው ደስተኞች ነን:: ይሁንና ራሳቸውን ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያቆራኙበትን የዚህን እምነትና ተስፋ ሁነኛ መንሥኤ ሊያስረዱን ይችላሉ?*

*ቄስ ኃይለ ጊዮርጊስ፡-* የኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የረጅምና አድካሚ ፍለጋችንና ጥያቄያችን መልስ ሆልስ ሆነው ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጡን ወላጆቻችን ናቸው:: መንሥኤውን ለማስረዳት የጃማይካውያን ብሔራዊ ጀግናና የጥቁሮች ነጻነት ታጋይ ከኾነው ማርከስ ጋርቬይ መጀመር ይኖርብናል:: ማርከስ ጋርቬይ ጥቁሮች ስለ ማንነታቸውና የጋራ እሴታቸው እንዲያውቁና እንዲጠነቀቁ በማንቃት ረገድ የመጀመሪያው ጥቁር ሰው ነው:: በ1930 እ.ኤ.አ. «ጥቁሩ ሰው» (THE BLACK MAN) የሚል ጋዜጣ ማሳተም ጀምሯል:: በዚህ ጋዜጣው ላይ «ከኢትዮጵያ ንጉሥ ሲመጣ በምታዩበት በዚያ ቀን ድኅነታችሁ (ነጻነታችሁ) ይፈጸማል:: ይደረጋል:: ወደ ብሪታንያው ንጉሥ ጆርጅ፣ ወደ ንግሥቲቷ ኤልሳቤጥ አትመልከቱ:: ራስታዎች ሆይ ÷ ፊታችሁን ወደ ኢትዮጵያ መልሱ፤ ወደ ጥንተ ርስታችሁ አፍሪካ ተመለሱ፤ በዚያ ተድላ ደስታ ይሆንላችኋል::» [When you see a king come from Ethiopia, that day salvation will be up on you.] ብሎ ጽፎ ነበር::

የጃማይካውያን የቀድሞ ትውልዶች አፍሪካውያን መሆናቸው ይታወቃል፤ ከአፍሪካ ወደ ጃማይካ የሄዱት ከ400 ዓመት በፊት ነበር፤ ለ400 ዓመታት ያህል ያለ አንዳች ክፍያ በአውሮፓውያን ሰፋፊ እርሻዎች ላይ በነጻ የጉልበት ብዝበዛና በባርነት ሥር ቆይተዋል:: ስለዚህ ዛሬ በባሪያ አሳዳሪነት ከገዟቸውና ከጨቆቸው የእንግሊዞች – አንግሊካን ወይም የሮማውያን–ካቶሊክ ወይም የጀር መኖች –ፕሮቴስታንት የእምነት ተቋማት ዘንድ መሄድን ፈጽሞ አይመርጡም:: የአንግሊካኖቹና የካቶሊኮቹ የእምነት ተቋማት ለሊቃነ ገባርያን (Slave Masters) ዓላማ የቆሙና የእነርሱ ጥቅም ተጋሪዎች ነበሩ:: ይሁንና «መጥምቃውያን» /Baptist/ ከሚባሉት መካከል ፓርት ቦገር የተባለ ሰው የአቋምና አመለካከት ለውጥ በማድረግ፣ ጥቁሮችን በማስተማር ጨቋኝ በነበሩት ላይ ተነሣሣ:: ስለ ባሪያ ጭቆና አስከፊነት ተናገረ፤ አብያተ መንግሥታትን አቃጠለ፤ በውጤቱም እ.አ.አ በ1838 የባሮች ጭቆና ተወግዶ ጥቁሮች ነጻ ኾነው የራሳቸውን የኑሮ መንገድና እምነት እንዲከተሉ አርነት ወጡ:: ወደ እናት ምድር አፍሪካ ብሎም ወደ ኢትዮጵያ የመመለስ ስሜት /Senti-

ment of Coming Back to Africa - Ethiopia) የተቀጣጠለው ከዚያ በኋላ ነው:: ማርከስ ጋርቬይ በ1930 እ.አ.አ ያስተጋባው ይህን ስሜት ነው::

የቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የ1966 እ.ኤ.አ የጃማይካ ጉብኝት ወደ አፍሪካ የመመለስን ስሜትና እንቅስቃሴ ወደ ላቀ ደረጃ አሸጋግሮታል:: ንጉሡ የጃማይካውያን ጥንተ ርስትና እናት ምድር ከኾነችው አፍሪካ መጥተዋልና ሁኔታው ማርከስ ጋርቬይ በ1930 እ.ኤ.አ የጻፈው ንግር ፍጻሜ (Fulfillment of the Prophecy) እንደ ኾነ ታመነበት:: በይበልጥም ደግሞ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ሳባ ለጉብኝት ወደ እሥራኤሉ ንጉሥ ሰሎሞን በሄደች ጊዜ ቀዳማዊ ምኒልክን እንደ ጸነሰችና እንደ እሥራኤል ሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥት (The same kind of kingship) በኢትዮጵያ እንደ ተመሠረተ፤ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴም ሰሎሞናዊ ዘር እንዳላቸው ጃማይካውያን ከክብረ ነገሥትና ከቅዱስ መጽሐፍ አንብበዋል:: በኢትዮጵያም እንደ እሥራኤል ያለ÷ እግዚአብሔር ራሱ የመሠረተው መንግሥት /መንግሥተ እግዚአብሔር/ እንደ ቆመ፤ «መለኮታዊው ተዋረድ» የዳዊት ዘር በኾነው የኢትዮጵያ ዘውዳዊ ሥርዓት በኩል እንደ ቀጠለ አመኑ:: ከሥርዓተ መንግሥት ጋርም ታቦተ ጽዮን፣ ሥርዓተ ክህነተ አሪት የእሥራኤላውያን ሊቀ ካህናት በነበረው በሳዶቅ ልጅ በአዛርያስ ሊቀ ካህንነት እንደ መጡና የአይሁድ እምነት እንደ ተጠናከረ ያምናሉ::

የሰሎሞናዊው ሥርወ መንግሥት፣ የቃል ኪዳኑ ታቦት፣ የሌዋውያን ክህነትና ሥርዓተ መቅደስ አሪት ወደ ኢትዮጵያ በመምጣቱ አገሪቱ ገነት እንደ ኾነች ያምናሉ:: ጽዮን እያሉም ይጠሯታል:: በ«ራስታዎች» እምነት ጥቁሮች ገነት ከሆነችው ከዚህች ምድር በባርነት ወደ ምዕራቡ ዓለም የመጡት አያት ቅድመ አያቶቻቸው ሁሉን የሚያውቀውንና ሁሉን የሚወደውን «ጃህን» /እንደ እነርሱ አነጋገር «ጃህ» ይሆዋ የሚለው ስመ አምላክ ነው/ የሚያስቀይም በደልና ኃጢአት በመፈጸማቸው ነው:: ለእነርሱ ሌላ ገነት የለችም:: ስለ ሌላዋ ገነትም አልሰሙም:: ብዙ የሰሙላትና የበለጠ ሊያውቋት የሚፈልጓት ገነት ኢትዮጵያ ናት:: ለኢትዮጵያ ያላቸው ከፍተኛ ፍቅርም ከዚህ የመነጨ ነው:: በተጨማሪም የመጀመሪያው ሰው አባታችን አዳም ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገርበት የነበረው ቋንቋ ግእዝ እንደ ኾነ ይናገራሉ:: ግእዝ ደግሞ በኢትዮጵያ የሥርዓተ አምልኮ ቋንቋ ነው:: ኢትዮጵያውያንም ይህን ቋንቋ ጠብቀው አቆይተውታል:: ታላቁ መጽሐፈ ሔኖክ በኢትዮጵያ እንዳለ፤ ሕዝበ እሥራኤልን ከግብፃውያን የባርነት ቀንበር ነጻ ያወጣውን ሊቀ ነቢያት ሙሴን አስተዳደር ያስተማረው ኢትዮጵያዊው ካህን ዮቶር እንደ ኾነ ያውቃሉ:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ ከሰብአ ሰገል መካከል ወርቅ ይዞ የመጣው በጊዜው የነበረው የኢትዮጵያ ንጉሥ ባዜን እንደ ኾነ ይናገራሉ:: ይህም «ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች» የሚለው ቃል ፍጻሜ ነው:: ይላሉ:: በሐዋርያት ሥራ ላይ እንደ ተገለጸው ኢትዮጵያ በንግሥቲቱ ሕንደኬ ጃንደረባ አማካይነት ጥምቀተ ክርስትናን በመቀበል የመጀመሪያ እንደ ኾነችውም ያምናሉ:: ንጉሥ ኢዛናም በ4ኛው መ.ክ.ዘ ኦርቶዶክሳዊ ክርስትናን ብሔራዊ የመንግሥት ሃይማኖት እንዲኾን ዐውጇል:: በመኾኑም ዕጣ ክፍላቸው ከነገረ እግዚአብሔር ጋር ከተያያዘው ከዚህ ሁሉ የኢትዮጵያውያን የታሪክ ሰንሰለትና የበረከት ሀብት ጋር እንዲኾን ይሻሉ፤ ይታገላሉም:: የጃማይካ መንግሥት ግን ይህን እንቅስቃሴ አይደግፍም:: ወደ አፍሪካ እንመለስ የሚሉትን ወገኖችም ያስራል ÷ ይቀጣል::

*ሐመር:- የመጀመሪያው ሰው አዳም ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገርበት የነበረው ቋንቋ ግእዝ እንደ ነበረ ነግረውናል:: ለዚህ እውነታ በእርስዎ በኩል የሚያቀርቡት ማስረጃ ምንድን ነው?*

*ቄስ ኃይለ ጊዮርጊስ፦* የጻድቁ አባታችን ኖኅ ትውልድ ከአዳም ነው:: እርሱ ግዙፍ መርከብን ሠራ:: ሁሉም ፍጥረት በጥፋት ውኃ ሲደመሰስ ከእርሱ ጋር ስምንት ቤተሰቦቹ ዳኑ:: ከጥፋት ውኃ በኋላ ከኖኅ ሦስት ልጆች አንዱ የነበረው ካም /ሐም/ ወደ አፍሪካ ምድር ሲመጣ የገባው ወደ ኢትዮጵያ ነው:: ካም ኩሽን ወለደ:: ኩሽም እንደ ካም ሁሉ በአምልኮተ እግዚአብሔር የጸና ነበር:: ኩሽ ÷ ኩሻዊ መንግሥትን (Cushtic Kingdom)

መሠረተ:: ይህም ኑቢያን፣ ግብፅን ይጨምር ነበር:: በሥልጣኔ ገናና የነበረው አክሱማዊ ሥርወ መንግሥት በኩሾች የተገነባ ነበር:: አኵሱም ደግሞ ከገናና የሥልጣኔ መገለጫዎቿ ጋር የሃይማኖት ማዕከል፣ የካህናት መዲና ነበረች:: ሥነ ጥበብና ኪነ ጥበብ ከጥንቱም ይራቀቅ የነበረው የቤተ መንግሥትና የሥርዓተ አምልኮ ቋንቋ በኾነው በግእዝ ቋንቋ ነበር:: ኩሾች በአባታቸው በካም በኩል ከኖኅ የተቀበሉትን የግእዝ ቋንቋ ጠብቀው መቆየት ስለ ቻሉ ግእዝ የሥርዓተ አምልኮ ቋንቋ ሆል:: ማስረጃው ይህ ነው::

*ሐመር:- መልካም:: «ራስ ተፈሪያኒዝም» አንድ የእምነት ክፍል ነውን?*

ቄስ ኃይለ ጊዮርጊስ:- «ራስ ተፈሪያኒዝም» አንድ የእምነት ክፍል ነው:: ነገር ግን ክርስቲያናዊ ቡድን /ወገን/ አይደለም:: ይሁንና በራሱ የቆመ ሳይሆን የክርስቲያኖችን ቅዱስ መጽሐፍ የሚጠቀም ነው:: በርግጥ «የጥቁሮች መጽሐፍ ቅዱስ» የሚሉትን «ቅዱስ ፒቢ» እንደሚጠቀሙበት የታወቀ ነው:: ከዚህ ሌላ ግን እምነቱን የሚያስፈጽሙበት ክርስቲያናዊ ሥርዓት የላቸውም::

*ሐመር:- የእምነቱ ተከታዮች «ቄሶች» የሚሏቸው ሽማግሌዎቻቸው እንዳሉ ያየኹ መሰለኝ . . .*

*ቄስ ኃይለ ጊዮርጊስ፦* መቼም በ«ራስ ተፈሪያን» እንቅስቃሴ የተለያዩ ቡድኖች ነው ያሉት:: «ራስታዎች» ቅስናቸውን በፀጉር አሠራራቸው ይወክላሉ:: ራሳቸውን «እኛ ቄሶች ነን» ብለው ይጠራሉ እንጂ በሹመት(Ordination) ያገኙት (የተቀበሉት) አይደለም :: በ«ቅስናቸው» እናጥምቅ ቢሉ እንኳ ጥምቀታቸው ሥልጣንና ተቀባይነት (Authenticity) የለውም:: አይጸናም:: ስለዚህ ወደ እኛ ቢመጡ ዳግመኛ አስተምረን የምናጠምቃቸው ይሆናሉ:: በነገራችን ላይ ጸጉራቸውን የሚያስረዝሙበት ተጨማሪ ምክንያት የይሁዳ አንበሳ ላይ ያለውን አንበሳ ምልክት ለመወከል ነው ይላሉ:: ነገር ግን በዚህ ስም የተጠሩት ነገሥታት ዐፄ ምኒልክና ዐፄ ኃ/ሥላሴ እንደ ነሱ ጸጉራቸውን አያስረዝሙም ነበር::

*ሐመር፦ ቀደም ሲል እንደ ገለጹልን «በራስ ተፈሪያውያን» እንቅስቃሴና በቤተ ክርስቲያናችን መካከል አለመግባባት አለ:: ይህ ሁኔታ በአሁኑ ወቅት የደረሰበትን ደረጃና ቤተ ክርስቲያናችን ችግሮቹን ተቋቁማ አገልግሎቷን ለማጠናከር የምታደርገውን ጥረት ቢገልጹልን?*

*ቄስ ኃይለ ጊዮርጊስ፦* እንደ ተናገርኩት «ራስ ተፈሪያውያን» ክርስቲያናዊ ክፍሎች አይደሉም:: በርግጥ ለቤተ ክርስቲያናችን እንቅስቃሴ ፈተናን ይደቅኑብናል:: ይሁንና ያን ያህልም ደግሞ የማንቋቋማቸው አይደሉም:: የበላይነትን ለመቆናጠጥ በመካከላቸው በሚያካሂዱት ውስጣዊ ትግል የተዳከሙ ናቸው::

*ሐመር:- «ራስ ተፈሪያውያን» ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማቅረብ ምን ጥረት እያደረጋችሁ ነው?*

*ቄስ ኃይለ ጊዮርጊስ፦* በጃማይካ ይህን ለማድረግ በእጅጉ ያስቸግረናል:: ምክንያቱም ክርስቲያን




©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ለመሆን÷ ክርስቲያን ለመባል «ንጉሥ ኃይለ ሥላሴ»ን ማምለክ ትተው በእውነትና በእምነት ክርስቶስን ማመንና መቀበል ይኖርባቸዋል። ይህን ለማድረግ በትሑት ሰብእና እስከ መጡ ድረስ እንቀበላቸዋለን ፤ ከዚህ በተጻራሪ ይህን እውነት የሚጋፋ ከኾነ ግን ከእነርሱ ጋር ኅብረት /አንድነት/ አይኖረንም። እንዲያ ሳናደርግ ከተቀበልናቸው ስሕተት ነው፤ ጥፋት ነው።

*ሐመር፦ ቄስ ኃይለ ጊዮርጊስ÷ ወደ ኢትዮጵያ ለምን መጡ?*

ቄስ ኃይለ ጊዮርጊስ፦ እኔ ወደ ኢትዮጵያ በዋናኛነት የመጣኹት ለቦብ ማርሌይ 60ኛ ዓመት የልደት በዓል አከባበር ነው። ተልእኮዬም በመታሰቢያው በዓል ላይ ጸሎትና ቡራኬ በመስጠት ማገልገል ነው።

*ሐመር፦ በርግጥ ጥር 29 ቀን 1997 ዓ.ም ለቦብ ማርሌይ 60ኛ ዓመት የልደት በዓል መታሰቢያ በጸሎትና ትምህርት ዝግጅቱን ሲከፍቱ እኛም ሆንን ሌሎች ኢትዮጵያውያን በቴሌቪዥን ተመልክተናል። ይህን በማየታችንም ግራ ተጋብተናል። የዓለም ጭፈራ የሚውልበትን ሥጋዊ ዝግጅት መጽር መስቀል ይዘው መባረክዎ ...*

ቄስ ኃይለ ጊዮርጊስ፦ /ፈጠን በማለት/ አይደለም። በጃማይካ በዓመቱ ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት የሙዚቃ ኮንሰርቶች ይዘጋጃሉ። በሁሉም ዝግጅቶች ላይ መንፈሳውያን አባቶችን ጋብዞ ማስባረክ በጃማይካውያን ዘንድ ልማድ ነው። ይህን በማድረግ የዝግጅታቸው ተልእኮና ግብ እንደሚሳካ ያምናሉ። ቤተ ክርስቲያንም ለምታካሂዳቸው የአገልግሎትና የግንባታ እንቅስቃሴዎች /የካቴድራል ሥራ/ የገንዘብ ድጋፎችን ታገኝበታለች። ከዚህም በላይ ለሙዚቃ ኮንሰርቱ ብሎ የመጣውን ሕዝብ ለማስተማር ከእነርሱም ጋር ለመወያየት የምትጠቀምበት አጋጣሚ ነው።

*ሐመር፦ ነገር ግን ጸሎቱና ቡራኬው መንፈሳዊ ÷እርስዎም ካህን እንደ መኾንዎ መጠን ዘፈንና ዳንስ በሚካሄድበት ዝግጅት ላይ ከመገኘትዎ ጋር ሁኔታው አይቃረንም ይላሉ?*

ቄስ ኃይለ ጊዮርጊስ፦ መቼም በማንኛውም ቦታ ልትጸልይ ትችላለህ። እኔ በዚህ ቦታ ላይ ስገኝ ለመጸለይ፣ ለማስተማር ነው። በዚያም ከተሰብሳቢው መካከል አንዲት ነፍስም ብትኾን ልትለውጥ፣ልታድን ትችላለህ። «ራስ ተፈሪያውያን» የሚያመልኳቸው ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ሰው እንጂ አምላክ አለመኾናቸውን በፊሊጥ ማስተማር ትልቅ ተግባር ነው።

ወደ ኢትዮጵያ እንደ መጣሁ ከብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ጳውሎስ ጋር ተገናኝቼ ነበር። እንደ ተገናኘንም «በኮንሰርቱ ላይ ጸሎትና ቡራኬ ልታደርግ ነው። ይህ ሥርዓትና ልማድ የማን ነው?» ብለው ጠየቁኝ። «የጃማይካውያን ልማድ ነው» ብዬ መለስኩላቸው። በርግጥም ይህ የኢትዮጵያውያን ሥርዓትና ልምድ እንዳልኾነ የታወቀ ነው። በእኛም ዘንድ ቢኾን መደበኛው ሃይማኖታዊ ሥርዓት ይህን አይፈቅድም። ወደ ቤተ ክርስቲያን ሊመጡ የማይችሉትን ብዙዎችን ለማግኘትና ለማስተማር ግን እንዲህ ዓይነቱ አደባባይ አመቺ ነው ብለን እናምናለን። በካሪቢያን አገሮች ያሉ ጳጳሳትና ቀሳውስት እንዲህ ባለው የጃማይካውያን ዝግጅት ላይ እየተገኙ ጸሎትና ቡራኬ ያደርጋሉ። ዓላማው ግልጽ ነው። ትችት ሊያጋጥም እንደሚችል የታወቀ ቢኾንም ትችቱ ግን አንዲት ነፍስን ከማዳን ተግባር አይበልጥብንም።

እንዲህ ዓይነት አጋጣሚዎችን ሕዝብን ለማስተማር መጠቀም እንዳለብን በግሌ አምናለሁ፤ ቢያንስ ለ15 እና ለ30 ደቂቃ ቢኾን ነው። ጌታችንም፦ «ሂዱ÷ አሕዛብን ሁለ እያስተማራችሁ በአብ በወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው» ነው ያለው። «ሂዱ» ማለት የተወሰነ ቦታ ረግታችሁ ተቀመጡ ማለት አይደለም። ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡትን ደጋጎች ብቻ ሳይሆን ርቀው ያሉትን ግፋዓን ወገኖች ሁሉ መኅብኘት፣ ማስታወስ ይገባናል። በዚያ ኮንሰርት ላይ ተገኝቼም ከቡራኬ በፊት ስለ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት ሰፋ ያለ ትምህርት ሰጥቼአለሁ። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት ማስተማሬም በዚያ ቦታ አንድን ሰው /ግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃ/ሥላሴን/ አምላክ ብለው የሚያምኑ ጃማካውያን በብዛት ስለ ነበሩ ነው። እንደ ሰማሁት የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ፕሮግራሙን በቀጥታ ማስተላለፍ የጀመረው ቡራኬ ሳደርግ ጀምሮ ነው። የሰጠሁት ትምህርት አልተላለፈም። ምናልባት በዚያ የተነሣ ወገኖቼ «እንዴት ዘፈን ይባርካል?» ብለው ቅር ሳይላቸው የቀረ አይመስለኝም። /በእርግጥ ከ«ቡራኬ» በፊት ሰፊ ትምህርት እንደሰጡ እኛም አረጋግጠናል/።

*ሐመር፦ አንዳንድ ክፍሎች በመስቀል አደባባይ የተካሄደው የሙዚቃ ኮንሰርት «በኢትዮጵያውያን ላይ የሚካሄድ ድብቅ የባሕል ወረራ ሸፋን ነው» ይላሉ። በዚህ ላይ የሚሰጡት አስተያየት ምንድን ነው?*

ቄስ ኃይለ ጊዮርጊስ፦ ኮንሰርቱ የተዘጋጀው በጃማይካውያን ልማድና ሥርዓት መኾኑን መረዳት ያስፈልጋል። ለኢትዮጵያውን ያልተለመደ ሊኾን ይችላል። በጃማይካውያን ዘንድ ለምዕተ ዓመት የኖረ ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያውያን ይህ ዝግጅት ከእነሱ ውጭ በሆነ ባሕልና ትውፊት የተዘጋጀ መሆኑን ተረድተው የራሳቸውን ድንቅ ባሕል መጠበቅና ማስጠበቅ አለባቸው። እንደኔ እንደኔ አንድ ሰሞን እዚህም እዚያም ከታየው ጃማይካዊ ባሕል የበለጠ ልትጠነቀቁበትና ሁሉም በየግሉም ሆነ በቤተሰብ ደረጃ ርምጃ ልትወስዱበት የሚገባ የባሕል ወረራ አለ በዚህ አገር። የአጠውሮፓውያን ሚስዮናውያን እምነት የሚመስል የባሕል ወረራ። ልንገራችሁ /ረጅም ትካዜ/። እነዚህ ሰዎች እኛን /ጃማይካውያንን/ በእምነት ስም ማንነታችንን ሲረግጡ፣ ባሕላችንን ሲያጠፉ፣ ጉልበታችንንና ገንዘባችንን ሲበዘብዙ ኖረዋል። ይህንን የሚያደርጉት በእምነት ስም መጥተው ነው። ነገር ግን በመጨረሻ እግዚአብሔርም ረዳንና ከትከሻችን አውርደን ጣልናቸው። ዛሬ እነዚህ መሰሪ ድርጅቶች በእኛ አገር የሉም። ቢኖሩም በስም እንጂ የሚቀበላቸው የለም። ስለዚህ ኢትዮጵያውያንም ራሳቸውን ከእነዚህ በዝባዦች ስውር ሴራ ራሳቸውን ይጠብቁ። እናገራለሁ ÷ የሃይማኖት ሰዎች አይደሉም። እንደዚህ ስል የጃማይካ ባሕልም ቢሆን የእናንተ አይደለምና ቦታ አትስጡት።


*ሐመር፦ በማዕከል ያለችው እናት ቤተ ክርስቲያን በክፍለ አህጉሩ ላሉት ምእመናንዋ እየሰጠች ያለችውን አገልግሎት እንዴት ይመዝኑታል፤ በቂ ነው ይላሉ?*

ቄስ ኃይለ ጊዮርጊስ፦ የሚሰጠው አገልግሎት በራሱ ጥሩ ቢሆንም ከዚያ የበለጠ ሊሠራ ግን ይቻላል፤ መልክአ ምድራዊ ገጽታው አለያይቶናልና። ለምሳሌ በጃማይካ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከ1973/74 እ.አ.አ መሠረቱን የጣሉትን ካቴድራል እስከ አሁን ድረስ ሠርተን ለማጠናቀቅ አልቻልንም። እርሱን ሠርተን ለማጠናቀቅ ብንችል ዐቅማችንን ያሳድግልናል፤ መጽሐፍ ቅዱስን ጨምሮ ቅዱሳት መጻሕፍትን በቋንቋችን ለመተርጎም እንችላለን። በተለይ ከግእዙና ከአማርኛው ቋንቋ ወደ ራሳችን ቋንቋ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመተርጎም በእጅጉ እንሻለን። ከግእዝና ከአማርኛ ወደ እንግሊዘኛ በብቃት የሚመልሱ ተርጓሚዎችም ያስፈልጉናል። እስከ አሁን የምንጠቀምባቸው ምዕራባውያን ጸሐፊዎችና ተርጓሚዎች ያዘጋጁትን የኪንግ ጀምስ ትርጉም [version] ÷እንዲሁም በእርሱ ላይ ተመሥርተው የሚጻፉትን ድርሳናት ነው። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የአተረጓጎም ስልትና ዘይቤ የተዘጋጁ የጉባኤ መጻሕፍት፣ የሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ወደ እንግሊዘኛ ተተርጉመው ለማንበብ እንጓጓለን። ካህናት እንደ መኾናችን መጠን ከእነርሱ ከምናገኘው የጥበብ ጸጋና ሀብት በቀር ሌላ ኃይል የለንም።

/ወደ ገጽ ፴፱ ዞሯል/



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org



*ይህ ዓምድ በሥርጭቱ ፍጥነትና በጥቃቱ ስፋት አሳሳቢ ደረጃ የደረሰውን ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ ማኅበረ ቅዱሳን ከአክሽን ኤይድ ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር የጀመረው ሰፊ ሥራ አካል ሆኖ ከዚህ እትም ጀምሮ የተከፈተ ነው:: ማኅበራችን ይህንን ሥራ ሲጀምር ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ባገኘው መልካም ፈቃድና መመሪያ መሠረት ሲሆን፣ አጠቃላይ የሥራ ሂደቱም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መምሪያ ክትትል እንዲደረግበት ሆኖ ነው::*

# የጠባይ ለውጥ እንዴት?

*ዲ/ን ፋሲል አስረስ*

ባለፉት ዐሠርት ዓመታት ውስጥ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በተመለከተ በአገራችን በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን አስከፊነቱንና መፍትሔ ሊገኝለት እንዲ ልቻለ ተነግሯል፣ ተዘክሯል:: ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያለባቸውን ጨምሮ የመንግሥት ባለሥልጣናት ምሁራን የሃይማኖት አባቶች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው የበሽታውን አስከፊነት ለሕብረተሰቡ ለማስገንዘብ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል::

በሀገር ደረጃ ርዕሰ መንግሥት በሆነው በጠቅላይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ሥር የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መቆጣጠሪያ ተከፍቷል:: መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም ዐቢይ ተግባር አድርገው በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ እየሰሩ ይገኛሉ በሃይማኖት ተቋማትም ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል ::

ዓለምን ያሸበረውና ከቁጥጥር ውጭ የሆነው፣ ያለማቋረጥ የሰዎችን ሕይወት እየቀጠፈ በአስደንጋጭ ሁኔታ በየጊዜው እየከፋ የመጣው ቫይረስ እንዴት መጣ? መጨረሻውስ ምን ይሆን? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ በሌላ ጽሑፍ የምንመለስበት ሲሆን ለዛሬው ባለፈው እትማችን ከዚህ ጨካኝ በሰው ዘንድ መፍትሔ ከጠፋለት በሽታ ለመዳን የጠባይ ለውጥ ማምጣት ትልቁ መፍትሔ በመሆኑ፣ የጠባይ ለውጥ ሊመጣ ያልቻለበትን ምክንያት ዘርዝረን የጠባይ ለውጥ ሊመጣ የሚችልበትን መንገድ እናያለን:: መልካም ንባብ::

ጠባይ ወይንም አመል በተለያዩ መንገዶች ይወረሳል:: የመጀመሪያው ከቤት ውስጥ ሲሆን በመቀጠልም በየደረጃው ከአካባቢ፣ ከትምህርት ቤት፣ ከመሥሪያ ቤት በጠቅላላው ከምንውልበት ቦታ የምንለምደው ዐመል ነው:: የተለመ ደን ጠባይ ደግሞ በጉም ይሁን መጥፎ በቀላሉ ከራስ ለማላቀቅ አስቸጋሪ ሊሆን ይቻላል::

በሥነ ምግባር ታንጾ ያደገ አንድ ሰው የሥነ ምግባር መርሆዎች ከሚጣስበት ቦታ ቢገኝ እስኪለማመደው ድረስ ይቸገራል:: ከለመደው በኋላ ግን ጠባዩ ያደርገውና አዲስ ጠባዩ ይሆናል:: በተቃራኒው እኩይ ምግባር ለምዶ የኖረን ሰው በአንዴ ካለበት ዐመል እንዲላቀቅ ቢሞከር ምንም እንኳ እየተጓዘበት ያለው ሕይወት እንደ ማይጠቅመው ቢረዳም ጠባዩን ለመለወጥ ይከብደዋል::

ማንኛውም ሰዉ በሥነ ምግባሩ የተመሰከረለት ዐመሉ የታረመ መሆኑ አስከፊ ከሆነው በሽታ ማምለጥ መቻሉ ብቻ ሳይሆን በሕብረተሰቡ ዘንድ ከበሬታን፣ ውስጣዊ ሰላምን ብሎም ከእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋን ያገኛል::

የጠባይ ለውጥ አምጥቶ የቫይረሱን ሥርጭት ለመቀነስ መፍትሔ የሚሆኑ የተለያዩ ሁኔታዎች ቢኖሩም ለዚህ እትም ግለሰቡ፣ ማኅበረሰቡ፣ መንግሥትና የሃይማኖት አባቶች ሊያደርጉ ይገባል ብለን ያመንበትን አቅርበናል::

## 1 ትምህርት

ስለ ትምህርት ሲነሣ ከላይ በመግቢያው ላይ እንደተገለጸው ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በተመለከተ በተለያዩ አካላት ትምህርት ይሰጣል:: የጠባይ ለውጥ ግን አልታየም:: ሕብረተሰቡ ትምህርቱን ሰማ እንጂ አልተለወጠም:: ለምን? ለማንኛውም ለውጥ ትምህርት ወሳኝነት አለው:: የሚሰጠው ትምህርት ደግሞ ፍሬአማ መሆን አለበት:: ትምህርት ሰጪ ትክክለኛውን መረጃ ለትምህርት ተቀባዩ ማስተላለፍ ከቻለ ውጤታማ ይሆናል::

የጠባይ ለውጥ እንዲመጣ የኮንዶምን የመከላከል ብቃት ማስተማር ሳይሆን እስከ ጋብቻ ድረስ እንዴት መታቀብ እንደ ሚቻል ማስረዳትና ተሞክሮዎችን ማሳየት ብሎም ጠቀሜታውን አጉልቶ መንገር ያስፈልጋል :: ለሕይወት ዋጋ መስጠት ማለት ጊዜያዊ ርካታን ሳይሆን ቋሚ ሕይወትን መጠበቅ እንደሆነ ማወቅ ነው::

ይህ የመኖርና ያለመኖር ጥያቄ የሆነው ጉዳይ ዛሬ በትምህርት ካልተስተካከለ ነገ ምን ሊያመጣ እንደሚችል ይታወቃል:: የመገናኛ ብዙኃን ትውልዱ ራሱን እንዲጠብቅ በሚያስታጥቁት «የመከላከያ ቦንብ» /ኮንዶም/ ራሱን እንዳያጠፋበት መጠንቀቅ ግድ ይላቸዋል::

ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያለባቸውም ሰዎች ተገቢ የሆነ ትምህርት ማግኘት አለባቸው:: ስለ በሽታው ሙሉ ዕውቀት ኑሯቸው በራሳቸው ፍላጎት ወጥተው የሚያስተምሩበት ሁኔታ ቢመቻች የሚጠበቀው የጠባይ ለውጥ ሊመጣ ይችላል::

ውጤቱም በትምህርት ቤት በሥራ ቦታ በሽታውን በተመለከተ መረጃ እንዲያገኙ ማድረግ አንዱ መፍትሔ ሲሆን በጽሑፍና በመሳሰሉት ማስተማሪያዎች ሙሉ እውቀት እንዲኖረው ማድረግም ተገቢ ነው::

## 2 ምክክርና ውይይት

ክርስቲያን አንዱ መለያው የንስሐ አባት መያዙ ነው:: የንስሐ አባት ደግሞ ከንስሐ ልጆቹ ጋር በየጊዜው እየተገናኘ በመንፈሳዊና ማኅበራዊ ጉዳዩች ዙሪያ ውይይት ማድረግ ይጠበቅበታል:: በዚህ ሂደት ንስሐ አባት ከንስሐ ልጅ ጋር መነጋገር ከቻለ የሚጠበቀው የጠባይ ለውጥ ሊመጣ ይችላል::

በተለይ ተሸፋፍኖና የንጻ ምስጢር ሆኖ የሚገኘው የኤች.አይ.ቪ. ጉዳይ ግልጽ ብሎ ንስሐ አባት ከልጆች ጋር፣ ማኅበረሰቡ ከማኅበረ ሰቡ ጋር፣ ቤተሰብ ከቤተሰብ ጋር ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ መነጋገር ከቻሉ የጠባይ ለውጥ ማምጣት ይቻላል:: በኤድስ ሥርጭት ግንባር ቀደም ሁና ትጠቀስ የነበረችው ኡጋንዳ አስደንጋጭ በሆነ መንገድ ስትጓዝ የቆየች ቢሆንም በሚያስገርም ሁኔታ የሥርጭት አድማሱን የገታችው ከፕሬዚዳንቷ ጀምሮ እስከታች ድረስ መነጋገርና መወያየት በመጀመሯ ነው::

ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር መወያየትና ልጆቻቸውን አግባብ ያለው ክትትል በማድረግ ማሳደግ ከቻሉ የጠባይ ለውጥ ሊመጣ ይችላል:: ክፉና ደጉን ያልለዩ ሕጻናት የግድ የወላጆቻቸው ክትትል ያስፈልጋቸዋል:: እየጠፋና እየተዘነጋ የመጣው የልጆች አስተዳደግ ሥርዓት አሁንም ሊተገበር ይገባዋል:: ልጆች እንዳሻቸው ተብሎ የሚለቀቁ ከሆነና መወያየት ካልተቻለ



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

የሚጠበቀው የጠባይ ለውጥ ሊመጣ አይችልም።

### 3. ቅዱስ ጋብቻን ማበረታታት

ስለ ጋብቻ ሲነሣ ተያይዘው መነገር ያለባቸው ብዙ ጉዳዮች አሉ። በትልቅ ጉጉት ይጠበቅ የነበረው የጋብቻ ቀን መርዶ እንደ ሚሰማበት ዕለት ተደርጐ መቆጠር ከጀመረ ውሎ አድሯል። ከፍተኛ ድግስ ካልተደገሰ ጋብቻ መመሥረት አይቻልም የተባለ እስኪመስል ድረስ ከዐቅም በላይ መደገስ ጋብቻን ለመመሥረት እንደ ዐቢይ ነገር ተደርጐ ተቆጥሯል።

የኑሮ ውድነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻቀበ የሔደበት ወቅት ነው። በአሁኑ ሰዓት የሠርግ ወጭ ማውጣት የማይችል ሰው ጋብቻን በመሸሽ ለረዥም ጊዜ በብቸኝነት መኖርን ይመርጣል። በመሐል ዕድሜን ጠብቆ የሚመጣውን ፍትወት መቆጣጠር ሲያቅተው ራሱ ሰውየውም ቢሆን የማይፈልገውን ተግባር ለመፈጸም ይገደዳል።

ሁሉንም ዜጋ እያሳሰበ ካለው ብዙ ስም ከተሰጠውና ቀሳፊ ከሆነው ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ለማምለጥም ሆነ የጠባይ ለውጥ ለማምጣት የተቀደሰ ጋብቻን ማበረታታት ይገባል። የጠባይ ለውጥ ለማምጣት የተቀደሰ ጋብቻን በማበረታታት ዕድሜው ለዐቅመ አዳ ምና ሔዋን የደረሰን ሰው በአንድ እንዲወሰን ማድረግ አማራጭ የሌለው መፍ ትሔ ነው።

በተለይ ይህን ፈታኝ የሆነ ዓለም ለማሸነፍ እስከ ጋብቻ ዕለት ድረስ ራሳቸውን ጠብቀው በድንግልና ለሚቆዩ ሰዎች የማበረታች ሽልማት በመስጠት ትውልዱ ድንግልናውን ጠብቆ እስከ ጋብቻው ዕለት ቢቆይ የሚያገኘውን ዋጋ ከትዳር አጋሩም ጋር የሚኖረውን መተማመንና . ፍቅር በጊዜአዊ ስሜት ዘላቂ ሕይወትን ማበላሸት ተገቢ አለመሆኑን ማስረዳት ከሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል የሚጠበቅ ኃላፊነት ነው።

### 4. ፖርኖግራፊ ፊልሞችን መቆጣጠር

ሰው አንድን ነገር ደጋግሞና አተኩሮ ሲመለከት በሚያየው ነገር ሊማረክ ይችላል። አዳምና ሔዋን ከእፀ በለስ ጋር አብረው ቆይተው ነበር። ነገር ግን አልተመኟትም። የሰይጣንን ድምጽ ከሰሙ በኋላ ነው ደጋግመው በማየት ቀጥፈው ለመመገብ የሞከሩትና ከፈጣሪአቸው ጋር የተጣሉት። ዘፍ.3÷6።

በሀገራችን ከታላላቅ ከተሞች ጀምሮ የመብራት አቅርቦት የሚገኝባቸውን ትንንሽ ከተሞች ጨምሮ የተለያዩ የውጭ ሀገር ሕገ ወጥ ፊልም ይታይ ባቸዋል። የፊልሞቹ ወደ ሀገራችን መምጣት በራሱ ከሃይማኖትና ከባሕላችን አንጻር ተቀባይነት የላቸውም። መንግሥትና የሚመለከታቸው አካላት ይህን ተከታትለው ማስወገድ ካልቻሉ የጠባይ ለውጥ ማምጣት ቀርቶ ሀገሪቷንም ምድረ በዳና የምግባረ ብልሹዎች መናኸሪያ እንዳያደርጋት ያሰጋል።

ሕገ ወጥ ፊልም ቤቶች ገንዘብ ተከፍሎ ዕብደት የሚማሩባቸው ቦታዎች ሁነው እያሉ በዝምታ መመልከት የኤች.አይ.ቪን እሳት ለማጥፋት በአንድ በኩል ውኃ በሌላኛው ነዳጅ እንደመርጨት ይቆጠራል።

በዚህ ሥራ ተሰማርተው የሚገኙ ግለሰቦችም የጉዳዩን አሳሳቢነት በመረዳት የሥራ መስካቸውን በሌላ ተክተው ኤች.አይ.ቪን ለመከላከል እየተወሰደ ላለው የጠባይ ለውጥ እንቅስቃሴ ተባባሪ መሆን ይጠበቅባቸዋል።

### 5. የምሽት ጭፈራ ቤቶችን መዝጋት

ለአንድ በሽታ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮች ከታወቁ ከመታመም በፊት እነርሱን ማስወገድ ማንም ጤናማ አዕምሮ ያለው ሰው ሊያደርገው የሚችለው ነገር ነው። ኤድስ የአንድ ሰው ችግር ሳይሆን የሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ብሎም የዓለም ኅብረተሰብ ችግር ነው። ይህን ችግር ለማስወገድ ምክንያት የሚሆኑ ነገሮች ደግሞ መወገድ እንደሚገባቸው ይታወቃል።

አበው ሲተርቱ «አመድ ላይ የወደቀ ሥጋ» ይላሉ። ጭፈራ ቤት ገብቶ ራሴን ጠብቄ እወጣለሁ ማለት ወፍጮ ቤት ገብቶ የዱቄት ብናኝ ሳይነካኝ እወጣለሁ እንደማለት ነው። የምሽት ጭፈራ ቤቶችም የሥራ መስካቸውን ለውጠው ትውልዱን አምራች ማድረግ የሚችሉ ሲሆን ይህ ሳይሆን የጠባይ ለውጥ ማምጣት ግን የማይቻል ነው።

በአገራችን አንዳንድ ክልሎች በክልላቸው ጫትና የመሳሰሉትን ኢሥነ ምግባራዊ የሆኑ ድርጊቶችን ከልክለዋል። ይህ የሚበረታታ ሲሆን ትውልዱን ለመታደግና የጠባይ ለውጥ እንዲመጣ በሁሉም የአገራችን ክፍሎች ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

### 6. ድህነትን መቀነስ

ኤች.አይ.ቪ ኤድስ በየትኛውም ቦታ የሚገኙ ሰዎችን የሚያጠቃ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት በከፍተኛ ሁኔታ እያጠቃ ያለው ከሰሐራ በታች ያሉ ድሃ አገራትን ነው።

የድህነት መገለጫው ብዙ ቢሆንም ለኤች.አይ.ቪ መባባስ ዋነኛ ተደርጐ የሚወሰደው ግን የዝሙት ተዳዳሪዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንዲመጣ በማድረጉ ነው። በዝሙት የሚተዳደሩ እኅቶቻችን ብዙዎች ያሉ በትን ሕይወት ወደውት ሳይሆን በቂ መተዳደሪያ በማጣትና ራሳቸውን አሸን ፈው ለመኖር ብለው የገቡበት ነው።

ለእነዚህ እኅቶቻችን ሥራ አድርገው የገቡበትን ሕይወት በመቀየር መንግሥት አማራጭ ሥራ በመፈለግ ኅብረተሰቡም የተለያዩ የሥራ ዕድሎችን በማፈላለግ ካሉበት ሕይወት ማውጣት ግድ ይላል።

ድኅነት ሊወገድ የሚችለው በሥራ እንደ መሆኑ ሁሉም ሥራን ባለመናቅ ቢሠራ ራሱን አሸንፎ ለሀገር ከመጥቀሙ በላይ ሥራ ፈትቶ ከሚያስባቸው የተለያዩ እኩይ ምግባራት ይጠበቃል። «ሥራ የፈታ አእምሮ የሰይጣን ቤተ ሙከራ ይሆናል» እንደተባለ፣ ሰው ያለምንም ተግባር ሲቀመጥ ተገቢ ወዳልሆነ አቅጣጫ ስለሚያመራ የጠባይ ለውጥ ማምጣት አይችልም።

### 7. ለወጣቱ አማራጭ የመወያ ቦታ መፍጠር

ወጣቱ እየተዝናና የሚማርባቸው የተለያዩ ቦታዎች ሊዘጋጁለት ይገባል። ወንበር ሳያዘጋጁ ለምን መሬት ላይ ተቀመጥክ ማለት አይቻልም። ይህን አታድርግ ሲባል ማድረግ የሚገባውንም መንገር ያስፈልጋል።

አስተማሪ የሆኑ የመዋያ ቦታ ከተዘጋጁለት ወደ ማይፈለጉ ነገሮች ከማዘንበል ይቆጠባል። ይህን ለማዘጋጀት ደግሞ የግድ ከመንግሥት ብቻ የሚጠበቅ አይደለም። ቀበሌዎች፣ ከኅብረተሰቡ ጋር ካላቸው ቅርበት አንጻር እየተወያዩ መሥራት ቢችሉም ዕድሮች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ባለሀብት ግለሰቦች በዚህ ዙሪያ ከፍተኛ ድርሻ አላቸው።

ነገ ሀገር ተረክቦ የሚያስ ተዳድር ትውልድ የሚገኘው ዛሬ በሥነ ምግባር ታንጾ ጤናማና ብቁ ሆኖ ያደገ ወጣት ሲኖር ነው። በዚህ ትውልድን በመቅረጽ ዘመቻ ላይ መረባረብ ከትክክለኛ ዜጋ የሚጠበቅ ነው።

ወጣት አምራች ኃይል ነው። በሁሉም በሠለጠነበት የሥራ መስክ ተሰማርቶ ቢሠራ ውጤታማ ይሆናል። ይህ ሊሆን የሚችለው ግን በቅድሚያ መኖር ሲቻል ነው። ለመኖር ደግሞ ራሱን ከኤች.አይ.ቪ ኤድስ መጠበቅ አለበት። ለዚህ ደግሞ በሥነ ምግባር የታነጸና ጠባዩ ያማረ ሲሆን ነው።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# በሃይማኖት ከማይመስሉን ጋር እንዴት እንኑር?

*ዲያቆን ያረጋል ገላው*

ይህ ዓለም ብዙ ነገሮች ተደባልቀው የሚገኙበት የውጥንቅጥ ስብስብ ነው:: ስንዴና እንክርዳድ ጥጋብና ረኃብ፣ ባለጸግነትና ድኀነት፣ ኃዘንና ደስታ፣ ጽድቅና ኃጢአት የመሳሰሉት ተቃራኒ የሆኑ ነገሮች በዚች ዓለም ጐን ለጐን ይኖራሉ:: ይህም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የሚቀጥል ሂደት መሆኑን ጌታችን ደቀ መዛሙርቱ «እንክርዳዱን እንንቀለውን?» ባሉት ጊዜ «ተውት እስከ መከር ድረስ አብረው ይኑሩ» በማለቱ ይታወቃል::

ክርስቲያኖችም በዚህ ዓለም ሲኖሩ በሃይማኖት ከማይመስሏቸው ሰዎች ጋር በተለያዩ ማኅበራዊና አካባቢያዊ ሁኔታዎች ያገናኛሉ:: ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን የላካቸው በተኩላቸው መካከል ነው:: ተኩላ የተባሉ በተፈጥሮአቸው ሰዎች ሲሆኑ በምግባራቸውና በእምነታቸው ከእውነተኛው መንገድ ወጥተው በጥፋት ጐዳና የሚጓዙና ሌሎችንም እየነጠቁ ወደ ጥፋት ጎዳናቸው የሚወስዱ ሰዎች ናቸው፤ «ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልለምንህም» ማለቱም ጌታችን ክርስቲያኖች ከክፉም ነገር እንዲጠበቁ እንጂ ዓለም ከተባሉ በሕይወታቸው ከማይመስሏቸው ሰዎች ሁሉ ተለይተው በሌላ የተለየ ዓለም እንዲኖሩ አለማድረጉን ነው::

እግዚአብሔር ጻድቃንንና ኃጥአንን፣ ክርስቲያኖችንና ከዚያ ውጭ ያሉትን ሁሉ በአንድ ዓለም እንዲኖሩ፣ በአንድ ሕግ እንዲመሩ መስጠቱ ለብዙ ምክንያት ነው፥ ከእነዚህም

1. ክርስቲያኖች እምነታቸው ተፈትኖ የሚወጣውና የሚጋለጠው የሚያዳክሙን የሚያሰናክሉ የተለያዩ ፈተናዎችና በእምነት የማይመስሉ አማንያን ባሉበት ዓለም ሆነው ይህንን ሁሉ ታግሰውሲያልፉና ሲያሸንፉ ስለሆነ ነው:: ደጋጐቹና ድል አድራጊዎቹ ተለይተው ይበራሉ:: ደምቀው ይታያሉ:: ያለ ውድድር ማሸነፍ ያለ ተጋድሎ ድል ማድረግ የለምና:: ለምሳሌ ኖኅም ጻድቅ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን ከዚያ ክፉ ትውልድ መካከል ጻድቅ ሆኖ ስለተገኘ ነው:: «ኖኅም በትውልዱ ጻድቅ ፍጹምም ሰው ነበረ::» እንዲል ዘፍ.8:: ፈተናና መሰናክል በሌለበት ጊዜና ሁኔታ ጻድቅ መሆንና ኖኅ በነበረበት ዘመን ከነበሩት ሰዎች ጋር እየኖሩ ያን ሁሉ አልፎ ጻድቅ መሆን አንድ አይደለምና::

2. ለኢአማንያንና ለኃጥአንም ከክርስቲያኖችና ከጻድቃን ጋር በአንድ ላይ መኖራቸው ጥቅም አለው:: ጻድቃን ሰዎችን ሲያዩ ወደ ጽድቅ አማንያንን ሲያዩ ወደ ሃይማኖት ይሳባሉና እግዚአብሔርን በሚያ ዩዋቸው በሚያውቋቸው በሰዎች ሊያዩትና ሊያውቁት በዚህም ወደ እርሱ ሊቀርቡ ይችላሉ::

ጌታችን ክርስቲያኖችን እናንተ የዓለም ብርሃን የምድር ጨው ናችሁ ብሏል:: ይኸውም በጨለማ ክህደት ያሉ ብርሃን ክርስቶስን ከክርስቲያኖች ከቃላቸው ሰምተው ከሕይወታቸው ተመልክተው ከክህደት ወደ ሃይማኖት እንዲመለሱ ያደርጋቸዋል፥ በኃጢአት አልጫ በሆነ ሕይወት ያሉትም የክርስቲያኖችን የተቀደሰ ሕይወት በማየት ወደ መልካምነትና ጣፋጭነት የመለወጥ ዕድል ያገኛሉና ነው:: እንዲሁም በእርሾ ተመስለዋል:: መንግሥተ ሰማያት ሁሉ እስኪቦካ ድረስ ሴት ወስዳ በሦስት መስፈሪያ ዱቄት የሸሸገችውን እርሾ ትመስላለች:: ማቴ.13÷33:: እርሾ የተባለ ሐዋርያት ጻድቃን በአጠቃላይ የክርስትናን ሕይወት የሚኖሩ ሲሆን ዱቄት የተባሉ ደግሞ ከዚህ ውጭ ያሉ ናቸው:: እርሾውና ዱቄቱ በአንድ ላይ መለወሱ ሁለቱም በዚህ ዓለም በአንድ ላይ ተደባልቀው የሚኖሩ መሆኑን የሚያመለክት ነው:: እርሾው ከዱቄት ጋር የሚለወሰው ዱቄቱን እንዲያቦካው እንደሆነ ሁሉ ጻድቃንም በዚህ ዓለም ከኃጥአን ጋር መኖራቸው እነዚህን በእነርሱ ባደረ መንፈስ ቅዱስ ኃይል ወደ ሃይማኖትና መልካም ምግባር እንዲያሸጋግሯቸው እንዲለውጧቸው ነው:: እርሾውና ዱቄቱ በተፈጥሮአዊ ይዘት ተመሳሳይ ናቸው ÷ ግን አንዱ ሌላውን ይቀይረዋል ÷ እንዲሁም ኃጥአንና ጻድቃንም ሁሉም በተፈጥሮ አንድ እንደሆኑ ሁሉ በሕይወታቸውና በዓላማቸውም አንድ ይሆኑ ዘንድ ሁለቱንም በአንድ ዓለም አኖራቸው::

እግዚአብሔር ለኃጥአንም ሆነ ለጻድቃን ÷ ለክርስቲያኖችም ሆነ ከዚህ ውጭ ላሉት ለኢጥሙቃን ሁሉ አንድ ሕግ ሠርቶ አንድ ዓለምን ሰጥቶ ለሁሉም እኩል የቸርነቱንና የማዳኑን ጸጋ በማቅረቡ የዚህ ጸጋ ተጠቃሚዎች ያልሆኑ፣ እግዚአብሔርን የሚወቅሱበትና ጥፋታቸውን በእርሱ የሚያመካኙበት ምክንያት እንዲያጡ ያደርጋቸዋል:: ለዚህ ነው በፍርድ ቀን የነነዌ ሰዎችና ንግሥተ አዜብ በአይሁድ ላይ ፈራጆች ሆነው እንደሚነሡ ጌታችን የተናገረው::

እንዲህ በዚህ ዓለም ሁሉም ተደባልቆ የሚኖር ስለሆነ ዋናው መሠረታዊ ነገር ክርስቲያኖች በእምነትና በሕይወት ከማይመስሏቸው ጋር ሲኖሩ ሊኖራቸው የሚገባው ግንኙነት ምን መምሰል አለበት? የሚለው ነው:: በዚህ ጽሑፍ በመጀመሪያ ከማይመስሏቸው ጋር የማይገባ አካሄድ የሄዱና በዚህም የተለያየ ችግርና ጉዳይ የደረሰባቸውን ሰዎች እናያለን:: ቀጥሎም ከማይመስሏቸው ጋር በጥበብና በአግባብ ተመላልሰው ራሳቸውን ጠብቀው ለሌላውም እስከ መትረፍ የደረሱትን እንመለከታለን:: በመጨረሻም ከሁለቱም አንጻር ሊስተዋሉ የሚገባቸውን መሠረታዊ ነገሮች ጠቅለል አድርገን ለማየት፣ ለመዳሰስ እንሞክራለን::

## ሀ. በማይገባ አካሄድ ምክንያት የተጐዱ

### 1. ሕዝበ እስራኤል

እስራኤላውያን ለ430 ዓመት ያህል በግብፅ ሲኖሩ ብዙ የግብጻውያንና የባዕድ አምልኮ ልማዶችና ሥርዓቶች ተለምደው ነበር:: እግዚአብሔር ይህ የጣዖት አምልኮ ልማድ በኋላ እንያስቸግራቸውና ዕንቅፋት እንዳይሆንባቸው የእርሱን እውነተኛ አምላክነትና ኃያልነት በዚያው በግብፅ ሳሉ የግብፅን ጠንቋዮች በሙሴ ፊት እንዲቆሙና በእግዚአብሔር ኃይል የሚሠራውን በሙሴ አማካይነት የሚገለጠውን የእርሱን ድንቅና የአምላክነት ሥራ አሳያቸው:: መጀመሪያ በትራቸውን በምትኀት እባብ ማስመሰል ቢችሉም የሙሴ በትር የእነርሱን በትር ሁሉ ዋጠች ÷ በኋላም በሰውና በእንስሳ ላይ የቁስል መቅሰፍት በታየ ጊዜ ጠንቋዮችም በቁስል ስለተመቱ ከነጭራሹ የሙሴ ፊት መቆም አልቻሉም:: ዘጸ.9÷11:: የግብጻውያንና የአማልክቶቻቸው ኃይልም እስከምን ድረስ እንደሆነ ግብጻውውያንን በባሕር በማስጠም? የእርሱን ኃይል ደግሞ ባሕር ከፍሎ በማሻገር መና በማውረድ ከዓለት ውኃ በማፍለቅና በመሳሰለው ተአምራዊ ሥራው ማንነቱን ገለጠላቸው::

እንዲሁም ለወደፊቱ ደግሞ የሚወርሷት ከነዓን ሲኖሩ ከአሕዛብ ጋር እንዳይደባለቁና አምልኮ ጣዖታቸውንና ግብረ ኃጢአታቸውን እንዳይለምዱ ደጋግሞ አዘዛቸው:- «አምላካህ እግዚአብሔር ልትወርሳት ወደ ምትገባበት ምድር ባመጣህ ጊዜ ከፊትህም ብዙ አሕዛብን ባወጣ ጊዜ





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ፈጽመህ አጥፋቸው፤ ከእነርሱም ጋር ቃል ኪዳን አታድርግ ፥ አትማራቸው፤ ከእነርሱም ጋር አትጋባ፤ ሴት ልጅህን ለወንድ ልጅ አትስጥ፥ ሴት ልጅህም ለወንድ ልጅህ አትውሰድ» በማለት አዘዛቸው፡፡ የዚህም ዋናው ምክንያት ምን እንደሆነ ራሱ እግዚአብሔር ሲናገር «እንዳይከተለኝ ሌሎችንም አማልክት እንዲያመልክ ልጅህን ያስታልና» ሲል ተናገረ፡፡ ይህንኑ የበለጠ ጽኑ ሲያደርግ እንዲህ አለ፡፡ «ነገር ግን እንዲህ አድርጉባቸው፤ መሠዊያቸውን አፍርሱ፥ ሐውልቶቻቸውንም ሰባብሩ ፥ የማምለኪያ ዐፀዶቻቸውንም ቁረጡ ፥ የተቀረጸውን ምስላቸውም በእሳት አቃጥሉ፡፡» ዘዳ. 7፥ 1–5፡፡

ኢያሱም በመጨረሻ ሊሞት ሲል በተናገራቸው ጊዜ «አሁን እንግዲህ በመካከላችሁ ያሉትን እንግዶች አማልክት አርቁ ፥ ልባችሁንም ወደ እስራኤል አምላክ ወደ እግዚአብሔር አዘንብሉ አላቸው፡፡» ኢያ.24፥23፡፡

ነገር ግን እግዚአብሔር እንዲህ አስቀድሞ ቢያስጠነቅቃቸውምና አስፈላጊውን ሁሉ ነገር ቢያደርግላቸውም እነርሱ ግን በግብፅ ሳሉ የለመዱት ልማድ እና ከዚያም በኋላ በመንገድና በከነዓን ካሉ አሕዛብ የተማሩት የጣዖት ማምለክ ጉዳይ ብዙ ጊዜ ሲስባቸውና በዚህም እግዚአብሔር በተገለጠበት ሲቀስፋቸው ይታያል፡፡ ገና ከግብፅ እንደወጡ በሲና ተራራ ስር እያሉ ከመከራ ያወጣቸውን እግዚአብሔርን ረስተው በዚያን ውለታ ከእግዚአብሔር አውጥተው ለሙሴ ሰጥተው «ከግብፅ ምድር ያወጣን ሙሴ» አሉ እንጂ ««ከግብፅ ምድር ያወጣን እግዚአብሔር» አላሉም፡፡

ልክ በግብፅ ይደረግ እንደ ነበረው የጥጃ ምስል ሠርተው ለዚያ መስዋዕት በማቅረብና መስገድ ጀመሩ ፥ አመለኩትም፡፡ በግብፅ የበሬና የላም አምልኮ በተለይም ሜምፊስና ሂሊዮፓሊስ በሚባሉት ቦታዎች በጣም የተለመደ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት በመቅሠፍት ሦስት ሺህ ሰዎች ሞቱ፡፡ «ከእናንተ እያንዳንዱ የዓይኑን ርኩሰት ይጣል ፥ በግብፅም ጣዖታት አትርከሱ» ያለው ለዚህ ነበር፡፡ ሕዝ.20፥7፡፡ ሌላ ጊዜም በበለዓም ረቂቅ ምክር ተረፈ መሥዋዕተ ጣዖት ይዘው ከመጡት ከሞዓባውያን ሴቶች ጋር በመገናኘታቸው በዝሙት ከመውደቅ ጀምሮ ሞዓባውያንን ጣዖት ብዔል ፌጎርን እስከ ማምለክ ደረሱ፡፡ በዚህም ምክንያት ሃያ አራት ሺህ ሰዎች ተገደሉ፡፡ ዘኁ. 25፡፡

በአጠቃላይ ብዙውን ጊዜ የአይሁድ ጥፋትና ቅጣት ከአሕዛብ ጋር ሲደባለቅና ሲላመዱ የሚወርዷቸውና በሚማሯቸው መጥፎ አሕዛባዊ ልማዶች ምክንያት የሚደርስ ባቸው ነበር፡፡

## 2. ዲና

ዲና ያዕቆብ ከልያ የወለዳት ሴት ልጁ ናት፡፡ ያዕቆብ ከሶርያ በተመለሰ ጊዜ በከዓን ምድር በሴኬም ሰፈረ፡፡ ዲናም የሴኬማውያን ሴቶች ልጆችን በማየት ከቤቷ ወጣች፡፡ በዚያን ጊዜ የአገሩ አለቃ የኤሞር ልጅ ሴኬምን አያት፡፡ ወስዷትም ከእርስዋም ጋር ተኛ፡፡ አስነወራትም፡፡ ስምዖንና ሌዊ በተንኰል እንዲገረዙ ካዘዙአቸው በኋላ በ3ኛው ቀን ሄደው እኅታችንን አርክሰዋል በማለት በሴኬም ያሉትን ወንዶች ሁሉ ገደሉ፡፡ ኤሞርንና ሴኬምንም በሰይፍ ገደሉ ፥ ሀገራቸውንም ዘረፉ፡፡ በዚህም ያዕቆብ እጅግ ተጨነቀ፡፡ «በዚች ሀገር በሚኖሩ ሕዝቦች ዘንድ የተጠላሁ ታደርጉኝ ዘንድ እኔን አስጨነቃችሁኝ ፥ እኔ በቁጥር ጥቂት ነኝ፡፡ እነርሱ በእኔ ላይ ይሰበሰቡና ይመቱኛል፡፡ እኔም ከወገኔ ጋር እጠፋለሁ» አለ፡፡ ዘፍ.34፡፡

እንዲህም ስላደረጉ ያዕቆብ ሊሞት ሲል ልጆቹን ሰብስቦ የሚያገኛቸውን ሲናገር ስምዖንንና ሌዊን እንዲህ አላቸው፡፡ «ስምዖንና ሌዊ ወንድማማች ናቸው፤ ሰይፎቻቸው የዓመፃ መሣሪያ ናቸው፡፡ በምክራቸው ነፍሴ አትግባ፤ ከጉባኤያቸውም ጋር ክብሬ አትተባበር፤ በቁጣቸው ሰውን ገድለዋልና በገዛ ፈቃዳቸውም በሬን አስነክሰዋልና፡፡ ቁጣቸው ርጉም ይሁን ፥ ጽኑ ነበርና ኵርፋታቸውም ብርቱ ነበርና፤

በያዕቆብ እከፋፍላቸዋለሁ ፥ በእስራኤልም እበታትናቸዋለሁ፡፡ ዘፍ.49፥ 5–7፡፡

ይህ ሁሉ ነገር የደረሰው ዲና ከአሕዛብ ሴቶች ጋር በመደባለቋ ነው፡፡ ራሷ ዲና ከክብር የተዋረደችው፥ በዚህ ስምዖንና ሌዊ ደም ወደማፍሰስ የሄዱት፥ ያዕቆብም እስከመጨነቅ የደረሰው፥በኋላም ያዕቆብ በስምዖንና ሌዊ ላይ እንዲህ ያለ ርግማን የተናገረው ዲና ከማይመስሏት ጋር በመደመሯ ነው፡፡

## 3.ሰሎሞን

በአባቱ በዳዊት እግር የተተካው ሰሎሞን እግዚአብሔር ጥበብንና ሀብትን አሟልቶ የሰጠው ነበር፡፡ ሰሎሞን የፊቱን ወደ ኋላ እንዲሉ በመጀመሪያ ጥበብን በመለመኑ በእግዚአብሔር ዘንድ የተመሰገነ ፥ ቤተ መቅደሱን ግሩምና ውብ አድርጐ ሠራ ፥ በዚህ በቤተ መቅደሱ ምርቃት ዕለትም ባደረገው ጸሎት እግዚአብሔር ተገለጠለት ፥ ለቤተ መቅደሱና ለአሕዛብ ቃል ኪዳን ተቀበለ፡፡ ሆኖም ግን ወደ ኋላ ከአሕዛብ ሴቶች ጋር የማይገባ ግንኙነት በመጀመሩና ይህንንም እየገፋበት በመሄድ በዚሁ ምክንያት ለጣዖት እስከ መሠዋትና እስከ መስገድ ደርሷል፡፡ ቅዱስ መጽሐፍ የሰሎሞንን የኋላ ሁኔታ እንዲህ ይገልጸዋል፡፡ 1ነገ. 11፥ 1–8፡፡

ሰሎሞን እንዲህ ሁለት ጊዜ ከተገለጠለትና ቸርነቱን ሁሉ ካደረገለት ከእግዚአብሔር ልቡን ስላራቀ ከአምልኮቱ ስለወጣ እግዚአብሔር ሰሎሞንን ተቈጣ «እግዚአብሔርም ሰሎሞንን አለው ይህን ሠርተሃልና ፥ ያዘዝሁህንም ቃል ኪዳኔንና ሥርዓቴን አልጠበቅህምና መንግሥትህን ከአንተ ቀድጄ ለባሪያህ እሰጣዋለሁ፡፡

በሰሎሞን ኃጢአት ምክንያት የእሥራኤል መንግሥት ከሁለት ተከፈለ ፥ አሥሩ ነገድ በሰሜን ሰማርያን ከተማቸው ሊያደርጉ ሁለቱ ነገድ ደግሞ በደቡብ በኢየሩሳሌም ቀሩ፡፡ ወዲያውም እግዚአብሔር ከኤዶምያስ ነገሥታት ዘር የሆነውን ሃድን በሰሎሞን ላይ ጠላት አድርጐ አስነሣው፡፡ ባሪያው የነበረው ኢዮርብዓምም ዐመፀበት፡፡ በዘመኑ ሁሉ ከጦርነት አሳርፎ በሰላም የጠበቀውን አምላኩን በአሕዛብ ሴቶች ምክንያት በማሳዘኑ በውስጥ በአፍአ ጭንቀትና መከራ ከበበው፡፡ ሽምግልናው በሐዘን ተደመደመ፡፡ የዚህ ሁሉ ምክንያት ከማይመስሉት ጋር በማይመች አካሄድ መሄዱ ነው፡፡

## 4. የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች

ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የመጀመሪያውን መልእክት እንዲጽፍ ያደረጉት ከእነርሱ ዘንድ የተከሠቱ ብዙ ችግሮች ነበሩ ፥ ከእነዚህም አንድ ስለትንሣኤ ሥጋ የነበራቸው እምነት የደከመና ከዚያም አልፎ ወደ ስህተት ያዘነበለ መሆኑ ነበር፡፡ ከዚህም ጋር በተሰጣቸው ጸጋ በመታበይና እርስ በርስ በመቀናናት እኔ የጳውሎስ ነኝ ፥ እኔ የአጵሎስ ነኝ... ወዘተ እያሉ አንጃ ፈጥረው በቡድን ተከፋፍለው ነበር፡፡

ቆሮንቶስ በግሪክ የምትገኝ ከተማ ስትሆን ግሪክ ደግሞ የተለያዩ የፈላስፎችና የፍልስፍና ሃሳቦች መነሃሪያ ነበረች፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ የአቴና አርዮስፋጐስ በተባለው ቦታ ተገኝቶ ስለ ትንሣኤ በተናገረ ጊዜ በዚያ የነበሩ ፈላስፎች ይህንን «የሙታንን ትንሣኤ በሰሙ ጊዜ እኩሌቶቹ አፌዙበት ፥ እኩሌቶች ግን «ስለዚህ ነገር ሁለተኛ እንሰማሃለን» አሉት፡፡ እንዲሁም ጳውሎስ ከመካከላቸው ወጣ፡፡ የሐዋ.1፥17–32፡፡ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች እንዲህ በሙታን ትንሣኤ ትምህርትና እምነት ከማያምኑና ከሚያፌዙ የአቴና ፈላስፎች ጋር በመደመራቸው እነርሱም የክርስትና መሠረት የሆነውን ትንሣኤ ሙታንን እስከ መጠራጠር ደርሰዋል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ «እንደ ሰው በኤፌሶን ከአውሬ ጋር



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ከታገልሁ ሙታንስ የማይነሡ ከሆነ ምን ይጠቅመኛል? ነገ እንሞታለንና እንብላና እንጠጣ» ሲል የገለጸው ይህንን ነው:: 1ቆሮ.15÷32::

ኢፒኩሪያንስ (Epicureans) የተባሉት የፍልስፍና አስተሳሰብ አራማጆች የሰው ሕይወት ዓላማና ተግባር በዚህ ዓለም ማግኘት የሚገባውን ርካታና ደስታ (pleasure ) ማግኘት ነው ብለው ያስተምሩ ነበርና:: ይህ ሃሳብም አንዳንድ ምእመናን ዘንድ ሥርዋጽ ገብቶ የሚመጣውን ሕይወት ተስፋ ማድረግን ሳይሆን በዚህ ዓለም መብላትንና መጠጣትን ኃጢአት ማድረግን እንደቁም ነገር ወደመቆጠር እያመሩ ስለነበር ነው::

እርስበርስ መለያየታቸውም የእነዚህ ፈላስፎች እርሾ ውጤት ነበር:: እነርሱ ውዳሴ ከንቱን በመውደድና የራሳቸውን ቡድን (sect) ለይተው በዚያ ላይ መሥራችና መምህር ተብሎ ለመጠራት እርስ በርሳቸው አይስማሙ ነበር:: የአንዱን ሃሳብ ሌላው ይቃወመዋል ÷ አንዱ የገነባውን ሌላው ያፈርሰዋል ÷ ሁልጊዜ አዲስ ነገር መጨመርና መናገር ይወዱ ነበር:: «የአቴና ሰዎች ሁሉና በዚያ የኖሩ እንግዶች አዲስ ነገርን ከመናገርና ከመስማት በቀር በሌላ ጉዳይ አይውሉም ነበርና» የሐዋ.17÷21:: የፍልስፍናው ጐራ ተከታዮችና ተማሪዎችም በየመምሮቻቸውና መሥራቾቻቸው ይመኩ ነበር ÷ በእነርሱም ስም ይጠሩ ነበሩ፤

የቆሮንቶስ ምእመናንም ይህንን መጥፎ ልማድና አስተሳሰብ ወደራሳቸው አስገብተው አዳዲስ ሃሳቦችን ቅዱስ ጳውሎስ ባስተማራቸው ላይ ጨመሩ ÷ በዚህ የተነሣም ከመስመር ወጡ ÷ በዚያውም ላይ በፈላስፎችና በትምህርታቸው እንዲሁም በተከታዮቻቸው እንዳዩት ራሳቸውን በተለያዩ መምህራን ሥር በመከፋፈል እኔ የጳውሎስ ነኝ ÷ የአጵሎስ ነኝ ÷ እኔ የኬፋ ነኝ እያሉ ተከፋፈሉ:: 1ቆሮ.1÷11–12:: ለዚህ ነው «አትሳቱ፤ ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል» ሲል የገሠጻቸው:: 1ቆሮ.15÷33:: ይህንንና ሌሎቹን ስህተታቸውን ለማስተካከል ቅዱስ ጳወሎስ መልእክቱን ጻፈላቸው::

## 5. ያዕቆብ

የዐሥራ ሁለቱ ነገድ አባት የሆነ ያዕቆብ በሴኬም ሳለ እግዚአብሔር «ተነሥተህ ወደ ቤቴል ውጣ ÷ በዚያም ኑር ÷ ከወንድምህ ከዔሳው ፊት በሸሸህ ጊዜ ለተገለጠልህ ለእግዚአብሔርም መሠዊያን አድርግ::» ባለው ጊዜ እርሱ ደግሞ ለቤተሰቡና ከእርሱ ጋር ላሉት ሁሉ እንዲህ አለ:: «እንግዶቹን አማልክት ከመካከላችሁ አስወግዱ÷ ንጹሐንም ሁኑ ÷ ልብሳችሁንም ለውጡ ÷...» ከዚያም «በእጃቸው ያሉትን እንግዶች አማልክት ሁሉ በጆሮአቸውም ያሉትን ጉትቶች ለያዕቆብ ሰጡት፤ ያዕቆብም በሴኬም አጠገብ ካላቸው የአድባር ዛፍ በታች ቀበራቸው::

ይህ የሚያሳየው የያዕቆብ ቤተሰቦች በሴኬም ሲኖሩ የዚያን ሀገር ጣዖታትና የተለያዩ የአለባበስና የጌጥ ልማዶች ተምረውና ወደዚያው ልማድ ገብተው የነበረ መሆኑን ነው፤ «እንግዶች አማልክት» ያላቸው ለዚህ ነው:: ሰው ከአሕዛብ ጋር እየኖረና እየተደባለቀ የእርሱ አስተሳሰብ ÷ ባህልና ልማድ አያሰቡኝም አይማርኩኝም ማለት እንዲያው በከንቱ መኩራራት ወይም ራስን አለማወቅ ካልሆነ በስተቀር ቀላል ነገር አይደለም:: እሳት ውስጥ ገብቶ አልቃጠልም ÷ ውኃ ውስጥ ገብቶ አልርስም እንደማለት ያለ ነው:: ይህ ሊባል አይቻልም ለማለት ሳይሆን ከባድና አስቸጋሪ መሆኑን ለመግለጽ ነው::

## 6. ታላቁ ቅዱስ ጴጥሮስ

እንዲያ ሁሉም ቢክድህ እኔ አልክድህም እያለ ሲናገር እንዳልነበረ ሦስት ጊዜ ወደ መካድ ያደረሰው ከሰቃልያነ ክርስቶስ ጋር እሳት እየሞቀ አብሮ ስለነበር ነው:: ይሁዳ ምንም እንኳ በልቡ ክዳትና ተንኰሉ የነበረ ቢሆንም ይህንን ወደ ተግባር ለውጦ ክፉ ሃሳቡን ወደመፈጸም ያደረሰው ከጌታችን ጋር እየዋለ በድብቅ ዳግሞ ከጸሐፍትና ከፈሪሳውያን ጋር እየሄደ ይገናኝ ስለ ነበር ነው:: በዚህም በውስጡ የነበረውን ሃሳብ እንዲገፋበት እንዲፈጽመው በገንዘብ ገፋፉት::

በአጠቃላይ ከማይመስሉ ጋር በማይመችና በማይገባ አካሄድ መጠመድ በሂደት በመሸርሸር የራስን እያጡ የሌላውን ገንዘብ ማድረግን ÷ ከዚያም ሳያውቁት በኀሊና መማረክንና መነሣትን ያስከትላል:: ሌሎችን ከመምሰል አልፎ ወደ መሆን ያደርሳል:: ሽክላና ብረት ድስት ቢጋጩ የሚጐዳው ሸክላው ነው:: የከበረ ነገርን የያዘ ሰውም ብዙ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው እርሱ ነው:: ስለሆነም ከማይመስሉን ጋር የሚኖር ተገቢ ያልሆነ ግንኙነት እንዳን ሰናከል ጥንቃቄ ያስፈልጋል::

*በሚቀጥለው እትም ደግሞ ከማይመስሏቸው ጋር በጥበብና በአግባብ የኖሩትን እናያለን::*

*ይቆየን*

## ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ...

*[ከገጽ 30 የዞረ/*

*ሐመር፡- በአሁኑ ወቅት የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር መለያየት በተመለከተ በግዕከል ያለችው እናት ቤተ ክርስቲያኛና በአህጉሩ የሚኖሩ ምእመናን ምን ማድረግ ይኖርባቸዋል?*

*ቄስ ኃይለ ጊዮርጊስ፡-* በጃማይካ ከሚኖሩ ማኅበረ ካህናት /ቀሳውስትና ዲያቆናት/ ጋር በጉዳዩ ላይ ጉባኤ አድርገን ነበር:: በጉባኤው ላይ እኔ በግሌ የሰላም፣ ዕርቅና ስምምነት ጉባኤ እንደ ሚያስፈልገን ተናግሬአለሁ:: ዛሬም እናገራለሁ:: ሁሉም አባቶች በመካከላቸው ያለውን ልዩነት ለማስወገድ ተቀምጠው በመወያየት ቤተ ክርስቲያንን በአንድነት ማገልገል ይኖርባቸዋል:: በወቅቱ የነበሩ የበላይ አካላትም በጉዳዩ ላይ አምነውበት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እንደ ሚነጋገሩበት አሳብ ሰጥተዋል:: በርግጥ ጉዳዩ አሁን በምን ሁኔታ ላይ እንደ ሚገኝ አላውቅም:: ለቤተ ክርስቲያናችን ወቅታዊ ችግር ሁነኛ መፍትሔ ለማምጣት ብቸኛው መንገድ ተቀምጦ መወያየት ነው:: መለያየት ለቤተ ክርስቲያን የሚስማማ ቋንቋ አይደለም:: ያ አላስፈላጊ ጉዳይ በምእመናን መካከል እንዳይከሰት አባቶች ማስተማርና መጸለይ ይገባቸዋል እንጂ ራሳቸው የልዩነቱ መንገድ ጠራጊ መሆን የለባቸውም:: ስለ እውነት ይህች ቤተ ክርስቲያን እኛን በዝርወት ያለንንና በጭንቀት ላይ የነበርን ሕዝቦችን እየሰበሰበች ባለችበት ወቅት እንደዚህ ያለው ችግር በአባቶቻችን መካከል ሲከሰት ስናይ የበለጠ እንጨነቃለን:: ስለዚህ ስለ አንድነታችን መጸለይ ይኖርብናል::

*ሐመር፡- ቄስ ኃይለ ጊዮርጊስ÷ ስለ ሰጡን ቃለ ምልልስ በአንባብያን ስም ከልብ እናመሰግናለን::*

*ቄስ ኃይለ ጊዮርጊስ፡-* እኔም አመሰግናለሁ::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# አርባ ቁጥር እና ምሥጢሩ

⇒ *ለምን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ጾመ?*

*/ጌታቸው በቀለ/*

በቅዱስ መጽሐፍ ዓይነታዊና መጠናዊ፣ እማሬያዊና ፍካሬያዊ፣ ምሳሌያዊና ምሥጢራዊ ትርጉምና ትንታኔ ካላቸው ጭብጦች መካከል ቁጥሮች ይገኛሉ:: ይህ ጽሑፍ ቁጥ ሮች በቅዱስ መጽሐፍ ካላቸው በርካታ መግለጫዎች በመነሣት ለአብነት ያህል የተወሰኑትን ያብራራል፤ ዋነኛ ትኩረቱንም በአርባ ቁጥር ላይ በማድረግ ከተለያዩ ማዕዘናት ይዳስሳል::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የራሷ የሆነ ከሌላው ዓለም የተለየ የቁጥር አቆጣጠር አላት:: አሐዱ /፩/፣ ክልኤቱ /፪/፣ ሠለስቱ /፫/፣ አርባዕቱ /፬/.... እያለች ትቆጥራለች:: «ዜሮ» ለምንለው ቁጥርም «አልቦ» የሚል አገላለጽ አላት::

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እንደ ምንመለከተው ቁጥሮች የሰውን፣ የዘመንን፣ የብዛትን፣ የመጠንና የነገሮችን ሁኔታ ይገልጻሉ:: ይህም በተለይ በዮሐንስ የራእይ መጽሐፍ ላይ ይታያል:: በዕብራውያን ዘንድ ብዛት ሲገለጥ ቁጥሩ በፊደል እንጂ በአኀዝ ምልክት ብዙ ጊዜ አልተጻፈም:: ለአብነት ያህል የተወሰኑ ቁጥሮችን አገላለጽ በቅዱሳት መጻሕፍት እንመለከታለን::

አንድ:- የአንድነትና የብቸኝነት መግለጫ ነው:: «እስራኤል ሆይ÷ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው...::» ዘዳ.6÷4::

ሰባት:- ሱባኤ፣ በእስራኤል ዘንድ በሥራም በቃልም የሚገለጥ ፍጹም ቁጥር ነው:: «ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር አምላክህ ሰንበት ነው::» ዘጸ. 20÷10::

አርባ:- ወደ አዲስ ሁኔታ የመግቢያ ምልክት ቁጥር ነው:: የጥፋት ውኃ አርባ ቀን ዘነበ፤ ሙሴ በደብረ ሲና አርባ ቀን ቆየ፤ እስራኤል በምድረ በዳ አርባ ዓመት ኖሩ፤ ነቢያት አርባ ÷ አርባ ቀን ጾሙ፤ ጌታችን ለአርባ ቀን ጾመ፤ ጌታችን ከትንሣኤው በኋላ እስከ ዕርገቱ ድረስ ለአርባ ቀናት ቆየ::

ለመግቢያ ይሆነን ዘንድ የተወሰኑ ቁጥሮችን መግለጫ በአጭሩ ከተመለከትን በዋናኝነት ወደ ተነሣንበት ወደ ፵ ቁጥር እንመለሳለን፤ ለመሆኑ ፵ ቁጥር በመጽሐፍ ቅዱስና በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት መሠረት በምን በምን ሁኔታ ተጠቅሶ እንደ ሚገኝ ለመረዳት በአራት ሁኔታዎች ከፍለን ለመመልከት እንችላለን:: ይኸውም አርባ ቁጥር በተለያየ አገባቡ አኀዝን ብቻ ሳይሆን ሥርዓትን፣ የእግዚአብሔርን ፍትሕ፣ አዲስ ምዕራፍን /የሽግግር ክስተትን/ እና ፍጹምነትን ያሳያል::

## ሥ ር ዓ ት

- በዕብራውያን ሥርዓት ብዙዎቹ የጾምና የንስሐ ቀናት በአርባ የተወሰኑ ናቸው:: ብዙ ሰዎችም ለአርባ ቀንና ሌሊት ጾመዋል:: ዘጸ.24÷18፤ 1ኛነገ.19÷8::
- በዕብራውያን ዘንድ አንድ ሰው ወንጀለኛ ሆኖ ሲገኝ አርባ ጊዜ በጅራፍ እንዲገረፍ የሙሴ ሕግ ያዝዛል:: ከአርባ በላይ በግርፋት መቅጣት ግን ክልክል ነው:: ዘዳ.25÷2-3:: በዚህ ሕግ መሠረት ቅዱስ ጳውሎስ አርባ ጊዜ ተገርፏል:: 2ኛቆሮ.11÷24::
- ከመስከረም 26 እስከ ኅዳር 5 ያለው አንድ ወር ከዐሥር ቀን ወይም ፵ ቀን ወርኀ ጽጌ፣ ዘመነ ጽጌ ተብሎ ይጠራል:: በዚህ ወቅት በፈቃድ የሚጾመው ለአርባ ቀን ነው::

## ፍትሐ እግዚአብሔር

- በኖኅ ዘመን የነበሩ ሰዎች ለእግዚአብሔር ባለ መታዘዛቸው በንፍር ውኃ ተቀጥተዋል:: አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ዘንቧል:: ዘፍ. 7÷1::
- እስራኤላውያን በምድረ ግብፅ በባርነት ቀንበር ለ400 ዓመታት ተጨቁነዋል፣ ተገዝተዋል:: 400 ዓመት በ40 ሲቀመር ዐሥር ቀመር ወይም /10×40 = 400/ ይሆናል:: ዘፍ.15÷13::
- እስራኤላውያን ከምድረ ግብፅ ወደ ከነዓን ሲጓዙ አርባ ቀን መጓዝ የሚገባቸውን ከኃጢአታቸው የተነሣ አርባ ዓመት ተጉዘዋል::
- እግዚአብሔር በመዓቱ አንዱን ቀን አንድ ዓመት እንደሚያደርግ፣ በምሕረቱም ደግሞ አንዱን ዓመት እንደ አንድ ቀን በመቁጠር አርባውን ዓመት እንደ አርባ ቀን ያደርጋል:: ሕዝ.4÷6::
- አይሁድ ጌታችንን በሐሰት ወንጅለው በግፍ ቢገድሉትም ለዚህ ኃጢአታቸው ንስሐ እንዲገቡ የአርባ ዓመት ዕድሜ ተሰጥቷቸው ነበር:: /ድርሳነ ማኅየዊ ዘዓርብ/::
- የእስራኤል ልጆች ጣዖት በማምለካቸውና ከአሕዛብ ጋር ኃጢአትን በመሥራታቸው ንስሐ የሚገቡበት የአርባ ዓመት ዕድሜ ተሰጥቷቸው ነበር:: መሳ.3÷7-11::

## ምዕራፍ /ሽግግር/

- ታላቁ የቤተ ክርስቲያን አባት ቅዱስ አትናቴዎስ በመጽሐፈ ቅዳሴው «አቤቱ ሕፃንን ከአባቱ አብራክ ከፍለህ፣ በእናቱ ማኅፀን የምታ ሳድረው አንተ ነህ፣ በረቂቅ ሰፋ ድል/የእንግዴ ልጅ/ የምትጠቀልለው አንተ ነህ፣ የሕይወት እስትንፋስ የምትሰጠው አንተ ነህ፣ ከማኅፀን ታወጣዋለህ፣ ዐይኑንም ትከፍታለህ» በማለት በአርባ ቀኑ አካል አግኝቶ ነፍስን ዘርቶ ፍጹም ሰው እንደ ሚሆን ገልጿል:: /አትናቴዎስ ቁ.12-13/::
- ሊቀ ነቢያት ሙሴ በደብረ ሲና አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት ከጾመ በኋላ ዐሥርቱ ቃላትን /ሕገ ኦሪትን/ ከእግዚአብሔር ተቀብሏል:: ሙሴ አርባው ዕለት እስኪፈጸም ድረስ እህል አልበላም፤ ውኃም አልጠጣም:: ዘጸ.34÷28-31:: ዘዳ. 9÷9-10:: ሙሴ ከተራራው ሲወርድ ሕዝቡ የፊቱን ቁርበት ለማየት እስኪሳናቸው ድረስ ገጹ እንደ ፀሐይ ያበራ ነበር:: በመጾሙም ይህን አገኘ::
- በዘመነ ኦሪት ወንድ ልጅ በተወለደ በአርባ ቀኑ በወላጆቹ አማካይነት ወደ ቤተ መቅደስ ተወስዶ መሥዋዕት ይሠዋለት ነበር:: ዘሌ.12÷1-8::
- ሊቀ ነቢያት ሙሴ አርባ ዓመት በፈርኦን ቤት ኖሯል:: አርባ ዓመት ደግሞ በበግ እረኝነት ሌላ አርባ ዓመትም ሕዝበ እስራኤልን መርቷል::
- አዳም በልጅነት ክብሮ በመላእክት ታጅቦ በእስያ ክፍለ ዓለም ከምትገኘው ከምድረ ኤልዳ ወደ ገነት የገባው በተፈጠረ በአርባ ቀኑ ነው:: ኩፋሌ 4÷9::
- መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የኦሪቱን ሕግ መሠረት በማድረግ በተወለደ በአርባ ቀኑ ወደ ቤተ መቅደስ ተወስዶ መሥዋዕት ተሠውቶለታል::
- እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ወንድ ልጅ በተወለደ በአርባ ቀኑ ወደ ቤተ ክርስቲያን ወስደን አስጠምቀን ምሥጢረ ቁርባንን ተቀብሎ ወደ ቤቱ እንዲመለስ እናደርጋለን፤ አዳም በእግዚአብሔር የጸጋ ልጅነት ክብሮ በቅዱሳን መላእክት ታጅቦ በተፈጠረ በአርባ ቀኑ ወደ ገነት እንደ ገባም ወንዶች ሕፃናትም ወደ ቤተ ክርስቲያን በወላጆቻቸው እቅፍ ሄደው ተጠምቀው ከቅድስት ሥላሴ ልጅ ነትን፣ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ይቀበላሉ::
- ጌታችን ሞትን ድል አድርጐ በተነሣ በአርባ ቀኑ ዐረገ:: እስከ ዐረገበትም ቀን ድረስ ለደቀ መዛሙርቱ ለአርባ ቀናት ታይቷቸዋል:: ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ከተነሣ በኋላ ባሉት አርባ ቀናት ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ምሥጢር ነገራቸው:: የሐዋ.1÷1-3:: ዳግመኛም እኒህ ቀናት ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረቱባቸው ናቸው:: /መጽሐፈ ኪዳን/::





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

- ክርስቲያን በሞተበት በአርባኛው ቀኑ ቁርባን ይቆረብለታል:: እህል ውኃ ለካህናትና ችግረኞች ይሰጣል፤ ይኸውም ነፍሱ በቅድመ እግዚአብሔር ቀርባ ፍርድን የምትቀበልበት በመሆኑ ነው::

ጽናት/ፍጹምነት/

- ነቢዩ ኤልያስ ንጉሥ አክአብና ንግሥቲቱ ኤልዛቤል እግዚአብሔርን በመተው ጣዖት ሲያመልኩ በመመልከቱ በመንፈሳዊ ቅንዓት ተነሣሣ:: በጣዖት አገልጋዮችና በእርሱ መካከል እግዚአብሔር እንዲፈርድ ከአክአብ ተነጋግሮ በቅድሚያ የጣዖቱ አገልጋዮች መሥዋዕት አቅርበው የጣዖትን ስም ጠርተው ልመና አቀረቡ፤ ጩኸታቸው ከንቱ ሆነ:: በተራው ነቢዩ ኤልያስ መሥዋዕት አቀረበ:: እግዚአብሔርም ወደ ኤልያስና መሥዋዕቱ ተመለከተ:: እሳት ከሰማይ ወርዶ መሥዋዕቱን በላ:: የጣዖት አገልጋዮችንም ከወንዝ አስወርዶ አስፈጅቷቸዋል:: በዚህም ምክንያት ንግሥት ኤልዛቤል ነቢዩ ኤልያስን አሳደደችው፤ በመንገድም ሲጓዝ ደከመው:: ከክትክታ ዛፍ ጥላ ዐረፈ፣ አንቀላፍቶም ተኛ:: በዚያም መልአክ እግዚአብሔር መጥቶ ቀሰቀሰው:: ቢነቃ ከራስጌው እንጐቻ በአገልግል፣ ውኃ በመንቀል ተዘጋጅቶ አገኘ:: ያን ተመግቦ ተመልሶ ተኛ:: ዳግመኛም ቀሰቅሶ የምትሄድበት መንገድ ሩቅ ነውና ብላ ጠጣ አለው:: ያን ተመግቦ አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት ያለ ድካም እስከ እግዚአብሔር ተራራ እስከ ኮሬብ ሄደ:: 1ኛነገ.19÷6-10::

## ጾመ አርባ

ጌታችን ለምን አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት ጾመ? ምሥጢሩ ምንድን ነው?

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተጠመቀ በኋላ ፵ መዓልትና ሌሊት ከቆመ ሳያርፍ ከዘረጋ ሳያጥፍ የጾመው ጾም በመሆኑ ዐቢይ ጾም ተብሏል:: ማቴ.4÷1-10:: እኛም ጌታችን የጾመውን በማስታወስ በረከቱን ለማግኘት፣ በግብር እርሱን ለመምሰል ፈቃደ ሥጋችንን ለፈቃደ ነፍሳችን በማስገዛት እንጾመዋለን:: ጌታችን የጾመው አንድም በመብል የወደቀ አዳምን በጾም ሊክሥለት ዳግመኛም እቀደስ፣ እከብር ወይም እነጻ ብሎ ሳይሆን ለእኛ አርአያ ሊሆነን ነው::

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጾሙን አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ያደረገበትንም ምክንያት ሊቃውንቱ እንደሚከተለው ያትቱታል:-

1. ቀድሞ ነቢያት አርባ፣ አርባ ጾመዋል:: ከዚህ ቢያተርፍ አተረፈ÷ ቢያጐድል አጐደለ ብለው አይሁድ ድርጊቱን ማለትም ሕገ ወንጌልን ከመቀበል እንዳይከለክሉ፣ አርባ መዓልት አርባ ሌሊት ጾመ::
2. ነቢዩ ሙሴ በአርባ ዘመኑ ለዕብራዊው ረድቶ ግብፃውያን ገድሎ አሸዋ ውስጥ ቀብሮታል:: ሙሴ የጌታችን፣ ዕብራዊው የአዳም፣ ግብፃዊው የዲያብሎስ፣ አሸዋ የመስቀል የሦስቱ አርእስተ ኃጣውእ ምሳሌ ነውና:: ጌታችንም በወንጌሉ «እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ» እንዳለ /ማቴ.5÷17/ ምሳሌውን ለመፈጸም አርባ መዓልት አርባ ሌሊት ጾመ::
3. ሊቀ ነቢያት ሙሴ አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት ጾሞ ሕገ ኦሪትን ሠርቷል:: ጌታችንም ፵ መዓልት ፵ ሌሊት ጾሞ ሕገ ወንጌልን የሚሠራ ነውና:: አንድም ሙሴ አርባ ዘመን በምድያም ኑሮ እስራኤልን ከግብፅ ባርነት መርቶ አውጥቷቸዋል:: ጌታም አርባ መዓልት አርባ ሌሊት ጾሞ ነፍሳትን ከሲኦል የሚያወጣ ነውና አርባ መዓልት አርባ ሌሊት ጾመ::
4. ሕዝበ እስራኤል አርባ ዘመን በበረሃ /ገዳም/ ኖረው ምድረ ርስት ገብተዋል፤ ነቢዩ ኤልያስም አርባ ቀንና ሌሊት ጾሞ ዐርጓል:: እናንተም አርባ መዓልትና ሌሊት ብትጾሙ ገነት፣ መንግሥተ ሰማያት ትገባላችሁ ለማለት አርባ ቀን አርባ ሌሊት ጾመ::
5. ነቢዩ ሕዝቅኤል በፀጋማይ ጐኑ አርባ ቀን ተኝቶ ስድስት መቶ ሙታንን አሥነስቷል:: እናንተም አርባ ቀንና ሌሊት ብትጾሙ ትንሣኤ ዘለክብር ትነሣላችሁ ለማለት አርባ ቀንና ሌሊት ጾመ::
6. ዕዝራ አርባ መዓልትና ሌሊት ከምግብ ተከልክሎ መጻሕፍትን አጽፏል:: እነዚያ ቀን ሲጽፉ እየዋሉ ማታ ይመገባሉ:: እርሱ ግን ቀን ሲያጽፈው የሚውለውን ሌሊት ሲያስበው ያድር ነበር፤ እናንተም አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት ብትጾሙ ምሥጢር ይገለጥላችኋል ሲል ዓርባ መዓልትና ሌሊት ጾመ::
7. እባብ አካሉ የደገደገበት እንደ ሆነ አርባ ቀን ከምግብ ተከልክሎ ይሰነብታል:: በስቁረተ ዕፅ /በእንጨት ቀዳዳ/፣ በስቁረተ እብንም ቢሉ አልፎ ሲሄድ ተገፍፎ ይወድ ቅለታል፣ ይታደሳል:: እናንተም አርባ ቀንና ሌሊት ብትጾሙ «ተሐድሶተ ነፍስ» ታገኛላችሁ ሲል ምሳሌውን አውቆ አስመስሏል:: ምሳሌው ይህ ይሁን፣ ፍጻሜው እንደምን ነው ቢሉ:- «አዳም በአርባ ቀን ያገኘውን ልጅነት አስወስዶ ነበርና ለእርሱ እንደ ካሠ ለማጠየቅ፤ በአርባ ቀን ተስእሎተ መልክአ ለተፈጸመለት ሰው ሁሉ ሊክስ እንደ መጣ ለማጠየቅ፤ ለአራቱ ባሕርያት ዐሥር ዐሥሩን ለመካሥ አምስተኛ ባሕርየ ነፍስን የጨመሩ እንደ ሆነ ስምንት ስምንቱን ሊክስ እንደ መጣ ለማጠየቅ» ነው:: /ትርጓሜ ወንጌል ዘማቴዎስ/::

ጾመ አርባ በተለያዩ ስያሜዎች ይጠራል:- ጾመ ሁዳዴ፣ የድል ጾም፣ የመሸጋገሪያ ጾም፣ ጾመ አስተምህሮ በመባል ይታወቃል::

በዐቢይ ጾም ተድላ ደስታ ማድረግ አይገባም:: ይህ ወቅት ክርስቶስ ስለ ሰው ልጆች ሁሉ በተቀበለው መከራ የምናዝንበት፣ ከሰይጣንና ከፈቃደ ሥጋ ጋር የምንጋደልበት እኛ በበደልን እርሱ ክሶ እንዳዳነን በማዘከር ወደ ኃጢአት ላለመመለስ ቃል የምንገባበት፣ ለሌሎች ጊዜያት የነፍስንና የመንፈስን ስንቅ የምንይዝበትና ከተኩላ የምንጠነቀቅበት በመሆኑ በዓመቱ ውስጥ ከሚኖሩት ቀናት ሁሉ ልዩ ነው:: ስለዚህ ስንጾም በረከት፣ ዋጋ እንድናገኝ አስበን፣ ተስፋ አድርገን መሆን አለበት::

አርባ ቁጥርን መሠረት አድርገን ጾመ ዓርባን ተመልክተናል:: በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት ክርስቲያን የሆነ ሁሉ እንዲጾማቸው ጊዜና ወቅት ተወስኖላቸው የተደነገጉ ሰባት የዐዋጅ አጽዋማት አሉ:: ከእነዚህ ዋናው ጾመ አርባ ነው:: ሐዋርያት የጾሟቸው፣ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በቀኖና ያጸኗቸው፣ ዲድስቅልያ እና ሌሎች የቀኖና መጻሕፍት ሥርዓት የሠሩላቸው ናቸው::

አጽዋማት ከመጀመራቸው በፊት የሚደረገው ዝግጅት «ቅበላ» ይባላል:: ጾዋሚዎቹ ለረጅም ቀናት ከጥሉላት መባልዕት የሚታቀቡ ስለሆነ ረጅሙን ጾም ለመቀበል እንደ የአቅማቸው የጥሉላት ምግቦችን ከተመገቡ በኋላ፣ ጾሙ በሚጀመርበት ዕለት «ጾሙን ለመጀመር ያበቃኸን ፈጣሪያችን ለመፈጸምም አብቃን፤ ኃይልና ብርታትን ስጠን» በማለት ይጀምሩታል:: ጾመው ለመግደፍ እንዲያበቃቸው ራሳቸውን ለፈጣሪያቸው አሳልፈው ይሰጣሉ::

ወርኃ ጾሙ ሲፈጸም ደግሞ ጾሙ ተፈስከ፣ «ተገደፈ» ይባላል:: ምእመናን እንደ የዐቅማቸው ጾሙን በጥሉላት መባልዕት ይፈስካሉ:: የተቸገሩ ጐረቤቶቻቸውን፣ ነዳያንን... ያገድፋሉ:: በርግጥም የትንሣኤን በዓል ስናከብር ከመቃብር ባልተሻለ ኑሮ የሚኖሩትን፣ በኃጢአት ዓለም የታሰሩትን፣ በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ ተይዘው የሚማቅቁትን ወገኖቻችንን ልናስባቸው ይገባል:: የትንሣኤን ቁርሳችንንና ምሳችንን ከእነርሱ ጋር ብንመገብ ሞትን ድል አድርጎ የተነሣው ክርስቶስ ማዕዳችንን ይባርክልናል:: በትንሣኤውም በረከት እንባረካለን::

*አምላካችን መዋዕለ ጾሙን አስፈጽሞ ለብርሃነ ትንሣኤው በሰላም ያድርሰን::*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ክህነት ÷ ካህናተ ኢትዮጵያና ተልእኮአቸው በሰሜን አሜሪካ

## "This is America ... It's Member's Right"

*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዓለም ዐቀፋዊት ናት ሲባል በሐዋርያዊው እግሯ ገሥግሣ ያልደረሰችበት፣ ደርሳም «ሑሩ ወስብኩ ውስተ ኵሉ ዓለም ወስብኩ ወንጌለ ለኵሉ ፍጥረት ÷ ወደ ዓለም ሒዱ ወንጌልንም ለሰው ሁሉ አስተምሩ» /ማር. 16 ÷ 15/ የሚለውን አምላካዊ ትእዛዝ በማክበር ቃለ እግዚአብሔርን ሰብካለች:: ቀደም ሲል በነበሩት የቤተ ክርስቲያናችን አባቶች ደገኛ አመራር ቤተ ክርስቲያናችን ከደረሰችባቸው ክፍላተ አህጉራት አንዱ ሰሜን አሜሪካ ነው:: በዚህ ክፍለ አህጉር ቤተ ክርስቲያናችን ከደረሰችበት ጊዜ ጀምሮ አስተዳደራዊ መቅቅሯን ዘርግታ፣ ልዑካን አሰማርታ መንጋዋን ስትሰበስብና ስትጠብቅ ቆይታለች:: አሁንም በመጠበቅ ላይ ትገኛለች:: ይሁንና ይህ በወርቃማ ቀለም ሲጻፍ የነበረው በአካባቢው የቤተ ክርስቲያናችን እንቅስቃሴ ዛሬ ሆን ተብሎም ሆነ ባለ ማወቅ በሚፈጠሩ ስሕተቶች ሊወይብ ሲዳዳው ይታያል:: ለዚህ ከሚጠቀሱት ምክንያቶች ውስጥ ደግሞ አንዱ ይህ ዛሬ በርዕስነት ያነሳነው ጉዳይ ነው:: የካህናትና የክህነት አገልግሎት ችግሮች::*

*ዲያቆን ዳንኤል ክብረት በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ማስተባበሪያ ክፍል ሐላፊ ለአገልግሎት ወደ ሰሜን አሜሪካ ተመላልሰዋል:: በአገልግሎት ጉዞአቸውም ከካህናትና ምእመናን ጋር ባደረጓቸው ውይይቶችና ከተመለ ከቷቸው አንዳንድ ክስተቶች በመነሣት ለዛሬ ባነሳነው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ሐ ሳብ እንዲያካፍሉን አድርገናል:: ዲያቆን ዳንኤልን ላካፈሉን ሁሉ እያመ ሰገንን አንባብያን ጽሑፉን አንብባችሁ ለችግሩ መቀረፍ የምትችሁን አስተዋ ጽኦ እንድታደርጉ አደራ እንላለን::*

### አስተዳደራዊ መዋቅር

በሰሜን አሜሪካ ያለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአገልግሎትና የአስተዳደር መዋቅር ሁለት መልኮች ያሉት ነው:: በአንድ በኩል በማዕከል በምትገኘው እናት ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ሥር የሚገኙ አሉ:: ይሁን እንጂ እነዚህ ራሳቸው ሦስት ገጽታዎች አሏቸው:: እንደ አንድ ሀገረ ስብከት በሊቀ ጳጳሱ ትእዛዝ ሥር ያሉ አሉ፣ በሊቀ ጳጳሱ የማይታዘዙ ነገር ግን በማዕከል ከምትገኘው እናት ቤተ ክርስቲያን ሥር ነን የሚሉ አሉ፣ በሊቀ ጳጳሱ ትእዛዝ ሥር ነን እያሉ ነገር ግን ራሳቸውን በቦርድ የሚያስተዳድሩ አሉ:: ብዙዎቹ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሀገረ ስብከት ጋር ያላቸው ግንኙነት የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ንና የሀገረ ስብከቱን ሊቀ ጳጳስ ስም በቅዳሴ ላይ ከመጥራት የማያልፍ ነው::

ሁለተኛው ደግሞ በማዕከል ከምትገኘው እናት ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የተለዩት ናቸው:: እነዚህ በራሳቸው በመካከላቸው ክፍፍል አለ:: በሰሜን አሜሪካ በተቋቋመው ሐሰተኛ «ሲኖዶስ» ሥር ነን የሚሉ አሉ፣ ይሁንና በዚያ የሚገኙትን 4ኛውን ፓትርያርክ ስም ከመጥራት የማያልፉ አሉ፣ በቀጥታ እዚያ በሚገኙት ሊቃነ ጳጳሳት የሚታዘዙ አሉ፣ እኛ ከማንም አይደለንም ብለው በገለልተኝነት የሚገኙ አሉ:: በገለልተኝነት ያለን ነን ቢሉም በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ በሰሜን አሜሪካ ተቋቋሚል ከሚባለው «ሲኖዶስ» ጋር የሚወግ ኑም አሉ::

ያም ኾነ ይህ የተዘረዘሩት የአስተዳደርና የአገልግሎት መዋቅሮች ሁሉ የሚጋሩት ነገር አላቸው:: በመጀመሪያ ደረጃ የአብያተ ክርስቲያናት ምሥረታና አወቃቀር ለትርፍ ያልቆሙ ድርጅቶች እንደ ሚባሉት ዓይነት ነው:: ለትርፍ ያልቆሙ ድርጅቶች ሲመሠረቱ ሊኖራቸው የሚገባው እንደ ጠቅላላ ጉባኤ፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ፣ ሥራ አስፈፃሚ ቦርድ፣ ተቀጣሪ ሠራተኞች የሚኗቸውን አስተዳደራዊ መዋቅሮች የያዙ ናቸው:: ሌላው በጣም አስደናቂ ነገር በብዙዎቹ ደንብ ላይ «ይህ ቤተ ክርስቲያን ቢፈርስ ገንዘቡ ለአሜሪካን መንግሥት ወይም ለበጎ አድራጊዎች ይከፋፈ ላል» ነው የሚለው:: ለወደፊቱ እንኳን ከእናት ቤተ ክርስቲያን ጋር አንድ ለመኾን በማያመች መንገድ ነው ብዙዎቹ መመሪያዎች የወጡ ት:: ከጠቅላላ ጉባኤው በላይ ሥልጣን ያለው ሌላ የበላይ አካል የለም::

### የካህናቱ ቦታ በመዋቅሩ

የካህናቱ ደረጃ «ተቀጣሪዎች» ከሚባሉት ጋር ነው:: ለትርፍ ባልቆሙ ድርጅቶች መመሪያ መሠረት ተቀጣሪ ሰው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል መኾን አይችልም:: ከዚህ አኳያ ካህናቱ ከላይ ተወስኖ የሚመጣላቸውን መመሪያ ከመፈፀም ያለፈ ምንም ዓይነት ሥልጣን የላቸውም::

በአንዳንድ ቦታዎች ካህናቱ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎች ናቸው ቢባልም የክህነት ጉዳዮችን ብቻ ካልሆነ አስተዳደራዊ ጉዳዮች አይመለከታቸውም:: በእርግጥ በካህናቱ ጥንካሬ አማካይነት ካህናት የሚያስተዳድሯቸው ጥቂት አብያተ ክርስቲያናት የሉም ለማለት ባይቻልም በብዛት ከላይ በተጠቀሰው አስተዳደራዊ መዋቅር መሠረት ነው የሚከናወነው::

በሁለተኛ ደረጃ ብዙዎች አብያተ ክርስቲያናት የሚጋሩት ካህናቱ ድምፅ የሌላቸው መኾናቸው ነው:: ምንም ዓይነት ድምፅ የላቸውም:: በእርግጥ መመሪያው አንዳንድ ቦታ «ካህናቱ በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ሥልጣን አላቸው» ይላል:: ይሁንና መንፈሳዊ እና አስተዳደራዊ በሚሉት ነገሮች መካከል ያለው ድንበር አይታወቅም:: በአንድ ወቅት አንዲት ምእመን ልጅዋን ክርስትና ለማስነሣት ትፈልጋለች:: ካህናቱ ግን ወላጂቱ /ሴትዮዋ/ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ምእመን እንዳልኾነች ያውቃሉ:: ሌላውም ምእመን ይህን ያውቃል:: ሴትዮዋ የልጅዋን የጥምቀት ክርስትና የምስክር ወረቀት የፈለገችበት ምክንያት አላት ነው የሚባለው:: ካህናቱ ስለ እርሷ ካላቸው መረጃ በመነሣት፡- «በሃይማኖት አትመስይንም፣ ንስሐ አባትም የለሽም» አሏት:: ሴትዮዋ በቀጥታ ለቦርድ ክስዋን አቀረበች:: ቦርዱም «የቤተ ክርስቲያኑ አባል ሁኚ፤ ከዚያ በኋላ መብትሽ ነው፤ ይፈቀድልሻል::» አላት:: እርስዋም አባል ኾነች፤ ተመዘገበች:: ከዚያን ጊዜ ወዲህ ግን የነበረችበትን ሃይማኖት ባትቀይርም ባለ መብት ናት:: የአባልነት ደብተር ተሰጥቷታል፤ በአባልነት መብቷ (Membership Right) መሠረት ክርስትና የማስነሣት፣ ፍትሐት የማግኘት ወዘተ. መብት አላት:: ይህ የአባልነት መብቴ ተነፈገኝ ብላ ፍርድ ቤት ብትከስ የቤተ ክርስቲያኑን የአገልግሎት ፈቃድ (Service License) ታስነጥቃለች:: ስለዚህም ልጅዋን በማስጠመቅ የጥምቀት ክርስትና ካርድ ወስዳለች:: ይህ እንግዲህ መንፈሳዊ ወይስ ሃይማኖታዊ ውሳኔን ነው የሚጠይቀው? እዚህ ላይ ከባዱ ነገር የምእመኑ መብት መከበሩ ሳይሆን የምእመኑ መብት ዳርቻ የሌለውና የካህናቱንም መብት የሚጋፋ መሆኑ ነው:: ከካህናቱ ደገኛ መንፈሳዊ ሥልጣን የጠቅላላ ጉባኤው፣ /አባላቱና ሕዝቡ/ ቦርዱ፣ የሥራ አስፈፃሚው እንደ ሚበልጥ ይህ ዓይነተኛ ማሳያ ነው:: ካህናቱ ከቅዳሴና ከውዳሴ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በቀር ሌላ ተግባር ውስጥ አይገቡም::
ይህ ቤተ ክርስቲያኒቱ መንፈሳዊ አቅ
ጣጫዋን ተከትላ እንዳትሄድ ያደር
ጋታል:: ሕዝቡም ካህኑ የሚለውን
ከመስማት ይልቅ ራሱን የበላይ አድ
ርጎ የማየት ሁኔታ አለ:: በፍትሐ
ነገሥት ያለው ቀኖና ቤተ ክርስቲያን
«እንዲህ አይልም» ስትላቸው «የለም
የእኛ ሕገ ማኅበርና መተዳደሪያ ደንብ
እንዲህ አይልም» ይሉሃል:: ለእነርሱ
ገዢው ሕግ የቤተ ክርስቲያኑ መመሥ
ረቻ ሕግ ነው:: በቤተ ክርስቲያን
አስተዳደር ትልቁን ችግር እየፈጠረ
ያለውም ይኸ ነው::

## የክህነት አገልግሎትና የካህናት ፈተናዎች

አሜሪካ ፍጹም ጠንካራ የሆኑ
ካህናት ያሉባት ሀገር ናት፤ፈተናውን
ታግሠው፣ያሩን ተቋቁመው፣የክህነቱን
አገልግሎት አክብረው የሚኖሩ አሉ::
አንዳንድ ካህናት በእውነት ከልባቸው
እግዚአብሔርን ለማገልገል የሚተጉ
ናቸው:: በዐቅማቸው ሰዓታቱን ቆመ
ው፣ ሌሎችን አስተባብረው ማኅሌቱን
አድምቀው፣የቅዳሴ ሥርዓቱን ሳያዛ
ንፉ ጠብቀው የሚኖሩ፣ለሕዝቡ የሃይ
ማኖት ተስፋ የሚሆኑ አሉ:: በዚያ
ድብልቅልቅ ዓለም ሱባኤ የሚይዙ፣ሕ
ፃናትን የሚያስተምሩ፣ወጣቶች በእም
ነት እንዲተጉ የሚመክሩ ጽኑዓን ካህ
ናት አሉ በአሜሪካ:: እዚያ ያለው ሕ
ዝብ ተስፋ ሳይቆርጥ ማንነቱንም ጠ
ብቆ እንዲኖር ያደረጉት የነርሱ
መኖር ነው::

በአሜሪካ የሚፈጸመው ነገር
ከልብ የሚየሳዝናቸው:: ጸሎታቸው
ለኢትዮጵያም ለአሜሪካም የሚተርፍ
ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ጠብቀው፣
ክህነታቸውን አክብረው የሚያገለ
ግሉ ጠንካራና ብቁ ካህናትም አሉ
በአሜሪካ:: እግዚአብሔር ይጠብቃቸው
ብቻ::

በሌላ በኩል ደግሞ ፈተናም
አለ::

ችግሩ የሚጀምረው ካህናቱ ከዚ
ህ ወደ አሜሪካ ሲሄዱ እዚያ ስላለው
አጠቃላይ ሁኔታ ትክክለኛው መረጃ
ባለመያዛቸው ነው:: ብዙ ጊዜ
የሚሄዱት በጠቅላይ ቤተ ክህነት
መዋቅር አይደለም:: በሚያውቋቸውና
በሚቀርቧቸው ዘመዶቻቸው የግብዣ
ጥሪ (Invitation) አማካይነት ነው
የሚሄዱት:: በአንድ አጥቢያ ቤተ
ክርስቲያንም ካህናት በሚፈለጉበት
ወቅት ቦርዱ «ካህናትን መቅጠር እን
ፈልጋለንና የምታውቋቸውን ካህ
ናት ጠቁሙን» ይልና ለሁሉም ቅፆ
ችን ያድላል:: በቅጹ ላይ በሰፈረው
የካህናቱ መረጃ ላይ በመመርኮዝ
ውድድር ይደረጋል:: አሸናፊ ኾነው
የተመረጡት ካህን ጥሪ (Invitation)
ይደርሳቸዋል:: እንግዲህ እኚህ ካህን
ከቀድሞውኑም አስበውትም
ይሁን ሳያስቡት እዚያ ሲሄዱ ከኢ
ትዮጵያና ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን
ቋንቋ፣ ባሕል፣ ሥርዓትና ትምህርት
አኳያ በአሜሪካ የቋንቋ አለመቻልና ባሕ
ል ልዩነት ችግር ይገጥማቸዋል::

በአሜሪካ ባለው የኢትዮጵያ
ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ከቀሳውስት
ካህናት ይልቅ መነኮሳት ካህናት ናቸው
የሚበዙት:: ምክንያቱም ቀሳውስቱን ከነ
ቤተሰባቸው /ሚስትና ልጆቻቸው/ ጋር
ለማምጣት ሂደቱም ኾነ የኑሮው ወጪ
ስለ ሚከብድ ነው:: በአንጻሩ ደግሞ
መነኮሳቱ ብቸኞች ናቸው:: እነዚህ መነ
ኮሳት በብዛት የሚመጡት ከገዳማት
ነው:: ስላለው አጠቃላይ የቋንቋና የኑሮ
ይትበሃል ሂደት ግንዛቤ ሳያገኙ ይሄ
ዳሉ:: በዚህ ዓይነት ከሄዱም በኋላ
የሚቀበሏቸው ሰዎች መነኮሳቱ ከሌሎች
ሰዎች ጋር በመተዋወቅ ስለ መብትና
ግዴታቸው ዐውቀው ይህ ቀረብኝ፣ ይህ
ጎደለብኝ እንዳይሉ «እነ እገሌን ብቻ
ቅረቡ፣ እነ እገሌን አትቅረቡ» እያሉ
የተሳሳተ ምክርና መመሪያ ስለሚሰ
ጧቸው በቅንነት ሊረዷቸው የሚችሏ
ቸውን ሰዎች ሁሉ እንዳይቀበሉ ያደርጓ
ቸዋል:: በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ በቀ
ደመ ሥርዓታቸውና እምነታቸው ጸን
ተው፣ኦርቶዶክሳዊ ሕይወታቸውን ጠብ
ቀው ለመኖር የሚተጉትን ካህናት
የአሜሪካ የተሐድሶ መንፈስ የነካቸው
ሰዎች «ጾም ኢትዮጵያ ቀረ፣ እዚህ
አገር የጾም ምግብ በቀላሉ አያገኙም፣
ስለዚህ አርፈው ያገኙትን ይብሉ» እያሉ
ከጾም ሊያዘናጓቸው የሚሞክሩ አሉ::
በዋናነት የተፈለጉበት የቅዳሴ፣ የውዳሴ
አገልግሎት የሚከናወነው በእሑድ ሰን
በት ብቻ ነው፤ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ
አገልግሎት የለም::ከጠዋት እስከ ማታ፣
ከሰኞ እስከ ሰኞ ያለ ዕረፍት ማገልገል
የለመደ ሕይወት እንዴት እንደሚፈተን
አስቡ:: እንዲህ እንዲህ እያሉ ኑሯቸውን
ሲገፉ፣ ትርጉም አልባው ምቾት እየ
ጨመረ ፈተናውም በዚያው ልክ እያየለ
ይመጣል:: አንድ አጥቢያ ይዘው በኣት
አጽንተው፣ እውነተኛ አገልግሎታቸውን
የሚያከናውኑት ካህናት የሕዝቡን መንፈ
ሳዊ ሕይወት መማረክ ሲጀምሩና ሕዝ
ቡም አጥቶት የነበረውን የሀገር ቤት ዓ
ይነት አገልግሎት ማግኘት ሲጀምር
በሁኔታው የተናደዱ የተሐድሶ መንፈስ
የተጠናዎታቸው ቢጽ ሐሳውያን «እኔ
እኮ ይህን ያህል ዶላር ነው የሚከፈለኝ፣
አንተ ስንት ነው የሚከፈልህ? ጨቁ
ነውኻል ማለት ነው፣ ለምን ወደ እኛ
አካባቢ አትመጣም? እኛ እኮ የካህን
እጥረት አለብን» እያሉ ለእነርሱ ያዘኑ
መስለው ያሰናክሏቸዋል:: ይህም ካህናቱ
ስሜታቸው መንፈሳዊ መኾኑ ይቀርና
ስለ ሚከፈላቸው ደመወዝ ብቻ እንዲ
ያስቡ ለማድረግ ነው::

ሌላው ካህናቱን የሚያዳክመው
ነገር «እዚህ ከመጣችሁ ላይቀር ቋንቋ
አጥኑ» የሚባለው ምክር ነው:: በመ
ሠረቱ ምክሩ በራሱ ጥሩ ነው:: የ[illegible]
ከፈላቸው ደመወዝ ግን ወደ ጥ[illegible]
ት/ቤት ለመግባት አያስችላቸውም[illegible]
ስለዚህ በዝቅተኛ ክፍያ ወደሚማሩበ[illegible]
ዝቅተኛ ትምህርት ቤት ይገባሉ:: እ[illegible]
ያ የሚያገኟቸው ደግሞ ከአካባቢያቸው[illegible]
የአነዋወር ሕግጋት ወጣ ያሉ፣ በ[illegible]
ተው ጠጥተው ሥጋቸውን ብቻ ማስ[illegible]
ሰት የሚወዱ፣ ያስደስተናል ያሉት[illegible]
ነገር ሁሉ ለማድረግ ወደ ኋላ የማይ[illegible]
ናቸው:: ግብረ ገብነት /ሞራል/ የላ[illegible]
ውም፣ ግድ የለሾች ናቸው:: እንኳን መ[illegible]
ኩሴ ጥሩ ካህን አይተው አያዉቁም::

አስተን ያሉ አንድ አባ[illegible]
የነገሩኝን አስታውሳለሁ:: «በጋንግስ[illegible]
ሮች ት/ቤት ስማር» አሉ ፥ «ሴቶች[illegible]
ይመጡና የሴት ጓደኛ (Girl frienc[illegible]
የለኽም ወይ?» ይሉኛል:: «እኔ መ[illegible]
ኩሴ ስለሆንኩ በእኛ ዘንድ እንዲ[illegible]
የሚባል ነገር የለም እላቸዋለሁ[illegible]
ቀጥለው ደግሞ «ለምን እንደንስም?[illegible]
ይሉኛል::» ኔበር ያሉኝ:: እንግዲ[illegible]
የእኛ አባቶች ዋጋውም አነስተኛ[illegible]
በመሆኑ ከእኒህ ዓይነቶቹ ጋር ነው[illegible]
የቋንቋ ትምህርቱን የሚማሩት[illegible]
ይህንም በቀን ለስድስትና ለሰባት ሰ[illegible]
ታት ያህል ይማራሉ:: የነዚያን ተ[illegible]
ማሪዎች ፈተና ተቋቁመው መማ[illegible]
ያለባቸውን ብቻ ተምረው ፣ለቤተ[illegible]
ክርስቲያንም ለሀገርም የሚበቃ ዕው[illegible]
ቀት ያተረፉና ዛሬም ወደ ሀገር ቤት[illegible]
ተመልሰው እያገለገሉ ያሉ ጠንካ[illegible]
አበው አሉ:: በሌላ በኩል ደግ[illegible]
በቆይታቸው መጠን የሰዎቹ አጉል[illegible]
አኳኋን ተጽዕኖ ያሳደረባቸውና:: እ[illegible]
ቆዩ በሄዱ መጠን ለነገሮች ትኩረት [illegible]
ማይሰጡ፣ ንዝህላል፣ግድ የለሽ ያደረ[illegible]
ቸውም አሉ::

ምንም እንኳን ሁሉንም ይወ[illegible]
ላል ባይባልም አልፎ አልፎ ቅድ[illegible]
ካልኩት የወር ገቢ በተጨማሪ በራ[illegible]
ሳቸው በመነኮሳቱ መካከል የሚፈጠሩ
ችግሮች አሉ:: ይኸውም ቤተ
ክርስቲያንን በሃይማኖት እናድሳለን
ብለው የተነሡት ሰዎች ሥልጣኔ
ማለት ፕሮቴስታንቲዝም ስለሚመስ[illegible]
ላቸው እነዚህን ጠንካራ አባቶች ሀገሩ
አሜሪካ እንደ መሆኑ ንቃትና ሥል
ጣኔ እንደ ሚገባ በተደጋጋሚ ይመክ[illegible]
ሯቸዋል:: «እንቺ እኮ ገና ጥሬ ነሽ፣
የዋልድባና የደብረ ሊባኖስ አባዜ ገና
አልለቀቀሽም፣ እዚያው እንዳለሽ ነሽ»
የሚል ዓይነት ሾኔ ይናገሯቸዋል::
ይህ ዓይነቱ ምክር አባቶች መሠረ[illegible]
ታቸውን እየለቀቁ፣ ሀገር ቤት በጠ
ባቂነትና አስጠባቂነት ይታገሉለት የነ
በረውን ሥርዓት እንዲረሱት ለማድ
ረግ ነው::

ከዋልድባ ሄደው ካሊፎርኒያ
የሚኖሩ አንድ አባት ሲያጫውቱኝ፡
- «ድሮ ዋልድባ እያለን በስምንተኛው
ሺ በአንድ ካህን ይቀደሳል እየተባለ
ይነገር ነበር:: እኛም ስንጸልይ ከዚያ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ዘመን አታድርሰን እንል ነበር፣ አሁን ግን ሁሉ ቀርቶ ራሳችን እያደረግን እየነው» አሉኝ::

ቀደም ሰል በገለጹኩት የቅድሚያ መረጃ ማጣት፣ የትምህርትና የሥልጠና ማጣት የተነሣ ካህናቱ ለብዙ ነገር አዲስ ናቸው:: እንዲያውም ሥልጣኔ ማለት ፕሮቴስታንቲዝም የሚመስላቸው ሰዎች ምነው እንዲህ ኾናችሁ ሲባሉ «This is America!» ኢትዮጵያ ብንኾን እንዲህ አናደርግም፤ አንሆንም» ነው መልሳቸው:: ከዚህ ሲሄዱ የሚቀበሏቸውም ሰዎች «ይህ አሜሪካ ነው፤ ሕዝቡ ይደክመዋልና ቅዳሴ እንዳያስረዝሙ፤ ሕዝቡ አይቀበልም» ይሏቸዋል:: ከቅዳሴ በኋላ ሠርሆተ ሕዝብ ሲደረግ ቀድሶ ያቀረበውን ካህን እጅ ልትሳለም የምትችለው በጥቂት አብያተ ክርስቲያናት ነው:: ብዙዎቹ መስቀል ነው የሚያሳልሙት:: ለምንድን ነው? ሲባል ሕዝቡ አይፈልግም ይሉሃል:: ግን እዚህ ሳለ የከተማውንም ኾነ የገጠሩን ካህን እጅ ሲስም፣ ሲሳለም የኖረ ሕዝብ ነው እዚያም ያለው:: የጠበል መጠጫ ዕቃ፣ ደሙን የምንቀበልበት ዕርፈ መስቀል ለምን ለእያንዳንዳችን አይዘጋጅም የሚሉ ቅምጥሎች አሉ፤ ለምንድን ነው? ስትሏቸው:- «ኢትዮጵያ ውስጥ ችግር ስለሆነ ነው፤ «This is America!» ይሉሃል:: ይህ የሁሉ ነገር ማሳበቢያቸው ነው::»

«ቀኖና ሊሻሻል ይችላል» በሚል ስም ቤተ ክርስቲያን ላይ የተዘመተው አሁን ነው፤ በፊት የነበረው ፈሊጥ ግን «ይህ አሜሪካ ነው፤ አይቻልም» የሚለው ነበር:: ያለ ቁርባን ተክሊል ማድረግ የተለመደ ነው፤ ሙሽሮቹ ቅዳሴ ሲያልቅ ወይም አምስት፣ ስድስት፣ ሰባት ሰዓት መጥተው ተክሊል አድርገው ይሄዳሉ:: ለምን? ሲባል «ይህ የአባላት መብት ነው፣ እንዳለው ባንፈጽምለት ሕዝቡ ይርቃል፤ ይልቁንስ ማቅረብ ያስፈልጋል ይባላል::

## እዚያው የሚሾሙ ካህናትና ፈተናቸው

በመሠረቱ በአሜሪካ ወጣቱ ትውልድ ተምሮ ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ፍላጎት አለው:: ነገር ግን ፈተናዎች አሉበት:: በእዚያው አገር ክህነት የሚቀበሉ ሰዎችን በተመለከተ ሁለት ዋነኛ ፈተናዎች አያለሁ:: የመጀመሪያው ብዙዎቹ ወደ እዚህ መጥተው ወይም ገና ሳይሄዱ መሠረታዊ ትምህርት ተምረው ካልሄዱ በቀር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲዘምሩ፣ ጠበል ሲቀዱ፣ ጥላ ሲይዙ ታይተው በዚያው ዲያቆን እንዲሆኑ ይደረጋል:: አንድ ጊዜ አትላንታ ውስጥ ቆሜ ሳስቀድስ የአገሩ ተወላጅ ነው የተባለ አፄድ ልጅ «አሐዱ» ሲባል ጀምሮ ጥላ ይዞ ፊቱን ወደ ቤተ መቅደሱ መልሶ እንደ ቆመ ቅዳሴው አለቀ:: በዚህ ዓይነት ሁኔታ እንግዲህ ስንቱን ነገር ይለምደዋል:: ጊዜ ወስዶ መሠረታዊውን ትምህርት የሚያስተምረው ሰው አያገኝም:: በቂ ዕውቀት አይኖረውም:: የብዙዎቹ ልጆች ፈተና ይኸው ነው:: በሌላ በኩል ለልጆቹ አርአያ የሚኾናቸው ሰው አያገኙም:: በአገር ቤትም ቢሆን ወደ ገዳም ስትሄድ፣ ወደ ታላላቅ አድባራት ስትገዝ፣ ደገኛ አባቶችን ስታገኝ ነባሩን ትምህርትና ሥርዓት እያየህ ትማራለህ:: በአሜሪካ ላሉት ልጆች ግን ትክክለኛውን ነገር እዚያው የሚያዩበት አጋጣሚ ጥቂት ነው:: በአገር ቤት ያለችውን እናት ቤተ ክርስቲያን የሚያውቁበት የሚያመዛዝኑበት ብዙ እድል አይኖራቸውም::

በአንዳንድ ቦታዎች ከግብፃውያኑ ጋር እየዋሉ፣ እያደሩ ተምረው በእነርሱ የተሾሙ ዲያቆናት ካህናት አሉ:: ምንም ትምህርታችንና ሥርዓታችንን አንድ ክህነቱም ትክክለኛ ቢሆን ሕይወቱ ግን ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተለየ ስለሚኾን ቤተ ክርስቲያናችንን ሳያውቁ ማገልገል ምንኛ ይከብዳል::

## ክህነት አልባ ካህናት

በአሜሪካ ሌላው የክህነት አገልግሎት አደጋ ክህነት ሳይኖራቸው ካህናት ነን የሚሉ ሰዎች ናቸው:: አሁን አንተ ብትሄድ በአገር ቤት አብረሃቸው ሳለህ መቼ ክህነት እንደ ተቀበሉ የማታውቃቸዉ ሰዎች «ክህነት አለን» ብቻ አይደለም «መነኩሴ ነን» ሲሉ ታገኛቸዋለህ:: መታወቂያውን ከየት እንዳሠሩት አይታወቅም:: ካህን በአሜሪካን አገር ክቡር እና ውድ ነው:: በተለይ የአሜሪካ መንግሥት እ.ኤ.አ. መስከረም 11 2001 በኒውዮርክ የንግድ ማዕከል ሕንፃዎች ላይ ከደረሰው አደጋ ወዲህ የኑዋሪዎቹን ሥነ ልቡና ይጠብቁለት ዘንድ ለሃይማኖት ተቋማትና አባቶች በገንዘብ ርዳታም ሆነ ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞችን በመስጠት ትኩረት ሰጥቷል:: ከእነዚህ ጥቅማ ጥቅሞች ውስጥ R1 የተባለ በየሦስት ዓመቱ የሚታደስ ቪዛ ለካህናት መስጠት ነው:: ይህንን ቪዛ ያገኘ ካህን ለሁለት ጊዜ እያሳደሰ ከተጠቀመ በኋላ በሦስተኛው የመኖሪያ ፈቃድ /Green Card/ ጠይቆ ማግኘት ይችላል:: ይህንን ጥቅም ለማግኘት ሲባል ይመስላል ራስን ካህን አድርጎ የማቅረቡ ችግር በአሜሪካ ይስተዋላል:: እነዚህ ሰዎች ቤተ ክርስቲያንንም ሆነ ዕውቀቷን አያውቁም:: ነገር ግን እዚህም እዚያም የካህናት እጥረት ስላለ እነዚህ ሰዎች ምንም ዓይነት ጥያቄ ሳይቀርብላቸው ተቀባይነትን ያገኛሉ:: ይህ እንግዲህ በማዕከል ያለ መሥራት የመጣው ችግር ይመስለኛል:: ስለዚህ ለማጠቃለል ለጥቅም ሲሉ ካህን ነን ብለው በሚቀርቡ፣ እዚህ ሀገር ቤት በኑፋቄ ጭምር በልዩ ልዩ ችግሮች ክህነትን በማፍረስ ክህነታቸውን ያጡ፣ የተወገዙ መናፍቃንና ሌሎች ሰዎች የሚያደርጉት እንቅስቃሴ በአሜሪካ ላለው የቤተ ክርስቲያናችን እንቅስቃሴ እንቅፋት ሆል::

## የምእመኑ ፍላጎት

ሕዝቡ በትክክል የሚያስተምሩትን በአግባቡ የሚያገለግሉትን እውነተኛ አባቶችን ይፈልጋል:: ከጾሙም፣ ከጸሎቱም በአጠቃላይ ከሥርዓቱ አፈጻጸም ሁሉ «አትቀንሱብን» ብሎ እንጂ «በዛብን» ብሎ የሚከራከር ምእመን አታገኙም:: እርሱ በአውቶቡስና በባቡር እየሄደ ለእውነተኞቹ ካህናት መኪና የሚገዛ ምእመን ነው ያለው:: ቤት ገዝቶ ኮ የሚሰጥ ሕዝብ ነው:: ለአንድ ቀን መጥተው አገልግለውት ቢሄዱ ገንዘብ ሰጥቶ የሚሸኝ ሕዝብ ነው:: በአሜሪካ ምድር ለጾመ ነነዌ፣ ለዐቢይ ጾም፣ ለጾመ ፍልሰታ ለማርያም ሱባኤ የሚይዝ ሕዝብ ነው:: መልካም እረኛ ቢያገኝ ልዩ ሕይወት የሚኖረው ሕዝብ ነው::

## በምእመናን ላይ ያመጣው ፈተና

በእውነት በዚህ ሁሉ ችግር መካከል ያሉት ምእመናን በእጅጉ ያሳዝናሉ:: ምእመናኑ በክህነቱ ከፍተኛ ደረጃ ከደረሱት አንዳንድ አባቶች የሚያዩት ለዘብተኛነትን ነው:: አንዲት ካሊፎርኒያ ያለች ልጅ በየጊዜው ስለ ኦርጋን፣ የአሳማ ሥጋ ስለ መብላት፣ ከነ ጫማ ወደ ቤተ መቅደስ ስለ መግባት፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የማይሆኑ መጻሕፍትን ተቀብላ እንደ ኖረች የሚያስተምሯትን ይዛ እየመጣች ከወንድሟ ጋር ትጨቃጨቃለች:: ወንድምዋ ደግሞ በቅርቡ ነው የዲቪ ሎተሪ ዕድለኛ ሆኖ ወደዚያ የሄደው:: ታዲያ የምታወራለት ሁሉ አይስማማውም:: በቤተ ክርስቲያኑ የሚደረገው ሁሉ ሥርዓት የጣሰ መኾኑን እየተቃወመ ይከራከራል:: ታድያ አንድ ቀን እኅቱ በረቡዕ ዕለት ጠዋት ወተት ስትጠጣ ያገኛታል:: «እንዴ፥ ያ ሁሉ ትምህርትሽ ለካ በረቡዕ ዕለት ጠዋት ወተት ለመጠጣት ነበር» ሲላት፡ «አይ፥ እኛ በረቡዕ ዕለት ጠዋት ወተት አትጠጡ የሚል ትምህርት አላስተማሩንም::» ብላው ዐረፈች::

እንግዲህ ከዚህ የምንረዳው ለዘብተኞቹ ካህናት «ጹሙ፣ጸልዩ፣ ስገዱ» የሚለውን ትምህርት ራሳቸውን እንደ መጨቆን ወስደውት ሲያበቁ ሕዝቡም በተመሳሳይ መንገድ እንዲያየው እያደረጉ መኾናቸውን ነው:: ራሳቸውን «ነፃ አውጪዎች» አድርገው የሚገምቱ ሰዎች አሉ:: እንዲያውም አባ ወልደ ትንሣኤ «ውላጤ ዘእንበለ ውላጤ» የሚሉት ትምህርት አላቸው:: «ሳይለወጡ መለወጥ»ነው የሚሉት ትርጉሙን:: በሀገረ አሜሪካ የኦርቶዶክስን ሃይማኖት ለዘብተኛ ማድረግ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ነው የትምህርታቸው ዓላማ::

አልፎ አልፎም አገልግሎቱን እንደ ንግድ /Business/ የያዙትም አሉ፤ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ስድስት፣ ሰባት ታቦት በአንድ ላይ ይጠራል:: «ሚካኤል ወገብርኤል፣ ማርያም ወሩፋኤል ወአቡነ አረጋዊ ወገብረ ክርስቶስ» እየተባሉ የሚጠሩ አብያተ ክርስቲያናት አሉ:: ይህ ሁሉ ታቦት መጠራቱ ክብረ በዓል እንዲበዛና ሕዝቡ በየበዓሉ ገንዘብ እንዲሰጥ ነው እንጂ በእኒህ ሁሉ በዓላት ስብሐተ ነግህ፣ ሰዓታት፣ ማኅሌት ቁመው አይደለም::

## መፍትሔ

በመፍትሔነት ከማዕከላዊው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር፣ እዚያ ካሉ ካህናትና ምእመናን የሚጠበቁ ሐሳቦችን ማቅረብ ይቻላል:: የመጀመሪያው ከማዕከላዊው የቤተ ክርስቲያናችን አስተዳደር የሚጠበቀው ነው:: ቤተ ክርስቲያናችን ማዕከላዊነቱን የጠበቀ «የባሕር ማዶ የሥምሪት ማዕከል» ሊኖራት ይገባል እላለሁ:: ልክ አንድ ዲፕሎማት ሀገሩን ወክሎ ወደ ውጭ ሲሔድ ስለዚያ ሀገር አጠቃላይ ሁኔታ ማወቅ ያለበትን ሁሉ በሚመለከተው አካል እንደሚያውቅ፤ ለአገልግሎት ወደ ውጭ የሚሔዱ ካህናትም በዚህ ማዕከል አማካይነት በዚያ ስላለው የቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ፣ ስለሀገሩ ቋንቋ፣ ታሪክና የኑሮ ሁናቴ እንዲያውቁ ማድረግ ይቻላል:: ነገር ግን ምናልባት ይህ ባይቻል እንኳን ካህናቱ ከዚህ ሲሔዱ ስለ ቦታው ዕውቀት ካላቸው ሰዎች በቂ ግንዛቤ ጨብጠው መሔድ አለባቸው::

ሌላው ስለ ውጭው ዓለም ያለን ርእዮት መስተካከል አለበት እላለሁ:: በእርግጥ:-

*ዋሺንግተን ዲ.ሲ. ወድቄ ብነሣ*
*የሥራ አካላቴ ወርቅ ይዞ ተነሣ*

የሚል አባባል በስፋት ከሚነገርበት ሀገር ይህንን ማድረጉ ይቸግር ይሆናል:: ነገር ግን ከዚህ ወደ እዚያ ለመሔድ ሐሳቡም ሆነ ፍላጎቱ ያላቸው ሰዎች ሊገነዘቡት የሚገባ አንድ ነገር ሊኖር ይገባል:: የሰው ሀገር የሰው መሆኑን፣ የተባለው ወርቅም እንዲሁ ወድቆ በመነሣት ብቻ አለመገኘቱን፣ ለማግኘት ቢቻል እንኳን በብዙ ጻማ መሆኑን ነው:: የመውደቅና የመነሣት ፍላጎቱና ችሎታው ካለን እዚህ ሀገራችንም ወድቀን /ተሯሩጠን ሠርተን/ ወርቅ ይዘን የማንነሣበት ምክንያት የለም:: ወደ ተጠየቁት ጉዳይ ስገባ ግን ካህናት ለማገልገል ሲሔዱ ማንነታቸውን ሊለውጡ አይገባም:: ምዕራባውያን አንተን የሚወዱህና የሚያከብሩህ አዲስ ነገር፣ የራስህ የሆነ ነገር ይዘህ ስትቀርባቸው ብቻ ነው:: የራስህን ጥለህ የእነሱን ስታንጠለጥል ይንቁሃል:: ቻይናዎች፣ ኮሪያዎች፣ ሜክሲካኖች ወ.ዘ.ተ. በአሜሪካ ኖረዋል፣ እየኖሩም ነው:: ታድያ አምስት ቻይናዎች በአንድ ቦታ መኖር ከጀመሩ «የቻይና ከተማ»ን /China Town/ ይመሠርታሉ:: በአሜሪካ የሚገኝ ማንኛውም የቻይና ዕቃ ከላይ በቻይንኛ ከታች በእንግሊዝኛ ነው ስሙ የሚጻፈው:: በዚህ የተነሣ በዚያ ሀገር እነዚህ ተባብረው የሚኖሩ የሌላ ሀገር ሕዝቦች ተከብረው ሲኖሩ አይቻለሁ:: የእኛዎቹ ካህናትም የራሳቸውን ማንነት እያጠፉ:- "This is America … It's Member's Right" /ይህ አሜሪካ ነው፤ … የአባላት /ምእመናን/ መብት ነው/ በሚል የሞኝነት አነጋገር ኢትዮጵያዊ መልካቸውን እነርሱ ለውጠው ሌሎች የቆብ ወንድሞቻቸውና ምእመናን እንዲለውጡ ማድረግ የለባቸውም::

በዚያ የሚኖሩ ምእመናንም ያላቸውን እምነትን፣ ሥርዓትን፣ ትውፊትንና ባሕልን የመጠበቅ የሚደነቅ ችሎታ አሁንም አጠንክረው በቤተ ክርስቲያናቸውና በማንነታቸው ላይ አንዳንድ ክፋዎችና መናፍቃን የሚያደርጉትን ዘመቻና መልክ የመቀየር እንቅስቃሴ መታገል አለባቸው:: ከካህናቱ የበለጠ ለሀገሩ አጠቃላይ አነዋወር ካላቸው ቅርበት የተነሣም ባለማወቅና በመደናገር የሚስቱትን አባቶች ልጅ አባቱን እንደሚመክር ሊመክሯቸውና ወደ ቀደመ ማንነታቸው ሊመልሷቸው ይገባል:: ሆን ብለው በዓላማ ቤተ ክርስቲያንና ልጆቿን ለመውጋት የተነሡትን ደግሞ ባላቸው ድምፅ ከተቀመጡበት ወንበር ሊያነሥዋቸውና ድምፅ አልባ ሊያደርጓቸው ይገባል::

በተረፈ ሕዝበ እስራኤልን በስደታቸው ሁሉ ያልተለየ እግዚአብሔር በስደት ያሉትን ልጆቹን ሁሉ በአባትነት መጠበቅ ይጠብቅልን::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*


# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

- ኢትዮጵያ፣ አክሱም፣ ኦርቶዶክስና ተዋሕዶ የሚሉትን ስሞች የት መጣና ዝርዝር ትርጓሜ ያውቃሉን?
- አምልኮ ጣዖት በዓለም በተንሰራፋበት ዘመን የአሪት እምነት እንዴት ወደ ኢትዮጵያ ገባ?
- ክርስትና ኢትዮጵያ ውስጥ በእነማን ተሰበከ?
- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ምን ይመስላል? ቤተ ክርስቲያን ምን ችግር አጋጥሟት ነበር? እንዴትስ ተፈቱ?
- በውጭ ሀገር /በኢየሩሳሌምና በሌሎች ሀገሮች/ ያሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት እነማን ናቸው? ታሪካቸውስ?
- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርታቸውን የምትቀበልላቸው ከሦስተኛው እስከ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሡ የኦርየንታል ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት እነማን ናቸው? ታሪካቸውስ?

ከላይ የተነሡትን ጥያቄዎች
ምላሾች መጽሐፉን በማንበብ ያገኛሉ::

*አዘጋጅ እና አሳታሚ:-* መምህር ሱሴ መልአኩ

*አከፋፋይ:-* በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን

**በሁሉም የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ማከፋፈያዎች ውስጥ ያገኙታል !!**

ስልክ:- 22-86-01/23-45-29/13-81-30
E-mail:mk_distribution@yahoo.com


# ወዴት ጣልሽው

*በ፲፱፻፺፱ ዓ.ም በግጥም የሥነ ጽሑፍ ዘርፍ*
*በተደረገው ውድድር አንደኛ የወጣ*

*የሥጋ ክምር ዳጠሮሽን፣*
*የአፍላነት ስጦታሽን፣*
*የዓመታት ሸክምሽን::*
*የት አረግሺው ጉብጠትሽን?*
*ወዴት ጣልሺው መለያሽን?*
*ከየት ተሰጠሽ ማንባቱ፣*
*እኔ ኃጥእ ነኝ ማለቱ::*
*ከወዴት መጣ ብልሃትሽ፣*
*ማረኝ ፈውሰኝ ማለትሽ::*
*አንቺ የ18 ዓመት ድውይ የኢያሪኮ ገመምተኛ፣*
*ዕጣሽ ዝምታ የሆነብሽ ዘመድ አልባ ገለልተኛ፣*
*ወዴት ሄዶ ከየት ገባ የጳጥኝ ክምር ሸክምሽ*
*እንደ ሻማ ነው የቀለጠው ? ወይስ*
*....እንደ ቅርፊት ነው የጣለልሽ?*
*ንገሪኝ እባክሽ ልረዳው፣*
*ጨቅላ አእምሮዬን አይጭነቀው::*
*እየተነነ እንደ ትነት በሰማይ ነው የተረጨ፣*
*ወይስ በደም ስሮች እየገባ በሰውነትሽ*
*.....ተሰራጨ::*
*ወዴት ገብቶ ነው የተቃናሽ፣*
*ያ ጉብጠትሽ የጠፋልሽ፣*
*ከረገጥሽት መሬት ውጪ በማይ*
*....ለማየት ያልታደልሽ፣*
*እጁ ሲያርፍብሽ ምን ተሰማሽ፣*
*....ቀና ስትይ ከጉብጠትሽ::*
*አልገረመሽም ወይ ድንቅ ሥራው*
*ክምሩን ሊበትነው ድካምሽን ሲፈታው*
*ንገሪኝ ባክሽ ልረዳው ጨቅላ አእምሮዬን አይጭነቀው::*
*ማገናዘቢያ:- ሉቃ.13÷10*
*አንዱ ዓለም በድሉ*
*ጎፋ ቅዱስ ገብርኤል ሰንበት ት/ቤት -አዲስ አበባ*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## ዐቢይ አንቀጽ /Main Verbs/

/ዲ.ን ደሣለኝ ቀለብ/

1. ቀዳማይ /ኃላፊ/ Past tense
2. ካልአይ /የአሁን እና የመጻኢ/ Present and Future
3. ዘንድ
4. ትዕዛዝ

ዘንድ እና ትዕዛዝ አንድ ናቸው::

ሀ. ቀተለ - ገደለ - ኃላፊ -Past

ለ. ይቀትል - ይገድላል - ካልአይ -Present and Future

ሐ. ይቅትል - ይግደል - ትዕዛዝ Command

መ. ይቅትል - ይገድል ዘንድ - ዘንድ /... to verbs/

### የግእዝ ግሶችን ወደ ካልአይ፣ ዘንድ፣ ትዕዛዝና ንዑስ አንቀ ጽ ለመለወጥ ያለው ደንብ

የግእዝ ግሶች ርባታ በቀዳማይ አንቀጽ ይጀምራል:: ከዚያም በደንቡ መሠረት ወደ ተጠቀሱት አናቅጽ ይለጠ ወጣል:: ይህም በግስ አርዕስቱ ይታወቃል::

### የግስ አርእስት /Root verbs of Regular verbs/

የግስ አርእስት በምንላቸው የጊዜያትን ግብር የሚመሩ እና በእነርሱ የአረባብ ዘዴ ሌሎች እነርሱን መስል ግሶች የሚሄዱ መሆናቸውን የሚለዩልን ግሶች ናቸው:: እነዚህ ግስ አርእስትም ሕጋውያን ግሶች /Regular verbs/ ናቸው::

የግስ አርእስት «ስምንት» ወይም «ሰባት» ሲሆኑ እነዚህም የየራሳቸው መለያ የፊደል ደረጃ አላቸው:: እነዚህም በተናጠል ቤት ይባላሉ:: ይሁንና እነዚህን የአርዕስት ክፍል ለግንዛቤ ይረዳን ዘንድ በአሥራ አንድ ከፍለን እንመለከታቸዋለን:: እነዚህም:-

| የፊደል ደረጃ | | | | | አነባበብ /Pronouncation/ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. ቀተለ | ግእዝ | ግእዝ | ግእዝ | ሆኖ | የለለ |
| 2. ቀደሰ | ግእዝ | ግእዝ | ግእዝ | ሆኖ | የ ጠ በ ቀ «ደ» ይጠብቃል:: |
| 3. ባረከ | ራብዕ | ግእዝ | ግእዝ | የለላ | |
| 4. ደንገፀ | ግእዝ | ሳድስ | ግእዝ | ግእዝ | የላላ |
| 5. ማህረበ | ራብዕ | ሳድስ | ግእዝ | ግእዝ | የላላ |
| 6. ዴገነ | ኃምስ | ግእዝ | ግእዝ | | የላላ |
| 7. ኖለወ | ሰብዐ | ግእዝ | ግእዝ | | የላላ |
| 8. ቆመ | ሰብዕ | ግእዝ | ግእዝ | | የላላ |
| 9. ሤመ | ኃምስ | ግእዝ | ግእዝ | | የላላ |
| 10. ብህለ | ሳድስ | ሳድስ | ግእዝ | ግእዝ | የላላ |
| 11. ገብረ | ግእዝ | ሳድስ | ግእዝ | ግእዝ | የላላ |

### የግስ አርእስቱ የጊዜ ሂደት

- የግስ እርባታ በግእዝ ቋንቋ በቀዳማይ አንቀጽ ይጀምርና ወደ መጻኢው ይጓዛል::
- ርባታውም በተውላጠ ስም «ውእቱ» /እሱ/ ይጀምራል::
- የግስ አርዕስቱን በሰምንት የሚከፈሉት ቀተለ፣ ቀደሰ፣ ባረከ፣ አእመረ /ማህረበ/፣ ቆመ፣ ሤመ፣ ብህለ፣ገብረ በ ማለት ሲሆን አሁንም በአንዳንድ ቅኔ ቤቶች ተግባራዊ ነው::
- ግስን ለማርባት /ወደ ካልአይ ዘንድ እና ትዕዛዝ/ ለመለወጥ ቤቱን ማወቅ ያስፈልጋል:: ይህም ቤቱ ማን ነው? ይባላል:: በማን ቤት ይረባል? ማንንስ ይመስላል? በአገባቡ በቀለሙ ቅርጽ ወዘተ::

ወደሰ ቤቱ ቀደሰ ነው:: ወይም የቀደሰ ቤት ነው::

ነጸረቤቱ ቀደሰ ነው:: » »

ነገረ ቤቱ ቀተለ ነው:: » የቀተለ ቤት ነው

ወደሰ የቀደሰ ቤት የሆነው ስለጠበቀ ነው::

| ቀዳማይ አንቀጽ /ኃላፊ Past tens/ ዘንድ/ትዕዛዝ | ካልአይ /የአሁንና የመጻኢ/ ንዑስ አንቀጽ / Infinitive |
|---|---|
| 1. ቀተለ - ገደለ | ይቀትል - ይገድላል |
| ይቅትል-ይግደል | ቀቲል/ቀቲሎት-መግደል |
| 2. ቀደሰ - አመሰገነ | ይቄድስ - ያመሰግናል |
| ይቀድስ-ያመሰግን | ቀድሶ/ቀድሶት - ማመስገን |
| 3. ባረከ - ባረከ | ይባርክ - ይባርክ |
| ይባርክ-ይበርክ | ባርኮ/በርኮት-መባረክ |
| 4. ደንገፀ - ደነገጠ | ይደነግፅ - ይደነግጣል |
| ይደንግፅ - ይደንግጥ | ደንግፆ/ደንግፆት-መግረክ |
| 5. ማህረበ - ማረከ | ይማህርክ - ይማርካል |
| ይምህርክ-ይማርክ | ማርኮ/ማህርቦት/መማረክ |
| 6. ዴገነ - ተከተለ | ይዴግን ይከተላል |
| ይዴግን-ይከተል | ዴግኖ/ዴግነት |
| 7. ኖለው ጠበቀ | ይኖሉ |
| ይኖሉ-ይጠብቅ | ኖልዎ/ኖልዎት |
| 8. ቆመ - ቆመ | ይቀውም - ይቆማል |
| ይቁም-ይቁም | ቀዊም/ቀዊሞት |
| 9. ሤመ-ሾመ | ይሠይም ይሾማል |
| ይሢም-ይሹም | ሠዪም/ወዲሞት |
| 10. ብህለ - አለ | ይብህል - ይላል |
| ይብሃል-ይበል | ብሂል/ብሂሎት |
| 11. ገብረ - ሠራ | ይገብር - ይሠራል |
| ይግበር-ይሠራ | ገቢር/ገቢሮት |

ማሳሰቢያና ማስታወሻ:-

እዚህ ላይ ግሶች ሁሉ እነዚህን የመሰሉ እንደነዚህ ግሶች በምሉዕ መስለው ላይረቡ ይችላሉ:: ይህም ሕ ጋውያን/Regular/ እና ሕጋውያን ያልሆኑ Irregular verbs / ግሶች መኖራቸውን ያመለክታል::

| ምሳሌ:- Present | past |
|---|---|
| work | worked |
| go | went |

ግሶች የመምሰል ደረጃ አላቸው /እንደ እንደራሴ፣ ራስ፣ ፊታውራሪ.../:: ይህም ሠራዊት ይባላል:: ይህ ማለት ግን ግስ ከግስ ይበልጣል ማለት አይደለም::

ይቀጥላል



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# መንገደኛው

## ወዴት እየሄድን ነው?

አሁንስ ግራ እየገባኝ ነው፡፡ አየሩ ሁሉ ተገላብጦ ተቀያይሮ ኢትዮጵያን የማውቃት ኢትዮጵያ ሳይሆን ሌላይቱ «ኢትዮጵያ» እያደረጋት ነው፡፡ ምን አየሩ ብቻ እንዳትሉኝ አደራ፤ ሰውም መቀየር ጀምሯል ልበል? ሰላምታውን አልረሳሁት መንገደኛው ልቤ ከድካሙ እስኪያገግም ነው፡፡ ሰላምታ ያላቀረብኩላችሁ፡ ሰላም ሰላም ሰላም...

አሁን አሁን መንገድ መሔድ እስጠልቶኛል፡፡ ለምን መሰላችሁ? አየሩ፣ መዚቃው፣ ወሬው በፋሽን ሰበብ እርቃናቸውን የሚሄዱ፣ በቀለም የተዥጎረጎሩ ሱሪያቸው ከመቀመጫቸው ሊወልቅ አንድ ደቂቃ የቀረ... ማየት ታከተኝ፡፡ እናንተ እንዳትስቁብኝና አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ፡፡ በውኑ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለን ኢትዮጵያውያን ነን ወይስ አገሪቷ ራሷ ኢትዮጵያ አይደለችም? ነቢዩ ኤርምያስ «በውኑ አትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዥንጉርጉርነቱን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን?» ያለው ቃል ከዘመን ብዛት የተነሣ ተሻረን ወይስ አትዮጵያዊነት ተሻረ?

መንገደኛው አንድ ነገር ያምናል፡፡ ነብር ዥንጉርጉርነትን አልለወጠም፡፡ አትዮጵያዊ ግን መልኩን ለውጧል፡፡ መልኩን፡፡ ውጫዊ መልኩን ውስጣዊ መልኩን፡፡ የሚከራከር ካለ መንገደኛው ደስተኛ ነው፡፡ የሚጠራጠር ካለም አራት ኪሎ ወይም ፒያሳ ወጣ ብሎ ማየት ይችላል፡፡ ለሕፃናት ማስፈራሪያ ተብሎ በሰው ሕሊና የተፈጠረውን «ጭራቅ» ከሚመስል ጎረምሳ ጀምሮ በሜክ አፕ ፊቷ ገርጥቶ ጠጉሯ በቀለም ዜግነቱን ቀይሮ ... እስከ ሚገኙት አርቲፊሻል /Artificial/ ፈረንጆች የመንገደኛው መረጃዎች ናቸው፡፡ /White men in black skin/ ይላቸዋል አንድ የመንገደኛው ጓደኛ፡፡

አየሩ ቢቀየር ምን ይገርማል? በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረው ሰው ከእግዚአብሔር በጸጋ የተሰጠውን መልክ ይቀይር የለ፡፡ ይኸውላችሁ ዘፋኙ ነው፡፡ መንገደኛው ዘፈን አይወድም፡፡ ኃጢአት ነዋ፡፡ ነገር ግን መንገኛው በየታክሲው በየሻይ ቤቱ የግዱን ይሰማል፤ ይታዘባል፡፡ ሰውዬው ይዘፍናል ለራሱ፡፡ የመንገደኛው ግን አንድ ሦስት ዓመት ሕፃን ልቅሶ ባልተፈታ ምላስ የማላዘን ዓይነት ነው፡፡ ለምን እንዳትሉ፡፡ እንደ ውጪዎቹ ለመሆን ነዋ፡፡ ግን እኮ ዘፈኑን የሚዘፍነው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነው፡፡ አንዳንዱ ደግሞ እንደ ጉራማይሌ ንቅሳት እንግሊዘኛ ጣልቃ ያስገባበታል፡፡ ውጪ መሆኑ ነው፡፡ ደግሞም የመሠልጠን ምልክት ነው፡፡

ድሮ ድሮ ነው አሉ፡፡ በሀገር ድርቅ በሽታ ሲመጣ እውነተኞች ኢትዮጵያውያን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሌላውም ሥርዓተ አምልኮውን ወደ ሚፈጽምበት ይሄድና ፈጣሪውን ይለምናል፡፡ ታቦት ወጥቶ መስቀል ቁሞ ወንጌል ተዘርግቶ ምእመናን ማቅ ለብሰው ትቢያ ነስንሰው እግዚአብሔርን ይለምኑታል፡፡ እነርሱም ይለምናቸዋል፡፡ አሁን አሁን ግን ድርቅ ረሃብ በሽታ ሰላም ማጣት... ሲከሰት መፍትሄው ክብ ጠረጴዛ፣ ወረቀት... ሻይ ቡና፣ ኩኪስ... ነው፡፡ ሌላም አለ፤ ዘፈን፡፡

መቼ ነበር ቀኑ... አዎ ባለፈው ቀን መስቀል አደባባይ የዘፈን አደባባይ ሆኗ ነበር፡፡ ለዚያውም እኮ ቅድስት አገር ኢትዮጵያን በጫማ አንረግጣትም ብለው በባዶ እግር መሔዳቸዉ በሚነገርላቸው ሰዎች፡፡ እነርሱስ ይዝፈኑ፤ ወጋቸው ባሕላቸዉ ስለሆነ፡፡ ኢትዮጵውያኑ አዳማቂዎች ግን ምን ሆኑ? ለአንድ ሰዓት ተኩል ቆሞ ቅዳሴ ማስቀደስ፣ አርባ ደቂቃ ቃለ እግዚአብሔር መስማት፣ አሥር ደቂቃ የታመመን መጠየቅ፣ ያዘነን ማጽናናት፣ የታሠረን መጎብኘት የ... ይሄን እንተውና ከሚስቱ ከባሏ ከልጆቻቸው ጋር አንድ ሰዓት መነጋገር ወይም ስለ ሥራቸው ውጤታማነት ከሚመለከተው አካል ጋር ለትንሽ ጊዜ ለመነጋገር ጊዜ ያጣው ጉልበት ትዕግስት የሌለው ሕዝብ ከጠዋቱ ሦስት ሰዓሦ እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት እንዴት ሆነለት? መንገደኛው የገረመው ነገር አለ፡፡ ሰውየው ጓደኛው ነው፡፡ ይሠራል፣ ይማራል፤ ባለትዳር ነው፡፡ ዕረፍት የለውም፤ ጊዜ የለውማ፡፡ ለቅሶ ለመድረስ ጊዜ የለውም፡፡ ትምህርቱን ለማጥናት፣ ከባለቤቱ ጋር ለማውራት፣ ልጁን ለማጫወት፣ ምሳ ለመብላትም ጊዜ የለውም፡፡ የዚያን ቀን የዘፈኑ የዕብደቱ ዕለት መንገደኛው ስልክ ይደውልለታል ፈልጎት፡፡ ያ ጊዜ ያልነበረው ሰው ጊዜ ተርፎት መስቀል አደባባይ ሊዘፍን ይሁን ሊያይ ሄዷል ፡፡

አይ መንገደኛው፤ የእርሱ መሄድ ምን ይገርማል? «ቄሱስ» ሄደው በመስቀላቸው ዘፈኑን ባርከውት የለ፡፡ የሰላም ዓርማውን፣ የፈጣሪ መታረቂያ ማስታረቂያውን፣ የአጋንንት ድል ማድረጊያውን መስቀል የአጋንንት ፈቃድ የዘፈን መባረኪያ አድርገውት ቁጭ፡፡ መንገደኛው ደግሞ በሞት ለተለየው ለቦብ ማርሌይ ጸሎተ ፍትሐት ሊያደርጉ በዘፈን እንደ ኖኅ ዘመን ዘመናቸውን ለሚጨርሱት ወንገኖች ንስሐ ግቡ ለማለት የሄዱ መስሎት ነበር፡፡ ቄሱ ለካ... ለካ ጊዜው ብቻ አይደለም የተቀየረው፤ ቄሱም መስቀሉም ጭምር ነው፡፡ ፍትሐ ነገሥቱን እንዲያነቡት ማን ገዝቶ በሰጠልኝ?

መንገደኛው የለውጡ ጉዳይ አሳስቦታል፡፡ «ለውጥ ጥሩ ነው፡፡» ይሉ ነበር አብዬ ቢሻው፡፡ ግን በአገራዊ ነባራዊ ሁኔታ ላይ ተመሥርቶ የራስን እክብሮ ክድህነት ወደ ብልጥግና መለወጥ ከድንቁርና ወደ ዕውቀት መለወጥ ሺጋ ነው፡፡ አንድ ሰሞን በቴሌቪዥን መስኮት እየተመለከትን ተአምር ወይም በቃ ሌላ በሉት መስሎ የቀረበልን የጃፓንና የቻይና ዕድገት በዘፈን በፋሽን ወይም አገራዊ ባሕላቸውን ትተው አይደለም፡፡ ያላቸውን አጥብቀው ይዘው ተግተው በመሥራታቸዉ ብቻ ነው፡፡

መንገድ ቢሄዱት አየር ቢተነፍሱት አያልቅ፡፡ የዛሬይቱ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያንም ነገር ቢታዘቡት አያልቅም፡፡ በሉ እስቲ እዚያ ዘፈን አደባባይ የቆምነውን ያህል ባይሆን ትንሽ ቆም ብለን እንወያይ፡፡ ወዴት እየሄድን ነው?

የማኅበረ ቅዱሳን ቁጥር ስድስት መዝሙር በሥርጭት ላይ ዋለ::

መዝሙሮቹ በያሬዳዊ ዜማ ምልክት የተመለከቱ /ባለምልክት/ መሆናቸው ካሴቱን ልዩ ያደርገዋል::

የመዝሙሮቹ ዜማዎች በሙሉ በመሠረታዊ የያሬድ ዜማ ስልቶች /በግእዝ፣በእዝልና በአራራይ/ የተቃኙ ናቸው::

በቴፕ ካሴትና በሲዲ ተዘጋጅቶ ቀርቦልዎታል!!

አዘጋጅ:- በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መ/የማኅበረ ቅዱሳን መዝሙርና ሥነ-ጥበባት ክፍል

አከፋፋይ:- ማኅበረ ቅዱሳን

በሁሚሉም የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ማከፋፈያዎች ውስጥ ያገኙታል!!
ስልክ 23 45 29/22 86 01/ 13 81 30
E-mail MK_distribution@yahoo.com

# አዳዲስ የቪዲዮ የስብከት ካሴቶች በሥርጭት ላይ ዋሉ

| ተ.ቁ | ርእስ | መምህር | ይዘት |
|---|---|---|---|
| 1. | የድፍረት ኃጢአት | ቀሲስ ስንታየሁ አባተ | የድፍረት ኃጢአት ምንነትና መንስኤውን እንዲሁም በሰው ልጆች ላይ የሚያስከትለውን ቅጣት ይተነትናል |
| 2. | ስለ ስደተኞች እንማልዳለን | ዲ/ን. ዳንኤል ክብረት | በስደት የሚኖሩ ወገኖችን መንፈሳዊ ኑሮና የሚያጋጥማቸውን ፈተናና መፍትሄን የሚጠቁም |

በሁሉም የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ማከፋፈያዎች ውስጥ ያገኙታል!!
ስልክ 23-45 29/22 86 01/13 81 30
E-mail MK_ distribution@yahoo.com



## መስዋዕተ ወንጌል

/ቅዱስ ቁርባን /

ስለ ምስጢረ ቁርባን ሰፊ መንፈሳዊ ትምህርን የሚሰጥ ግልጽ በሆነ አቀራረብ ማራኪ ቅደም ተከተል ባላቸው ስድስት ምዕራፎች የተዘጋጀ መጽሐፍ እነሆ *በያዕቆብ ስንደቁ* አዘጋጅነት ለምእመናን ቀረበ::

- ዘወትር ለመቁረብ እየፈለጉ በብዙ ምክንያት ለሚዘገዩ
- ይህን መንፈሳዊ ሕይወት አስበው ለማያውቁ
- ጋብቻቸውን በቅዱስ ቁርባን ለመፈጸም ለሚፈልጉ ሁሉ

ይህን መጽሐፍ ካነበቡ በኋላ ከቅዱስ ቁርባን መቀበረ የሚያስገኘውን መንፈሳዊ ጸጋና በረከት በሚገባ ይረዳሉ፥ ለጥያቄዎ መልስ ለችግሮ መፍትሄ ያገኛሉ:: ዋጋው 12.00 ብቻ::

*መጽሐፍን ለማግኘት*
- *በማኅበረ ቅዱሳን ማከፋፈያዎች*
- *በማን መጽሐፍት መደብር መርካቶ ራጉኤል ቤክ ፊትለፊት*

*09-63-63-93 20-04-38*



## ሀብታምና ድሀ

### ሀብታምና ድሀ

*ታላቅ የምሥራች ለምእመናን በሙሉ !*

*በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳስ የነበረው ታላቁ አባት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ካዘጋጃቸው በርካታ መንፈሳዊ መጻሕፍት መካከል «በባለጸግነትና ድህነት ላይ»(On Wealth and Poverty) የተባለውን መጽሐፉን በተዛማጅ የአማርኛ ርዕስ «ሀብታምና ድሀ» በሚል በእያሴው ዘኢየሱስ ተተርጉሞ ለምዕመናን ቀረበ::*

*ይህ መጻፍ:*
- *ባለጸጋው ነዌና ድሀው አልዓዛር በዚህኛውና በወዲያኛው ዓለም ስለነበራቸው ኑሮ አጉልቶ ያሳያል::*
- *በብልጽግና ሕይወት ውስጥ ምን የተሳሳተ ነገር እንዳለና በድህነት ኑሮ ውስጥ ምን በጎ ነገር እንዳለ ያብራራል::*
- *ሀብታሞች በሙሉ እንደማይኮነኑ ድሆችም በሙሉ እንደማይጸድቁ ነገር ግን የባለጸጋው ከፍተኛው ስህተት ምጽዋት አለመስጠቱና ድሆችን አለመርዳቱ መሆኑን ይተነትናል::*

*ምዕመናን በብር 10.00 ብቻ ገዝተው በማንበብ ከዚህ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን አባት የስብከት በረከት እንዲሳተፉ መንፈሳዊ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን::*

*መጽሐፉ የሚገኘው :-*
- *በመኅበረ ቅዱሳን ማከፋፈያዎች*

*የስልክ ቁጥሮች :- 48-33-15 09-61-59-15 09- 63-63-93*

ዋጋ ብር 3.50

ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

©ማኅበረ ቅዱሳን

ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፣እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው፡፡